ፍጹም ሁን

የቆላስይስ መልእክት

ጽሑፍ በዋረን ደብልዩ ዊርዝቢ

ትርጉም - በግርማዊ

እርማት - በጌቱ ግዛው እና በተስፋዬ መስፍን።

Copyright ©1996 by SIM, Addis Ababa Ethiopia, Originally published in English under the title of BE COMPLETE, copyright © 1981 by SP Publications, Inc., Wheaton, Illinois, USA. All rights reserved.

ማውጫ

ገጽ

መቅድም

1. በፍቅር የተጻፈ፥ የጳውሎስ ደብዳቤ 1
2. በቆላስይስ የተደረጉ ተአምራት 14
3. የእስረኛው ጸሎት 26
4. ከሁሉም በላይ አንግሡት! 39
5. የአንድ ሰው አገልግሎት 52
6. ሕያዋንና ንቁ የሆኑ ቅዱሳን 65
7. አማኝ ሆይ፥ ተጠንቀቅ! 78
8. ገነት በምድር ላይ 91
9. ወደ አንድ ሰፍራ ለመሄድ የታጠቁ ሰዎች ... 104
10. የቤተሰብ ጉዳይ 115
11. ንግግር ቀላል አይደለም! 126
12. ወዳጆች፥ ሮማውያንና፥ የአገሬው ሰዎች ... 137

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው ጥቅሶች የተወሰዱት በብዛት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲሆን፥ የተቀሩት ደግሞ በ1980 ዓ.ም. ከታተመው አዲስ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ የተወሰዱ ናቸው። በተጨማሪም ዓመተ ምሕረቶች በሙሉ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር መሆናቸውን ለመግለጽ እንሻለን።

መቅድም

ይህ መልእክት ጳውሎስ በደብዳቤ ካስተላለፋቸው እጅግ የጠለቁ መልእክቶች አንዱ በመሆኑ፥ ማዘጋጀት የጀመርሁት በታላቅ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ነበር። እንዲሁም መጽሐፉን አዘጋጅቼ እንዳጠናቀቅሁ፥ በቆላስይስ መልእክት ውስጥ የሚገኘውን የመንፈሳዊ እውነት ጥልቀት በይበልጥ ተረድቻለሁ።

የዚህ ደብዳቤ መልእክት ዛሬ እጅግ ተፈላጊ ነው። በርካታ ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ ሌላ ነገር እንደሚያስፈልገኝ ሲናገሩ እሰማለሁ። አስደናቂ የሆነ ልምምድ፥ አዲስ ትምህርት፥ በክርስትና ልምምዴ ላይ ሌላ ተጨማሪ ነገር እንደሚያሻኝ ይናገራሉ። ሆኖም ጳውሎስ እንደሚያረጋግጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘሁትን በረከት በተግባር ላይ ማዋል እንደሚገባኝ ያሳስበኛል። «እንዲሁም እናንተ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል»።

እንዲሁም ደግሞ ሊፈርዱብኝና በክርስቶስ ያለኝን የተሟላ ነጻነት ሊገፉኝ የሚሹትንም ሰዎች እሰማለሁ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሁሉ ጳውሎስ፡- «ማንም አያታልላችሁ፤ ማንም አያበላሻችሁ፤ ማንም አይፍረድባችሁ» እያለ ሲናገር መስማት ምንኛ የሚያጽናና ነው። የምንፈልገው ነገር ቢኖር የክርስቶስን ሙላት ነው፤ በመሆኑም ሰው-ሠራሽ ሥርዓቶችና ሕግጋት በእግዚአብሔር ልጅ አማካኝነት ያገኘሁትን ባለጸግነት ሊተኩልኝ ከቶውንም ብቃት የላቸውም።

እነዚህ ጥቂት ምዕራፎች በዚህ መልእክት ውስጥ ያሉትን ሀብቶች በሙሉ ቆፍረው ለማውጣት አይችሉም። ዳሩ ግን እነዚህ ቀለል ያሉ ጥናቶች በክርስቶስ ያለዎትን ሙላት ለማመልከት ከቻሉና ይህንኑ ሙላት ከልብ እንዲያደንቁ ከገፋፋዎት፥ ለጌታ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እውነተኛ አማኞች ሁሉ የቆላስይስ መጽሐፍ በሚያስተላልፈው መልእክት ለመኖር ከቆረጡ፥ በየአብያተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መነቃቃት እንደሚኖረን ይሰማኛል።

ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

_ 1 _

በፍቅር የተጻፈ፥ የጳውሎስ ደብዳቤ

ቆላስይስ 1፡1-2

የከዋክብት እንቅስቃሴ በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸው ይሆን? በየቀኑ በሕይወታቸው ላይ ስለሚደርሰው ነገር ከኮከብ ቆጣሪዎች ምክርን የሚጠይቁ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለዚህ ጥያቄዬ ከስተት «አዎን» የሚል ምላሽ እንደሚሰጡኝ አስባለሁ። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚታተሙ 1750 ያህል ዕለታዊ ጋዜጦች ሲኖሩ፥ ከእነዚህም ውስጥ 1220ዎቹ የኮከብ ቆጠራ ዘገባዎችን ያቀርባሉ።

*** በምግብና በመንፈሳዊ ሕይወት መካከል ግንኙነት ይኖር ይሆን?**

*** እግዚአብሔር የሚናገረን በቀጥታ በአእምሮአችን ነው ወይስ የእርሱ ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ብቻ ነው?**

*** ምሥራቃውያን ሃይማኖቶች ለወንጌል አማኝ ክርስቲያን የሚሰጡት አንዳች ነገር ይኖር ይሆን?**

እነዚህ ጥያቄዎች በጣም ዘመናዊ ይመስላሉ። ዳሩ ግን ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈው አስደናቂ መልእክት ውስጥ የጠቀሳቸው ዐበይት ቁም ነገሮች ናቸው። በ60 ዓ.ም. ጳውሎስ መልእክት ለጻፈላቸው ሰዎች አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ፥ ለእኛም ይህ እጅግ ጠቃሚ ደብዳቤ ያስፈልገናል።

ከተማዪቱ

ቆላስይስ ከኤፌሶን ወደ 160 ኪሎ ሜትር አካባቢ ገባ ብለው ከሚገኙ ሦስት ከተሞች አንዷ ነበረች። ሌሎች ሁለቱ ከተሞች ሎዶቅያና ኢያራ (ሂራፖሊስ) ነበሩ (ቆላ. 4፡13፥ 16)። በዚያ በኩል ጠቃሚ የንግድ መስመር ስለነበር፥ ይህ ስፍራ የምሥራቅና የምዕራብ መገናኛ ማዕከል ነበር። በአንድ ወቅት፥ ሦስቱም ከተሞች እያደጉና እየበለጸጉ ሄደው ነበር። ዳሩ ግን ቆላስይስ ቀስ በቀስ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ እያለች ወደ ትንሽ ከተማነት ተቀየረች። ይሁን እንጂ በዚህች ከተማ ውስጥ

የነበረች ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያው ጳውሎስን ትኩረት ለመሳብ በቅታ ነበር።

በዚህ የበርካታ አገሮች ልምዶችና ባህሎች በተጨናነቀች ከተማ የፍልስፍና ዓይነቶች በሙሉ መቀላቀል ያዙ። ደግሞም የሃይማኖት አታላዮች ተበራከቱ። በቆላስይስ ውስጥ ብዙ አይሁዶች ሰፍረው ነበር። ከወደ ምሥራቅም ደግሞ የማያቋርጡ አዳዲስ አሳቦችና ትምህርቶች ወደዚህች ከተማ ይጎርፉ ነበር። ለሃይማኖታዊ መላ-ምትና ለሐሰት ትምህርቶች መስፋፊያ አመቺ ስፍራ ነበረች።

ቤተ ክርስቲያን

በከተማይቱ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን የተነሣ ባትጠቀስ ኖሮ፥ ምናልባት ቆላስይስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በፍጹም ላትጠራ ትችል ነበር። ጳውሎስ የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን ስላልመሠረተና ጎብኝቷትም ስለማያውቅ፥ ከተማዪቱ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳ አልተጠቀሰችም። ጳውሎስ ስለ እምነታቸው ቢሰማም (ቆላ. 1፡4፥9)፥ እነዚህን አማኞች ፊት ለፊት አይቶአቸው አያውቅም ነበር (2፡1)። እንግዲህ በቆላስይስ መልእክት ውስጥ የምንመለከተው፥ በትንሽ ከተማ ውስጥ ያልታወቀ ሕዝብ የሚገኝባት ቤተ ክርስቲያን፥ ከታላቁ ሐዋርያ ከጳውሎስ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያረፈበትን ደብዳቤ ስትቀበል ነው!

የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ተመሠረተች? ለዚህች ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ምክንያት የሆነው፥ ጳውሎስ በኤፌሶን ያበረከተው የሦስት ዓመታት አገልግሎት ነው (የሐዋ. 19፤ 20፡17-38)። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ስኬታማ በመሆኑ፥ «በእስያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል» ሰሙ (የሐዋ. 19፡10)። ይህም በቆላስይስ፥ በሎዶቅያና በኢያራ የነበሩትን ሰዎች ያካትት ነበር።

ጳውሎስ ከእስር ቤት የጻፋቸው መልእክቶች (ኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስ፥ ቆላስይስ፥ ፊሊሞና እና 2ኛ ጢሞቴዎስ) ውስጥ ተሳታፊ የነበሩትን ሰዎች ስንመረምር፥ የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበትንም ታሪክ አብረን ልንመለከት እንችላለን። ጳውሎስ በኤፌሶን ያገለግል በነበረበት ወቅት፥ ቢያንስ ሁለት የቆላስያስ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል። እነዚህም ሰዎች ኤጳፍራና ፊሊሞና ነበሩ (ፊሊ. ቁ. 23 ይመልከቱ)። ኤጳፍራ በዚያ ለነበሩት ወዳጆቹ ወንጌልን ስለሰበከላቸው (ቆላ. 1፡7)

በቆላስይስ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ከመሠረቱት ዋነኛ ሰዎች አንዱ ነበር። እንዲሁም በኢያራና በሎዶቅያ ከተሞች አገልግሎት ነበረው (ቆላ. 4፡12-13)።

በፊሊሞና ቤት ውስጥ የምትሰበሰብ ቤተ ክርስቲያን ነበረች (ፊሊ. ቁ. 2)። በዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት አፍብያና አርክጳ፥ እንደ ቅደም-ተከተላቸው የፊሊሞና ሚስትና ልጅ ሳይሆኑ አይቀሩም። በተጨማሪም አክሪጳ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ሳይሆን አይቀርም (ቆላ. 4፡17)።

በዚህ ስፍራ ለራሳችን የሚሆን ጠቃሚ ትምህርት እናገኛለን፡- እግዚአብሔር አንድን አገልግሎት ለመመሥረትና ለመገንባት ሁልጊዜም ሐዋርያ፥ ወይም «ሙሉ ጊዜውን የሰጠ ክርስቲያን አገልጋይ» አይፈልግም። ወይም ደግሞ ያሸበረቁ ሕንጻዎችንና ሰፋፊ ድርጅቶችን አይፈልግም። በዚህ ስፍራ የምንመለከተው ቢያንስ በሦስት ከተሞች ውስጥ አገልግሎቶችን ለመጀመር እግዚአብሔር የተጠቀመባቸውን ሁለት ተራ ሰዎችን ነው። እንደ ኤፌሶን በመሳሰሉ ሰፋፊ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ወደ ትናንሽ ከተሞች በመሄድ የወንጌሉን ቃል እንዲያካፍሉ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። የእርስዎ ቤተ ክርስቲያን፥ «ለትናንሽ ከተሞች» ወንጌልን ለማዳረስ የምትችለውን እገዛ እያደረገች ነውን?

የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በይበልጥ ከአሕዛብ ወገን የመጡ ምእመናን የሚበዙበት ነበር። ጳውሎስ የጠቀሳቸው ኃጢአቶች (ቆላ. 3፡5-9) ባመዛኙ ከአሕዛብ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፥ ስለ ምሥጢር የሚናገረውም ከአይሁዳውያኑ ይልቅ ከአሕዛብ ጋር የተያያዘ ነው (1፡25-29)። ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በጻፈበት ወቅት፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተመሠረተች ምናልባት አምስት ዓመታት ሳይሆን አይቀርም።

ችግሩ

ጳውሎስ በቆላስይስ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ይህን ደብዳቤ የጻፈው ለምን ነበር? ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎት ሊያወድም የተቃረበ ችግር ተፈጥሮ ስለ ነበር ነው። በእስር ቤት ሆኖ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች በማወዳደር፥ የሚከተሉትን ክስተቶች ለማስተዋል እንችላለን፡-

በዚያን ወቅት ጳውሎስ በሮም ወኅኒ ቤት ውስጥ ነበር (የሐዋ. 21፡17-28፡31)። በዚያም ከጌታው ዘንድ ኮብልሎ የመጣ አናሲሞስ የሚባል ባሪያ አገኘ። አናሲሞስ የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከነበሩት አንዱ የሆነው የፊሊሞና አገልጋይ ነበር። ጳውሎስ አናሲሞስን ወደ ክርስቶስ መራው። ወዳጁ ለነበረው ለፊሊሞና ደብዳቤ በመጻፍ፥ አናሲሞስን ይቅር እንዲለውና በክርስቶስ እንደተወደደ ወንድም አድርጎ እንዲቀበለው ይጠይቀዋል።

በዚህ ጊዜ፥ ኤጳፍራ የጳውሎስን እርዳታ ስለፈለገ ወደ ሮሜ መጣ። በቆላስይስ አንዳንድ አዳዲስ ትምህርቶች እየተከሰቱ ቤተ ክርስቲያንን በመበከል ችግር እየፈጠሩ ነበር። ስለዚህ የእነዚህን የሐሰት ትምህርቶች ሐሰተኛነት በማረጋገጥ እንዲያወግዙዋቸውና የወንጌሉን እውነታ እንዲመሠርቱ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ለቆላስይስ ሰዎች ጻፈ

ኤጳፍራ ከጳውሎስ ጋር በሮም ሰነበተ (ቆላ. 4፡12-13)። አናሲሞስና ቲኪቆስም የጳውሎስን መልእክቶች ወደተላኩባቸው ስፍራዎች ይዘው ሄዱ (ኤፌ. 6፡21፤ ቆላ. 4፡7-9፤ እና ፊሊሞና)። ኤጳፍራ ከጳውሎስ ጋር «አብሮ እንደታሰረ» ተገልጾአል። ይኸው ተመሳሳይ ሁኔታ ስለ አርስጥሮኮስም ተጠቅሶ ይገኛል (ፊሊሞና ቁ. 24፤ ቆላ. 4፡10)። ይህም የሚያመለክተው ኤጳፍራ ጳውሎስን ለመርዳት ሲል በራሱ ፈቃድ አብሮት በወኅኒ ቤት ውስጥ እንደሰነበተ ነው። ኤጳፍራም ሆነ አርስጥሮኮስ ሕግ ጥሰው የታሰሩ ሳይሆኑ፥ ጳውሎስን ለመርዳት ብለው የራሳቸውን ምቾት በፈቃዳቸው የሠሙ የእርሱ ተባባሪዎች ነበሩ።

ለመሆኑ የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን ሰላምና ንጽሕና በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ የጣለው የሐሰት ትምህርት ምን ነበር? ይህ የሐሰት ትምህርት የምሥራቃውያንን ፍልስፍናና የአይሁድን ሕግ-አጥባቂነት በአንድነት የያዘ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን «ኖስ-ቲ-ሲዝም» ከሚሉት ፅንሰ-አሳብ ክፍሎች ጋር ተዋሕዶ የቀረበ ነበር። ይህ ቃል ኖሲስ (ኖው-ሲስ) ከተሰኘው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፥ ትርጉሙም «ማወቅ» ማለት ነው። (ግኖስቲክ ደግሞ የማያውቅ ማለት ነው)። ኖስቲኮች የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምሥጢራት «እናውቃለን» የሚሉ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «መንፈሳዊ ባለሥልጣናት» ነበሩ።

ይህ የሐሰት ትምህርት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲህ የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ «መንፈሳዊ ፍጹምነት» እንደሚያገኙ ቃል

ይገባላቸው ነበር። መንፈሳዊ ሙላት ሊያገኙ የሚችሉት በተዘጋጁት ትምህርቶችና ሥርዓቶች አኳያ የተመላለሱ እንደሆነ ብቻ ነበር። እንዲሁም ደግሞ በትምህርቱ የገፉት ብቻ የሚደርስበት «ሙሉ እውቀት» ወይም ጥልቅ መንፈሳዊነት እንዳለ ያስተምራሉ። ይህ «ጥበብ» ከምድራዊ ነገሮች አላቅቆ ከሰማያዊ ነገሮች ጋር እንደሚያስተሳስራቸው ይገመት ነበር።

በመሠረቱ፥ ይህ ትምህርት በልማዳዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ሰው-ሠራሽ ፍልስፍና እንጂ በመለኮታዊ እውነት ላይ የተደገፈ አልነበረም (ቆላ. 2፡8)። ፍጥረት ሁሉ በቅዱስ አምላክ የተፈጠረ ከሆነ፥ በዚህች ዓለም ላይ ክፉ ነገር የሚገኘው ለምንድን ነው? በዚህ የፍልስፍና ጥያቄ በመመሥረት የተለያዩ መላ-ምቶችን ከዳሰሱ በኋላ፥ እነዚህ የፍልስፍና አዋቂዎች ቁስ-አካል ክፉ ነው ወደሚል የተሳሳተ ማጠቃለያ ደረሱ። ቀጣዩ ሐሰተኛ ድምዳሜያቸውም፥ ቅዱሱ አምላክ ከክፉ ዓለም ጋር መገናኘት ስለማይችል፥ ከእግዚአብሔር ወደ ፍጥረቱ የሚደርሱ ተከታታይ የአሳብና የስሜት፥ ወዘተ. «ጨረሮች» መኖር እንደነበረባቸው የሚናገር ነበር። የሰው ዘርን ለማጥቃት ቁሳዊ ነገሮችን የሚጠቀም ከፍተኛ ኃይል ያለው መንፈሳዊ ዓለም እንዳለ ያምናሉ። የመላእክት ተፈጥሮ ያላቸው ነገሮች የከዋክብትን እንቅስቃሴ እንደሚገዙና በምድር ላይ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያስከትሉ ስለሚያምኑ፥ የኮከብ ቆጠራ ዓይነትንም ይከተላሉ (ቆላ. 1፡16፤ 2፡10፥ 15 ይመልከቱ)።

በእነዚህ የምሥራቃውያን መላ-ምቶች ላይ የአይሁዶች ሕግ-አጥባቂነት ተጨምረዋል። መምህራኑ ግዝረት ለመንፈሳዊ ዕድገት ጠቃሚ እንደሆነ ያምኑ ነበር (ቆላ. 2፡11)። የብሉይ ኪዳን ሕግ፥ በተለይም የምግብ ሕግጋት መንፈሳዊ ፍጹምነት ለማግኘት ጠቃሚዎች እንደሆኑም ያስተምሩ ነበር (2፡14-17)። የትኞቹ መልካም እንደሆኑና የትኞቹ ክፉ እንደሆኑ የሚናገሩ ሕግጋትና መመሪያዎች ነበሯቸው (2፡21)።

ለእነርሱ ቁስ-አካል (ዓለም) ክፉ ስለሆነ፥ ፍጹምነትንም በማግኘቱ ፍለጋ ውስጥ የራሳቸውን ሰብአዊ ባሕርያት ለመቆጣጠር አንድ መንገድ ማግኘት ነበረባቸው። ከዚህም የተነሣ ሁለት የተለያዩ ልምምዶች ተከስተዋል። አንደኛው የአስተሳሰብ ክፍል ክፉውን ዓለም ለማሸነፍ ብቸኛው መንገድ የማይታጠፉ ግትር ሥርዓትን መከተልና ራስን ማጎሳቆል ሲሆን (2፡23)፥ ሌላኛው ክፍል ደግሞ፥ ዓለም ራስዋ ክፉ ስለሆነች፥

በሁሉም ዓይነት ኃጢአቶች ውስጥ መሳተፍ አለብን የሚል ነበር። በቆላስይስ ውስጥ በበላይነት የምንመለከተው የመጀመሪያውን አመለካከት ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት የክርስትናን እምነት መሠረት እንዴት እንዳዳከመው መረዳት አስቸጋሪ አይሆንም። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ይህ የሐሰት ትምህርት የኢየሱስ ክርስቶስን ስብእናና ሥራ ይቃወም ነበር። ክርስቶስ ለእነርሱ፥ እግዚአብሔር ወደዚህች ዓለም ከላካቸው በርካታ መልእክተኞች «ጨረሮች» አንዱ እንጂ፥ በሥጋ የተገለጠ የእግዚአብሔር ልጅ አልነበረም። በሥጋ መገለጡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ሲሆን (ማቴ. 1፡23)፥ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ግን እግዚአብሔር ከእኛ ርቆ እንደሚኖር ያስተምራሉ። በእግዚአብሔር ልጅ ካመንን ወዲያ፥ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ ፍጥረታት ማስቀመጡ አስፈላጊ አይደለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ ለኃጢአት መፍትሔ ከመሰጠቱ ሌላ (ቆላ. 1፡20)፥ የሰይጣን ኃይሎችን ሙሉ ለሙሉ ድል ነሥቶአል (2፡15)። እርሱ የሕግን ጥያቄ ፈጽሞታል (2፡14-17)። በእርግጥ፥ ከሁሉም በላይ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው! (1፡18፤ 3፡11)። ለአማኙም የሚያስፈልገው ኢየሱስ ብቻ ነው!

በመሠረቱ ቁስ-አካል ክፉ አይደለም፤ በመሆኑም የሰው ሰውነት ክፉ ነው ማለት አይቻልም። እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ሰውነትን ለመቆጣጠር ከሚፈልግ ኃጢአተኛ ባሕርይ ጋር ቢሆንም፥ ሰውነት ግን በራሱ ክፉ አይደለም። ችግሩ ያ ቢሆን ኖሮ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር አይመጣም ነበር። እንዲሁም በምድር ላይ በአገልግሎቱ ወቅት በሠርግ በዓላትና በራት ግብዣዎች ላይ ባልተገኘም ነበር። ምግቦችና ሥነ-ሥርዓቶች ለአንድ ሰው ጤንነት መልካም ቢሆኑም፥ እውነተኛ መንፈሳዊነትን ለማሳደግ የሚያበቃ ኃይል የላቸውም (2፡20-23)።

የከዋክብት ቆጠራ፥ መላእክትና የከዋክብት እንቅስቃሴ በሰው ልጅ ላይ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰበውን ተጽዕኖ ጳውሎስ በከፍተኛ ደረጃ ተቃውሞታል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሰይጣን ኃይሎች ሁሉ ላይ ሙሉ ድል ተቀዳጅቷል (2፡15)። ስለሆነም፥ ክርስቲያኖች ወደ ዓለማዊ ሥርዓት መመለስ አያስፈልጋቸውም (2፡8-20)። በዚህ ስፍራ

የሰው ወግና ዓለማዊ የመጀመሪያ ትምህርት ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ቀለል ያሉ ነገሮች» ወይም «ጥልቅ ያልሆኑ መመሪያዎች» እንደ ግለት ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው፥ (በኖስቲኮች አመለካከት) የከዋክብት እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ ኃይሎች እንዳሉ የሚያመለክት ሲሆን፥ እነዚህም በተራቸው በምድር ላይ የሚከሰቱትን ነገሮች ይቆጣጠራሉ። በኮከብ ቆጠራ የሚመሩ አማኞች ከመለኮታዊ መገለጽ ይልቅ ጥንቆላን ይቀበላሉ፤ የኢየሱስ ክርቶስንም ማንነትና የቤዛነት ሥራ ይክዳሉ።

ይህ የሐሰት ትምህርት የበርካታ ነገሮች ማለትም፡- የአይሁዳውያንን ሕግ-አጥባቂነት፥ የምሥራቃውያን ፍልስፍና፥ የአረማውያን የኮከብ ቆጠራ፥ የሰመመን ልምምድ፥ ራስን የማጎሳቆል አስተሳሰብ እና በመጠኑም ቢሆን የክርስትና እምነትም የሚገኝበት ቅንብር ነበር። በዚህ ባሕርይው ለሁሉም ሰው የሚስማማ የተወሰነ ነገር ነበረው። ትምህርቱንም ይበልጥ አደገኛ ያደረገው ይኸው ነበር። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች የክርስትናን እምነት እየካዱ ሳይሆን፥ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እያሳደጉት እንደሆነ ይናገሩ ነበር። የተሟላ ሕይወትና ነፃነትን፥ በዕለታዊ ኑሮአቸው ሰዎች ለሚገጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ የሚሆን አርኪ ሕይወትን እንደሚሰጡ ይናገሩ ነበር።

ዛሬስ እንደዚህ ዓይነት የሐሰት ትምህርት ይኖር ይሆን? በእርግጥ አለ፤ ይህም ደግሞ እንደቀድሞው ሁሉ አታላይና አደገኛ ነው! ኢየሱስ ክርስቶስንና የክርስትና እምነት መገለጽን ከጠቅላላው ሃይማኖታዊ መንገድ ወይም ፍልስፍና ውስጥ አንዱ አካል ብቻ አድርገን የምንመለከት ከሆን፥ ክርስቶስን ከሁሉም በላይ ከፍ ለማድረግ አንችልም። በሰው-ሠራሽ ሕግጋት፥ ሥነ ሥርዓቶች፥ ወይም ሃይማኖታዊ ደንቦች አማካኝነት «መንፈሳዊ ፍጹምነት» ወይም «መንፈሳዊ ሙላት» ለማግኘት ስንፍጨረጨር፥ ወደፊት በመጓዝ ፈንታ ወደኋላ እንሸራተታለን። ክርስቲያን አማኞች እንደ ዮጋ፥ ጥልቅ የሰመመን ጥበብ፥ የምሥራቃውያን ሃይማኖት ልምምድና እነዚህን ከመሳሰሉት ነገሮች ጋር የክርስትና እምነታቸውን በጭራሽ መደባለቅ አይኖርባቸውም። እንዲሁም ደግሞ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከመሰጠት የሚያግድ፥ የድልና የሙላት ብልሃት ከሚያቀርቡ የ«ጥልቅ ሕይወት» መምህራንም መራቅ አለብን። በነገር ሁሉ፥ የመጀመሪያውን ስፍራ ለክርስቶስ እንሰጣለን።

ይህ የሐሰት ትምህርት ከጳውሎስ ትምህርት ጋር የሚቃረን ነበር። የሚመለከተውም የሕይወትን አሉታዊ ገጽታ በመሆኑ፥ «እግዚአብሔር ከእኛ የራቀ ነው፤ ቁሳዊው ዓለም ክፉ ነው፤ አጋንንታዊ ኃይሎች ሁልጊዜም እየዛቱብን ናቸው» የሚል ትምህርት ያስተምራል። ዳሩ ግን የክርስትና ትምህርት የሚያስተምረን እግዚአብሔር ቅርባችን መሆኑን፥ እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ (ለክፉ ዓላማ ሊውሉ ቢችሉም) መልካም አድርጎ እንደሠራቸውና ክርስቶስ ሕዝቡን ከጨለማ ኃይላት ነፃ እንዳወጣቸው ነው (ቆላ. 1፡13)። ይህ የሐሰት ትምህርት የምንኖርበትን ዓለም ልክ እንደ አስፈሪ ወኅኒ ቤት አድርጎ ሲመለከተው፥ ኢየሱስ ግን የእርሱ የሆኑትን ለመታደግ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ እየሠራ መሆኑን ነው ግልጽ ያደረገው። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በምግቦችና በሥርዓቶች አማካኝነት የሰዎችን ውጫዊ ሕይወት ለመለወጥ ይሞክራሉ። ዳሩ ግን እውነተኛ መንፈሳዊ ዕድገት የሚመነጨው ከውስጥ ነው።

መልእክቱ

ከዚህ መሠረታዊ ሁኔታ በመነሣት፥ አሁን ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን ደብዳቤ ልንመለከትና የመልእክቱንም ጭብጥ ልናገኝ እንችላለን። ለኤፌሶን ሰዎች ያዘጋጀው ደብዳቤ የተጻፈውና የተላከውም የቆላስይስ መልእክት በተጻፈበት ተመሳሳይ ጊዜ እንደነበረ እናውቃለን። ይህንን እውነታ በአእምሮአችን አድርገን፥ በሁለቱ መልእክቶች መካከል አብረው የሚሄዱ በርካታ አሳቦችን ልናገኝ እንችላለን። ዳሩ ግን በኤፌሶኑ መልእክት ውስጥ ትኩረት የተሰጠው የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፥ የቆላስይስ መልእክት የሚያተኩረው ግን የአካሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ላይ ነው።

በዚህ መልእክት ውስጥ፥ ጳውሎስ የሐሰተኛ አስተማሪዎችን ቃላት ቢጠቀምም እነርሱ በሚሰጡዋቸው ፍችዎች ግን አልተጠቀመም። እነዚህን ቃላት የተጠቀመባቸውም ክርስቲያናዊ ፍቺና ገለጻ እየሰጠ ነው። የቆላስይስን መልእክት በምናጠናበት ጊዜ «ሙላት»፥ «ፍጹም»፥ «ሙሉ» የመሳሰሉትን ቃላት በተደጋጋሚ እናገኛለን። እነዚህ ሁሉ የኖስቲክ ሐሰተኛ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ቃላት ነበሩ። ጳውሎስ «ሁሉ» የምትለውን አነስተኛ ቃል ከ30 ጊዜያት በላይ ተጠቅሞባታል። በኖስቲክ የቃላት አጠቃቀም ውስጥ ዋነኛ ቃል ስለሆነው

ጥበብም ጽፎአል፤ ስለ መላእክትና መንፈሳዊ ኃይላትም ብዙ የሚለው ነገር አለው።

የመልእክቱ ዋና አሳብ የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይነት ነው (ቆላ. 1፡18፤ 3፡11)። እኛ ስለ አማላጅ መላእክት ወይም ስለ መንፈሳዊ ኃይላት ልንጨነቅ አይገባም። እግዚአብሔር ልጁን እንዲሞትልን ልኮልናል! በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ማንም ቢሆን የዳነና የአካሉ ግለትም የቤተ ክርስቲያን ክፍል ነው። ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው (1፡18)። እኛም አስደናቂና ሕያው በሆነ ግንኙነት ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነናል!

በተጨማሪም፥ እያንዳንዱ አማኝ «በእርሱ ሙሉ» (2፡10) ስለሆነ፥ በዚህ ግንኙነት ውስጥ ምንም የምንጨምረው የለም። የእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ በክርስቶስ ይኖራል (2፡9)። እኛም ያንኑ ሙላት እንካፈላለን! «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና ... በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል» (2፡9-10)።

በአውሮፕላን ጣቢያ ውስጥ የምንጓጓዝበትን አውሮፕላን በመጠበቅ ላይ እያለሁ፥ አንድ መጽሐፍ ለመሸጥ የሚፈልግ ወጣት ወደእኔ መጣ፤ ገና አብረቅራቂ ሽፋኑን እንደተመለከትሁ መጽሐፉ በምሥራቃውያን ልብ ወለድ ታሪክ ፍልስፍና የተሞላ መሆኑን ተረዳሁ።

ለወጣቱም፥ «መሻቴን ሁሉ የሚያሟላልኝ መጽሐፍ እዚህ አለኝ» አልሁትና ቦርሳዬን ከፍቼ መጽሐፍ ቅዱሴን አወጣሁ።

«ታዲያ፥እኛ መጽሐፍ ቅዱስን አንታወምም›› አለኝ። ቀጥሎም፥ «ይኼ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያልተገለጡ ብዙ ነገሮች፥ ስላሉት እምነታችንን ከእናንተ የተሻለ ያደርገዋል» አለኝ።

እኔም፥ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠኝ በላይ ሊሰጠኝ የሚችል ማንም የለም» ብዬ መለስሁለትና አሳቤን ለማስረገጥ ቆላስይስ ምዕራፍ 2 አውጥቼ ላነብለት በመዘጋጀት ላይ እያለሁ ወጣቱ እየተቻኮለ ሄደ።

በርካታ ክርስቲያኖች፥ አንድ ሰው የሃይማኖት ክፍል ወይም ሥርዓት በመንፈሳዊ ልምምዳቸው ላይ የሚጨምረው ነገር እንዳለ አድርገው ማመናቸው የሚያሳዝን ነው። ዳሩ ግን ለምንጊዜውም የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብእናና ሥራ ውስጥ አግኝተዋል።

ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች ለጻፈው ደብዳቤ የመልእክቱን ቅደም-ተከተል (ማውጫ) አዘጋጅቶ ቢሆን ኖሮ የሚከተለውን ሊመስል ይችል ነበር፡-

ዋናው አሳብ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም በላይ ነው (1፡18)

ሀ. መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፡- የክርስቶስን የበላይነት መግለጹ - ምዕራፍ 1

1. በወንጌል መልእክት - 1፡1-12
2. በማዳን ሥራው - 1፡13-14
3. በፍጥረት - 1፡15-17
4. በቤተ ክርስቲያን - 1፡18-23
5. በጳውሎስ አገልግሎት - 1፡24-29

ለ. ይጠንቀቁ፡- የክርስቶስን የበላይነት ለማጽናት የቀረቡ አሳቦች - ምዕራፍ 2

1. ከከንቱ ፍልስፍና ስለ መራቅ 2፡1-10
2. ከሃይማኖታዊ ወግ-አጥባቂነት መጠንቀቅ - 2፡11-17
3. ከሰው-ሠራሽ ሥርዓቶች መራቅ - 2፡18-23

ሐ. ተግባር፡- የክርስቶስ የበላይነት ሲረጋገጥ - ምዕራፍ 3-4

1. በየግል ሕይወት ንጽሕና - 3፡1-11
2. በክርስቲያናዊ ኅብረት - 3፡12-17
3. በቤት ውስጥ - 3፡18-21
4. በዕለታዊ ተግባር ውስጥ - 3፡22-4፡1
5. በክርስቲያናዊ ምስክርነት - 4፡2-6
6. በክርስቲያናዊ አገልግሎት - 4፡7-18

በእርግጥ ይህ በሰው አሳብ የተዘጋጀ ማውጫ ስለሆነ በመለኮታዊ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንደተዋቀረ ተደርጎ መታየት የለበትም። የእግዚአብሔር ቃል የሚጠናባቸውና የመልእክቱን ቅደም ተከተል ማስቀመጥ የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ። ይሁን እንጂ የትኛውም ቢሆን የእግዚአብሔርን ቃል ሊተካ አይችልም።

ዳሩ ግን ከላይ በተሰጠው ቅደም ተከተል መሠረት መልእክቱን ስናጠና ጳውሎስ ይህንን ችግር እንዴት እንደተመለተውና መፍትሔ ለመስጠት እንደሞከረ እንረዳለን። መልእክቱን የጀመረው በቀጥታ የሐሰት አስተማሪዎችንና ትምህርታቸውን በመቃወም አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ በማድረግና በአምስት ነገሮች ማለትም በወንጌሉ መልእክት፥ በማዳን ሥራው፥ በፍጥረት፥ በቤተ ክርስቲያንና በራሱ በጳውሎስ አገልግሎት ነበር የጀመረው። ጳውሎስ የሚጽፍላቸው ሰዎች ክርስቲያኖች የሆኑት በኤጳፍራ በኩል ከደረሳቸው የወንጌል መልእክት የተነሣ ነበር። እንግዲህ ይህ መልእክት ስሕተት ከሆነ በፍጹም አልዳኑም ማለት ነው።

ጳውሎስ የክርስቶስን የበላይነት ካረጋገጠ በኋላ የሐሰት አስተማሪዎችን በራሳቸው ትምህርት መሠረት ላይ ቆሞ ይቃወማቸዋል። በምዕራፍ 2 የትምህርቶቻቸውን ሐሰተኛ ምንጭ በማጋለጥ፥ እርሱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ካስተማራቸው ነገሮች ሁሉ ጋር እንዴት እንደሚቃረኑ አሳይቷል። ይህንን ምዕራፍ በሚገባ የተረዳ አማኝ በአንዳንድ ማራኪና መስሕብነት ባላቸው «አዳዲስና የተሻሻሉ የክርስትና ዓይነቶች» አይወሰድም።

ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎችን ሐሰተኛነት በማረጋገጥ ብቻ አልተወሰነም። ለቤተ ክርስቲያን የሚያስተላልፈው ጠቃሚ መልእክትም አቅርቦአል። በምዕራፍ 3 እና 4 ጳውሎስ የሐሰት ትምህርትን ለመግታት ዋንኛ መፍትሔ የሆነውን ነገር ይገልጻል፤ ይህም በፈሪሃ-እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሕይወት ነው። «መልካም ሕይወት እየመራህ እስከሆነ ድረስ፥ ስለምታምነው ነገር ግዴለኝም» የሚሉ ሰዎች አስተሳሰብ በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። የምናምነው ነገር ባሕርያችንን ይወስነዋል። ቁሳዊ አካል ክፉ እንደሆነ ብናምን፥ ሰውነታችንን በአንድ መንገድ ብቻ ነው የምንጠቀምበት፤ ዳሩ ግን ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደሆነ ብናምን፥ በዚያው መሠረት እንኖራለን።

ምንጊዜም ቢሆን ሐሰተኛ ትምህርት ወደ ተሳሳተ አኗኗር ይመራል። እውነተኛ ትምህርት ደግሞ ወደ ትክክለኛ አኗኗር መምራት አለበት። ጳውሎስ በመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ በዕለታዊ የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ የክርስቶስን የበላይነት አስመልክቶ ጽፎአል። ክርስቶስ በሕይወታችን ውስጥ እውነትም የበላይ ከሆነ፥ በንጽሕና በመመላለስ፥

ከሌሎች ቅዱሳን ጋር ኅብረት በማድረግ፥ በቤት ውስጥ እርስ በርሳችን በመዋደድና በሥራ ቦታችን ታማኞች በመሆን፥ እንዲሁም ለክርስቶስ በመመስከርና በተሳካ ሁኔታ በማገልገል፥ እናስከብረዋለን። መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ወደ ተግባር እስካልመራን ድረስ ለእኛ የሚሰጠው ፋይዳ አይኖረውም።

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የቆላስይስ መጽሐፍ ጳውሎስ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች ሁሉ እጅግ የጠለቀ መልእክት እንደያዘ ይናገራሉ። ይህም አባባል ይህንን ግሩም መልእክት ከማንበብና ከማጥናት ወደኋላ ሊያሸሽን አይገባም። ይሁን እንጂ በእነዚህ ምዕራፎች ላይ እንዲሁ ላይ ላዩን የሆነ ጥናት ከማድረግ መጠንቀቅ አለብን። እንዲያስተምረን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የማንደገፍ ከሆነ፥ እግዚአብሔር እንድናውቃቸው የሚፈልጋቸውን እውነቶች አንረዳም።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ያለ ጥርጥር የቆላስይስን መልእክት ትፈልጋለች። «እንደ ማንኛውም ሃይማኖት የራሱ የሆነ እውነት አለው፤ ስለዚህ ልንቀበለው ይገባል» የሚል አስተሳሰብ በሰፈነበት ዘመን ነው ያለነው። አንዳንድ ሰዎች ከተለያዩ ሃይማኖቶች ውስጥ የተሻለ የሚመስላቸውን ክፍል ቀንጭበው በመውሰድ የራሳቸውን የግል ሃይማኖት ለመፈልሰፍ ይሞክራሉ። ለብዙ ሰዎች፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከበርካታ ታላላቅ የሃይማኖት መምህራን አንዱ ነው። ከእነርሱም የበለጠ ሥልጣን የለውም። ታዋቂና ተፈላጊ ሰው ሊሆን ይችላል፤ ዳሩ ግን በምንም ዓይነት ከሁሉም በላይ አይደለም።

ይህ የ«ጥምረት» ዘመን ነው። ሰዎች የተለያዩ አሳቦችን በማስማማትና በማዋሐድ አንድ ታላቅ ሃይማኖት ለማስገኘት እየተሯሯጡ ናቸው። ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናታችን የሌሎችን እምነት ለመረዳት ባላቸው ጉጉት የራሳቸውን እምነት የመቀየጥ አደጋ እያንዣበበባቸው ይገኛል። የተመስጦ ልምምድ፥ ሕግ-አጥባቂነት፥ የምሥራቁ ዓለም ሃይማኖቶች፥ ጥልቅ መንፈሳዊ ልምምድ ለማግኘት ሲባል ራስን የማጎሳቆል መንገድ፥ እንዲሁም ሌሎች ሰው-ሠራሽ ፍልስፍናዎች በስውር ወደ አብያተ ክርስቲያናት ሰርገው እየገቡ ናቸው። እነዚህ ፍልስፍናዎች ፊት ለፊት ክርስቶስን አይቃወሙም፤ ዳሩ ግን ከሚገባው የበላይነት ዙፋን ዝቅ እያደረጉ ያስተምራሉ።

ይህንን አስደናቂ መልእክት በምናጠናበት ጊዜ፥ የጳውሎስን ማስጠንቀቂያዎች ልብ ልንል ይገባል፦ «ማንም እንዳያስታችሁ» (2፡4)፤ «ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ» (2፡8)፤ «ማንም አይፍረድባችሁ!» (2፡16)።

በቆላስይስ የተደረጉ ተአምራት

ቆላስይስ 1፡3-8

ታዋቂው እስኮትሻዊ ሰባኪ አሌክሳንደር ዋይት አድናቆታቸውን ለሌሎች ሰዎች በመግለጽ የታወቁ ነበሩ። ላደረጉላቸው በጎነት ወይም በረከት ሰዎችን በማመስገን፤ የምስጋና ካርዶችን ይልኩላቸው ነበር። በእነዚያም የምስጋና ካርዶች ላይ የሚጽፏቸው መልእክቶች ለብዙዎች ልብ በተፈላጊው ሰዓት ከፍተኛ መጽናናት አምጥተዋል። ምስጋናን መግለጽ ለነፍስ ትልቅ መድኃኒት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሌሎችን የሚያደንቅና የሚያበረታታ ነበር፤ ለዚህም ይህ የቆላስይስ መልእክት ራሱ ማስረጃ ሊሆን ይችላል። በዚህ ክፍል ላይ በቆላስይስ ክርስቲያኖች ላይ ስለተደረገው ሁሉ ለክርስቶስ ምስጋና ሲያቀርብ እንመለከታለን። (ቆላ. 1፡3-8 በግሪክኛው መጽሐፍም ረጅም ዐረፍተ ነገር ነው።) እንዲሁም በዚህ ደብዳቤ ውስጥ በሌሎች አምስት ስፍራዎች ምስጋና ያቀርባል፡- 1፡12፤ 2፡7፤ 3፡15፤ 17፤ 4፡2። ጳውሎስ ይህንን መልእክት የጻፈው በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ ነበር፤ ይህም ደግሞ የአመስጋኝነት ዝንባሌውን ይበልጥ እንድናደንቅ ያደርገናል።

እንደ ጳውሎስ ሁሉ እኛም እግዚአብሔር በሌሎች ወገኖች ሕይወት ውስጥ ስለሚፈጽመው ሥራ ምስጋና ማቅረብ ይገባናል። ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን መጠን ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ነን (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። የአንድ አካል መበርታት ሌላውን አካል ያበረታታዋል። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመነቃቃት ሕይወት ብታገኝ ይህ በረከት ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እገዛ ያደርጋል። ጳውሎስ በዚህ ምስጋናውን በገለጸበት ክፍል ውስጥ በቆላስይስ አማኞች መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ የነበሩትን የዕድገት ደረጃዎች አሳይቷል።

ወንጌሉን ስሙ (ቆላ. 1፡5-7)

የወንጌሉ የምሥራች ቃል ወደ ከተማቸው አልደረሰም ነበር። ወንጌል ለእነዚህ ሰዎች መድረስ ስለነበረበት በኤጳፍራ በኩል ተላከላቸው። ኤጳፍራ ራሱ የቆላስይስ ተወላጅ ሲሆን (4፡12-13)፥ ከጳውሎስ ጋር ተገናኝቶ ወንጌልን ከሰማ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖአል። ይህም

የሆነው ምናልባት ጳውሎስ ለሦስት ዓመታት በኤፌሶን ከተማ ባደረገው ታላቅ አገልግሎት ወቅት ሊሆን ይችላል (የሐዋ. 19፡10)።

ኤጳፍራ ደኅንነት ካገኘ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ ይህንን አስደሳች ዜና ለዘመዶቹና ለጓደኞቹ አካፈላቸው። ምናልባት ለኤጳፍራ እጅግ በርካታ አስደናቂ ነገሮች በሚፈጸሙባት በኤፌሶን ከተማ ከጳውሎስ ጋር መቆየት ሳያስደስተው አይቀርም ነበር። ዳሩ ግን የመጀመሪያ ኃላፊነቱ ወንጌሉን ለራሱ ከተማ ማድረስ ነበር (ማር. 5፡19 ይመልከቱ)።

ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ፥ በመቀበሩና በትንሣኤው የኃጢአትን ዕዳ እንዳስወገደ የሚናገር የምሥራች ነው። ወንጌል ማለት «የምሥራች» ማለት ነው። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ሰዎች ወንጌልን የፍርድና የመርገም መልእክት አድርገው ማቅረባቸው ነው።

እንደ ክርስቲያን ምስክር ሳይሆን፥ ልክ እንደ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚናገር አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ትዝ ይለኛል። ምንም እንኳ ባለማቋረጥ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው ቢወቅሰም፥ በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን ይቅርታ የሚያመለክተውን መልካም ዜና ለማካፈል ግን አልቻለም ነበር።

እኛም ከዚህ ሰው ሕይወት የምንማረው አለን። ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ለሌሎች ስንመሰክር በወንጌሉ የምሥራች ላይ ማተኮር አለብን (1ኛ ቆሮ. 15፡1-8 ይመልከቱ)። ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈው በዚህ መልእክትም ውስጥ ጳውሎስ አስደናቂ የወንጌል ባሕርያት ይገልጻል።

የወንጌሉ ዋና ትኩረት መለኮታዊ ሰውነት ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። ማዕከላዊ አካል ያደርገዋል። የዚህ መልእክት ዋና አሳብ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይነት ነው። በእርግጥም ክርስቶስ በወንጌል ውስጥ የበላይ ነው። የወገኖችን ጎብረት የሚያውኩ በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ግን የኢየሱስ ክርስቶስን የበላይነት አይቀበሉም ነበር። የእርሱን የበላይነት አለመቀበል ማለት ደግሞ ወንጌሉን ማጥፋት ማለት ነበር። ለእኛ የሞተውና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ነው። የወንጌል መልእክት የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንጂ በፍልስፍና፥ በመሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ወይም በሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባር ላይ ሊመሠረት አይችልም። መሠረቱ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ወንጌል «የእውነት ቃል» ነው (1፡5)። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ስለሆነ ልንታመንበት እንችላለን ማለት ነው። «ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ. 17፡17)። እውነት ያላቸው በርካታ መልእክቶችና አስተሳሰቦች ቢኖሩም፥ እውነት ተብሎ ሊጠራ የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ሰይጣን ሐሰተኛ ነው፤ የእርሱን ሐሰት መቀበል ማለት ደግሞ ወደ ሞት መነዳት ማለት ነው (ዮሐ. 8፡44)። ኢየሱስ እውነት ስለሆነ (ዮሐ. 14፡6) በእርሱ በመታመን ሕይወትን እናገኛለን። ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ለማጥፋት ቢታገሉም አልተሳካላቸውም። አሁንም የእውነት ቃል በስፍራው ጸንቶ ቆሞአል!

ሰው ሁሉ በአንድ ነገር ያምናል። ዳሩ ግን የእምነት መልካምነት የሚለካው አንድ ሰው ባመነበት ነገር ብቻት ነው። በገጠር የሚኖር አረማዊ የድንጋይን አምላክ ሲያመልክ፥ በከተማ የሚኖረው ሥልጡን አረማዊ ግን ገንዘብ ወይም ሀብትን ወይም ደግሞ ሥልጣንን ያመልካል። የሁለቱም እምነት ከንቱ ነው። እውነተኛ ክርስቲያን አማኝ እምነቱን የሚያደርገው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው፤ ያም እምነት በእውነት ቃል ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላው ዓይነት እምነት ሁሉ ማዳን የማይችል የጣዖትና የአስማት አምልኮ ብቻ ነው የሚሆነው።

ወንጌል የእግዚአብሔር ጸጋ መልእክት ነው (1፡6)። በክርስቲያኖች ዘንድ የተዛባ ትርጉም የሚሰጣቸው ሁለት ቃላት አሉ፤ እነዚህም ጸጋና ምሕረት ናቸው። እግዚአብሔር በጸጋው አማካይነት የማይገባኝን ሰጦታ ይሰጠኛል። በምሕረቱ ደግሞ የሚገባኝን ቅጣት አይሰጠኝም። ጸጋ ማለት ምንም ለማይገባቸው ኃጢአተኞች የሚገለጽ የእግዚአብሔር ችሮታ ነው። ወንጌል የምሥራች የሆነው ከጸጋ የተነሣ ነው። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን ፈቃደኛ ነው። የማዳን ብቃትም አለው።

ጆን ሴልደን (1584-1654) በእንግሊዝ አገር ውስጥ የታወቀ የታሪክ አዋቂና ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ሰው ነበር። ይህም ሰው 8000 መጻሕፍትን ያካተተ ቤተ መጻሕፍት የነበረውና በትምህርቱም የታወቀ ነበር። ለሞት በሚያጣጥርበት ጊዜም ለሊቀ-ጳጳስ ኡሼር፡- «ከሰው ልጆች መካከል የሚገኘውን አብዛኛውን ትምህርት ቀስሜአለሁ። ስለ ተለያዩ ርእስ ጉዳዮች የሚያወሱ አያሌ መጻሕፍትን አንብቤአለሁ። አሁን ግን ካነበብኳቸው መጻሕፍት ሁሉ ነፍሴን ላሳርፍ የምችልበት ክፍል

አላገኘሁም። በዚህ ወቅት ለነፍሴ ዕረፍት ሊሆንኝ የሚችለው ‹ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና (ቲቶ 2፡11)› የሚለው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ብቻ ነው» ብሏል።

ወንጌል ለዓለም ሁሉ ነው (1፡6)። ወጣት መጋቢ በነበርሁ ጊዜ ከምወዳቸው ሰባኪያን መካከል አንዱ የካንሳስ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ዶክተር ዋልተር ዊልሰን ነበሩ። የቆዩ እውነቶችን አዳዲስና አስደሳች አድርጎ የማቅረብ ልዩ ስጦታ ነበራቸው። አንድ ጊዜ ዮሐንስ 3፡16ን ከጠቀሱ በኋላ፥ «ለዓለም ሰዎች ሁሉ ተስማሚ የሆነ ስጦታ መስጠት ቢያስፈልጋችሁ ምን ታቀርቡ ነበር?» በማለት ጠየቁ።

ከዚያም በርካታ አማራጮችን አቀረቡና እነዚያ ስጦታዎች እንዴት ለሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ ተስማሚ ሊሆኑ እንደማይችሉ ገለጹ። መጻሕፍት እንዳይባል ብዙ ሰዎች ማንበብ አይችሉም፤ ምግብ እንዳይባል በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ሕዝቦች የሚመገቡት የተለያየ የምግብ ዓይነት ነው፤ ልብስም ቢሆን በተለያየ የአየር ጠባይ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የተለያየ የአለባበስ ባህል አላቸው። ገንዘብም ቢሰጣቸው በገንዘብ የማይገለገሉ ሰዎች አሉ። በመጨረሻም ወደ ትክክለኛው ማጠቃለያ በመምጣት፥ ወንጌል የዘላለምን ሕይወት ስለሚሰጥ ለሰው ሁሉ ተስማሚ እንደሆነ ተናገሩ። በእርግጥም ማብራሪያቸው ትክክል ነበር።

ጳውሎስ ወንጌል በዓለም ሁሉ ፍሬ እያፈራ እንደሆነ ይናገራል። በዓለም ሁሉ በየትኛውም ስፍራ ሊዘራ የሚቻለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። በተዘራበት ስፍራም ፍሬ ያፈራል። «ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ» ሊሰበክ ይችላል (ቆላ. 1፡23)። የጳውሎስ ትኩረት በ «ሰው ሁሉ» ላይ ነበር (1፡28)። ሐሰተኛ አስተማሪዎች ግን መልእክቶቻቸውን ለዓለም ሁሉ አያሰራጩም። ወንጌል ወደ ደረሰባቸው ስፍራዎች በመሄድ አማኞችን ለማሳሳት ይሞክራሉ። ለጠፉ ኃጢአተኞች የሚሆን መልካም የምሥራች የላቸውም!

ሰዎች እንዲድኑ ከተፈለገ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መስማት ያስፈልጋቸዋል። ወንጌልን እንዲሰሙ ከተፈለገም የዳንነው እኛ መልእክቱን ማድረስ አለብን። እርስዎስ የድርሻዎን እየተወጡ ይሆን?

በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል (ቆላ. 1፡4)

የእግዚአብሔር ቃል በሚሰሙት ሰዎች ሕይወት ውስጥ እምነትን የመፍጠር ኃይል ቢኖረውም፥ ሰምቶ አለማመንም ይቻላል (ሮሜ

10፡17)። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የደኅንነትን መልካም የምሥራች ሰምተው አላመኑም። ዳሩ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች የዘላለምን ሕይወት ስጦታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላሉ (ዮሐ. 3፡14-28)።

የዳንነው በእምነት ብዛት ሳይሆን፥ ነገር ግን እምነታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ብቻ ነው። ዛሬ ስለ እምነት ብዙ እንሰማለን፤ ይሁን እንጂ የሚናገሩት እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ስለማመን አይደለም። አንዳንድ ተወዳጅ ዘፈኖች እንኳ ሳይቀሩ ስለማመን ይናገራሉ። ዘመን አመጣሹ አመለካከት «ካመንህ ከፉ አይደርስብህም» የሚል ነው። ዳሩ ግን ጥያቄው «በምን ልመን?» የሚል ሲሆን፥ መልሱም «ዝም ብለህ እመን!» የሚል ይሆናል።

የዳንነው የመሠረተ ክርስትና ትምህርቶችን በማመናችንም አይደለም። ታላቁ የወንጌል አገልጋይ ጆርጅ ውትፊልድ ለአንድ ሰው ሲመሰክር ስለሆነው ታሪክ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ። ውትፊልድ ሰውዬውን «እምነትህ በምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው። ሰውዬውም «ቤተ ክርስቲያኔ የምታምነውን ነገር አምናለሁ» በማለት መለሰለት። ወንጌላዊውም «ቤተ ክርስቲያንህ የምታምነው ምንድን ነው?» ቢለው፥ «እኔ የማምነውን» በማለት መለሰለት። ተስፋ ያልቆረጠው ዋይት ፊልድ እንደገና፥ «ሁለታችሁም በምንድነው የምታምኑት?» በማለት ጠየቀው። ሰውዬውም በተሰላቸ ድምፅ «ሁለታችንም በአንድ ዓይነት ነገር ነው የምናምነው» በማለት መለሰ።

የሚያድን እምነት አእምሮን፥ ስሜትንና ፈቃድን ያካትታል። በአእምሮአችን የወንጌሉን እውነት እንረዳለን፤ በልባችንም ጽኑ እምነትና የደኅንነት አስፈላጊነት ይሰማናል፤ ዳሩ ግን ሂደቱ ፍጻሜ የሚያገኘው በፈቃደኛነት ራሳችንን ለክርስቶስ በምንሰጥበት ጊዜ ነው። መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶቹ ምንም ያህል እውነት ቢሆኑም፥ እምነት ማለት ትምህርቱን በአእምሮ መቀበል ማለት ብቻ አይደለም። እምነት ስሜታዊነት አይደለም። እምነት ማለት ራስን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት ማለት ነው።

ጆን.ጂ.ፓተን የተባሉ ሚሲዮናዊ መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ቋንቋ በሚተረጉሙበት ጊዜ፥ ማመን የሚለውን በትክክል የሚተካ ቃል ለማግኘት ብዙ ሙከራ አድርገው ነበር። በመጨረሻም የቃሉ ትርጉም

«ሁለንተናን በአንድ ነገር ላይ ማስደገፍ» መሆኑን አስተዋሉ። የሚያድን እምነት ሁለንተናን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማስደገፍ (መጣል) ማለት ነው።

የሚያድን እምነት በወንጌል ላይ የተመሠረተ ነው (ቆላ. 1:23)። ዋስትና የሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጌታ እያደግን በሄድን ቁጥር እምነታችን ይጸናል (2:5)፤ ይጠነክራልም (2:7)።

ወደ ቆላስይስ የመጡት የሐሰት አስተማሪዎች በክርስቶስና በቃሉ ላይ የተመሠረተውን የቅዱሳን እምነት ለማዳከም ሞክረው ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ ችግር ዛሬም ቢሆን የሚታይ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ዝቅ በማድረግ ወይም ደኅንነት በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ መሆኑን በመካድ ሌላ የደኅንነት መንገድ ለማቅረብ የሚፈልግ ማንኛውም የሃይማኖት ትምህርት ፀረ-ክርስትናና ከሰይጣን የመነጨ ነው።

አንድ የመጨረሻ አሳብ፦ የቆላስይስ ክርስቲያኖች ልምምድ አስደናቂ ስለ ነበር፥ ሰዎች ሁሉ ስለ ጉዳዩ ይነጋገሩ ነበር። ጳውሎስ ይህንን ከኤጳፍራ ሰማ። የሐሰት አስተማሪዎችም ሰምተው የቆላስይስን ምእመናን ለመጎብኘት ወሰኑ። ይህንንም ያደረጉት ለራሳቸው ጠቃሚ ለውጥ ለማምጣት ነበር።

አንዴ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሰው ዝም ለማለት አይችልም። የእርስዎ የክርስትና ሕይወት ሌሎችን የሚያበረታታና ለምስክርነት የሚጋብዛቸው ዓይነት ነውን? የቤተ ክርስቲያን ጎብረትዎ የማያምኑ ሰዎች እንኳ እስኪደነቁ ድረስ የሚያስደስት እንቅስቃሴ ያለው ነውን?

ደቀ መዛሙርት ሆነዋል (ቆላ. 1:7)

ኤጳፍራ የቆላስይስን ሰዎች ወደ ክርስቶስ አምጥቶ ብቻ አልተዋቸውም። ቃሉን በማስተማር በእምነታቸው እንዲበረቱ ይፈልግ ነበር። በቁጥር 7 «እንደተማራችሁ» የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ደቀ መዝሙር ከሚለው ቃል ጋር የተዛመደ ነው። ኢየሱስ «ከእኔም ተማሩ» (ማቴ. 11:29) ወይም በትምህርቴ «ደቀ መዛሙርቴ ሁኑ» በማለት ከተናገረው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነው።

እነዚህ አዳዲስ አማኞች ከእውነት ተመልሰው የሐሰት አስተማሪዎችን በመከተል አደገኛ አዝማሚያ ላይ ነበሩ። ወደ ክርስቶስ የመራቸው፥ ደቀ መዛሙርት ያደረጋቸውና ቃሉን ያስተማራቸው ኤጳፍራ እንደነበር ጳውሎስ ያስታውሳቸዋል። አስቀድማችሁ የሚለው ቃል (ቆላ.

1፡5) ምናልባት «እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ከመምጣታቸው አስቀድሞ» ለማለት የተሰነዘረ ሳይሆን አይቀርም። እንደ ቆላስይስ ሰዎች እኛም የጠፉትን ነፍሳት ለመመለስ ብቻ ሳይሆን፥ ከሌሎች መንጋዎች ውስጥ «በጎችን ለመስረቅ» ከሚመጡ የሃይማኖት መሪዎች መጠንቀቅ አለብን።

አዳዲስ ክርስቲያኖች ወደ ደቀ መዝሙርነት ደረጃ ማደግ እንዳለባቸው በፍጹም መዘንጋት የለብንም። አዲስ የተወለደ ሕፃን ለራሱ እንክብካቤ ማድረግ እስኪጀምር ድረስ የፍቅር እንክብካቤና ጥበቃ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ አዲሱ ክርስቲያንም ወደ ደቀ መዝሙርነት የሚመራውን ሰው ይፈልጋል። ታላቁ ተልእኮ የጠፉትን በማዳን ብቻ አይወሰንም፤ ምክንያቱም በዚያው ተልእኮ ውስጥ ኢየሱስ የዳኑትን ቃሉን በማስተማር እንድናሳድጋቸው አዝዞናል (ማቴ. 28፡19-20)። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጎብረት ዓላማም ይኸው ነው። አዲስ ኪዳን ዛሬ የሚታየውን ዓይነት «የግል ክርስትና» አያስተምርም። ዛሬ ሰዎች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጎን ትተው ከመጻሕፍት፥ ከሬድዮ፥ ከቴሌቭዥን፥ ወይም ከካሴቶች መንፈሳዊ ምግብን ለማግኘት ይሞክራሉ።

ኤጳፍራ ታማኝ አገልጋይ ነበር። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ብቻ ሳይሆን ቃሉን በማስተማር እንዲያድጉ ረድቶአቸዋል። እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የበሰለ ሕይወት እንዲኖራቸውም ይጸልይላቸው ነበር (ቆላ. 4፡12-13)። የሐሰት ትምህርት አደጋ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ በማንጎበጎብ ላይ በነበረበት ወቅት ኤጳፍራ ወደ ሮም በመሄድ ከጳውሎስ መንፈሳዊ ምክር ይቀበል ነበር። ሕዝቡን ይወዳቸው ስለ ነበር ጎብረቱን ሊያጠፉና መንፈሳዊ ዕድገታቸውን ሊገቱ ከሚቃጡት የሐሰት ትምህርቶች ሊጠብቃቸው ወሰነ።

ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከ260 ጊዜ በላይ ተጠቅሶአል። «እንደ ደቀ መዝሙር ለመማር» የሚለው ቃል ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ 25 ጊዜ ተጠቅሶአል። በዚያን ጊዜ ደቀ መዝሙር ሲባል ቁጭ ብሎ መምህሩ የሚያስተምረውን የሚያዳምጥ ብቻ ማለት አልነበረም። ይልቁንም ከመምህሩ ጋር እየኖረ በመስማት፥ በማየትና በመኖር የሚማር ሰው ነበር። ደቀ መዝሙርነት በትምህርት ቤት ውስጥ ከመመዝገብና የመምህሩን ገለጻ ከማዳመጥ የበለጠ ነው። ደቀ መዝሙርነት ሙሉ ለሙሉ ራስን ለመምህሩ መስጠት ማለት ነው።

በመኖር መማር ማለት ነው። ምናልባት የዘመናችን የሕክምና ወይም የሙያ ተማሪዎች የደቀ መዝሙርነትን ምንነት ለመግለጽ ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የቆሎ ተማሪዎችም የደቀ መዝሙርነትን ሕይወት አጉልተው ሊያሳዩን ይችላሉ።

ሌሎችን አማኞች ወደ ደቀ መዝሙርነት ሕይወት ለማምጣት የምንሠራ ሰዎች በጣም መጠንቀቅ አለብን። ደቀ መዝሙር የምናደርጋቸው ለራሳችን ሳይሆን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰዎች እርሱን እንዲወዱትና እንዲታዘዙት ወደ እርሱ ልናመጣቸው ይገባል። ኤጳፍራ በታማኝነት እያስተማረ ሕዝቡን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መርቶአቸዋል። የሐሰት አስተማሪዎች ግን «ደቀ መዛሙርቱን ለመሳብ» ሞከሩ። (ዶክተር ሉቃስ ስለዚህ ችግር ያስጠነቅቃል፥ የሐዋ. 20:28-30 ተመልከት።) የሰው ተፈጥሮ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ወደ መከተል ያዘነብላል። ከወንጌሉ መሠረታዊ እውነቶች ይልቅ «አንድ አዲስ ነገር» የመፈለግ አዝማሚያ ይታይበታል።

ቀጥሎ የኤጳፍራን የጥረት ውጤቶች እንመለከታለን።

በክርስቶስ የታመኑ ሆኑ (ቆላ. 1:6፥ 8)

የእግዚአብሔር ቃል ዘር ነው (ሉቃ. 8:11)። ይህም ማለት ቃሉ በውስጡ ሕይወት አለው ማለት ነው (ዕብ. 4:12)። በሰው ልብ ውስጥ በሚዘራበት ጊዜ ፍሬ ሊያፈራ ይችላል። «ይህ መልካም ዜና በእናንተ መካከል በሆነው ዓይነት በመላው ዓለም በማፍራትና በማደግ ላይ ነው» (ቆላ. 1:6 አዲስ ትርጉም)።

በለንደን ከተማ ውስጥ በሚገኝ በአንድ መካነ መቃብር ውስጥ ከሌሎች ልዩ የሆነ መቃብር አለ። ይህም የኤግኖስቲክ እምነት ተከታይ የነበረችው የእመቤት አን ግርምስተን መቃብር ነው። ይህች ሴት ከመሞቷ በፊት ለጓደኛዋ የሚከተለውን የምጸት ንግግር አሰምታ ነበር፡- «በሰውነቴ ላይ ዛፍ እንደሚበቅል፥ እኔም ደግሞ ሕያው እንደምሆን እርግጠኛ ነኝ።» የእመቤት አን ግርምስተን ከሞተች በኋላ ሕይወት እንዳለ አታምንም ነበር። ይሁንና መቃብሯ ላይ ዛፍ በቀለ። የአንድ ትንሽ ዘር ሥር እየሰደደና እያደገ፥ እብነበረዱን ከመሰንጠቁም በላይ መቃብሩን ያጣበቀውን ብረት እንኳ ሊበጣጥሰው በቅቶአል። በአንድ ዘር ውስጥ ሕይወትና ኃይል እንዳለ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ቃልም ውስጥ ከዚያ የላቀ ሕይወትና ኃይል አለ።

የእግዚአብሔር ቃል ከተተከለና ከተኮተኮተ ፍሬ ያፈራል። እምነት፥ ተስፋና ፍቅር የመንፈሳዊ መከር ፍሬዎች ናቸው። እነዚህ መንፈሳዊ ጸጋዎች አንድ ሰው በእውነት ዳግም እንደ ተወለደ ከሚያሳዩ መረጃዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው (1ኛ ተሰ. 1፡3፤ ሮሜ 5፡1-4፤ ዕብ. 6፡9-12፤ ኤፌ. 1፡13-15፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡3-9 ተመልከት)።

እምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነው (ሮሜ 10፡17)። የክርስትና ሕይወታችን በእምነት ይጀመራል። ይሁን እንጂ፥ ይህ ጅማሬ ብቻ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። በእምነት መመላለስን እንማራለን (2ኛ ቆሮ. 5፡7)። በእምነት መሥራትን እንለማመዳለን (1ኛ ተሰ. 1፡3)። ለጸሎት ኃይል የሚሰጠው እምነት ነው (ሉቃስ 17፡5-6)። እምነት እንደ እሳት ከሚንበለበሉ የሰይጣን ፍላጻዎች ጋሻ በመሆን ይከላከልልናል (ኤፌ. 6፡16)።

ፍቅር ሌላው የእውነተኛ ደኅንነት ማረጋገጫ ሲሆን፥ ያልዳነው ሰው ግን ስለራሱ ብቻ ያስባል (ኤፌ. 2፡1-3)። እነዚህ ሰዎች ቅዱሳንን ሁሉ መውደዳቸው እግዚአብሔር እንደለወጣቸውና የዘላለምን ሕይወት እንደሰጣቸው የሚያሳይ ነበር። የክርስትና ፍቅር እኛ የምናዘጋጀው ባዶ ስሜት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ የሚሠራው ነው (ቆላ. 1፡8፤ ሮሜ 5፡5)። በቆላስይስ መልእክት ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ቆላ. 1፡8 ብቻ መሆኑንና ይህም ከፍቅር ጋር በተያያዘ ሁኔታ መቅረቡን ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

ይህ ከመንፈስ ቅዱስ የመነጨ ፍቅር ለ«ቅዱሳን ሁሉ» (1፡4) የተሰጠ እንጂ ለጎብረታቸው አባላት ብቻ የተሰጠ አልነበረም። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን እኛም የእግዚአብሔርን የፍቅር ስፋት ልንረዳና ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ልንካፈለው ይገባናል (ኤፌ. 3፡17-19)። ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን እውነተኛ መንፈሳዊ አንድነት እንዲኖር አማኞች «በፍቅር መተሳሰር» አለባቸው (ቆላ. 2፡2)። አንድ የሚያደርገን ማሰሪያ ፍቅር ነው (ቆላ. 3፡14)። በሁሉም ነገር አንድ ዓይነት ሆኖ የመገኘት ሙከራ የውጫዊ ግፊት ውጤት ሲሆን፥ አንድነት ግን አንዱ ለሌላው በማሰብ ከውስጥ የሚመነጭ ስሜት ነው።

ተስፋም የአማኙ ባሕርይ ሌላው ገጽታ ነው። ያልዳኑ ሰዎች እግዚአብሔርን ስለማያውቁ (ኤፌ. 2፡11-12) ያለ ተስፋ ይኖራሉ። ከክርስቶስ ውጭ ያሉ ሰዎች ተስፋ የላቸውም (1ኛ ተሰ. 4፡13)።

መጽሐፍ ቅዱስ ተስፋ ሲል «ምናልባት» ማለቱ አይደለም። በክርስቶስ ላይ ያለን ተስፋ በክርስቶስ ላይ እንዳለን እምነት ግልጽና እርግጠኛ ነው። ክርስቶስ በውስጣችን ስላለ፥ «የክብር ተስፋ» አለን (ቆላ. 1፡27)።

የሐሰት አስተማሪዎች የቆላስይስ አማኞችን ለማወክና ከወንጌሉ ተስፋ ለማዘናጋት ሞክረው ነበር (ቆላ. 1፡23)። ዳሩ ግን ጳውሎስ ይህ ተስፋ ለአማኞች በሰማይ «እንደ ተዘጋጀላቸው» በግልጽ ይናገራል (1፡5)። «ተዘጋጅቶላችኋል» የሚለው ቃል «ለአንድ ሰው ተለይቶ የተቀመጠ» እንደ ማለት ነው። ተደብቆ በጥንቃቄ የተቀመጠ ገንዘብን ለማመልከት የተሰነዘረ ቃል ነው። የግሡ የጊዜ አመልካች እንደሚያሳየን፥ ይህ ተስፋ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተቀመጠልን ስለሆነ ምንም ነገር ሊወስድብን አይችልም። ይህ ተስፋ ለኛ ተጠብቆ ከመቀመጡ ሌላ ኢኛም አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማይ ሐሤት እንደምናደርግ እርግጠኞች ለመሆን እንድንችል በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቀን እንኖራለን! (1ኛ ጴጥ. 1፡1-5)። ለክብር ተጠብቀን እንኖራለን!

በእምነት፥ በተስፋና በፍቅር መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በመሠረቱ አንድን ሰው ይበልጥ በወደድን ቁጥር የበለጠ እናምነዋለን። ባጋጣሚ የተገናኘነውን ሰው በደንብ የምናውቀውን ሰው ያህል አናምነውም። እግዚአብሔርን ይበልጥ ባወቅነው መጠን፥ ይበልጥ እንወደዋለን፤ በበለጠም እናምነዋለን። ፍቅርና እምነት እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው።

ተስፋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። የእምነትና የፍቅር ትስስር ባለበት ስፍራ ሁሉ ተስፋም ይኖራል። አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሲፋቀሩና በዚያው ፍቅር እርስ በርሳቸው መተማመንን ሲማሩ የወደፊት ነገራቸው ዘወትር እያበበ ይሄዳል። ጳውሎስም ተስፋ ለፍቅርና ለእምነት አንቀሳቃሽ ኃይል እንደሆነ አስተምሮአል፤ «በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሣ ... ስለ እምነታችሁ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ...» (ቆላ. 1፡5) በማለት ይጽፍላቸዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስን የማየትና ከእርሱም ጋር ለመኖር ወደ መንግሥተ ሰማይ የመሄዱ የተባረከ ተስፋ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ኃይል አለው። በመንግሥተ ሰማይ የሚኖረንን ደስታ በተረዳን ቁጥር ጌታን ይበልጥ እንድንወደው ያደርገናል። ከእርሱ ጋር በክብር እንደምንኖር ማወቃችን ደግሞ የበለጠ በእርሱ እንድንታመን ያበረታታናል። በዚህ

ምድር ላይ የሚያጋጥሙን ችግሮችና መከራዎችም እንኳ ከዚያ ተስፋ እንድናፈገፍግ ሊያደርጉን አይችሉም።

ስለ ወደፊቱ የደስታ ሕይወት ግሰብ ሰዎች የበለጠ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ የማድረግ ኃይል እንዳለው ተረድቻለሁ። የገና በዓል ወይም ቤተሰብ ለሽርሽር የሚሄድበት ጊዜ ሲቃረብ የሕፃናትን ሁኔታ ልብ ብለው ያውቃሉን? ይህንን በመሰለ ሁኔታ የመንግሥተ ሰማይ ብሩህ ተስፋ እምነታችንን ያበረታታዋል፤ የፍቅር አድማሳችንንም ያሰፋዋል። የአሁኑን ሕይወታችንን ይበልጥ አስደሳች፥ የሚመጣውንም ደግሞ ይበልጥ ተናፋቂ ለማድረግ እምነትና ፍቅር አብረው ይሠራሉ።

በክርስቲያኖች መካከል የሚደረግ ክፍፍልና አለመግባባት በጣም የሚያሳዝን ነው። ይበልጥ መፈቃቀርና እርስ በርሳችን መግባባት እንደሚያስፈልገን ለማሳየት እንጂ ምንም እንከን የሌለባት የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለብን ማለቴ አይደለም። ሁላችንም በመንግሥተ ሰማይ አብረን ስለምንኖር በዚህ ምድር ላይ እርስ በርሳችን መዋደድ ይኖርብናል። ክርስቶስ ክብሩን በውስጣችን ያስቀመጠበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው። «እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ... የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ» (ዮሐ. 17፡22)። ገጣሚው እንዳስቀመጠው፡-

ከምንወዳቸው ቅዱሳን ጋር
ለዘለዓለም በላይ ስንኖር
አቤት ያለው ታላቅ ክብር!
ከምናውቃቸው ቅዱሳን ጋር
እስከ ጊዜው በምድር ስንኖር
መቼም አንቅር ከማማረር!

ክርስቶስን የማየትና ወደ መንግሥተ ሰማይ የመሄዱ ተስፋ ለፍቅርና ለእምነት ብቻ ሳይሆን፥ ለተቀደሰ አኗኗርም የሚጠቅም መነቃቂያ ነው። «በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል» (1ኛ ዮሐ. 3፡3)። ወጣት ክርስቲያን በነበርሁ ጊዜ፥ በዕድሜ የሚበልጠኝ አንድ ወዳጄ፡- «ኢየሱስ ሲመለስ የሚያሳፍርህን ነገር እየሠራህ አትገኝ!» በማለት ያስጠነቀቀኝ ነበር። ይህ ማስጠንቀቂያ የተወሰነ አግባብነት ቢኖረውም፥ ለመንግሥተ ሰማይ ተስፋ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖር ያደርጋል። በእርግጥ ዮሐንስ በክርስቶስ ባንኖር፥

(በታዛዥነት ከእርሱ ጋር ኅብረት ባናደርግ) በሚመለስበት ጊዜ ልናፍር እንደምንችል ያስጠንቅቀናል (1ኛ ዮሐ. 2፡28)።

ይሁን እንጂ ለዚህ እውነት አንድ አዎንታዊ ጎን አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ በእኛና በእርሱ መካከል ዕንቅፋት የሚሆን ነገር እንዳይገኝብን ሕይወታችንን በንጽሕና መጠበቅ አለብን። ደስታና ክብር ወደሞላበት ማደሪያው በእምነትና በፍቅር እንገባለን! ጴጥሮስ ይህን ወደ ዘላለሙ መንግሥት የመግባት «ሙሉ መብት» ይለዋል (2ኛ ጴጥ. 1፡11 አዲስ ትርጉም)።

የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ በመከራ ጊዜም ማበረታቻ ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡4-9)። አማኞች እንደመሆናችን የምናልፍበት የራሳችን የሆነ መከራ ይኖረናል። ይሁን እንጂ በመከራ ውስጥ «በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት» (1ኛ ጴጥ. 1፡8) ደስ ሊለን ይችላል። የማያምኑ ሰዎች መከራ ሲደርስባቸው ተስፋ ቆርጠው ነገር ዓለሙን ለመተው ይፈልጋሉ። ክርስቲያኖች ግን መከራ በሚቀበሉበት ጊዜ ተስፋቸው እየፈካ ስለሚሄድ፥ እምነታቸው ሊጠነክርና ፍቅራቸው ሥር ሊሰድ ይችላል።

ይህ ተስፋ እንዳለን እንዴት እናውቃለን? የተስፋ ቃሉ «በወንጌል እውነት ቃል» (ቆላ. 1፡5) ተሰጥቶናል። እኛ ክርስቲያኖች ተስፋ የሚኖረን ተስፋ ያለው ስሜት ሲሰማን ብቻ አይደለም። የማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል ተስፋችን በክርስቶስ ኢየሱስ አስተማማኝ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። እንዲያውም ይህ ተስፋ ሊናወጥ ወይም ሊነቃነቅ በማይችል መልሕቅ ተመስሏል (ዕብ. 6፡19)።

ጳውሎስ በቆላስይስ ስለሚገኙ አማኞች እግዚአብሔርን ማመስገኑ አስደናቂ አይሆንብንም። እግዚአብሔር ለጳውሎስ በኤፌሶን «ልዩ ተአምራት» ሠርቶለታል (የሐዋ. 19፡11)። ዳሩ ግን ማንኛውም ተአምር ከጠፋው ኃጢአተኛ መዳን አይበልጥም። ኤጳፍራ ታማኝ ምስክር ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር በቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ የጸጋ ተአምራትን አደረገ።

እርስዎስ የደኅንነትን ተአምራት ተለማምደው ይሆን? ከሆነ በእምነትዎ በማደግና ለጌታ ፍሬ በማፍራት ይመላለሱ። በክርስቶስ ባመኑበት ጊዜ ሕይወት የሰጠዎትን ቃል ያንኑ ሕይወት በመመገብ ታማኝና ፍሬ የበዛበት ክርስቲያን እንዲሆኑ ይረዳዎታል።

እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ የጸጋው «ወንጌል ተአምራት» እየተፈጸሙ ናቸውን?

- 3 -

የእስረኛው ጸሎት

ቆላስይስ 1፡9-12

ጳውሎስ በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ በጻፋቸው መልእክቶች ውስጥ የሚገኙ ጸሎቶች በጣም የተለዩ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ የሚጸልየው ለሌሎች እንጂ ለራሱ አልነበረም። የጸሎት ጥያቄዎቹ የሚያተኩሩት በቁሳዊ ወይም በሥጋዊ ነገሮች ላይ ሳይሆን በመንፈሳዊ በረከቶች ላይ ነበር። በእርግጥ ለሥጋዊ ወይም ለቁሳዊ ነገሮች መጸለይ ስሕተት አይደለም። ዳሩ ግን መንፈሳዊ ጉዳዮች ከሥጋዊ ነገሮች እጅግ የሚበልጥ ጠቀሜታ አላቸው።

አይተዋቸው ለማያውቋቸው ሰዎች እንዴት ይጸልያሉ? ጳውሎስ በቆላስይስ ስለነበሩት አማኞች የሚያውቀው ነገር ሁሉ ከታማኙ መጋቢያቸው ከኤጳፍራ በሰማው መሠረት ነበር። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን በመፈታተን ላይ ስለሚገኘው የሐሰት ትምህርት ሰምቶ ስለ ነበር ጸሎቱም በዚያው ችግር ላይ የሚያተኩር ነው። ጳውሎስ በጸሎቱ ውስጥ ሦስት የጸሎት ጥያቄዎችን አቅርቧል።

መንፈሳዊ እውቀት እንዲኖራቸው ጸልዮአል (ቆላ. 1፡9)

የቆላስይስ አማኞች አዳዲሶቹን ትምህርቶች ከተቀበሉ «እውቀት»ን እንደሚያገኙ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎቹ ተስፋ ሰጥተዋቸው ነበር። እውቀት፥ ጥበብ፥ እና መንፈሳዊ ማስተዋልን የመሳሰሉ ቃላት ከሃይማኖታዊ ቋንቋቸው ውስጥ ይገኙ ስለ ነበር፥ ጳውሎስ እነዚህኑ ቃላት በጸሎቱ ውስጥ ይጠቅሳቸዋል።

ሰይጣን በጣም አታላይ ነው! በመሆኑም ለማሳሳት እንዲያመቸው በክርስቲያናዊ ቃላት ይጠቀማል። ይሁን እንጂ ክርስቲያናዊ መዝገበ ቃላት በሚሰጣቸው ፍቺ አይደለም የሚጠቀምባቸው። ከረዥም ዘመን በፊት የሐሰት አስተማሪዎች እነዚህን ቃላት ለራሳቸው እንደሚስማሙ አድርገው ተጠቅመውባቸዋል። ቃላቱ ግን ቀድሞውኑ በክርስትና እምነት ውስጥ የነበሩ ናቸው።

«ስለዚሁ» የሚለው ሐረግ፥ ጳውሎስ በቁ. 6 «የእግዚአብሔርንም ጸጋ በእውነት ከሰማችሁበትና ካወቃችሁበት ...» በማለት ካሰፈረው ጸሎት ጋር ይያያዛል። ጳውሎስ እነዚህ ክርስቲያኖች በእርግጥ ክርስቶስን እንደሚያውቁና ዳግም እንደተወለዱ የሰማው ከኤጳፍራ ምስክርነት ነበር። ዳሩ ግን ከእርሱና ስለ እርሱ መማር የሚገባቸው ገና ብዙ ነገሮች ነበሩ። ጳውሎስ «በተቀበላችሁት እውነት ማደግ እንጂ አዲስ የተለየ መንፈሳዊ ልምምድ አያስፈልጋችሁም» እያለ ነበር የሚጽፍላቸው።

አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ በሚወለድበት ጊዜ ለእድገትና ለብስለት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ አሟልቶ ነው የሚወለደው። የቆላስይስ መልእክትም ዐቢይ አሳብ ይኸው ነው፡- «በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል» (2፡10)። ከአዲስ ልደት በቀር ሌላ ልምምድ አስፈላጊ አይደለም። እንዲህ በማለት ቤተ ክርስቲያንን ያስጠነቅቃል፡- «በመጀመሪያ በተቀበላችሁት እውነት ማደጋችሁን ቀጥሉ እንጂ ሌላ አዲስ ነገር አትፈልጉ» (ይህ የደራሲው አገላለጽ ነው)።

እያንዳንዱ አማኝ «የፈቃዱ እውቀት» ሊኖረው ይገባል። በዚህ ክፍል «እውቀት» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «ሙሉ እውቀት» የሚል ትርጉምን ነው የሚያመለክተው። ሁልጊዜም ለሕይወታችን ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱ በይበልጥ የምንማረው ነገር አለ። ወደተሟላ የእውቀት ደረጃ ላይ «እንደደረሰ»ና ከዚህም በላይ መማር እንደማያስፈልገው ለመናገር የሚደፍር ክርስቲያን ከቶውንም ሊኖር አይችልም። በ «ዓለም ታሪክ» ላይ የ10 ገጽ ዘገባዎችን እንዳቀረበው የኮሌጅ ተማሪ፥ «አውቄ ጨርሻለሁ» የሚል ክርስቲያንም ቢኖር አላዋቂነቱን መግለጹ ነው።

ለተሳካ ክርስቲያናዊ ሕይወት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናውቅና (የሐዋ. 22፡14) እንድንረዳ (ኤፌ. 5፡17) ይፈልጋል። እግዚአብሔር በሩቅ ሆኖ ትእዛዛትን የሚሰጥና የሰጠውንም መመሪያ ፈጽሞ የማያብራራ አምባገነን አምላክ አይደለም። ወዳጆቹ ስለሆንን ምን እንደሚያደርግና ለምን እንደሚያደርግ ልናውቅ እንችላለን (ዮሐ. 15፡13-15)። ቃሉን በምናጠናበትና በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስላለው ፈቃድ አዳዲስና አስደናቂ እውነቶችን ይገልጽልናል።

«ሙላት» የሚለው ቃል በቆላስይስ መልእክት ውስጥ ዋነኛ ቃል ነው። ይህ ቃል የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያንን ባጥለቀለቁ የሐሰት ትምህርቶች ውስጥም ደግሞ ቁልፍ ቃል ነበር። ጳውሎስ ይህንን ቃል ብዙ ጊዜ ተጠቅሞታል (ቆላ. 1፡19፥ 25፤ 2፡2፥ 9-10፤ 4፡12፥ 17)። ቃሉ የተሟላ እውቀትንና የተሟላ ዝግጅትን ያመለክታል። ለጉዞ የተዘጋጀውን መርከብ ለመግለጽ ያገለግል ነበር። አማኙ ለሕይወት ጉዞው የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በክርስቶስ በኩል ተሟልቶለታል። «በእርሱ [በክርስቶስ] ሆናችሁ ተሞልታችኋል» (2፡10)። «እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና» (ዮሐ. 1፡16)።

በአዲስ ኪዳን ቋንቋ መሞላት ማለት «በአንድ ነገር ቁጥጥር ሥር መዋል» ማለት ነው። በቁጣ ስንሞላ በቁጣ ቁጥጥር ሥር እንሆናለን። «በመንፈስ መሞላት» (ኤፌ. 5፡18) ማለት «በመንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆን» ማለት ነው። ስለሆነም የጳውሎስ ጸሎት እነዚህ አማኞች በእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ እውቀት ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ ነው።

ዳሩ ግን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አማኞች በእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ እውቀት ማደግ የሚችሉት እንዴት ነው? ጳውሎስ በቁጥር 9 መደምደሚያ ላይ የተጠቀመባቸው ቃላት መልሱን ይሰጡናል፡- «በጥበብ ሁሉና በመንፈሳዊ ማስተዋል» (ቀጥተኛ ትርጉም)። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት እንረዳለን። ራሳችንን ለእርሱ ቁጥጥር በሰጠን መጠን መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል (ዮሐ. 14፡26፤ 16፡13)። ስንጸልይና የእግዚአብሔርን እውነት በቅንነት ስንሻ በመንፈሱ አማካኝነት የሚያስፈልገንን ጥበብና ጥልቅ ማስተዋልን ይሰጠናል (ኤፌ. 1፡17)።

እግዚአብሔር ለልጆቹ ሁሉ ያለው አጠቃላይ ፈቃድ በቃሉ ውስጥ በግልጽ ተቀምጦአል። ለማንኛውም ዓይነት ሁኔታ በተናጠል የሚሰጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ በቃሉ ውስጥ ከገለጸው እውነት ጋር መስማማት አለበት። የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ይበልጥ በተረዳን ቁጥር ለዕለታዊ ሕይወታችን የሚሰጠንን ምሪቶች ለመወሰን የበለጠ ይቀለናል። ጳውሎስ የቆላስይስ አማኞች ራእዮችን እንዲፈልጉ ወይም ድምፆችን እንዲጠብቁ አላበረታታቸውም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት እንዲረዱና በዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተመለከተ ታላቅ ጥበብና ማስተዋል እንዲያገኙ ይጸልያል። «ጥበብ ሁሉ» እንዲኖራቸው

ይፈልጋል። ይህም ሁሉንም ነገር ያውቃሉ ማለት ሳይሆን ውሳኔዎችን ለማስተላለፍና እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ለመኖር የሚያስፈልግ ጥበብ ሁሉ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

መንፈሳዊ እውቀት ለተሳካና ፍሬያማ የክርስትና ሕይወት የመጀመሪያ ደረጃ ነው። እግዚአብሔርን ባለማወቅ ሁኔታ ላይ ምርቃት የለውም። አንድ ጊዜ አንድ ሰባኪ እንዲህ እያለ ሲናገር ሰማሁ፡- «በፍጹም ወደ ትምህርት ቤት ሄጄ አላውቅም። እኔ መሐይም ክርስቲያን ነኝ። በዚህም ደስ ይለኛል።» አንድ ሰው መንፈሳዊ እውቀት ለማግኘት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የግድ አያስፈልገውም፤ ደግሞ ባለመማሩም ብዙ መደነቅ አያስፈልገውም።

እንደ ቻርልስ ስፐርጀን፥ ጂ. ካምበል ሞርጋን እና ኤች.ኤ. አይረንሳይድ የመሳሰሉ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ትምህርት ቤት ገብተው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሥልጠና ለመውሰድ ዕድል አላገኙም፤ ዳሩ ግን ጊዜያቸውን በጥናት በማሳለፍ፥ ያጠኑትን በማሰላሰልና በጸሎት ጥልቅ ምሥጢራቱን የተረዱ፥ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ የቃሉ ተማሪዎች ነበሩ። ወደ ሕይወት ሙላት የመጀመሪያው ደረጃ መንፈሳዊ እውቀት ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ በእግዚአብሔር ፈቃድ ማደግ ማለት ነው።

ተግባራዊ የመታዘዝ ሕይወት እንዲኖራቸው ይጸልያል (ቆላ. 1፡10)

በቆላስይስ የሚገኙ የሐሰት አስተማሪዎች «መንፈሳዊ እውቀት» እንሰጣለን በማለት ሕዝቡን ያታልሉ ነበር። ዳሩ ግን ይህንን እውቀት ከሕይወት ጋር ለማዛመድ አልቻሉም ነበር። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እውቀትና መታዘዝ የማይነጣጠሉ ናቸው። በመማርና በመኖር መካከል ልዩነት አይኖርም። ጳውሎስ የጸለየበት ጥበብ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊ እውቀቶችን በአእምሮ ማካበት አይደለም (1፡28፤ 2፡3፤ 3፡16፤ 4፡5 ተመልከት)። እውነተኛ መንፈሳዊ ጥበብ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ ለውጥ ማምጣት አለበት። ጥበብና ተግባራዊ እውቀት አብረው መሄድ አለባቸው (ዘጸ. 31፡3፤ ዘዳ. 4፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡19 ተመልከት)።

በመጋቢነት አገልግሎቴ «የመጽሐፍ ቅዱስን ጥልቅ እውነቶች ብቻ በማጥናት» ጊዜያቸውን ባንድ ርእስ ላይ ብቻ የሚያጠፉ ሰዎች

አጋጥመውኛል። እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የተለያዩ መጻሕፍትን ያነበቡ፥ ወይም ደግሞ የአንዳንድ መምህራንን የካሴት መልእክቶች አዳምጠው ይሆናል። ከዚህም የተነሣ ስለ ክርስትና ሕይወት መታወቅ የሚገባውን ሁሉ አጠናቅቀው የጨረሱ ይመስላቸዋል፤ ግን ደንቁረዋል! ይህ «ጥልቅ እውቀት» ከተግባራዊ የክርስቲያን አኗኗር ሲያዘናጋቸው እንጂ ሲጠቅማቸው አይታይም። ለክርስቶስ የተሰጠ የሚቃጠል ልብ (ሉቃስ 24፡32) ከማግኘት ይልቅ እውቀት ብቻ ይሆኑና በቤታቸውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮችን መፍጠር ይጀምራሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ሁሉ ተግባራዊ እንጂ በቃል አውርተን የምናልፋቸው «ቲዎሪ» አይደሉም። በእውቀት የምናድግ ከሆነ፥ በጸጋም ማደግ አለብን (2ኛ ጴጥ. 3፡18)።

መራመድና መሥራት የሚሉ ሁለት ቃላት የክርስትናን ሕይወት ተግባራዊነት በአጭሩም ቢሆን ሊገልጹ ይችላሉ። ቅደም ተከተሉ አስፈላጊ ነው፤ በመጀመሪያ ጥበብ፥ ከዚያ መራመድ፥ ከዚያም መሥራት። ከእግዚአብሔር ጋር እየተራመድሁ ካለሆነ ለእርሱ ልሠራለት አልችልም። ፈቃዱን የማላውቅ ከሆነ ደግሞ ከእርሱ ጋር ልራመድ አልችልም። በየዕለቱ ቃሉን በማጥናትና በጸሎት የሚተጋ አማኝ (የሐዋ. 6፡4) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ከእርሱ ጋር ሊራመድና ለእርሱ ሊሠራ ይችላል።

ነገር ግን እኮ፥ የሕይወታችን ዓላማ ራሳችንን ማስደሰት ሳይሆን ጌታን ማስደሰት ነው። ለመጠራታችንና (ኤፌ. 4፡1) ለወንጌሉ (ፊልጵ. 1፡27) እንደሚገባ ልንመላለስ ይጠበቅብናል። ይህም ማለት ለእግዚአብሔር እንደሚገባ እንመላለሳለን ማለት ነው (1ኛ ተሰ. 2፡12)። ባጭሩ እግዚአብሔርን ለማስደሰት መመላለስ አለብን (1ኛ ተሰ. 4፡1)።

ለእግዚአብሔር የምንሠራው እኛ አይደለንም፤ ዳሩ ግን የጸጋውን ፍሬ ለማፍራት በእኛ ውስጥና በእኛ አማካኝነት የሚሠራው እግዚአብሔር ራሱ ነው (ፊልጵ. 2፡12-13)። የአንድ ክርስቲያን አገልግሎት የሚለካው ራሱን ለጌታ በሰጠበት መጠን ነው። የምንፈጽመው ሥራ ከምንኖረው ሕይወት የሚመነጭ ነው። ፍሬ ለማፍራት የምንችለው በክርስቶስ ውስጥ በመሆን ነው (ዮሐ. 15፡11-17)

እግዚአብሔር ሥራውን ከመሥራቱ በፊት ሠራተኛውን መቅረጽ አለበት። እግዚአብሔር ዮሴፍን በግብፅ ለሚጠብቀው አገልግሎት 13

ዓመታት ያህል አዘጋጅቶታል። የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ ደግሞ ሙሴን ለ80 ዓመታት አዘጋጅቶታል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት ፍሬ እንደሚያፈሩ ለማስተማር 3 ዓመታት ሲያሳልፍ፥ የተማረው ሐዋርያ ጳውሎስ እንኳን እግዚአብሔርን በሙላት ከማገልገሉ በፊት በዐረብ በረሃ የ«ድህረ-ምረቃ ኮርስ» መከታተል አስፈልጎት ነበር። አንድ አዲስ የተወለደ ሕፃን በለቅሶ ሕልውናውን ይገልጻል እንጂ ሊሠራ አይችልም። አንድ አዲስ ክርስቲያን ለክርስቶስ ሊመሰክርና ነፍሳትን ሊማርክ ይችላል፤ ዳሩ ግን ኃላፊነትን በሚጠይቅ የአገልግሎት ስፍራ ከመቀመጡ በፊት የእግዚአብሔርን ጥበብ ስለሚማርበትና ስለሚመላለስበት ሁኔታ ትምህርት ሊሰጠው ይገባል።

የእግዚአብሔር ጥበብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጻል። ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስንታዘዝ ለእርሱ ልንሠራና ፍሬ ልናፈራ እንችላለን። «በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራን» (ቆላ. 1፡10) እንጂ እግዚአብሔርን በአጋጣሚ አልፎ አልፎ ብቻ አናገለግልም። ዳሩ ግን ከዚህ የሚመጣ የተባረከ ውጤት አለ፤ እርሱም፡- «በእግዚአብሔር እውቀት ማደግ» ነው (ቁ. 10)። ከእግዚአብሔር ጋር ስንራመድና ለእግዚአብሔር ስንሠራ የበለጠ እያወቅነው እንሄዳለን።

የክርስትና ሕይወታችን ሚዛናዊነት ያስፈልገዋል። በግል ሕይወታችን ስንጸልይና በቃሉ ላይ ስናሰላስል እግዚአብሔርን በበለጠ እንደምናውቀው እርግጥ ነው። እንዲሁም በዕለታዊ ሕይወታችን ሌሎችን ወደ እርሱ በማምጣትና ሕዝቡንም በመሪዳት ስንመላለስ ደግሞ እያወቅነው እንድሄዳለን።

አምልኮና አገልግሎት የሚፎካከሩ ነገሮች ሳይሆኑ ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው። ጌታችን በምድር ላይ በሚያገለግልበት ወቅት አገልግሎቱን አቁሞ ይጸልይ ነበር፤ ከጸሎትም ወደ አገልግሎት ይሄድ ነበር። እኛም በተግባር ሊገለጹ የማይችሉትን ሰመመንና ከንቱ ሥጋዊ ስሜታዊነትን ማስወገድ ይገባናል። ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ጊዜ ባሳለፍን መጠን፥ እርሱንና ለሕይወታችን ያለውን ፈቃድ ይበልጥ እየተረዳን እንመጣለን፤ እንዲሁም እርሱን በመታዘዝ ስንመላለስ ደግሞ ይበልጥ እየተማርን እንሄዳለን።

በተግባር የሚገለጽ ታዛዥነት ማለት እግዚአብሔርን ማስደሰት፥ ማገልገልና እርሱን በበለጠ ማወቅ ማለት ነው። ማንኛውንም አማኝ በዙሪያው ካለው ዓለም የሚያገለው ትምህርት መንፈሳዊ ትምህርት ሊሆን

አይችልም። ወንጌላዊ ዲ.ኤል. ሙዲ ብዙውን ጊዜ፡- «እያንዳንዱ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሱን በመጫማት መመላለስ አለበት» ይሉ ነበር። ጳውሎስም በዚህ አሳብ ይስማማል።

ጳውሎስ መንፈሳዊ እውቀት እንዲኖረንና ይህም እውቀት በተግባር የሚታይ መታዘዝን እንዲያስከትል ይጸልይ ነበር። እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸውን ሁለት ርእሶች የሚያሟላ ሌላ ሦስተኛ አስፈላጊ ነገር አለ፤ ያለ እርሱ የክርስትና ሕይወት የተሟላ ሊሆን አይችልም።

ሰናይ ምግባር እንዲኖራቸው ጸለየ (ቆላ. 1፡11-12)

ጥበብና ጠባይ ከመልካም ሥነ-ምግባር ጋር ምንጊዜም መዛመድ አለባቸው። ዛሬ በወንጌል አገልግሎታችን ውስጥ ከሚታዩ ታላላቅ ችግሮች አንዱ እነዚህን አስፈላጊ ነገሮች ማለትም «መንፈሳዊ እውቀት» እና የ«ክርስቲያን አገልግሎት» ከግል መልካም ባሕርይ ጋር ሳያገናኙ መቅረታቸው ነው። ያላቸውን ተዛምዶ በመዘንጋት በመንፈሳዊ እውቀትና አገልግሎት ላይ ብቻ ትኩረት ይደረጋል።

ለምሳሌ አንዳንድ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች የእግዚአብሔር ጥበብ እንዳላቸው ይናገራሉ። ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች እንደ ፍቅር፥ ቸርነትና የክርስትናን ሕይወት ውብና የተለየ የሚያደርጉ ሌሎች ባሕርያት ይጎድሉዋቸዋል። አንዳንድ «ነፍሳትን በመማረክ» የታወቁ ክርስቲያኖችም እንኳ እግዚአብሔርን በማገልገሉ ሥራ ስለሚጣደፉ፥ ሐቅን ለማጣራት ጊዜ ስለማይኖራቸው ስለ ሌሎች ክርስቲያኖች ከእውነት የራቁ ወሬዎችን ያሰራጫሉ። ለጥቂት ወራት አንድ የተወሰነ የሃይማኖት የጎትመት ውጤት ሳነብ ነበር። ዳሩ ግን «በአዘጋጁ የደብዳቤ» ዓምድ ላይ (ከምስጋና በቀር) የተጻፉ ነገሮች እንደሌሉና ለፊጸሙት ስሕተት ማረሚያ ወይም ይቅርታ ያዘሉ ዓረፍተ ነገሮች እንዳላሰፈሩ ስመለከት፥ ይህን መጽሔት ማንበብ አቆምሁ።

ሁልጊዜም እውቀት፥ ጠባይ፥ አገልግሎትና መልካም ባሕርይ አብረው መሄድ አለባቸው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለምናውቅ እንታዘዘዋለን። በመታዘዛችንም እርሱን እያገለገልን በክርስቲያናዊ ባሕርይ እናድጋለን። ማናችንም ብንሆን በእነዚህ አራት ነጥቦች ሙሉ ለሙሉ ሚዛናዊነት ቢጎድለንም በተቻለን መጠን ሚዛናዊ ለመሆን መጣር አለብን።

በኃይል የሚያስታጥቀን የእግዚአብሔር ጉልበት ነው። ቁጥር 10-12 እንዲህ ይላል፡- «እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ ...»። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጉልበት ለመግለጽ ሁለት የተለያዩ የግሪክ ቃላት ተጠቅሞአል፤ እነርሱም፡- «ዱናሚስ» ማለትም «አብሮ የተፈጠረ ኃይል» እና «ክራቶስ» ማለትም «በተግባር የሚገለጽ ኃይል» ማለትም በሥራ ላይ ሲውል የሚታይ ኃይል የሚሉ ናቸው። የክርስትና ሕይወታችን ጸጋ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ የሚሠራው ሥራ ውጤት ነው። መንፈሳዊ እድገትና ብስለት ሊመጣ የሚችለው ራሳችንን ለእግዚአብሔር ኃይል አሳልፈን ስንሰጥና በውስጣችን እንዲሠራ ስንፈቅድ ብቻ ነው።

ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጸው በታላላቅ ነገሮች ውስጥ ብቻ ይመስለናል። እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን ሲያቋርጡ፥ ዳዊት ድልን የተቀዳጀ ሠራዊት ሲመራ፥ ወይም ጳውሎስ ሙታንን ሲያስነሣ በምንመለከትበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ የእግዚአብሔር ክብር እንደሚገለጽ አድርገን እናስባለን። በዚህ ስፍራ ትኩረት የተደረገው ግን ትዕግሥት፥ ራስን መግዛት፥ ደስታና ምስጋና በመሳሰሉ ክርስቲያናዊ ባሕርያት ላይ ነው። ውስጣዊ የነፍስ ድሎች በታሪክ ውስጥ ከተመዘገቡት የአደባባይ ድሎች የሚበልጡ እንጂ የሚያንሱ አይደሉም። ጎልያድን በጦር ኃይል ድል ከማድረግ ይልቅ ይሰድበውና ያዋርደው የነበረውን ሳሚን በትዕግሥት ማለፍ ለዳዊት የበለጠ ድል ነበር። መታገሥ ጎሊያድን ከመጣል የበለጠ ድል ነበር (2ኛ ሳሙ. 16፡5-13)። «ኃይለኛ ከመሆን ይልቅ፥ ታጋሽ መሆን ይሻላል፤ ብዙ ከተሞችን በጦርነት ድል ነሥቶ ከመያዝ ይልቅ፥ ራስን መቆጣጠር ይበልጣል»። (ምሳሌ 16፡32 አዲስ ትርጉም)።

ትዕግሥት የሚለው ቃል «ሁኔታዎች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ ጸንቶ መቆም» ማለት ነው። ቃሉ የተሰፋ መቁረጥ ተቃራኒ ነው። ይህ ቃል እግዚአብሔርን ፈጽሞ የሚመለከት አይደልም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ምንም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ስለማያጋጥሙት ነው። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም (ኤር. 32፡27)።

ትዕግሥት የበሳል ክርስቲያን ባሕርይ ነው። ትዕግሥትን ካልተማርን ሌላ ነገር ለመማር አንችልም። አማኞች እንደመሆናችን መጠን በመከራችን እንኳን ልንደሰት እንችላለን። ምክንያቱም «መከራ ትዕግሥትን እንደሚያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን

እንደሚያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን» (ሮሜ 5፡3-4)።

ትዕግሥት ቸልተኝነት ማለት አይደለም። ትዕግሥት በተግባር ላይ ጸንቶ መቆም ማለት ነው። ሁሉንም ነገር እግዚአብሔር እስኪያደርግልን ድረስ እጆቻችንን አጣጥፈን መቀመጥ ትዕግሥት አይደለም። ጉዞው አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ለፍልሚያ ተዘጋጅቶ የሚቆምን ወታደር የሚያመለክት ነው። ድል ለመቀዳጀት ካለው ጉጉት የተነሣ ለአፍታ እንኳ ለመዘናጋት የማይፈልግ ሯጭን ይገልጻል (ዕብ. 12፡1)።

እጅግ በርካታ ክርስቲያኖች ሁኔታዎች አስቸጋሪ ሲሆኑባቸው ከሩጫው ሜዳ አቋርጦ የመውጣት ዝንባሌ ይታይባቸዋል። የቀድሞው የዊተን ኮሌጅ (ኢሊኖይ) ፕሬዝዴንት የነበሩት ዶክተር ቪ. ሬይሞንድ ኤድማን ተማሪዎችን «ተስፋ ለመቁረጥ ጊዜው ገና ነው» በማለት ይናገሩ ነበር።

በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ ስሆን ብዙ ጊዜ ስለዚህ ዓረፍተ ነገር አስባለሁ። ለድል ዋስትና የሚሰጠን ትዕግሥት እንጂ ያለን ችሎታ ወይም ያገኘነው ሥልጠና አይደለም። ቻርልስ ስፐርጅን፡- «ቀንድ-አውጣ በትዕግሥት በመጓዝዋ ወደ ኖኅ መርከብ ወጣች» ብለዋል።

ከትዕግሥት ጎን ራስን መግዛትም ያስፈልገናል። የዚህ ቃል ትርጉም «ራስን መቆጣጠር» የሚል ሲሆን የብቀላ ተቃራኒ ነው። ትዕግሥት በይበልጥ ከሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ ራስን መግዛት ግን ከሰዎች ጋር ይያያዛል። እግዚአብሔር ከፍቅሩና ከጸጋው የተነሣ የሰዎችን ሁኔታ በትዕግሥት ይመለከታል (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። ራስን መግዛት ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ ነው (ገላ. 5፡22)። የአማኝ ነፍስ ልትለብሰው ከሚገባት «ከጸጋ አልባሳት» ውስጥ አንዱ ነው (ቆላ. 3፡12)።

አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በትዕግሥት ያለፉ ሰዎች የቅርብ ጓደኞቻቸውንና ወዳጆቻቸውን መታገሥ እንዴት እንደሚሳናቸው ሳስብ በጣም ነው የሚገርመኝ። ሙሴ በግብፅ ከፈረዖን ጋር በተከራከረበት ጊዜ ትዕግሥት ነበረው፤ ዳሩ ግን ከገዛ ሕዝቡ ጋር በተጋጨ ጊዜ ትዕግሥት በማጣቱ ወደ ተስፋዩቱ ምድር የመግባት መብቱን አጣ (ዘኁ. 20)። «ቅጥር እንደሌላት እንደፈረሰች ከተማ፥ መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው» (ምሳሌ 25፡28)።

በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን ከሆነ ትዕግሥትና ራስን መግዛት ጎን ለጎን ይሄዳሉ። ጳውሎስ እነዚህን ባሕርያት የእውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ ምልክቶች እንደሆኑ ዘርዝሮአቸዋል (2ኛ ቆሮ. 6፡4-6)። በግል ሕይወቱም እነዚህን ጸጋዎች አሳይቶአል (2ኛ ጢሞ. 3፡10)። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለትዕግሥትና ራስን ለመግዛት ታላቅ ምሳሌ የሚሆነን ኢዮብ ነው (ያዕ. 5፡10-11)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን እናገኛለን።

በፍጥረት ውስጥ የሚገኘው ነገር ሁሉ ትእዛዙን ስለሚጠብቅ፥ ተአምራትን ማድረግ ለእግዚአብሔር ቀላል ነገር ነው። ኢየሱስ የማልኮስን ተቆርጦ የወደቀ ጆሮ መፈወስ ሲችል፥ የጴጥሮስን ልብ ሊለውጥና በውስጡ የነበረውን ጥላቻና ዓመፅ ግን በቅጽበት ሊያስወግድ አልቻልም ነበር (ሉቃስ 22፡50-51)። እግዚአብሔር ውኃን ከዓለት ሊያወጣ ሲችል፥ ሙሴ ታጋሽ እንዲሆን ግን ሊያስገድደው አልቻለም ነበር።

አንድ መጋቢ ከፍተኛ የቃጠሎ አደጋ የደረሰበትን ወጣት ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ይጎበኝ ነበር። ወጣቱ አሁንም ለሰዓታት መተኛት የግድ ያስፈልገው ነበርና ለሕይወት የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ነገሮች እንኳን ማሟላት እጅግ ያስቸግረው ነበር።

አንድ ቀን ወጣቱ ለመጋቢው፡- «እግዚአብሔር ተአምር ሠርቶ ቢፈውሰኝ ደስ ይለኛል» አለው።

መጋቢውም መልሶ፡- «አንተ የምትፈልገውን ዓይነት ባይሆንም፥ እግዚአብሔር ተአምር እያደረገ ነው። በነዚህ ሳምንታት ውስጥ በትዕግሥትና በቸርነት እያደግህ ስትሄድ አይቻለሁ። ያ ለኔ ከአካላዊ ፈውስ ይልቅ የሚበልጥ ተአምር ነው» አለው።

የእግዚአብሔር ኃይል በሕይወታችን የሚታየው በትዕግሥትና ራስን በመግዛት ብቻ ሳይሆን በደስተኛነታችንም ጭምር ነው። ሁኔታዎች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ ደስታ የሞላበትን ትዕግሥት ማሳየት አለብን፤ ከአስቸጋሪ ሰዎች ጋር ስንኖር እንኳ ራስን በመግዛትና በደስታ ልንቀበላቸው ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ደስታ የለሽ ትዕግሥት ሊኖረን ይችላል። «ያለ ደስታ ነገርን ችሎ የሚያሳልፍ» ትዕግሥት አለ። ጳውሎስ የቆላስይስ ክርስቲያኖች ደስታ ያለበትን ትዕግሥትና ራስ-መግዛት እንዲለማመዱ ይጸልይላቸዋል።

ብዙ ጊዜ ደስታና ሐሜት የሚሉትን ቃላት እየለዋወጥን እንጠቀምባቸዋለን። ይሁን እንጂ በሁለቱ ቃላት መካከል ልዩነት አለ። ደስታ ብዙውን ጊዜ በክስተቶች ላይ ይደገፋል። ሁኔታዎች ተስፋ የሚጣልባቸው ዓይነት ከሆኑና በዙሪያችን የሚገኙ ሰዎች በቸርነት የተሞሉ ከሆኑ ደስተኞች ነን። ዳሩ ግን ሐሜት በሰዎችም ሆነ በሁኔታዎች ላይ አይደገፍም። ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክቶች ሁሉ ሐሴት የሞላበት መልእክት ለፊልጵስዩስ ሰዎች የጻፈው ነው። የጻፈውም በወኅኒ ቤት ሆኖ ለእምነቱ መሥዋዕትነትን እየተቀበለ በነበረበት ወቅት ነበር።

በሚያስቸግሩ ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍና ችግር ባለባቸው ሕዝቦች መካከል ስንመላለስ ደስታ ሊሰጠን የሚችለው በውስጣችን የሚሠራው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። «የመንፈስ ፍሬ ... ደስታ ነው» (ገላ. 5:22)። እኛ ራሳችን ደስታን «የምንፈጥረው» ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ራሱ በውስጣችን የሚሠራው ሥራ ነው። «በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ» ነው (ሮሜ 14:17)።

ከገጠሙኝ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሣ ለሽንፈትና ለተስፋ መቁረጥ የተቃረብሁባቸውን ወቅቶች አስታውሳቸዋለሁ። ይሁንና ልቤ ከእግዚአብሔር ብቻ ሊመጣ በሚችል መንፈሳዊ ደስታ ተሞልቶ ነበር። እንዲሁም ደግሞ ዙሪያዩን በከበቡኝ ችግሮች ውስጥ ተዘፍቄ ደስታንና ድልን ያጣሁባቸውን (እጅግ በርካታ!) ጊዜያት በሐዘኔታ አስታውሳለሁ።

የእግዚአብሔር ኃይል በሕይወታችን ውስጥ የመኖሩ አራተኛው ማስረጃ ደግሞ ምስጋና ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ክርስቲያኖች ደስተኞችና አመስጋኞች ናቸው (ኤፌ. 5:18-20)። ደስታችንን ስናጣ ማጉረምረምና በሌሎች ላይ መፍረድ እንጀምራለን።

የቆላስይስ መልእክት በምስጋና የተሞላ መልእክት ነው። ጳውሎስ በቆላስይስ ስለነበረችው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ያመሰግንና (ቆላ. 1:3)፥ ደግሞ ራሳቸውም እግዚአብሔርን በማመስገን ሕይወት እንዲያድጉ ይጸልይላቸው ነበር (1:12)። የክርስቲያን ሕይወት በምስጋና የተሞላ ሕይወት መሆን አለበት (2:7)። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ውስጥ መንፈሳዊ ዕድገትን ከሚያሳዩ ማስረጃዎች አንዱ ምስጋና ነው (3:15-17)። የሁልጊዜ ጸሎታችን ምስጋናን ማካተት አለበት (4:2)። በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ የተሞላ፥ እንዲሁም በጸሎት የሚተጋ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በማወደስና በማመስገን ዝንባሌው ይህንን ያረጋግጣል።

አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮአቸው አመስጋኞች ሲሆኑ ሌሎች ግን አይደሉም፤ በመሆኑም በተለይ እነዚህ የጓለኞቹ ምስጋና ማቅረብን እንዲለማመዱ የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልጋቸዋል። መልካም ስጦታ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሚመጣና (ያዕ. 1፡17) የሥነ- መለኮት ምሁራን እንዳስቀመጡት እርሱ «የነገሮች ሁሉ ምንጭ፥ ድጋፍና ፍጻሜ» እንደሆነ ልናስታውስ ይገባል። የምንተነፍሰው አየር እንኳ እግዚአብሔር በነጻ የሰጠን ስጦታ ነው።

በእቨንስተን እልኖይ ያለው ኖርዝዌስተርን ዩኒቨርስቲ ከቤቴ ቅርብ ነው። ከዓመታት በፊት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች በሚሽገን ሐይቅ ላይ በጀልባ የሚጓዙትን ሰዎች ረዱ፤ የሕይወት አድን ቡድኖች ነበሩአቸውና። ሴፕቴምበር (መስከረም) 8 ቀን 1860 ዓ.ም. ሌዲ ኤልጂን የተባለች የመንገደኞች ጀልባ በእቨንስተን አጠገብ በመገልበጧ ከተረኛው የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች የሕይወት አድን ቡድን ውስጥ፥ ኤድዋርድ እስፔንሰር 17 ሰዎችን አዳነ። ሌሎችን ለማዳን ያደረገው ትግል ጤንነቱን ስላቃወሰው ትምህርቱን ለመቀጠል አልቻለም ነበር። ከጥቂት ዓመታት በኋላ በሞት እስከተለየበት ጊዜ ድረስ፥ ካዳናቸው 17 ሰዎች መካከል አንዳቸውም እንኳ ምስጋናቸውን ሊገልጡለት እንዳልመጡ ታውቋል።

ማመስገን የራስ-ወዳድነት ተቃራኒ ነው። ራስ-ወዳድ ሰው፡- «የሚገባኝን ነው ያገኘሁት! ሌሎች ሰዎች እኔን ማስደሰት አለባቸው!» ይላል። የበሰለ ክርስቲያን ግን ሕይወት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ እንደሆነና የሕይወት በረከቶችም ከለጋስ እጆቹ እንደሚመጡ ይገነዘባል።

ከማንኛውም ይልቅ «በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን» (ቆላ. 1፡12) አምላክ ልናመሰግነው ይገባል። «መብቃት» ማለት «መስፈርቱን ማሟላት» ማለት ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ለመንግሥተ ሰማይ ብቁዎች አድርጎናል! የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ስንጠባበቅ ሳለ፥ በእርሱ አማካኝነት ባገኘነው መንፈሳዊ ርስት ሐሤት እናደርጋለን (ኤፌ. 1፡11፥ 18-23)።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የከነዓንን ምድር ምድራዊ ርስት አድርገው ተቀብለው ነበር። ዛሬም ክርስቲያኖች በክርስቶስ አማካኝነት መንፈሳዊ ርስት አላቸው። በመንግሥተ ሰማይ ጦርነትም ሆነ ሽንፈት ስለማይኖር፥ ከነዓን የመንግሥተ ሰማይ ተምሳሌት ልትሆን አትችልም። ከነዓን ዛሬ በክርስቶስ ያገኘነውን ርስት የምታመለክት ነች።

በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በመቆም በእምነት ርስታችንን ማወጅ አለብን (ኢያሱ 1፡1-9)። ዕለት በዕለት በረከቶቻችንን መቁጠር አለብን፤ ይህም ለእግዚአብሔር የበለጠ ምስጋና እንድናቀርብ ይረዳናል።

ይህንን አስደናቂ ጸሎት እንደገና ስንመለከት ምን ያህል ልብን የሚነካ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። እግዚአብሔርን በሚያስደስት ሕይወት ልንመላለስ ከፈለግን መንፈሳዊ እውቀት ያሻናል። እንዲሁም በእርምጃችንና በሥራችን ሁሉ በተግባር የሚታይ ታዛዥነት ያስፈልገናል። ዳሩ ግን የዚህ ሁሉ ውጤት ውስጣዊውን ሰው የሚያበረታታ ኃይል ማግኘት መሆን አለበት። ይህም ኃይል በደስታ መታገሥንና ራስ-መግዛትን ከምስጋና ጋር ወደምንለማመድበት ሕይወት ሊመራን ይገባል።

እርስዎስ በዚህ ዓይነት እየጸለዩ ይሆን?

- 4 -

ከሁሉም በላይ አንግሡት

ቆላ. 1፡13-20

በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ዛሬ በኛ ዘመን እንዳሉት የሐሰት አስተማሪዎች ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን አስፈላጊነት አይክዱም ነበር። አስፈላጊ እንጂ ከሁሉም በላይ መሆኑን ግን አይቀበሉም ነበር። ስለዚህም ከተገቢ ስፍራው ዝቅ አድርገውታል። በእነርሱ ፍልስፍና መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ወደ እግዚአብሔር ከሚቀርብባቸው ብዙ መልእክተኞች አንዱ ብቻ ነበር። ጳውሎስ በዚህ ክፍል የተቃውሞ ምላሽ የሚሰጠውም ለዚህ ጉዳይ ነበር።

ምናልባት በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የዚህን ምንባብ ያህል ጥልቀትና ስፋት ያለው ትምህርት ጳውሎስ አላቀረበም ማለት ይቻላል። ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን የበላይነት ለማረጋገጥ የጻፈውን ብናስታውስ ወደ ስሕተት ጎዳና ከማምራት እንቆጠባለን። ሐዋርያውም የጻፋቸው አራት ማረጋገጫዎች የማያከራክሩ ነጥቦች ነበሩ።

ክርስቶስ አዳኝ ነው (ቆላ. 1፡13-14)

የሰው ልጅ ትልቁ ችግር ኃጢአት ነው። ኃጢአት በፈላስፋዎች ወይም በሃይማኖት መሪዎች መፍትሔ ሊገኝለት ያልቻለ ችግር ነው። ኃጢአተኞች አዳኝ ይፈልጋሉ። እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ክርስቶስ በኛ ምትክ የወሰዳቸውን አራት የማዳን ተግባራት በግልጽ ያቀርባሉ።

እርሱ አድኖናል (1፡13)። ይህም ማለት «ከአደጋ ታድጎናል» እንደ ማለት ነው። ራሳችንን ከኃጢአት ኩነኔና ቅጣት ልናድን አንችልም፤ ኢየሱስ ግን ሊያድነን ይችላል፤ አድኖናልም። ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር በመለየት አደጋ ውስጥ ነበርን። የእግዚአብሔር የፍርድ ሰይፍ ከራሳችን በላይ እየተምዘገዘገ ነበር!

ይህ ማዳን ሌላም የሚጨምረው ነገር አለው፤ ይህም፡- ከሰይጣን ሥልጣንና ከጨለማው ኃይላት ነፃ መውጣታችን ነው። ኖስቲክ የተባሉት የሐሰት አስተማሪዎች ዓለምን ይቆጣጠራሉ ብለው በሚያስቧቸው

የተደራጁ የክፉ መናፍስት ያምኑ ነበር (ቆላ. 1:16፤ 2:10፥ 15 ተመልከት)። እነዚህም መላእክት፥ ሊቃነ-መላእክት፥ ሥልጣናት፥ ኃይላት፥ አገዛዞችና ዙፋናት ነበሩ። ጆን ሚልተን የተባሉ ሰው «ፓራዳይስ ሎስት» በተባለው መጽሐፋቸው የሰይጣንን ኃይላት ለመግለጽ እነዚህን መመሪያዎች ተጠቅመውባቸዋል።

አፈለሰን (1:13)። ይህ ቃል ከአንድ አገር ወደ ሌላው የሚደረገውን የሕዝብ ሽግግር የሚያመለክት ነው። ታላቁ አንቲዩከስ ቁጥራቸው ቢያንስ 2000 የሚደርስ አይሁዶችን ከባቢሎን ወደ ቆላስይስ እንዳፈለሳቸው ታሪክ ይናገራል።

የፍቅሩ ልጅ ማለት በእግዚአብሔር ፍቅር ምክንያት የተላከ ልጅ ማለት ነው፤ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ከባርነት ቀንበር ያላቀቀን ያለ ዓላማ እንድንከራተት አልነበረም። ወደ ብርሃኑ መንግሥት በመሰብ በሰይጣን የጨለማ ግዛት ላይ በድል አድራጊነት እንድንመላለስ ሊያደርገን ነው። ምድራዊ ገዢዎች የተሸነፉትን ሰዎች ከአንዱ አገር ወደ ሌላው ያጓጉዙዋቸዋል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ድል የነሡትን ሰዎች ያፈልሳል።

ኢየሱስ በተጠመቀበትና ክብሩንም በገለጸበት ወቅት ኢየሱስ «የሚወድደው ልጁ» እንደሆነ እግዚአብሔር ራሱ መስክሮለታል (ማቴ. 3:17፤ 17:5)። ይህ እውነት አብ ልጁን ለእኛ በሰጠ ጊዜ የከፈለውን ዋጋ ያስታውሰናል። እንዲሁም የእርሱ መንግሥት የፍቅርና የብርሃን መንግሥት እንደሆነ ያስታውሰናል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እስራኤላውያን ያለፉበት ሁኔታ የዚህ መንፈሳዊ ልምምድ ምሳሌ ነበር። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ የባርነት ሕይወት ነፃ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድራቸው መርቶአቸዋል። እግዚአብሔር እኛንም ከአንድ ነገር ያወጣን ወደ ራሱ መንግሥት ሊያስገባን ነው።

ቤዛ ሆነልን (1:14)። ቤዛ የሚለው ቃል «እስረኛን ለማስለቀቅ የሚከፈል ክፍያ» ማለት ነው። ጳውሎስ ይህን ሲል ኢየሱስ እኛን ከጨለማው መንግሥት ነፃ ለማውጣት ለሰይጣን ቤዛ እንደከፈለ መናገሩ አይደለም። ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው የእግዚአብሔርን ሕግ ቅዱስ መስፈርቶች አሟላ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፋችን ጥፋተኞች እንደሆንን ስለሚያውቅ ሊከሰንና የገዛ በደላችን እስረኛ

ሊያደርገን ይፈልጋል። ዳሩ ግን ቤዛው በመስቀሉ ላይ ስለተከፈለ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነፃ ወጥተናል።

የኃጢአት ስርየት አገኘን (1፡14)። ቤዛነትና የኃጢአት ስርየት አይነጣጠሉም (ኤፌ. 1፡7)። «ስርየት» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ፈትቶ መልቀቅ» ወይም «ዕዳን መሰረዝ» ማለት ነው። ክርስቶስ እኛን ነፃ ማውጣትና ወደ አዲስ መንግሥት ማሻገር ብቻ ሳይሆን ዳግመኛ በባርነት ቀንበር ሥር እንዳንወድቅ ዕዳችንንም ሁሉ ሰርዞልናል። ስለሆነም ሰይጣን እኛን ለመክሰስ የሚያበቁትን ማናቸውንም ነገሮች ከመዝገቡ ውስጥ ሊያገኝ አይችልም።

ካለፉት ቅርብ ዓመታት ውስጥ፥ ቤተ ክርስቲያን በኃጢአት ስርየት የሚገኘውን ነጻነት እንደገና ተገንዝባለች። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይቅር ማለቱ የጸጋው ሥራ ነው። ይቅርታ የሚገባን አልነበርንም፤ ደግሞም በጥረታችን ይቅርታን ለማግኘት አንችልም ነበር። ይቅርታ ማግኘታችንን ማወቅ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት ለማድረግ በጸጋው ሐሤት ለማድረግና ፈቃዱን ለመፈጸም ያስችለናል። ይቅርታ ለኃጢአት የሚቀርብ ማመካኛ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ የሚያበረታታን ጉዳይ ነው። በመሆኑም እኛ ይቅር ስለተባልን ሌሎችን ይቅር ለማለት እንችላለን (ቆላ. 3፡13)። ሌሎችን ይቅር አለማለት ወደ ባርነት እንደሚመራ፥ ይቅርታን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነው ሰው ምሳሌነት መመልከት ይቻላል (ማቴ. 18፡21-35)።

በማዳን ሥራ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም የላቀ ድርሻ አለው። ማንም ሌላ ሰው ሊያድነን፥ ኃጢአታችንን ሊያስተሰርይ፥ ከሰይጣን መንግሥት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያሸጋግረን አይችልም ነበር። ደግሞም ሙሉ ለሙሉ በጸጋው ይህንን ሊያደርግ የሚችል ሰው የለም። «በደሙ» የሚለው ቃል የደኅንነታችን ዋጋ ምን ያህል ውድ እንደሆነ ያስታውሰናል። ሙሴና እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ ለመውጣት የበግ ደም ብቻ ማፍሰስ ነበረባቸው፤ ኢየሱስ ግን እኛን ከኃጢአታችን ነፃ ለማውጣት የራሱን ደም ማፍሰስ አስፈለገው።

ክርስቶስ ፈጣሪ ነው (ቆላ. 1፡15-17)

የሐሰት አስተማሪዎች ስለ ፍጥረት አፈጣጠር ግራ ተጋብተው ነበር። የሰውን አካል ጨምሮ ቁሳዊው ዓለም ክፉ እንደሆነ ያስተምሩ ነበር። እንዲሁም ሥጋ መልበስ ከዚህ ክፉ ከሆነው ቁሳዊ ዓለም ጋር

ስለሚያገናኘው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋዊ አካል እንዳልነበረው ነበር የሚያስተምሩት። የእነዚህ የሐሰት ትምህርቶች ውጤት አሳዛኝ ነበር፤ በአንድ በኩል ከልክ ያለፈ ራስን የማጎሳቆል ሕይወት ሲታይ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ገደብ የለሽ ልቅ የኃጢአት ልምምድ ይጧጧፍ ነበር። በመሠረቱ ሥጋ ኃጢአትን ማሸነፍ ካቃተው አንድም በኃጢአት ለመኖር የመደሰት ጉዳይ አለ፥ አልያም ሥጋን በጽኑ የመቆጣጠር ሁኔታ አለ።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጥረት ጋር ያለውን ዝምድና በአራት ገጽታዎች ያቀርበዋል፡-

እርሱ ከፍጥረት በፊት ነበረ (1፡15)። በኩር የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጊዜን ሳይሆን ቦታን ወይም ደረጃን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ በኩር የሚለው ቃል የመጀመሪያ ፍጥረት መሆኑን አይደለም የሚያመለክተው። በኩር ማለት «በአስፈላጊነት፥ በማዕረግ፥ በደረጃ የመጀመሪያው» ማለት ነው። ሰሎሞን ከዳዊት ልጆች ሁሉ በመጀመሪያ የተወለደ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ በኩር ተብሏል [መዝ. (89)፡27]። ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሲል «ከፍጥረታት ሁሉ በላይ» ማለቱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ እንጂ ፍጡር አይደለም።

ጳውሎስ ይህንን እውነት በግልጽ ለማብራራት «ምሳሌ» የሚል ቃል ተጠቅሟል። የቃሉም ትርጉም «ትክክለኛ ውክልና ያለውና እውነተኛው መገለጽ» የሚል ነው። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ኢየሱስ ክርስቶስ «የባሕርዩ ምሳሌ» (ዕብ. 1፡3) እንደሆነ ይናገራል። ኢየሱስ ክርስቶስም «እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ዮሐ. 14፡9) ብሎአል። እግዚአብሔር የማይታይ አምላክ ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለእኛ ገልጾታል (ዮሐ. 1፡18)። ተፈጥሮ እግዚአብሔር መኖሩን ኃይሉንና ጥበብን ይገልጣል፤ ነገር ግን ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ማንነት መግለጽ አይችልም። የማይታየው አምላክ በፍጹምነት የተገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ማንኛውም ተራ ፍጥረት እግዚአብሔርን በፍጹምነት ለመግለጽ አይችልም፤ ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆን አለበት።

ሁሉ በርሱ ተፈጥረዋል (1፡16)። ክርስቶስ ሁሉንም ፈጥሮአል፤ እርሱ ግን በማንም አልተፈጠረም። በዚህ ክፍል ውስጥ «በእርሱ ተፈጥረዋልና» የሚለው ቃል «በእርሱ ስለተፈጠሩ» ተብሎ ሊተረጎም

ይችላል። ነገሮች ሁሉ በእርሱ ስለተፈጠሩ ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉም በኩር ነው። ነፋሳትና ማዕበሎች ለእርሱ መታዘዛቸውና በሽታዎችና ሞት ከእርሱ የሸሹት እርሱ የሁሉም ጌታ ስለሆነ ነበር፤ ስለዚህም ጉዳዩ የሚደነቅ አይደለም። «ሁሉ በእርሱ ሆነ» (ዮሐ. 1፡3)። ይህም በሰማይና በምድር ውስጥ የሚገኙትን፥ የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረታት ሁሉ ያጠቃልላል። ነገሮች ሁሉ በርሱ ትእዛዝ ሥር ናቸው።

ሁሉ ለእርሱ ተፈጥሮአል (1፡16)። ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ በእርሱም አማካኝነት ተፈጥሮአል። ነገሮች ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ውስጥ ናቸው፤ የነገሮች ሁሉ ጥበብ እርሱ ነው፤ ነገሮች የተፈጠሩትም ለእርሱ ነው።

ጳውሎስ ሦስት የተለያዩ መስተዋድዶችን የተጠቀመው የሐሰተኛ አስተማሪዎችን ፍልስፍና ለማፍረስ ነበር። የመስተዋድዶቹ አገባብ፥ ለበርካታ ዓመታት የግሪክ ፈላስፋዎች ማንኛውም ነገር የመነሻ ምክንያት፥ ቀስቃሽ የሆነ ምክንያትና የመጨረሻ ምክንያት ያስፈልገዋል ብለው ያስተምሩ ነበር። የመነሻው ምክንያት ዕቅድ፥ ቀስቃሽ የሆነው ምክንያት ደግሞ ኃይል ሲሆን፥ የመጨረሻው ምክንያት ዓላማ ነበር። ፍጥረታትን ስናስብ ኢየሱስ ክርስቶስ የመነሻ ምክንያት ሆኖአል፤ ይህም የእርሱ ዕቅድ ስለሆነ ነው። ቀስቃሽ ምክንያት የሆነልን እርሱ ስለፈጸመው ነው፤ የመጨረሻ ምክንያት የሆነው እርሱን ደስ እንዲለው ነው።

በፍጥረት ውስጥ ሁሉም ነገር ለእርሱ ከተፈጠረ (ከኖረ) ከሰይጣንና ከወደቁት መላእክቱ በቀር በራሱ ክፉ ሊሆን የሚችል ነገር የለም። እነርሱንም ቢሆን እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም ይጠቀምባቸዋል። የእግዚአብሔርን ፍጥረት በመጠቀሙ ረገድ እንኳ የኖስቲክ መመሪያዎች ማስተዋል የጎደላቸው ናቸው (ቆላ. 2፡20-23)። የእግዚአብሔር ፍጥረት ለኃጢአት ባርነት እየተገዛ ቢሆንም እንኳ (ሮሜ 8፡22) ለእግዚአብሔር ክብርና ለሕዝቡም ደስታ ሊውል ይችላል ማለት ነው (1ኛ ጢሞ. 6፡17)።

እርሱ ሁሉን ነገር በአንድነት አጋጥሞ ይዞአል (1፡17)። «ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።» አንድ አስጎብኚ የተወሰኑ ጎብኚዎችን ቡድን ወደ አቶሚክ ላብራቶሪ ወሰዳቸውና ቁሳዊ ነገሮች ሁሉ በፍጥነት ከሚንቀሳቀሱ፥ከትናንሽ የኤሌትሪክ ክፍሎች የተሠሩ መሆናቸውን ገለጸላቸው። ጎብኚዎቹ የሞሌኪዩሎቹን ተምሳሌት በመመልከት፥ ቁሳዊ

ነገሮች ይህን ግዙፍ ፍጥረተ ዓለም በውስጣቸው የያዙ መሆናቸውን ሲረዱ እጅግ ተደነቁ። በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ከጎብኚዎቹ መካከል አንዱ «ቁሳዊው ዓለም የሚንቀሳቀሰው በዚህ ዓይነት ከሆነ፥ ሁሉንም በአንድነት የሚያያይዘው ምንድን ነው?» በማለት ጠየቀ። አስጎብኚው ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ አልነበረውም።

ክርስቲያን መልስ አለው፡- ነገሮችን ሁሉ አጋጥሞ የያዘ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው! እርሱ «ከፍጥረት ሁሉ በፊት ስለሆነ» ሁሉንም ነገር አያይዞ ሊያቆመው ይችላል። ይህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ የሚያመለክት ሌላ ማረጋገጫ ነው። ከፍጥረት ሁሉ በፊት እግዚአብሔር ብቻ ስለነበረ እግዚአብሔር ብቻ ፍጥረትን ሊያያይዝ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስን ከእግዚአብሔር ማሳነስ ማለት እርሱን ከክብር ዙፋኑ ማውረድ ማለት ነው።

«ይህ የአባቴ ዓለም ነው» የሚለውን የእንግሊዝኛ መዝሙር መዘመር ያስፈራኝ ነበር። ሰይጣንና ኃጢአት ይህንን ዓለም እንደሚቆጣጠሩ ነበር የማስበው። አሁን ግን አእምሮዬ ስለተለወጠ መዝሙሩን በደስታና በድል አድራጊነት መንፈስ እዘምራለሁ። ኢየሱስ ነገሮችን ሁሉ ፈጥሯቸዋል፤ ነገሮችን ሁሉ ይቆጣጠራቸዋል፤ እንዲሁም ነገሮች ሁሉ በእርሱ ተያይዘው ቆመዋል። በርግጥም ይህ የአባቴ ዓለም ነው!

ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው (ቆላ. 1፡18)

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ተምሳሌቶች ተሰጥተዋል። የሰው አካል ደግሞ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ተምሳሌቶች አንዱ ነው (ሮሜ 12፡4-21፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡14፤ ኤፌ. 4፡8-16)። ማንኛውም የእምነት ክፍል ወይም አጥቢያ ጉባኤ «የክርስቶስ አካል ነኝ» ሊል አይችልም። ምክንያቱም ያ አካል እውነተኛ አማኞች ሁሉ የሚገኙበት በመሆኑ ነው። አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ የዚህ አካል ክፍል ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነበት ጊዜ ስለሚፈጸም ከመለወጥ በኋላ የሚከሰት ነገር አይደለም።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የዚህ መንፈሳዊ አካል አባል ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የአካሉ ራስ ነው። በግሪክ ቋንቋ ራስ ማለት «ምንጭ» እና «መነሻ» እንዲሁም «መሪ፥ ገዥ» የሚል ትርጉም አለው። ኢየሱስ

ክርስቶስ የአካሉ፥ የቤተ ክርስቲያን መነሻና መሪ ነው። ጳውሎስ «መጀመሪያ» ብሎታል፤ ይህም ቤተ ክርስቲያኒቱን በተመለከተ ኢየሱስ ክርስቶስ የጊዜ ቅድሚያ እንዳለው ያስታውሰናል። ጀማሪ የሚለው ቃል «መገኛ ምንጭ» ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል።

የትኛውንም ዓይነት ስም ብንጠቀም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የበላይነት ያመለክታል። በመጀመሪያ ደረጃ ቤተ ክርስቲያን የተገኘችው ከእርሱ ነው፤ ዛሬም የምትንቀሳቀሰው በእርሱ ነው። የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ መሆኑ መጠን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈሱ አማካኝነት ሕይወትን ይሰጣታል። ለሰዎች መንፈሳዊ ስጦታውን በመስጠት የተቀበሉትንም ሰዎች በተገቢው ስፍራ ሆነው እንዲያገለግሉ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያስቀምጣቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ አማካኝነት ቤተ ክርስቲያንን ይመግባታል፤ ያነጻታልም (ኤፌ. 5፡25-30)።

ማንኛውም አማኝ ቢሆን የቤተ ክርስቲያን ራስ ሊሆን አይችልም። ይህ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ነው። የተለያዩ የሃይማኖት መሪዎች አብያተ ክርስቲያናትን ወይም የእምነት ክፍሎችን መሥርተው ይሆናል፤ ዳሩ ግን የአካሉ ማለትም የቤተ ክርስቲያን መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን የእውነተኛ አማኞች ሁሉ ስብስብ ስትሆን የተወለደችውም በበዓለ-ኃምሳ ዕለት ነበር። መንፈስ ቅዱስ የመጣውና አማኞችን በጥምቀት አንድ አካል ያደረጋቸው በዚያን ዕለት ነበር።

በዚህ ዓለም ውስጥ «አንድ አካል» የመኖሩ እውነታ (ኤፌ. 4፡4)፥ የአጥቢያ አካላት (ቤተ ክርስቲያንን) አስፈላጊነት አይጻረርም ወይም አስፈላጊነቱን አይቀንሰውም። የዓለም-አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆኔ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔ ካሉብኝ ኃላፊነቶች ነጻ አያደርገኝም። አብያተ ክርስቲያናትን በሙሉ ለማገልገል ባልችልም፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማገልገል፥ ቤተ ክርስቲያንን ላጠናክርና ላንጽ እችላለሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስና ጀማሪ ከመሆኑም በላይ ከሙታን በመነሣትም በኩር ነው። ይህን በኩር የሚለውን ቃል በቆላ. 1፡15 ላይ እንመለከታለን። ከሙታን ለመነሣት ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው አይደለም፤ ጳውሎስ ለማመልከት የፈለገውም ይህንን

አይደለም። ከሙታን ከተነሡት ሁሉ ዋናና የመጀመሪያው እርሱ ነው ማለቱ ነበር። ምክንያቱም ያለ እርሱ ትንሣኤ ሌሎች ሊነሡ አይችሉም ነበር (1ኛ ቆሮ. 15፡20-58)።

«መወለድ» የሚለው ቃል «ሞት» ከሚለው ጋር ተቃራኒ በመሆኑ ጳውሎስ ሁለቱን አሳቦች አያይዞ ማቅረቡ አግባብነት ያለው አይመስልም። መቃብር ኢየሱስ ድል አድርጎ የወጣበት ማኅፀን ነው፤ ምክንያቱም የሞት ጣር እርሱን ይዞ ሊያስቀረው አልቻለምና (የሐዋ. 2፡24)። ልጁ በትንሣኤው ተወለደ (መዝ. 2፡7፤ የሐዋ. 13፡33)።

ይህም ወደ ጠቅላላው ዐቢይ ክፍል አሳብ ይመራናል። ይኸውም፡- «እርሱ በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ» (ቆላ. 1፡18) የሚለው ነው። እግዚአብሔር ልጁን አዳኝ፥ ፈጣሪ፥ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ራስ ሲያደርገው ዓላማው ይኸው ነበር። ፊተኛ (የበላይ) ተብሎ የተተረጎመው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከዚህ ውጭ የትም ስፍራ አልተጠቀሰም። ይህም በኩር ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ጋር የተዛመደ ሲሆን የኢየሱስ ክርስቶስን የተለየ ስፍራ አጉልቶ ያሳያል። «ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው» (ቆላ. 3፡11)።

በ1893 በሺካጎ (በአሜሪካ) ዓለም አቀፍ ኤግዝብሽን ለሕዝብ ቀርቦ ነበር፤ ይህንኑ እግዚብሽን ከ21 ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ ጎብኝቶት ነበር። ከኤግዚብሽኑ ክፍል «የዓለም ሃይማኖቶች ፓርላሜንት» የሚል ነበር። ይህ ፓርላማ የዓለም ሃይማኖቶች ተወካዮች የሚገኙበት ሲሆን፥ የስብሰባውም ዓላማ «ሁሉም የላቁ ወይም የተሻሉ» ነጥቦቻቸውን ለማቅረብና ለዓለም አዲስ ሃይማኖት ለማስገኘት ነበር።

ወንጌላዊ ዲ.ኤል.ሙዲ ይህንን አጋጣሚ ለወንጌል መስፋፋት እንደ ታላቅ ዕድል አድርገው ነበር የተመለከቱት። ስለዚህም (እግዚብሽኑ በማይካሄድበት ጊዜ) የኢየሱስ ክርቶስን ወንጌል ለማስተላለፍ የአብያተ ክርስቲያናት አዳራሾችን፥ ቲያትር ቤቶችንና የተለያዩ ትዕይንቶች የሚቀርቡባቸውን ድንኳኖች ሳይቀር ተከራዩና የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መስበክ ጀመሩ። ወዳጆቻቸው «የሃይማኖቶችን ፓርላሜንት» እንዲያወግዙ ቢገፋፏቸውም፥ ሙዲ ግን ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም። እንዲያውም፡- «ሰዎች ወደ እርሱ ይመለሱ ዘንድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን በጣም ማራኪ አድርጌ አቀርበዋለሁ» በማለት መለሱላቸው። ሙዲ ኢየሱስ ክርስቶስ በታሪክ ውስጥ ከታዩት በርካታ «የሃይማኖት መሪዎች»

አንዱ ሳይሆን፥ እርሱ ከሁሉም የላቀ አዳኝ እንደሆነ አጥብቆ የተረዳ ሰው ነበር። የ1893ቱ «የሺካጎ የወንጌል ዘመቻ» ምናልባትም በዲ. ኤል ሙዲ ሕይወት ውስጥ ከሁሉም የበለጠ የወንጌል አዝመራ የተዘራበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። በመሆኑም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በክርስቶስ አመኑ።

በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ግን ለኢየሱስ ክርስቶስ የበላይነቱን ስፍራ አልሰጡትም ነበር። ምክንያቱም በፍልስፍናቸው መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ከበርካታ የእግዚአብሔር መልእክተኞች አንዱ ብቻ እንጂ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ (ዮሐ. 14፡6) አልነበረም። «ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉም ጌታ ካልሆነ ከቶውንም ጌታ ሊሆን አይችልም» የሚለው አባባል ማንኛችንም ግምት ልንሰጠው የሚገባን አባባል ነው።

እስካሁን የኢየሱስ ክርስቶስን የበላይነት የሚያመለክቱትን ሦስት አሳቦች ተመልክተናል። እነርሱም፡- አዳኝነቱ፥ ፈጣሪነቱና የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑ ናቸው። እነዚህም ነጥቦች ከጠፉት ኃጢአተኞች፥ ከዓለምና ከአማኞች ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታሉ። ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ከአባቱ ጋር ያለው ግንኙነትስ እንዴት ያለ ይሆን?

እርሱ በአብ የተወደደ ነው (ቆላ. 1፡19-20)

ቀደም ሲል ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን «የፍቅሩ ልጅ» (ቁ. 13) በማለት ጠርቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ሰዎች «በውድ ልጁ» ተቀባይነትን አግኝተዋል (ኤፌ. 1፡6)። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ወዳጆቼ ብሎ ይጠራናል (ቆላ. 3፡12)።

ከዚያም ጳውሎስ ከፍተኛ እርምጃ ወደ ፊት በመራመድ የእግዚአብሔር «ሙላት ሁሉ» በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለ ይናገራል! «ሙላት» ተብሎ የተተረጎመው «ፕለይ ሮማ» ከሚለው ግሪክኛ ቃል ነው። ይህም በናስቲክ የሐሰት አስተማሪዎች መዝገበ ቃላት ውስብስብ ቃል ሲሆን ትርጉሙም «የመለኮታዊ ኃይላትና ባሕርያት ሁሉ ጠቅላላ ድምር» እንደ ማለት ነው። ጳውሎስ ይህንን አስፈላጊ ቃል በቆላስይስ መልእክት ውስጥ ስምንት ጊዜ በመጥቀስ፥ የሐሰት አስተማሪዎችን በገዛ መሠረታቸው ላይ ቆሞ እንዳጋለጣቸው አስቀድመን ተመልክተናል።

«መኖር» ወይም «ማደር» የሚለውም ቃል በእኩል ደረጃ አስፈላጊ ነው። በጊዜያዊነት ከ «መቅረት» መኖርን የሚያመለክት ሳይሆን

«በቋሚነት በቤት ውስጥ መኖርን ነው» የሚያመለክተው። የታወቁት የግሪክ ምሁር ዶክተር ኬነት ኤስ. ዊስት በቆላስይስ መልእክት ላይ ባዘጋጁት በጣም ጥሩ ማብራሪያቸው ውስጥ፥ ግሡ የሚያመለክተው ይህ ሙላት «በእርሱ ተፈጥሮ ውስጥ የሌለና በኋላ የተጨመረውን ነገር ሳይሆን ይልቁንም ለዘለቄታው ከአስፈላጊው ተፈጥሮው ውስጥ የሚገኘውን ነገር» እንደሆነ ገልጸዋል (Ephesians And Colossians In The New Testament, Eerdmans, p.187)።

እግዚአብሔር በዘላቂነት «ፕለይ ሮማውን» ለሰው አይሰጥም። የሙላቱ በክርስቶስ ውስጥ መገኘት «አብን ደስ የማሰኘቱ» እውነታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል። «እኛ ሁላችን ከሙላቱ [ከክርስቶስ ሙላት] ተቀብለን» (ዮሐ. 1፡16)። «በእርሱ [በኢየሱስ ክርስቶስ] የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» (ቆላ. 2፡9)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ ማንም ተራ ሰው ለዘለዓለም ሊሠራው የማይችለውን የጠፉ ኃጢአተኞችን ከተቀደሰው አምላክ ጋር አስታረቀ። የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ወንድና የመጀመሪያዋ ሴት ኃጢአትን በማድረግ በእግዚአብሔር ላይ ቢያምፁም፥ እግዚአብሔር ግን በእነርሱ ላይ ጦርነት አላወጀም፤ ይልቁንም እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈለጋቸው፤ ለኃጢአታቸው መሸፈኛ የሚሆን ነገርም ሰጣቸው።

ያልዳነ ሰው ተፈጥሮአዊ አእምሮው ዛሬም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር በመዋጋት ላይ ይገኛል (ሮሜ 8፡7)። ኃጢአተኛው ታማኝ፥ ሃይማኖተኛና ምግባረ-ሠናይ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር በመዋጋት ላይ ይገኛል።

ቅዱሱ አምላክ ከኃጢአተኛ ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችላል? እግዚአብሔር መለኪያ ሚዛኑን በማዛባት ኃጢአትን ችላ በማለት ከሰዎች ጋር ሊተባበር ይችል ይሆን? ይህን ቢያደርግ ዓለም ጸንታ ባልቆመች ነበር! እግዚአብሔር የማይለወጥና የራሱን ቅዱስ ሕግ የሚጠብቅ መሆን አለበት።

ምናልባት ሰው እግዚአብሔርን በአንዳንድ ነገሮች ሊያስደስት ይችል ይሆናል። ዳሩ ግን ሰው በተፈጥሮው ከእግዚአብሔር ተለይቶአል፤ በሥራውም ከእግዚአብሔር ተራርቆአል (ቆላ. 1፡21)። ኃጢአተኛ ሰው «በኃጢአቱና በበደሉ ሙት» ነው (ኤፌ. 2፡1-3)። በመሆኑም ራሱን

ለማዳን ወይም እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ለማስደሰት የሚያበቃ ተግባር ከቶውንም የለውም (ሮሜ 8፡8)።

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ዕርቅ እንዲደረግ ከተፈለገ፥ እግዚአብሔር የራሱን እርምጃ መውሰድ አለበት። በመሆኑም እግዚአብሔር ከሰው ጋር የታረቀው በክርስቶስ አማካይነት ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡19)። ዳሩ ግን ይህንን ዕርቅ ከፍጻሜ ያደረሰው የክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር መምጣት ወይም በሰዎች መካከል በመኖር ያሳየው ምሳሌነት አልነበረም። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰላም የተፈጠረው በሞቱ በኩል ነበር። እርሱም «በመስቀሉ ደም ሰላም አደረገ» (ቆላ. 1፡20)።

በእርግጥ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰላምን የሚያመጣ አሳብ አቅርበው ነበር። ዳሩ ግን እነርሱ ያቀረቡት ዕርቅ የተሟላ ወይም ፍጻሜ ያለው አልነበረም። በኖስቲክ አስተማሪዎች አስተሳሰብ፥ መላእክትና ሌሎች ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚላኩ መልእክተኞች ሰውን በሆነ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ይችላሉ ብለው ያስተምሩ ነበር። ይሁን እንጂ በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነው ዕርቅ ፍጹም፥ ምሉዕና የመጨረሻ ነው። ከዚህም በላይ በክርስቶስ የሚገኘው ዕርቅ ዓለሙን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው! «በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማይ ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአል» (ቁ. 20)።

ዳሩ ግን ዓለም-አቀፋዊ ዕርቅ ከዓለም አቀፋዊ ደኅንነት ጋር አንድ ዓይነት እንደሆነ በማሰብ መሳሳት የለብንም። «ዓለም-አቀፋዊነት» ክርስቶስን የተዉትን ጨምሮ ፍጥረታት ሁሉ አንድ ቀን እንደሚድኑ የሚያስተምር ነው። ጳውሎስ በዚህ አያምንም ነበር። ኃጢአተኞች ደኅንነትን ለማግኘት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንዳለባቸው በግልጽ ስላስተማረ «ዓለም-አቀፋዊ ደኅንነት» ከጳውሎስ የሥነ-መለኮት ትምህርት ክፍል አይደለም (2ኛ ተሰ. 1)።

ጳውሎስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የኃጢአትን ቋጠሮ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደፈታው ጽፏል። ይህም ማለት አንድ ቀን እግዚአብሔር ለእርሱ የሆኑትን ሁሉ በክርስቶስ ወደ አንድነት ሊያመጣቸው ይችላል ማለት ነው (ኤፌ. 1፡9-10)። አማኞችን የሚያከብርበትና ያላመኑትን ደግሞ የሚቀጣበት ቀን አለው። ይህንንም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ የተነሣ በጽድቅ ይፈጽመዋል።

የኃጢአት ጉዳይ በመስቀል ላይ በቂ መፍትሔ ስላገኘ ማንም ሰው ሰይጣንም እንኳ ቢሆን እግዚአብሔርን በፍትሕ-አልበኝነት ሊከሰስ ከቶውንም አይችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ተራ ሰው፥ ወይም ከእግዚአብሔር የተላከ ተራ መልእክተኛ፥ ወይም የአምላክ ነጸብራቅ ብቻ ከሆነ እግዚአብሔርንና ሰውን የማስታረቅ ብቃት አይኖረውም ማለት ነው። እግዚአብሔርንና ሰውን በአንድ ላይ ለመዳኘት የሚችል መካከለኛ እራሱ እግዚአብሔርና ሰው የሆነ ብቻ ነው። ከናስቲኮች ትምህርት በተቃራኒ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋ የለበሰ እውነተኛ ሰው ነበር። የሰውን ሥጋ ለብሶ የተገለጸ አምላክ ነበረ (ዮሐ. 1፡14)። በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ለሰው ኃጢአት መቀጮውን ስለ ከፈለ የሕጉን ትክክለኛ መጠይቆች አሟልቶአል (1ኛ ጴጥ. 2፡24)። ዕርቅ በመስቀል ላይ ተፈጸመ (ሮሜ 5፡11)።

ይህንን መሠረታዊ ክፍል ስናጠና (ላይ ላዩን ብቻ በመነካካት ነው) በርካታ ጠቃሚ እውነቶችን ልብ ልንል እንችላለን።

በመጀመሪያ፥ ነገሮች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነዋል። ሁሉም በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋል። እርሱ ከሁሉም በፊት ነበረ፤ ዛሬም ሁሉን በአንድነት አገጣጥሞ ይዞአል። በመስቀሉ በኩል ነገሮችን ሁሉ ወደ ዕርቅ አምጥቶአል። ስለሆነም ጳውሎስ፡- «በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ» (ቆላ. 1፡18) ማለቱ አስገራሚ አይሆንም።

ሁለተኛ፥ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ በእርሱ ስለሚገኝ፥ «በእርሱ ሆነን ተሞልተናል» (ቆላ. 2፡10)። በኢየሱስ ክርስቶስ ስብእና ወይም ሥራ ላይ ምንም ነገር መጨመር አያስፈልገንም። አንዳች ነገር መጨመር ማለት ከክብሩ ላይ መቀነስ ማለት ነው። ከሁሉም በላይ በማስቀደም ፈንታ የአስፈላጊነትን ወይም የእውቅናን ወንበር ብቻ መስጠት እርሱን ከዙፋኑ ማውረድ ማለት ነው።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲከበርና የበላይነት ስፍራ ሲሰጠው ደስ ይለዋል። ክርስቲያኖች እንደሆኑ የሚናገሩና ዳሩ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ችላ የሚሉ ወይም የሚክዱ ሰዎች አሉ። «አብን እናመልከዋለን። የሚያስፈልገውም ነገር ይኸው ነው» ይላሉ።

ዳሩ ግን ለአብ እንደሚደረግ ሁሉ ለወልድም አምልኮ ሊቀርብለት እንደሚገባ ኢየሱስ ክርስቶስ ግልጽ አድርጎአል። «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ... ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም» (ዮሐ. 5፡22-23)።

በሬድዮ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በማቅረብ የታወቁት ዶክተር ኤም. ኢር. ዴሐን፥ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ከካደ የሐሰት አስተማሪ ጋር ክርክር ስላደረገ ሰባኪ የሚከተለውን ብለው ነበር፡-

የሐሰት አስተማሪው፡- «ሁልጊዜም አባት ከልጁ በዕድሜ ስለሚልቅ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ሊሆን አይችልም» ሲል ተከራከረ። «አባት ዘላለማዊ ካልሆነ፥ እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው። ኢየሱስም የእርሱ ልጅ ከሆነ፥ ዘላለማዊ አይደለም» ብሎአል።

ሰባኪውም እንዲህ በማለት መለሰለት፡- «አንድን ሰው አባት የሚያሰኘው ልጅ ያለው ከሆነ ነው። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ዘላለማዊ አባት ከሆነ፥ ዘላለማዊ ልጅ ሊኖረው ይገባል! ይህም ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ነው፤ አምላክም ነው ማለት ነው!»

ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ፥ ፈጣሪ፥ የቤተ ክርስቲያን ራስና በአብ የተወደደ ልጅ ነው። እርሱ ዘላለማዊ አምላክ ነው። በመሆኑም በሕይወታችን ውስጥ ከሁሉም የላቀውን ስፍራ ልንሰጠው ይገባል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በእርስዎ ሕይወት ውስጥ የበላይ ነውን?

የአንድ ሰው አገልግሎት

ቆላስይስ 1፡21-2፡3

ሁከት በማስነሣቱ ምክንያት ተከሰሶ በእስር ቤት ከተጣለ ከአንድ ከማያውቁት ሰው ደብዳቤ ቢደርስዎት የሚሰጡት ምላሽ ምን ይሆን?

የቆላስይስ አማኞች እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አጋጥሟቸዋል። መጋቢያቸው ኤጳፍራን በክርስቶስ እንዲያምን ያመጣው ሰው ጳውሎስ መሆኑን ያውቁ ነበር። እንዲሁም ደግሞ ኤጳፍራ ከጳውሎስ ጋር ለመማከር ወደ ሮም እንደሄደና ከጉዞውም እንዳልተመለሰ ያውቁ ነበር። የቤተ ክርስቲያኑ ምእመናን በቲኪቆስና በአናሲሞስ በኩል የመጣላቸውን ደብዳቤ ተቀብለዋል። ይሁንና በቆላስይስ የሚገኙ የሐሰት አስተማሪዎች ጳውሎስን ዋጋ በማሳጣት በሰዎች አእምሮ ውስጥ ጥርጣሬን እየዘሩ ነበሩ። «በፖለቲካ ጉዳይ የታሠረውን ሰው ለምን ትሰሙታላችሁ? ለመሆኑ የሚናገረውንስ ታምኑታላችሁ?» በማለት እየጠየቁዋቸው ነበር።

ጳውሎስ አዝማሚያው እንደዚህ እንደሚሆን ስለተረዳ በዚህ ደብዳቤው የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ አንዳንድ የማብራርያ ቃላት ከመስጠት ተቆጥቦ ነበር። በጽሑፉ ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ በማድረጉ ጉዳይ ስለተጠመደ ምንም ስለ ራሱ የመጻፍ ፍላጎት አላሳየም ነበር። በዚህ ክፍል ግን ጳውሎስ ሦስት አገልግሎቶቹን ይገልጻል።

ወንጌሉን መስበክ (ቆላ. 1፡21-23)

ምንም እንኳ ጳውሎስ በቀጥታ ለቆላስይስ ሰዎች የወንጌሉን ቃል ባይናገርም የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት ያደረገው በኤፌሶን የሰጠው አገልግሎት ነበር። ጳውሎስ «አገልጋይ ሆንሁ» ይላል (1፡25)። ከአገልግሎቱ ብዙው ክፍል በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የደኅንነት የምሥራች መስበክን የሚያጠቃልል ነበር። መልእክቱ የዕርቅ አገልግሎት ነበር (2ኛ ቆሮ. 5፡17-21)። ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ የራሳቸውን ሃይማኖታዊ ታሪክ እንደገና ያነሣባቸዋል።

አስቀድመው የተለዩ ነበሩ (1፡21)፥ «የተለያችሁ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «የተጣላችሁ» የሚል ፍች ይሰጣል። እነዚህ

በቆላስይስ የነበሩ አሕዛብ ከእግዚአብሔር ተጣልተው ከእስራኤል መንፈሳዊ በረከቶች ተለይተው ነበሩ (ኤፌ. 2፡11-22)። የሚያመልኳቸው አማልክት የውሸት አማልክት ስለነበሩ የሃይማኖት ሥርዓቶቻቸው ስለ ኃጢአታቸው ወይም ስለጥፋታቸው ምንም ሊያደርጉላቸው አልቻሉም ነበር።

ዳሩ ግን ይህ ጥል አሕዛብ በመሆናቸው ብቻ የተፈጸመ ሳይሆን ከኃጢአት ልምምዶችና አመለካከቶችም ጭምር የመነጨ ነበር። አሕዛብ የእግዚአብሔር ጠላቶች ነበሩ፤ ይህ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ኃይለኛ ጠላትነት እንዳላቸው ያሳያል። እነዚህ አሕዛብ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸውን ዓይነት ቅዱስ ሕግ ባይቀበሉም፥ በተፈጥሮና በሕሊና አማካኝነት ስለ እግዚአብሔር እውነተኛውን ነገር ያውቁ ነበር (ሮሜ 1፡18-32)። ፍጹም በሆነው በጻድቁ እግዚአብሔር ፊት አላዋቂነትን ምክንያት በማድረግ ሊያመልጡ አይችሉም።

የአእምሮአቸውም ጠላትነት ወደ እኩይ ተግባር መራቸው። በዝንባሌም ሆነ በተግባር ከእግዚአብሔር ጋር ይዋጉ ነበር። «ስለ ሥጋ ማሰብ [የማያምኑ ሰዎች አስተሳሰብ] በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና» (ሮሜ 8፡7)። ይህም አንድ የማያምን ሰው ደኅንነትን ከማግኘቱ በፊት ለምን ንስሐ መግባትና አእምሮውን መቀየር እንዳለበት ይገልጻል።

አሁን ያገኙት ዕርቅ (1፡21-22)፥ እነርሱ ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር አላስታረቁም። ዳሩ ግን በፍቅሩና በጸጋው ለዕርቅ የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰደው እግዚአብሔር ነበር። ኃጢአተኞች ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁ ዘንድ አብ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት ላከው። «ደካሞች» (ሮሜ 5፡6) እና ራሳችንን ለማዳን ምንም ብቃት የሌለን ሆነን ሳለን፥ ኢየሱስ ለኛ ሲል ሞተ። «ገና ኃጢአተኞች» እና «ጠላቶቹ ሳለን»፥ ሞተልን (ሮሜ 5፡8፥ 10)።

ጳውሎስ በመስቀል ላይ ለተሰቀለው ለኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዊ አካል ልዩ ትኩረት ሰጥቶአል። የሐሰት አስተማሪዎች የክርስቶስን በሥጋ መገለጽ ክደው እውነተኛ ሰብአዊ አካል እንዳልነበረው እያስተማሩ ነበር። ቁሳዊ አካል በሙሉ ክፉ ነው የሚለው ፍልስፍናቸው ይህንን ማጠቃለያ እንዲመሠርቱ ገፋፋቸው። ዳሩ ግን ኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ ሰብአዊ አካል እንደነበረውና በዚያም አካሉ ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ እንደተሸከመ አዲስ ኪዳን በግልጽ ያስተምራል (1ኛ ጴጥ. 2፡24)።

የዚህ ዕርቅ ዓላማ ግላዊ ቅድስናን ማስገኘት ነው። እግዚአብሔር ሰላምን ካላደረገ (ቆላ. 1:20) በዓመፀኛነታችን እንቀጥላለን። እኛን ከራሱ ጋር ያስታረቀን ከሕይወቱና ከቅድስናው እንድንካፈል ነው። «ነውርና ነቀፋ የሌለን ቅዱሳን» ሆነን በእግዚአብሔር ፊት ቀርበናል (ቁ. 22)።

ቅዱስ የሚለው ቃል «መለየት፥ ለእግዚአብሔር መሰጠት» የሚል አሳብ ያንጸባርቃል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ ቅዱሳን የሚለው ቃል በሕይወት ዘመናችን ተአምራት የሠሩና ኃጢአት አድርገው የማያውቁ ሙታንን የሚገልጽ አይደለም። የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን በኢየሱስ ክርስቶስ የታመኑ ሕያዋን ሰዎች ነበሩ። ጳውሎስም ይህንን መልእክት የሚጽፈው ለእነዚሁ በሕይወት ላሉ ቅዱሳን ነው (ቆላ. 1:2)።

«ነውር የሌለበት»፥ ይህ ቃል ነውር የሌለባቸው ሆነው ስለሚቀርቡት የቤተ መቅደስ መሥዋዕቶች ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ነው። እግዚአብሔር ወደ ልጆቹ ተመልክቶ ከላያቸው ላይ አንድም ነውር አለማየቱ የሚያስደንቅ ነው! እግዚአብሔር «ቅዱሳንና ነውር የሌለን» እንድንሆን መርጦናል (ኤፌ. 1:4)።

የማይነቀፍ ወይም «ነቀፋ የሌለበት» ማለት «ከክስ የነፃ» ማለት ነው። አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅን ምንም ክስ ሊቀርብብን አይችልም (ሮሜ 8:31-34)። የወንድሞች ከሳሽ የሆነው ሰይጣን በእኛ ላይ ክስ ለመመሥረት ቢፈልግም ክሶቹ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም (ዘካ. 3 ይመልከቱ)። ሰዎች በኛ ላይ ክስ ሊያቀርቡ ይችሉ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ሊለውጡ አይችሉም።

በክርስትና ሕይወታችን ከሁሉም የሚልቀው ነገር በራሳችን ወይም በሌሎች እይታ ያለን ስፍራ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር እይታ ያለን ስፍራ ነው (1ኛ ቆሮ. 4:1-4)። ያለፈውን ኃጢአትና ውድቀት ያለመርሳት ችግር ያጋጠማትን አንዲት ክርስቲያን እኅት በምክር እንዳገለገልኋት አስታውሳለሁ። ሌሎች ሰዎች እንዲተችዋት የምትፈልግ ትመስላለች። በእግዚአብሔር አመለካከት እርሷ ማን እንደሆነች አስታወስኳት። በውድቀቷ ላይ የማያቋርጥ ትኩረት ማድረጓ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራላትን ሥራ እንዳታስተውል አድርጓት ነበር። ይህንንም ለማስተካከል ብዙ ጊዜ ወሰደባት። ዳሩ ግን በመጨረሻ በኢየሱስ ክርስቶስ

ያላትን አስደናቂ ስፍራ በመቀበል ራሷን በራሷ በመንቀፍና በጭንቀት ላይ ድልን ተቀዳጀች።

ጳውሎስ በእግዚአብሔር ፊት በሚኖረን የተቀደሰ አቋም ላይ የሰጠው ትኩረት በሐሰት አስተማሪዎች ላይ የቀረበ ተቃውሞ መሆኑ እርግጥ ነው። ምክንያቱም የሐሰት አስተማሪዎች ለተከታዮቻቸው ምንም ነገር ሊሰጥ የማይችለውን «ፍጹምነት» እንደሚሰጡአቸው ቃል ገብተውላቸው ነበር። ጳውሎስ፡- «እናንተ በክርስቶስ ፍጹምነት አግኝታችኋል። እንግዲህ ፍጹምነትን ከሌላ ስፍራ ለምን ትሻላችሁ?» በማለት ጽፎአል።

የወደፊት ክብራቸው (1፡23)። «የወንጌል ተስፋ» ማለት የተባረከው ተስፋችን የጌታችን መመለስ ነው (ቲቶ 2፡13)። ጳውሎስ አስቀድሞ ይህንን ተስፋ ጠቅሶአል፡- «በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሣ» (ቆላ. 1፡5)፤ በኋላም በዚያው ምዕራፍ ውስጥ ይህንኑ ተስፋ «የክብር ተስፋ» (1፡27) በማለት ጠርቶታል።

እነዚህ የቆላስይስ አሕዛብ ያለተስፋ የነበሩበት ወቅት ነበር (ኤፌ. 2፡12)። ምክንያቱም ያለ እግዚአብሔር ነበሩ። ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ጋር በታረቁ ጊዜ አስደናቂ የክብር ተስፋ ተሰጣቸው። የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ አንድ ቀን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ይኖራሉ (ዮሐ. 17፡24)። እንዲያውም ፍጻሜያችን እጅግ አስተማማኝ በመሆኑ ጳውሎስ ነገሩ እንደተፈጸመ ሁሉ ከብረናል በማለት ጽፎአል (ሮሜ 8፡30)። የምንጠብቀው ነገር ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ የሚሆነውን የዚህን ክብር መገለጽ ነው (ሮሜ 8፡17-19)።

ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የሚያስተላልፈው መልእክት በወደፊት ክብራችን ዋስትና ላይ የጽልመት ጥላ የሚጥል ይመስላል (ቆላ. 1፡23 ይመልከቱ)፤ አንድ አማኝ ደኅንነቱን ሊያጣ ይችል ይሆን? በፍጹም አያጣም። የክፍሉ አሳብ ጥርጣሬን የሚያመለክት ወይም «እኛ ደኅንነታችንን የምንጠብቅበትን» ቅድመ-ሁኔታ የሚያስቀምጥ አይደለም።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ፥ ጳውሎስ የሕንፃ ግንባታ ምሳሌ ተጠቅሞአል፤ ይህም በመሠረቱ ላይ ጸንቶ የቆመውን ቤት በማመልከት ነው። የቆላስይስ ከተማ የተቆረቆረችው የመሬት መንቀጥቀጥ በሚበዛበት ስፍራ ስለነበር፥ «ሳትናወጡ» የሚለው ቃል «የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም መናወጥ ሳያናጋችሁ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ጳውሎስ፡- «በእውነት ከዳናችሁና በጽኑ መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ከታነፃችሁ በእምነት

መመላለሳችሁን ትቀጥላላችሁ፤ የሚያናውጣችሁም ነገር አይኖርም። ወንጌሉን ሰምታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስን አምናችኋል፤ እርሱም አድኖአችኋል» ማለቱ ነበር።

በሌላ አነጋገር፥ የዳንነው በእምነት መመላለስ በመቀጠላችን አይደለም። ዳሩ ግን በእምነት በመሆናችን መዳናችንን እናረጋግጣለን። እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማረጋገጥ የራሱን እምነት ሊፈትንና ልቡንም ሊመረምር ይገባል (2ኛ ቆሮ. 13፡5፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡10-21)።

ለአሕዛቦች መሠቃየት (ቆላ. 1፡24-27)

የጳውሎስ ጠላቶች ታላቁ ሐዋርያ የሮም እስረኛ መሆኑን አብዝተው ይናገሩ ነበር። ምናልባትም በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች በጳውሎስ ላይ ከመሳለቃቸውም በላይ፥ የወንጌሉን እውነታ ለመቃወም ይህንን እንደ መከራከሪያ ሳይጠቀሙበት አልቀሩም። ዳሩ ግን ጳውሎስ ጠላቶቹን ለማጥቃትና በቆላስይስ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር የቀረበ ግንኙነት ለመፍጠር ይህንኑ እነርሱ ያቀረቡትን መከራከሪያ ይጠቀማል።

የጳውሎስ ደስታ (1፡24)፥ «በመከራዬ በማፈር ፈንታ፥ እየተደሰትሁበት ነው!» አንድ ሰው እንዴት በመከራ ሊደሰት ይችላል? ቀድሞ ነገር፥ ጳውሎስ መከራ እየተቀበለ ያለው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን «መከራ መካፈል» ነበር (ፊልጵ. 3፡10)። እንደ ቀደሙት ሐዋርያት፥ ጳውሎስም «ለስሙ ይናቅ ዘንድ የተገባው ሆኖ ስለተቆጠረ» (የሐዋ. 5፡41) ደስ አለው። አንድ ክርስቲያን «በሌብነት ወይም በክፉ አድራጊነት» ከቶውንም መከራ መቀበል የለበትም። ዳሩ ግን «ክርስቲያን በመሆኑ ምክንያት መከራ ቢደርስበት» ይህ ታላቅ ክብር ነው (1ኛ ጴጥ. 4፡15-16)። ለክርስቶስ መከራን ለሚቀበል ታማኝ ክርስቲያን ልዩ በረከትና ሽልማት በላይ በሰማያት ተዘጋጅቶ ይጠብቀዋል (ማቴ. 5፡10-12)።

ጳውሎስ በመከራው የሚደሰትበት ሌላም ምክንያት ነበረው። ይኸውም መከራን የሚቀበለው በአሕዛብ ምክንያት ነው። ጳውሎስ ለአሕዛብ የተመረጠ ሐዋርያ ነበር (ኤፌ. 3፡1-13)። እንዲያውም በሮም ወኅኒ ቤት ይማቅቅ የነበረው ለአሕዛብ ከነበረው ጽኑ ፍቅር የተነሣ ነበር። የሐሰት ክስ ተመሥርቶበት በኢየሩሳሌምም ታስሮ ለፍርድ በቀረበ ጊዜ፥ አሕዛብ የሚለውን ቃል እስካነሣበት ጊዜ ድረስ አይሁዶች የመከላከያ

ሙግቱን በትዕግሥት ሲያደምጡት ነበር (የሐዋ. 22፡21-30 ይመልከቱ)። ቁጣቸው እንዲገንፍልና የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት ለመጠየቅ ያነሣሣቸው ይኸው ቃል ነበር። (ሙሉው ታሪክ በሐዋ. 21-28 የተጻፈ በጣም የሚያስደንቅ ታሪክ ነው።)

ስለሆነም በቆላስይስ የነበሩ አሕዛብ አማኞች ጳውሎስን ለመውደድና ላበረከተላቸውም ልዩ አገልግሎት ምስጋና ለማቅረብ በቂ ምክንያት ነበራቸው። በተጨማሪም ጳውሎስ የሚደሰትበት ሦስተኛ ምክንያት ነበረው፤ ይኸውም፡- መከራን የሚቀበለው የክርስቶስ አካል ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን መሆኑ ነው። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ያሳደደበትና መከራ ያመጣባት ጊዜ ነበር፤ በኋላ ግን ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ለመንከባከብ የራሱን ሕይወት አሳልፎ ሰጥቷል። ጳውሎስ አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደሚያደርጉት፥ «ከዚያ ምን አገኛለሁ?» ብሎ አልጠየቀም። ይልቁንም «እግዚአብሔር ምን ያህል እንዳገለግል ይፈልግ ይሆን?» ብሎ ነበር የጠየቀው። ጳውሎስ እስረኛ መሆኑ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጠቱን አላገደውም።

ይሁንና እነዚህ ጳውሎስ የተቀበላቸው መከራዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከተቀበላቸው መከራዎች ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው ልብ ማለት ያሻል። ለዓለም ኃጢአት ሁሉ ሊሞት የቻለው ኃጢአት ያልነካው የእግዚአብሔር በግ ብቻ ነበር (ዮሐ. 1፡29)። ጳውሎስ «በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እየፈጸመ» ነበር (1፡24)። መከራ የሚለው ቃል የሕይወት ውጣ-ውረድን፥ ጳውሎስ ያለፈባቸውን ስደቶች ያመለክታል። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን የመሥዋዕትነት መከራዎች ለማመልከት አላገለገለም ነበር።

የክርስቶስ የመሥዋዕትነት መከራ አብቅቶአል። ዳሩ ግን አካሉ ማለትም ቤተ ክርስቲያን ለእምነት ባላት አቋም ምክንያት መከራን ትቀበላለች። በሰማያት ያለው የቤተ ክርስቲያን ራስ ሕዝቡ የሚጋፈጠው መከራ ይሰማዋል። («ሳውል፥ ሳውል፥ ስለምን ታሳድደኛለህ?» የሐዋ. 9፡4)። ጳውሎስ እነዚህን መከራዎች በመካፈል የድርሻውን እየተወጣ ሲሆን ሌሎችም ምሳሌነቱን ይከተላሉ። ጳውሎስ በደረሰበት መከራ አላጉረመረመም። «የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደበዛ፥ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናልና» (2ኛ ቆሮ. 1፡5) ይል ነበር።

የጳውሎስ ኃላፊነት (1፡25-27)፦ ጳውሎስ ከአይሁዶች ጋር ቢተባበርና አሕዛቦችን ከማገልገል ቢታቀብ ኖሮ ይህን ያህል መከራ ባልደረሰበት ነበር። ዳሩ ግን ለግል ደኅንነትና ምቾት በማሰብ ጥሪውን ችላ ለማለት አልፈለገም። በእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ ተሹሞ ነበር፤ የ«መጋቢነት» ሥልጣን ስለ ተሰጠውም፦ ለጥሪው ታማኝ መሆን ነበረበት (1ኛ ቆሮ. 4፡2)። ይህም የምርጫ ጉዳይ አልነበረም። የተጠራው የእግዚአብሔርን ቃል ለመፈጸም ነበር። ስለዚህም «ቃሉን በሙላት መስበክ አለብኝ። አንዳችም እውነት ወደ ጎን መተው የለብኝም» እንዲል አደረገው። እንዲሁም ደግሞ፡- «በእግዚአብሔር ቃል ስለታዘዝሁ፦ አገልግሎቴን ለመፈጸም ታማኝ መሆን አለብኝ» እንዲል አድርጎታል።

ጳውሎስ ለአሕዛብ የሚያስተላልፈው ልዩ መልእክት «ምሥጢር» ብሎ ከጠራው ነገር ጋር የተያያዘ ነበር። ዛሬ ለኛ ምሥጢር ያልተለመደና ምናልባትም የሚያስፈራ ነገር ነው። ይህ ቃል በጳውሎስ ዘመን የነበረው ትርጉም ግን እንደዚህ አልነበረም። የሐሰት አስተማሪዎች የሃይማኖታቸውን ውስጣዊ ምሥጢርና ድብቅ ነገር ለመግለጽ ነበር በዚህ ቃል የሚጠቀሙት። ምሥጢሩ ግን በፊት ተሰውሮ የኖረና አሁን ግን በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸ «ቅዱስ ምሥጢር» ነው (ኤፌ. 3፡1-13 ይመልከቱ)።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የራሱ ሕዝብ እንዲሆን ጠርቶታል። (የክህነትና የመሥዋዕት ሥርዓቶችን ጨምሮ) ሕጉንና መልካም ምድርን ሰጣቸው። አንድ ቀን ክቡር መንግሥት የሚመሠርትና ለአብርሃምና ለዳዊት የተሰጡትን በርካታ የተስፋ ቃሎች የሚፈጽም ንጉሥ ሊሰጣቸው ቃል ገባላቸው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት መከራን ስለሚቀበል በኋላም የመንግሥትን በትር ስለሚጨብጥ መሢሕ ጽፈዋል። ዳሩ ግን በሁለቱ ጉዳዮች መካከል ያሉትን ግጭት መሰል አሳቦች ለማብራራት አልቻሉም (1ኛ ጴጥ. 1፡9-12 ይመልከቱ)። መሢሑ ወደ ክብር ዙፋን ከመውጣቱ በፊት፦ መጀመሪያ መከራ መቀበል እንደነበረበት አልተገነዘቡም ነበር (ሉቃስ 24፡13-27)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህች ምድር በመጣ ጊዜ፦ የገዛ ወገኖቹ እንኳ ስላልተቀበሉት፦ በስቅላት ሞቶአል። ከሞትም ተነሥቶ ወደ ሰማይ ዐርጓል። ይህ ማለት እግዚአብሔር ለእስራኤል ተስፋ የገባላቸው መንግሥት አሁን ቀርቶአል ማለት ነውን? አይደለም። ምክንያቱም

እግዚአብሔር አዲስ መርሐ-ግብር አውጥቷል። ይህም የዕቅዱ ምሥጢር በብሉይ ኪዳን ነቢያት አልተብራራም ነበር። ይህ ምሥጢር ሲብራራ በዛሬው ዘመን አሕዛብንና አይሁድን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት አንድ እያደረጋቸው ነው (ኤፌ. 2፡11-22)። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሲፈጸም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለስና ሕዝቡን ወደ ሰማይ ይወስዳቸዋል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። ከዚያም ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እንደገና በመሥራት በተስፋ ቃሉ የተናገረውን መንግሥት ይመሠርታል (የሐዋ. 15፡12-18)።

ይህ መልእክት ለአሕዛብ ምን ትርጉም ሊሰጣቸው እንደሚችል ያስተውሉ። አሁን ከእግዚአብሔር ጸጋ ክብርና ባለጸግነት የተገለሉ አይደሉም። በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ አንድ አሕዛብ ከእስራኤል በረከቶች ለመካፈል ቢፈልግ ወደ አይሁዲነት መለወጥ ነበረበት። ዳሩ ግን በአዲሱ ዘመን አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት ብቻ ይድናሉ (ሮሜ 10፡12-13)። ጳውሎስ፡- «ምንም ልዩነት የለም!» በማለቱ የአይሁድ አስተማሪዎች ቢቃወሙት አያስደንቅም።

በክርስቲያኖች አካባቢ ያደግን ሰዎች ይህን ሁሉ ቀላል አድርጎ የማየት አዝማሚያ ይታይብናል። ዳሩ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ላልቆዩ አዳዲስ ክርስቲያኖች ይህ መልእክት ሊያመጣ የሚችለውን አድናቆትና ደስታ ልብ ይበሉ። አሕዛብ በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውጭ ነበሩ፤ አሁን ግን የቤተሰቡ አባላት ሆነዋል። በአንድ ወቅት በመንፈሳዊ ድንቁርናና ሞት ውስጥ ነበሩ፤ አሁን ግን ሕያዋንና በክርስቶስ አማካኝነት የእግዚአብሔርን የጥበብ ብልጽግና እየተካፈሉ ነው። በአንድ ወቅት ተስፋ ያልነበራቸው ሲሆኑ፥ አሁን ግን ክርስቶስ በውስጣቸው ስለሚኖር የክብር ተስፋ አላቸው። ዛሬ እኛም ቀድሞ የተለማመድነው «የመጀመሪያ ፍቅር» አስደሳች ገጽታ እንደገና ቢታደስልን ምንኛ መልካም በሆነ ነበር።

ለሦስት ሳምንታት በአፍሪካ ውስጥ የማገልገል ዕድል አጋጥሞኝ ነበር። በሕይወቴ ካገኘኋቸው ክርስቲያኖች ሁሉ እጅግ አስደሳች ከሆኑ አንዳንድ ወገኖች ጋር ተዋውቄ ነበር። ለአንድ ሳምንት ያህል ከ500 ለሚበልጡ ኬንያውያን መጋቢዎች ቃሉን አስተምሬ ነበር። እያንዳንዱም አገልግሎት ራስን የመመርመርና የታላቅ በረከት ጊዜ ነበር። ብዙዎቹ

መጋቢዎች የአረማዊነትና የጣዖት አምልኮ ምልክቶች በአካሎቻቸው ላይ አሁንም ይታዩ ነበር። ይሁን እንጂ ፊታቸው በጌታ ደስታ ያንጸባርቅ ነበር። ወደ አፍሪካ የሄድሁት እነርሱን ለማገልገል ሲሆን፥ ዳሩ ግን እነርሱ እኔን አገለገሉኝ! በክርስቶስ ያገኘሁትን የክብር ባለጸግነት እንደ ዋዛ እንዳልመለከት አሳሰቡኝ።

ለቅዱሳን መጋደል (ቆላ. 1:28-2:3)

ቀደም ብለን ሰባኪው ጳውሎስ ወንጌሉን ለሌሎች ሲያካፍልና እስረኛ ሆኖ ደግሞ ለአሕዛቦች መከራን ሲቀበል ተመልክተናል። አሁን ደግሞ የጸሎት አርበኛው ጳውሎስ፥ ቅዱሳን በእምነት ይጠነክሩ ዘንድ በጸሎት ሲጋደል እንመለከታለን። «መጋደል» (1:29፤ 2:1) የሚለው ቃል በውድድር ውስጥ ያሉ የሯጮችን እንቅስቃሴ የሚያመለክት ነው። በመሆኑም አንድ ሯጭ ውድድሩን በድል አድራጊነት ለመደምደም የሚያደርገውን ከፍተኛ ጥረት ይገልጻል።

የጳውሎስ ትምህርት (1:28)፥ እርሱ የሚለው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት ነው። «ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና» (2ኛ ቆሮ. 4:5)። የሐሰት አስተማሪዎች ራሳቸውንና «መንፈሳዊ» ድሎቻቸውን ነበር የሚያነሱት። እነርሱ የማስተማር ዘዴን ሲሰብኩ፥ ጳውሎስ ግን የሰበከው አካላዊ ሕልውናን ነበር። ኖስቲኮች ፍልስፍናንና ከንቱ ልማዶችን ሲሰብኩ (ቆላ. 2:8)፥ ጳውሎስ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን አውጆአል። የሐሰት አስተማሪዎች ሕግጋትና ደንቦችን ሲዘረዝሩ (ቆላ. 2:16፥ 20-21)፥ ጳውሎስ ግን ክርስቶስን አቅርቦአል። የአገልግሎቶቻቸው ልዩነት እጅግ ከፍተኛ ነበር።

ጳውሎስ የሰበከው «የምሥራቹን ሥልጣን ማወጅ» ሳይሆን ማስጠንቀቂያም ሰጥቶአል። መልካሙን እውነት ማወጅ ተገቢ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በጠላት የውሸት ቅስቀሳዎች እንዳይታለል ማስጠንቀቁም አስፈላጊ ነው (የሐዋ. 20:31)። በመሠረቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ አንዱ ከሌላው ማስጠንቀቂያ ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለበት (በቆላ. 3:16 ላይ ተግሳጽ ተብሏል)። ጳውሎስ ራሱን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አባት አድርጎ ስለሚቆጥር ልጆቹን ማስጠንቀቅ የእርሱ ኃላፊነት ነበር (1ኛ ቆሮ. 4:14)።

በተጨማሪም ጳውሎስ የእውነት አስተማሪ ነበር። ሰዎችን ማስጠንቀቅ ብቻውን በቂ አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በአዎንታዊ ገጽታ

ማስተማርም አለብን። መንገዱ እፈለግንበት ስፍራ እንደሚያደርሰን ባናውቅ ኖሮ ምን ያህል ርቀን ለመጓዝ ዝግጁ እንሆናለን? እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም ያህል ርቀን አንሄድም። አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ማምጣትና ያንን ሰው ስለሚጠብቁት አደገኛ ሁኔታዎች ማስጠንቀቅ ሁለቱም መልካም ነገሮች ናቸው። በተጨማሪም ያንኑ ሰው የክርስትናን ሕይወት መሠረታዊ እውነታዎች ማስተማር ይገባል።

ጳውሎስ ክርስቶስን መስበክ ብቻ ሳይሆን «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ እንደሆነ (ቆላ. 2፡3) አስተምሮአል።» አንድ አማኝ ማወቅ የሚያስፈልገው ሁሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ሌላ አዲስ ትምህርት ማቅረብ አስፈላጊ አልነበረም። የጳውሎስ አሳብ «ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ ማስተማር» ነበር (ቆላ. 1፡28)። ጥበብ በተገቢው መንገድ እውቀትን ማቅረብ ማለት ነው። የሐሰት አስተማሪዎች ለሕዝቡ «በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲበለጽጉ» የሚያደርጋቸውን «የተሰወረ ጥበብ» እንደሚሰጡ ቃል ገብተው ነበር። ዳሩ ግን መንፈሳዊ ጥበብ ሁሉ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

የጳውሎስ መሻት (1፡28)፦ ጳውሎስ እያንዳንዱን አማኝ «በክርስቶስ ፍጹም አድርጎ» ለማቅረብ ይፈልግ ነበር። «ፍጹም» የሚለው ቃል በናስቲክ አስተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅ ነበር። ይህም ልምድ የሌለውን አዲስ ደቀ መዝሙር ማለት ሳይሆን የበሰለና የሃይማኖቱን ምሥጢራት ሙሉ ለሙሉ የተረዳውን ሰው የሚያመለክት ነበር። ጳውሎስ በዚህ ቃል የተጠቀመው «ምሉዕ፦ በክርስቶስ የበሰለ» ለማለት ፈልጎ ነው። የመስበክ፦ የማስጠንቀቅና የማስተማር ግብ ይኸው ነው።

የዚህ መንፈሳዊ ብስለት ማስረጃዎች ምንድናቸው? ቀጥሎ ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ይገልጻል (ቆላ. 2፡2)።

መጽናናት - «ልባቸው እንዲጽናና» ይላል። ሰዎችን ማጽናናት ማለት ለእነርሱ አዲስ ልብ መስጠት ማለት ነው። ጥልቀት የሌለው መጽናናት በፊት ከነበሩበት አሳዛኝ ሁኔታ የባሰ እንዲያዝኑ ያደርጋቸዋል። ነገር ግን እውነተኛ የሆነ መጽናናት በፊት ከነበሩበት አሳዛኝ ሁኔታ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንዲገኙ ይረዳቸዋል። በሰዎችም ሕይወት ውስጥ ከሁሉ የተሻለው መልካም ነገር እንዲፈጸም ያደርጋል።

ፍቅር - «በፍቅርም ተባብረው»፦ የበሰለ ክርስቲያን ወንድሞችን ስለሚያውቅ አስታራቂ ነው እንጂ በጥባጭ ወይም ችግር ፈጣሪ

አይደለም። ይህ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈሳዊ አንድነት ተካፋይ ነው። ያልበሰለ ክርስቲያን ግን ራስ-ወዳድነት ስለሚያጠቃው መከፋፈልን ያመጣል።

ባለጠግነት - «ወደ መረዳት ባለጠግነት»፥ ቀደም ሲል ጳውሎስ የክርስቶስን ባለጠግነት ጠቅሶአል (ቆላ. 1፡27)። እጅግ ብዙ ክርስቲያኖች እንደ ነገሥታት መኖር ሲገባቸው እንደ ጎስቋላ ምስኪኖች ይኖራሉ። የበሰሉ ክርስቲያኖች ስላጧቸው ወይም ስለሌላቸው ነገሮች አያጉረመርሙም። ይልቁንም በክርስቶስ አማካኝነት ባገኙዋቸው በርካታ ሀብቶች ተደስተው ይኖራሉ።

ማስተዋል - «በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት»፥ የበሰለ ክርስትያን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ዋስትና በልቡ ውስጥ አለው። በክርስቶስ ያገኘው መንፈሳዊ እውቀት ያለማቋረጥ በማስተዋል እንዲመላለስ ይመራዋል። የደኅንነት ዋስትና ያጡትን ክርስቲያኖች በማማከር ብዙ ጊዜ አገልግያለሁ። ከእነዚህ ሰዎች በተደጋጋሚ ያስተዋልኩት የእግዚአብሔርን ቃል ችላ በማለት በመንፈሳዊ ድንቁርና እንደሚኖሩ ነው።

ልጆቹ እንደመሆናችን መጠን እግዚአብሔር «ማስተዋል» እንዲሁም «ጥበብና እውቀት» እንዲኖረን ይፈልጋል (2፡2-3)። ማስተዋል ተብሎ የተተረጎመው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም «በአንድ ላይ ሰብስቦ ማስቀመጥ» እንደ ማለት ነው። ይህም ነገሮችን የመገምገም ብቃት ማለት ነው። ጥበብ የተረዳነውን ነገር አጥብቀን ይዘን የመቆም ችሎታችንን ያመለክታል። እውቀት ደግሞ እውነትን የመረዳት ችሎታ ነው። እነዚህ ቃላት ኖስቲኮችም አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ቃላት ናቸው።

የጳውሎስ ምልጃ (1፡29-2፡1)፥ በቆላ. 1፡29 የተጠቀሰው አሳብ በቀጥታ ሲተረጎም «ለዚህም እስክንታክትና እስክንሠቃይ ድረስ እየሠራን እንደክማለን» የሚል መልእክት አለው። ጸሎትን በጣም ውብ በሆኑ ቃላት የሚገልጽ አሳብ ነው። አብዛኛው ጸሎታችን የተረጋጋና ምቾትም ያለበት ሲሆን፥ ጳውሎስ ግን አንድ የግሪክ ሯጭ በኦሎምፒክ ውድድሮች ላይ ለማሸነፍ ጡንቻውን በማሠራት እንደሚጋደል መንፈሳዊ ሽንጡን ገትሮ ይታገላል። ኤጳፍራንም በዚሁ መንገድ እንዲጸልይ አስተምሮታል (ቆላ. 4፡2)።

እንዲህም ስለተባለ ሥጋዊ ብርታትና ኃይላችን ለጸሎት ሕይወታችን ድርሻ ወይም አስተዋጽኦ አለው ማለት አይደለም። ወይም «ከእግዚአብሔር ጋር ታግለን» መሻታችንን እንዲያሟላልን እርሱን ማድከም አለብን ማለት አይደለም። ጳውሎስ መንፈሳዊ ተጋድሎ ምን እንደሆነ ገልጾአል። ይኸውም በሕይወቱ ውስጥ የሚሠራ የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን ነው። እውነተኛ ጸሎት ወደ አብ (ማቴ. 6:9)፥ በልጁ ስም በኩል (ዮሐ. 14:13-14)፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል (ይሁዳ ቁ. 20) ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ሲሠራ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በመሆን በኃይል ልንጸልይ እንችላለን።

መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ሕይወታችን የሚረዳን እንዴት ነው? መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ያስተምረናል፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያሳየናል (ዮሐ. 16:13-15)። ጸሎት የእግዚአብሔርን አእምሮ መረዳትና እንደ ፈቃዱ መጠየቅ እንጂ የእግዚአብሔርን አእምሮ ለመለወጥ መሞከር አይደለም (1ኛ ዮሐ. 5:14-15)። ምንም እንኳ እኛ ድምፁን ባንሰማም፥ መንፈስ ቅዱስ ባለማቋረጥ ይቃትትልናል (ሮሜ 8:26-27)። የአብን ፈቃድ ስለሚያውቅ በዚያው ፈቃድ መሠረት እንድንጸልይ ይመራናል።

ጸሎት ለመጸለይ ስሜታችን የማይነሣሣበት ጊዜ አለ። ነገር ግን አብዝተን ልንጸልይ የሚገባን በእንዲህ ዓይነት ጊዜ ነው። ከስሜታችን በተቃራኒ፥ መንፈስ ቅዱስ በጸሎት የምንተጋበትን መለኮታዊ ኃይል ይሰጠናል። የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤው ኃይል በሕይወታችን ውስጥ በሙላት ይሠራል (ኤፌ. 3:20-21)።

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ አገልግሎቱን በመግለጽ የጠላትን ክሶች ጸጥ አሰኝቶአል። እንዲሁም ምን ያህል እንደደከመላቸው በመግለጽ አማኞች ለእርሱ የነበራቸውን ፍቅር ቀስቅሶአል።

ሁላችንም ሐዋርያት ለመሆን ባንጠራም፥ እያንዳንዳችን ከእግዚአሔር የተሰጠ የአገልግሎት ድርሻ አለን። ወንጌሉን በመስበክ ብዙ ነፍሳት ለመማረክ እንችላለን። ለክርስቶስ መከራ ልንቀበልና እግዚአብሔር የሰጠንን አገልግሎት ልንፈጽም እንችላለን። ለእግዚአብሔር ሕዝብ በጸሎት ልንጋደልና ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርሱ ልናበረታታቸው እንችላለን። ጳውሎስ ግለሰቦችን ለማገልገል ጊዜ ወስዶአል፤ ይህንን ለመረዳት በቆላስይስ 1:28 «ሰውን ሁሉ» (እያንዳንዱን ሰው) በማለት

ያቀረበውን ድግግሞሽ ማየት ይቻላል። ጥቂት አማኞችን ስናገለግል ጠቅላላ ምእመኑን እያገለገልን ነው ማለት ነው።

እግዚአብሔር የሰጠዎትን አገልግሎት እየፈጸሙ ነዎት?

- 6 -

ሕያዋንና ንቁ የሆኑ ቅዱሳን

ቆላስይስ 2፡4-15

በአንድ ትምህርት ቤት አካባቢ ስለተከፈቱት አላስፈላጊ የንግድ ቤቶች ጉዳይ ስላሳሰበው ስለ አንድ መጋቢ ታሪክ አስታውሳለሁ። የንግድ ቤቶችን አላስፈላጊነት በመግለጽ አጥብቆ ይቃወማቸው ነበርና ይሽው አቋሙ በመጨረሻ ወደ ፍርድ ቤት ችሎት እንዲቀርብ አደረገው። የነጋዴዎቹ ጠበቃም የወንጌሉን አገልጋይ ለማሳፈር የሚችለውን ሁሉ አደረገ።

ዳኛውም፡- «አንተ መጋቢ አይደለህምን?» በማለት ጠየቀው አክሎም፡- «መጋቢ ማለት እረኛ ማለት አይደለምን?» አለው።

አገልጋዩም በፍችው ተስማማ።

«መልካም፤ እረኛ ከሆንህ፥ ለምን ዐርፈህ በጎችህን አትጠብቅም?» አለው።

መጋቢውም ፡- «ምክንያቱም ዛሬ ተኩላዎችን እየተዋጋሁ ነኝ» በማለት ፈጣን መልስ ሰጠው።

በቆላስይስ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ጠላቶች እያጠቁአት እንደነበር በማወቅ፥ ጳውሎስ ለምእመናን የማበረታቻ መልእክት ይጽፍላቸዋል። ምክሩን ከተቀበሉ፥ የቆላስይስ ሰዎች ጠላቶቻቸውን ያሸንፋሉ።

በመንፈሳዊ ዕድገት በርቱ። (ቆላ. 2፡4-7)

በክርስትና ሕይወት ውስጥ ወደ ፊት መራመድ ወይም ቀስ በቀስ ወደ ኋላ መንሸራተት እንጂ ከቶውንም ባሉበት መርገጥ አይቻልም። «ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት እንገስግስ!» የሚለውን ጥሪ ልንታዘዘው የሚገባን ጥሪ ነው። (የዕብ. 6፡1 ቀጥተኛ ትርጉም)። መንፈሳዊ ዕድገትን የማያሳይ ክርስቲያን ለጠላት የተጋለጠ ዒላማ ነው። ጠላት ሊያጠቃውና ሊያጠፋው የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

የዕድገት አስፈላጊነት (2፡4)፥ ሰይጣን አታላይ ስለሆነ አማኞችን ወደ ስሕተት ሊመራ ይፈልጋል። ይህንንም የሚያደርገው በማታለያ ቃላት

በመጠቀም ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል አንድ የሕግ ባለ ሙያ ተከሳሹን ሰው ለማሳመን የሚያቀርበው የመከራከሪያ አሳብ ዓይነት ነው። ሰይጣን ሐሰተኛ ስለሆነ (ዮሐ. 8፡44)፥ በሐሰተኛ ቃሉ አማኞችን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሊመራቸው ይፈልጋል። ስለሆነም መንፈሳዊ የመለየት ተግባራትን መለማመድና መንፈሳዊ እውነትን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

የዕድገት ባሕርይ (2፡5-7)፥ ጳውሎስ ለምክሩ አጽንዖት ለመስጠት፥ መንፈሳዊ ዕድገትንም ለማብራራት በርካታ ምሳሌያዊ ገለጻዎችን አቅርቦአል።

ሠራዊቱ (ቁ. 5)፥ ሥርዓትና ጽናት የሚሉት ቃላት ወታደራዊ ቋንቋዎች ናቸው። በመሆኑም በጠላት ላይ በጎብረት የተሰለፈው ሠራዊትን ያመለክታሉ። ሥርዓት የሚለው እያንዳንዱ ወታደር ተገቢ ስፍራውንና ደረጃውን ጠብቆ መሰለፍ እንዳለበት ይገልጻል። ሁሉም ሰው ጄኔራል ሆኖ ጦሩን ሊመራ አይችልም፤ ጄኔራሉም ደግሞ ብቻውን ሊዋጋ አይችልም። ጽናት በውጊያ ሜዳ በጠላቶቻቸው ላይ ጠንካራ አቋም ያላቸውን ወታደሮች ያመለክታል። ወታደሮች በጦር ሜዳ ላይ እንደሚያደርጉት ሁሉ ክርስቲያኖች በሥነ-ሥርዓትና በታዛዥነት ዕድገት ማሳየት ይኖርባቸዋል።

ተጓጮች (ቁ. 6)፥ የክርስትና ሕይወት ከጉዞ ጋር ተወዳድሮአል። በመሆኑም አማኞች እንዴት በእምነት መጓዝ (መመላለስ) እንዳለባቸው መማር አለባቸው። ቀደም ሲል ጳውሎስ አንባቢዎቹን «በጌታ እንደሚገባ ይመላለሱ ዘንድ» (ቆላ. 1፡10) ሲያበረታታቸው ተመልክተናል። ይህንኑ ገለጻ እንደገና ይጠቀምበታል (3፡7፤ 4፡5)። ከቆላስይስ መልእክት ጋር አብሮ በተጻፈው የኤፌሶን መልእክት ውስጥ ጳውሎስ ይህንን ገለጻ ቢያንስ ሰባት ጊዜ ያህል ተጠቅሞበታል (ኤፌ. 2፡2፥ 10፤ 4፡1፥ 17፤ 5፡2፥ 8፥15)።

በመጀመሪያ ክርስቶስን በእምነት በተቀበልንበት ዓይነት ሁኔታ መመላለስ አለብን። የኖስቲክ አስተማሪዎች ለክርስቲያናዊ ብስለት አንዳንድ «አዳዲስ እውነቶችን» ለማስተዋወቅ ቢፈልጉም፥ ጳውሎስ ግን አውግዞአቸዋል። እንዲሁም፡- «በክርስቶስ ስለጀመራችሁ፥ በእርሱ መቀጠል አለባችሁ፤ በእምነት ስለጀመራችሁ በእምነት መቀጠል

አለባችሁ። መንፈሳዊ ዕድገትን ለማግኘት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው» ብሎአቸዋል።

ዛፍ (ቁ. 7)፥ ሥር ሰድዳችሁ የሚለው ቃል ከዕፅዋት ወይም ከግብርና ጋር የተያያዘ ቃል ነው። የግሪኩ ቃል የጊዜ አመልካች የሚያመለክተው «ለአንዴና ለዘለዓለሙ ሥር ሰድደው» እንዲታነጹ ነው። ክርስቲያኖች በእያንዳንዱ «የትምህርት ነፋስ የሚፍገመገሙ» (ኤፌ. 4፡14) ሥር የሌላቸው ደካማ ዕፅዋቶች መሆን የለባችውም፤ ወይም ከአንዱ ዐፈር ወደ ሌላው የሚዘዋወሩ «ችግኞች»ም መሆን የለባቸውም። አንድ ጊዜ በክርስቶስ በማመን ከተተከልን ዐፈሩን የምንቀይርበት ምክንያት የለም። ሥሮቹ ምግብና ውኃን ከመሬት ውስጥ ስለሚስቡ ዛፉ ሊያድግ ይችላል። እንዲሁም ሥሮቹ ለዛፉ ጥንካሬንና ጽናትን ይሰጣሉ።

ሕንፃው (ቁ. 7)፥ ታነፁ የሚለው የሕንፃ ጥበብ ቋንቋ ነው። ይህ «ታነፁ» የሚለው ቃል የአሁን ጊዜን ነው የሚያመለክተው። ክርስቶስ እንዲያድነን በእርሱ በምንታመንበት ጊዜ በመሠረቱ ላይ ቆመናል ማለት ነው። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በጸጋ እያደግን እንሄዳለን። በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ አብዝቶ የሚገኘው ግንኙ የሚለው ቃል «መገንባት» የሚል ትርጉም አለው። የመንፈሳዊ ዕድገት ማለት ለእግዚአብሔር ክብር በቤተ መቅደሱ ሕንፃ ላይ እየገነቡ መሄድ ማለት ነው።

ትምህርት ቤቱ (ቁ. 7)፥ ክርስቲያንን የሚያንፀውና የሚያጠነክረው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ኤጳፍራ በታማኝነት የቃሉን እውነት ለቆላስይስ ሰዎች አስተምሮአል (1፡7)። ዳሩ ግን የሐሰት አስተማሪዎች ያንን ትምህርት እያቃለሉት ነበር። ዛሬ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያጠኑ ክርስቲያኖች በእምነት ጸንተው ይቆማሉ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን የተማሩትን አማኞች ሰይጣን በቀላሉ ሊያስታቸው አይችልም።

ወንዝ (ቁጥር 7)፥ መብዛት የሚለውን ቃል ጳውሎስ አዘውትሮ ይጠቀምበታል። ይህም በወንዙ ዳርቻ ምልቶ የፈሰሰውን የወንዝ ሙላት ያሳያል። በጌታ ያለን የመጀመሪያው ልምምዳችን የሕይወትን ውኃ በእምነት መጠጣት ሲሆን ይህም በውስጣችን የሚፈልቅና የሚፈስ የውኃ ምንጭ ይሆናል (ዮሐ. 4፡10-14)። ዳሩ ግን ያ የሚፍለቀለቅ የውኃ ምንጭ ጥልቅ የሆነ «የሕይወት ውኃ ወንዝ» (ዮሐ. 7፡37-39) መሆን አለበት። ምናልባት በጳውሎስ አእምሮ ውስጥ ያለው ነገር ከመቅደሱ የሚፈሰውና (ሕዝ. 47) በየጊዜው ጥልቀቱን እየጨመረ የሚሄደውን የውኃ

ምንጭ ምሳሌ ሳይሆን አይቀርም። በጣም የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቻችን ዕድገት አናሳይም። ሕይወታችን ኃያል ወንዝ በመሆን ፋንታ የደካማ ኩሬ ዓይነት ነው።

አሁንም ጳውሎስ «ምስጋና»ን ጠቅሶአል (ቆላ. 1፡3፥ 12 ይመልከቱ)። አመስጋኝ መንፈስ የክርስቲያናዊ ብስለት ምልክት ነው። አንድ ክርስቲያን ምስጋና የሚበዛለት ከሆነ እውነትም መንፈሳዊ ዕድገት እያሳየ ነው ማለት ነው።

እነዚህን የመንፈሳዊ ዕድገት መግለጫዎች በመመልከት አዳጊ ክርስቲያን እንዴት ጠላትን በቀላሉ እንደሚያሸንፍና ወደ ጥፋትም እንደማያመራ እንመለከታለን። መንፈሳዊ ሥሮቹ በክርስቶስ የጠለቁ ከሆኑ፥ ሌላ ዐፈር አይፈልግም። መሠረቱ በእርግጥ ክርስቶስ ከሆነ፥ ከዚያ እግሩን መንቀል አያስፈልገውም፤ ቃሉን እያጠናና እያደገ ከሆነ፥ በቀላሉ በሐሰት ትምህርት ሊፈታ አይችልም። እንዲሁም ልቡ በምስጋና የተሞላ ከሆነ፥ በክርስቶስ ካገኘው ሙላት ፈቀቅ ለማለት አሳብ እንኳ አይኖረውም። አስተማማኝ መሠረት ያለው፥ የሚያድግና የሚያመሰግን ክርስቲያን ወደ ጥፋት ሊያመራ አይችልም።

ከመንፈሳዊ ችግሮች ተጠንቀቁ (ቆላ. 2፡8-10)

ጳውሎስ በዚህ ማስጠንቀቂያ ውስጥ እንደገና ወታደራዊ ቋንቋ ሲጠቀም እንመለከተዋለን፡- «ማንም ሰው እንዳይማርካችሁ ተጠንቀቁ» (ቀጥተኛ ትርጉም)። እንደ ማንኛቹም የሐሰት ትምህርት ተከታዮች ሁሉ እነዚህም የሐሰት መምህራን ሌሎችን ሰዎች ወደ ክርስቶስ ሲያመጡ አይታዩም። ተከታዮቻቸውን ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው የሚያጠምዱት! ወደ ፀረ-ክርስትና እምነት ከተወሰዱት ውስጥ ብዙዎቹን አነጋግሬ እንደተረዳሁት እነዚህ ሰዎች ወደዚያ የሐሰት ትምህርት ከመግባታቸው በፊት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ጎብረት የነበራቸው ወይም ራሳቸው ክርስቲያኖች እንደነበሩ አስተውያለሁ።

የሐሰት አስተማሪዎች ሰዎችን የሚያጠምዱት እንዴት ነው? መልሱ ቀላል ነው፡- እነዚህ «ምርኮኞች» የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት ስለማያውቁ ነው ወደ ሐሰት ትምህርት የሚነዱት። ስለዚህም በሐሰተኛ አስተማሪዎች ፍልስፍናና ባዶ ማታለያ ይማረካሉ። (ይህ ማለት ፍልስፍና ሁሉ ስሕተት ነው ማለት አይደለም። ምክንያቱም ክርስቲያናዊ የሕይወት ፍልስፍና አለ። «ፍልስፍና» የሚለው የቃሉ ትርጉም «ጥበብን

መውደድ» ማለት ነው)። አንድ ሰው የክርስትና እምነት ትምህርቶችን ጠንቅቆ ካልተረዳ በቀላሉ በሐሰተኛ ሃይማኖቶች ሊወሰድ ይችላል።

ይህ የሐሰተኛ አስተማሪዎች ፍልስፍና ከበርካታ ምክንያቶች የተነሣ «መሠረት የለሽና ከንቱ ማታለያ» ነው (ቁ. 8)። ቀድሞ ነገር ይህ፥ የሰዎች ወግ እንጂ የእግዚአብሔር እውነት አይደለም። ወግ ማለት «ከቀደሙት የተወረሰ ባህል» እንደ ማለት ነው። በእርግጥ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ወግ አለ (2ኛ ተሰ. 2፡15፤ 3፡6፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡3-11)። ለማንኛውም ትምህርት ወሳኙ ጉዳይ ምንጩ ነው፡- የመጣው ከእግዚአብሔር ነው ወይስ ከሰው? በጌታችን ዘመን የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች የራሳቸው የሆኑ ወጎች ስለነበሯቸው ለወጋቸው ለመታዘዝና ለመጠበቅ አጥብቀው ይጥሩ ነበር (ማቴ. 15፡1-20)። ሐዋርያው ጳውሎስም እንኳ ጌታን ከማግኘቱ በፊት «ለአባቶች ወግ ከመጠን በላይ ይቀና» ነበር (ገላ. 1፡14)።

አንድ አዲስ ክርስቲያን ከሩቅ አገር ቢመጣና አብዛኛዎቹን አብያተ ክርስቲያናታችንን ቢጎበኝ፥ የእግዚአብሔር ቃል ድጋፍ የሌላቸው አሳቦችና ልምምዶች በመመልከት መደነቁ አይቀርም። ሰው-ሠራሽ ወጎቻችንን እግዚአብሔር ከሰጠን የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች በላይ አስፈላጊዎች አድርገን ይዘናቸዋል። መንፈሳዊ ቅርሶቻችን የሚያስታውሱን የቤተ ክርስቲያን ወጎች መጥፎ ባይሆኑም፥ እነዚህን ወጎችና ልማዶች ከእግዚአብሔር ቃል በላይ እንዳናደርጋቸው መጠንቀቅ አለብን።

የሐሰት አስተማሪዎቹ ወጎች «መሠረት የለሽና ከንቱ ማታለያዎች» የሆኑበት ሌላው ምክንያት፡- «የመጀመሪያ ዓለማዊ ሥርዓት» አካትተው የያዙ በመሆናቸው ነው። በዚህ ስፍራ «የመጀመሪያ ትምህርት» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «ከተርታዎቹ ወይም ከመደዳዎቹ አንዱ» የሚል ፍች አለው። ቃሉም በርካታ የተያያዙ ትርጉሞች አሉት፡- (1ኛ) የመጀመሪያ ድምፆች ወይም ፊደሎች፥ ሀ- ሁ... ማለት ነው። (2ኛ) በ2ኛ ጴጥ. 3፡10-12 በተጠቀሰው መሠረት ዓለማት የተሠሩበት ጥንተ-ተፈጥሮ ማለት ነው። (3ኛ) ዕብራውያን 5፡12 ላይ በተጠቀሰው መሠረት የአንድ ዓይነት አሠራር መሠረታዊ ዕውቀት ማለትም ሀሁ እንደ ማለት ነው። በጥንታዊቷ ግሪክ አስተሳሰብ መሠረት ይህ ቃል «ሰማያዊ አካላት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ መላእክትንና የዓለም መናፍስታዊ አካላትን»

የሚያጠቃልል ትርጉም ነበረው። በዚያን ጊዜ ሃይማኖታዊ የከዋክብት ቆጠራ በሚያደርጉ ሰዎች መዝገበ ቃላት ውስጥ ከሚገኙ ቃላት መካከል ይህ አንዱ ነበር።

መላእክትና ሰማያዊ አካላት በሰዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ኖስቲኮች ያምኑ ነበር። ምንም እንኳ አይሁዶችም የራሳቸው የቀን አቆጣጠር ቢኖራቸውም (ገላ. 4:10)፥ ቀናትን፥ «የወር መባቻን» እና ሌሎች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን አስመልክቶ ጳውሎስ ማስጠንቀቂያ የሰጠው በቆላስያስ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ነበር (ቆላ. 2:16)። ለሰዎቹ የሰጠው ማስጠንቀቂያ (ቆላ. 2:16) ከዚህ የኖስቲኮች ትምህርት ጋር ሳይዛመድ አይቀርም። አንድ ነገር ግን እውነት ነው፡- ይኸውም ስለ አጋንንትና መላእክት የቀረቡት እንደዚህ ዓይነት ትምህርቶች የእውነተኛ ክርስቲያናዊ ትምህርት ክፍል አይደሉም፤ እነዚህ ትምህርቶች ሰይጣናዊ ናቸው።

ይህ ትምህርት ከክርስቶስ ስላልሆነ ከኮከብ ቆጠራ እና ከሌሎች የመናፍስት ልምምዶች እንድንርቅ ማስጠንቀቂያ ሊሆነን የሚበቃ ነው። የከዋክብትን እንቅስቃሴ የሚያመለክተው ትንቢታዊ ቃል በሙሉ ከቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ጋር የሚቃረን ነው። ለዚህ ዓይነቱ ሰመመናዊ ልምምድና የሐሰት ትምህርት መጠነኛ ፍላጎት የሚያሳይ ክርስቲያን በራሱ ላይ መከራን ይጋብዛል።

በክርስቶስ ሙላትን ሁሉ ካገኘን ለምን ባዶ ፍልስፍና እንከተላለን? ይህ አርኪውንና ንጹሑን የምንጭ ውኃ ትቶ ለሸንት ቤት ማጠቢያ ከተጠራቀመ የዓለም ቆሻሻ ውኃ እንደመጠጣት የሚቆጠር ነው (ኤር. 2:13)። በመሠረቱ በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች አማኞች ክርስቶስን እንዲተዉ አልጠየቋቸውም፤ ዳሩ ግን ክርስቶስን ከአዲሱ የፈጠራ ብልሃት አንዱ አካል አድርገው እንዲከተሉ ነበር ፍላጎታቸው። ይህ ግን ክርስቶስን ከተገቢው የበላይነት ስፍራው የሚያዋርደው ነበር።

ስለዚህ ጳውሎስ እውነተኛና ዘላቂ መፍትሔ ለሐሰት አስተማሪዎች በሙሉ ይሰጣል፡- ሙላት ሁሉ በክርስቶስ ስለሆነ፥ እናንተም በእርሱ ተሞልታችኋል። እንግዲህ ለምን ሌላ ነገር ትፈልጋላችሁ? (ቆላ. 2:9-10 ተመልከት)።

ቀደም ብለን «ሙላት» (ፕለይሮማ) የተባለውን ቃል ተመልክተናል (1:19)። የቃሉም ትርጉም «የእግዚአብሔር፥ የእርሱነቱና የባሕርይው

ጠቅላላ ድምር» ማለት ነው። ኖስቲኮች በዚህ ቃል ቢጠቀሙበትም፥ ጳውሎስ የሰጠውን ዓይነት ትርጉም አልሰጡትም ነበር። በእነርሱ አስተሳሰብ «ፕለይሮማ» ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሊመጡ የሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነበር። በኖስቲክ የሃይማኖት ልምምድ ውስጥ ትልቁ ነጥብ «የፕለይሮማ» ተካፋይ መሆን ነበር።

በመሠረቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጡ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች የሉም። በሰማይና በምድር መካከል ያለው ሽለቆ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለባሽነት ድልድይ ተሠርቶበት ተስተካክሎአል። እርሱም «አማኑኤል፥ እግዚአብሔር ከኛ ጋር» (ማቴ. 1፡23) ተብሎ ታውጆአል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሙላት ሲሆን ያም ሙላት ባለማቋረጥ ሁልጊዜም በእርሱ ውስጥ በአካል ይኖራል። ጳውሎስ ቁሳዊ አካል ከፉ እንደሆነና ኢየሱስ ሰብአዊ አካል እንዳልነበረው የሚናገረውን የኖስቲኮች ትምህርት እንደገና ውድቅ ያደርገዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው በሰብአዊ አካል ነው። በእርግጥ አካሉ የከበረ አካል ነበር፤ ቢሆንም እውነተኛ አካል ነበር። ከትንሣኤው በኋላ ጌታችን የቀድሞውን አካል የለበሰ ያው ቀድሞ የሚያውቁት ሰው እንጂ መንፈስ ወይም ምትሐት እንዳልሆነ ለደቀ መዛሙርቱ አረጋግጠ ነግሮአቸው ነበር (ዮሐ. 20፡19-29 ተመልከት)። ይህ የከበረ ሰው ዛሬም በሰማይ አለ! ሰውም እግዚአብሔርም የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሙላት ይዞአልና።

በጣም ደስ የሚያሰኘው ነገር ደግሞ፥ እያንዳንዱ አማኝ የዚያ ክብርና ሙላት ተካፋይ መሆኑ ነው። «በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል» (ቆላ. 2፡10)። የግሪኩ ቃል የጊዜ ጠቋሚ እንደሚያመለክተው ይህ ሙላት ዘላቂ እንጂ ጊዜያዊ አለመሆኑ ነው። በጣም ቀጥተኛ ሆኖ በማስፋፋት የተተረጎመው የዶክተር ኬነት ዌስት ትርጉም ፡- «በፍጹም በእርሱ ምሉዓን ሆናችሁ አሁን ባላችሁበት ደረጃ በእርሱ ተሞልታችኋል። በእርሱ ሆናችኋል» በማለት ይገልጸዋል።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ዳግም በሚወለድበት ጊዜ በክርስቶስ ሙሉ ሆኖ ነው የሚወለደው። መንፈሳዊ ዕድገቱም መንፈሳዊ ምግብን በመመገብ እንጂ በሌላ ተጨማሪ ነገር አይደለም። ከውስጥ ወደውጭ ያድጋል እንጂ ከውጪ የሚጨመርለት የለም። እርሱ

የእግዚአብሔር ሙላት ስለሆነ በክርስቶስ ላይ ምንም ነገር መጨመር አያስፈልግም። አንድ አማኝ ወደ ክርስቶስ ሙላት በሚቀርብበት ጊዜ «እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ድረስ» ተሞልቶአል (ኤፌ. 3፡19) ማለት ነው። ከዚህ በላይ ምን ያሻው ይሆን?

እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ክርስቲያንን የተለያዩ መንፈሳዊ ችግሮች ይገጥሙታል። ለማንኛውም ሃይማኖታዊ ትምህርት ማቅረብ ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ፥ «ለኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለሰብዓዊነቱና ለፈጸመው ሥራ የሚሰጠው ስፍራ ምንድን ነው?» የሚል መሆን አለበት። ከደረጃው ያወርደዋል? አምላክነቱን ወይም ሰብአዊነቱን ይክዳል? ከክርስቶስ ጋር የሚያደርገውን ልምምድ ለማጎልበት አማኙ አንዳንድ አዳዲስ ልምምዶችን መጨመር እንዳለበት ይናገራል? ይህ ከሆነ ያ ትምህርት የተሳሳተና አደገኛም ነው ማለት ነው።

መንፈሳዊ ስጦታዎቻችሁን ተጠቀሙ (ቆላ. 2፡11-15)

የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን ያስጨንቅ የነበረው የሐሰት ትምህርት ከተለያዩ የአስተሳሰብ ክፍሎች የተውጣጣ እንደነበር ልብ ይበሉ። ከእነዚህም ውስጥ የምሥራቃውያን ሰመመን፥ የከዋክብት ቆጠራ፥ ፍልስፍና፥ እንዲሁም የአይሁድ ሕግ-አጥባቂነት ይገኙበት ነበር። ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ የሚያነሣው የመጨረሻውን ነጥብ ማለትም የአይሁድ ሕግ አጥባቂነትን ነው። የሐሰት አስተማሪዎች ተከታዮቻቸውን እንዲገረዙና የብሉይ ኪዳን ሕግ እንዲጠብቁ አጠንክረው ያስተምሯቸው ነበር።

የኖስቲኮች ሕግ-አጥባቂነት፥ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክት ሐሰተኛነታቸውን ካረጋገጠባቸው አይሁዶች ሕግ ጋር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ አልነበረም። ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ የተቃወማቸው የአይሁድ አስተማሪዎች መገረዝና ለሕግ መታዘዝ ለደኅንነት አስፈላጊ እንደሆነ ያስተምሩ ስለ ነበሩ ነው። (በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ አሳብ ለማግኘት የሐዋ. 15ን አንብብ።) የኖስቲኮች ሕግ-አጥባቂነት፥ ክርስቲያኖች የአይሁድን ሕግ ቢከተሉ ይበልጥ መንፈሳዊ ለመሆን ይረዳቸዋል የሚል አስተሳሰብ ነበረው። የግርዘትን ሥርዓት ከፈጸሙ፥ የአመጋገብ ጥንቃቄ ካደረጉና የበዓል ቀናትን ካከበሩ «የመንፈሳዊ ብቃት» አካላት ይሆናሉ የሚል ነበር። ዛሬም በአብያተ ክርስቲያናችን እንደዚህ ዓይነት አሳብ ያላቸው ሰዎች መኖራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው።

ጳውሎስ ክርስቲያን በምንም ዓይነት ለብሉይ ኪዳን ሕግ የመገዛት ግዴታ እንደሌለበትና የበለጠ መንፈሳዊ ለመሆን ሕግ ሊያደርግለት የሚችለው ምንም በጎ ነገር እንደሌለ በግልጽ አስተምሮአል። የእግዚአብሔር ሙላት በሙሉ በእርሱ ውስጥ ስላለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ለመንፈሳዊ ፍላጎታችን ሁሉ በቂ ነው። እርሱ የአካሉ ራስ ስለሆነና (ቆላ. 1፡18)፥ እኛም የአካሉ ክፍሎች ስለሆንን (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)፥ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ተባብረናል። ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር የተባበርንበትንና ከማንኛውም ዓይነት ሕግ አጥባቂነት ጋር መተባበር አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ኃጢአትም የሆነባቸውን አራት ሁኔታዎች ይገልጻል።

በእርሱ ተገርዛችኋል (2፡11)። ግዝረት እግዚአብሔር ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን የማድረጉ ምልክት ነው (ዘፍ. 17፡9-14)። ግዝረት ሥጋዊ ተግባር ቢሆንም እንኳ መንፈሳዊ ጠቀሜታ ነበረው። ችግሩ፥ የአይሁድ ሕዝቦች መንፈሳዊውን ነገር ዘንግተው በሥጋዊ ልምምድ ላይ መደገፋቸው ነበር። ሥጋዊ ተግባር ብቻውን መንፈሳዊ ጸጋ ሊያስገኝ አይችልም (ሮሜ 2፡25-29)። ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ተመልሰው መንፈሳዊ የልብ መገረዝ እንዲለማመዱ ያስጠነቅቃቸው ነበር (ዘዳ. 10፡16፤ 30፡6፤ ኤር. 4፡4፤ 6፡10፤ ሕዝ. 44፡7)። ዛሬም ሰዎች እንደ ጥምቀት ወይም ቅዱስ ቁርባን የመሳሰሉ አንዳንድ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች እንደሚያድኗቸው በማሰብ፥ በእነዚህ ሥርዓቶች ላይ ሲደገፉ፥ የቀድሞውን ስሕተት መድገማቸው ነው።

አማኙ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመተባበር አስቀድሞ መንፈሳዊ ግዝረትን ስላደረገ ለሥጋዊ ግዝረት ሥርዓት መገዛት አያሻውም። ዳሩ ግን እዚህ ላይ በአይሁዶች ግዝረትና በአማኞች መንፈሳዊ ግዝረት መካከል ንጽጽር አለ፡-

የአይሁዶች ግዝረት	የአማኞች ግዝረት
. ውጫዊ የአካል ግዝረት	. ውስጣዊ የልብ ግዝረት
. ከሰውነት ክፍሎች አንዱን ብቻ የሚያካትት ሲሆን	. ኃጢአትን በሙሉ
. የሚፈጸመው በእጅ ነው	. ያለ እጅ የሚፈጸም ተግባር ነው

. ኃጢአትን ለማሸነፍ የሚሰጠው መንፈሳዊ ፋይዳ የለም።

. ኃጢአትን ለማሸነፍ ያስችላቸዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተና በተነሣ ጊዜ በኃጢአት ላይ ሙሉና ፍጻሜ ያለው ድል ተቀዳጀ። ለኃጢአታችን (ደኅንነት) ብቻ ሳይሆን፥ «ለኃጢአት ሞተ» (ቅድስና፥ ሮሜ 6፡10-14 ይመልከቱ)። ለሕግ ያልተቻለውን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጸመልን። አሮጌው ተፈጥሮ ማለት ከሥጋ የመነጨ ኃጢአት በሙሉ ስለተወገደ ከዚህ በኋላ ለሥጋዊ ምኞት ባሪያዎች መሆን አያስፈልገንም። አሁንም ኃጢአት መሥራት ስለምንችል አሮጌው የኃጢአት ተፈጥሮ አልተደመሰሰም (1ኛ ዮሐ. 1፡5-2፡6)። ዳሩ ግን ለክርስቶስ ራሳችንን ስንሰጥና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንመላለስ፥ የኃጢአት ኃይል ይዳከማል፤ በመጨረሻም ይሸነፋል።

በእርሱ ሕያዋን ሆናችኋል (2፡12-13)፤ በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የጥምቀትን ምሳሌያዊ ገለጻ ይጠቀማል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ጥምቀት» የሚለው ቃል ቀጥተኛና ምሳሌያዊ ትርጉም እንዳለው ልብ ይበሉ። ቀጥተኛው ትርጉም ፡- «ውኃ ውስጥ መግባት፥ መስመጥ» የሚል ሲሆን፥ ምሳሌያዊ ትርጉሙ ግን ከክርስቶስ ጋር «መተባበር» ማለት ነው። ለምሳሌ የአይሁድ ሕዝብ ቀይ ባሕርን በሚያቋርጡበት ጊዜ «ከሙሴ ጋር ይተባበሩ ዘንድ ተጠመቁ» (1ኛ ቆሮ. 10፡1-2)። በዚህ ጥምቀት ውስጥ ምንም ውኃ የለም፤ በደረቅ መሬት ነበር የተሻገሩት። በዚህ ወቅት ሕዝቡ ከሙሴ ጋር ተባብረው ነበር።

ምንም ያህል በርሜል ውኃ ቢከማች እንኳ አንድን ሰው ከክርስቶስ ጋር ሞቶ በክርስቶስ ሕያው ሆኖ እንዲኖር ሊያደርግ ስለማይችል፥ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ጥምቀት የሚለውን ቃል የተጠቀመው በምሳሌያዊ ትርጉሙ ነው። ውኃ ውስጥ በመጥለቅ የሚፈጸመው ጥምቀት ይህንን መንፈሳዊ ልምምድ ይገልጻል። አንድ ሰው ሲድን ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የክርስቶስ አካል ለመሆን ይጠመቃል (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። እንዲሁም ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ይተባበራል። ይህም መተባበር በክርስቶስ ላይ የደረሰው ሁሉ በእኛም ላይ እንደደረሰ ያስረዳል። እርሱ በሞተ ጊዜ፥ እኛም ከእርሱ ጋር ሞተናል፤ እርሱ በተቀበረ ጊዜ፥ እኛም ተቀብረናል፤ እርሱ በተነሣ ጊዜ፥ እኛም ከእርሱ ጋር ተነሥተን የአሮጌውን ሕይወት የመቃብር ልብሶች ወደኋላ ጥለናል (ቆላ. 3፡1-14)።

ይህ ሁሉ የሆነው «በእግዚአብሔር አሠራር በማመን» ነው (ቁ. 12)። የለወጠን የእግዚአብሔር ኃይል እንጂ የውኃው ኃይል አይደለም። የእግዚአብሔር መንፈስ እኛን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስላስተባበረን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል፤ ከእርሱ ጋር ተነሥተናል፤ እንዲሁም ከእርሱ ጋር በሕይወት እንኖራለን! (የግሪክ ቋንቋ ግሦች ይህንን በደንብ ይገልጻሉ፡- አብረን ተቀብረናል፤ አብረን ተነሥተናል፤ አብረን በሕይወት እንኖራለን።) እግዚአብሔር ልጁን ከሞት ስላስነሣው የዘለዓለም ሕይወት አለን።

የዚህ ትምህርት ተግባራዊ ተዛምዶ በጣም ግልጽ ነው፤ ይኸውም፡- እኛ ከክርስቶስ ጋር ስለተባበርንና ክርስቶስም የእግዚአብሔር ሙላት ስለሆነ ከዚህ በተጨማሪ ምን ያስፈልገናል? የሚል ነው። በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔርን ኃይል ከተለማመድን ዘንዳ፥ ወደ ሞተ የሕግ ሥርዓት ስለምን እንመለሳለን? እግዚአብሔር በደላችንን ሁሉ ይቅር ስላለን (ቁ. 13)፥ በፊቱ ፍጹምና ንጹሕ የሆነ አቋም አለን።

በእርሱ ከሕግ ባርነት ነጻ ሆናችኋል (2፡14)፥ ኢየሱስ ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ መሸከም ብቻ ሳይሆን (1ኛ ጴጥ. 2፡24)፥ ሕጉንም ወደ መስቀሉ በመውሰድ ከመንገድ አስወግዶ እዚያው ጠርቆታል። የሚፈልግብንን የተቀደሱ ትእዛዛት ለማሟላት ስለማንችል ሕጉ ተቃዋሚያችን እንደነበር እርግጥ ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር አሠርቱ ትእዛዛትን ለአሕዛብ ባይሰጥም፥ የሕጉ የጽድቅ ትእዛዛት ማለት የእግዚአብሔር ቅዱስ መመዘኛዎች «በልባቸው ውስጥ ተጽፈው» ነበር ማለት ነው (ሮሜ 2፡12-16)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአተኞች ደሙን ስላፈሰሰ፥ በእግዚአብሔር ቅዱስ ትእዛዝ ባመፁት ኃጢአተኞች ላይ የተከመረውን ከፍተኛ ዕዳ አስወገደ። መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን ብዙውን ጊዜ ሒሳብ ነክ የሆኑ ጉዳዮች በብራና ላይ ነበር የሚጻፉት። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብራናው ይታጠብና ጽሑፉ እንዲደመሰስ ይደረጋል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚሰጠው ገለጻም ይህን ይመስላል።

ዕዳን ፍቆ በማስወገድ ቅዱሱ እግዚአብሔር እንዴት ጻድቅ ሊሆን ይችላል? ልጁ በመስቀል ላይ በመሞት የዕዳውን ሙሉ ዋጋ ከፍሎአል። አንድ ዳኛ ጥፋተኛውን ሰው በነጻ ቢለቀው ሕጉን ዋጋ ከማሳጣቱም በላይ ተበዳዩን ወገን ያለ ካሳ ሊያሰናብተው ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር

ልጁን በመስቀል ላይ በመስጠት የኃጢአትን ዕዳ ከመክፈሉም በላይ የገዛ ራሱ ሕግ ቅድስና አረጋግጦአል።

እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ዕዳን ከመሰረዝ የላቀ ነገር አድርጓል፤ ከእንግዲህ ወዲህ በእርሱ አገዛዝ ውስጥ እንዳንሆን የሚቃወመንን ሕግ ከመንገድ አስወገደው። «ከሕግ ተፈትተናል» (ሮሜ 7፡6)። «ከጸጋ በታች ነን እንጂ ከሕግ በታች አይደለንም» (ሮሜ 6፡14)። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንመላለስ የሕግ ጽድቅ በእኛ ውስጥ ስለሚፈጸም ሕግ-አልበኞች ነን ማለት አይደለም (ሮሜ 8፡4)። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣ እግዚአብሔርን የምንታዘዘው ለእርሱ ባለን ፍቅር ምክንያት እንጂ የፍርሃት ባርያዎች ስለሆንን አይደለም።

በእርሱ ድል አድራጊዎች ሆናችኋል (2፡15)፤ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃጢአትንና ሕግን ብቻ ሳይሆን ሰይጣንንም አሸንፎአል። ስለ ስቅለቱ በሚናገርበት ጊዜ ኢየሱስ፡- «አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል» (ዮሐ. 12፡31) ብሎአል። የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ለሰይጣን ታላቅ ድል መስሎት ነበር፤ ዳሩ ግን ሰይጣን መልሶ ሊያንሰራራ የማይችልበት ታላቅ ሽንፈት ሆኖ ተገኘ።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሦስት ታላላቅ ድሎችን ተቀዳጅቶአል። በመጀመሪያ፥ «አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፍፎአል» (ቆላ. 2፡15)። ይህንንም ያደረገው ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ማንኛውንም ዓይነት ትጥቅ በማስፈታት ነበር። አማኝ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ራሱን ሲጎዳ በዚያን ጊዜ ሰይጣን አማኙን ሊያቆስለው ይችላል። ሰይጣን የጦር መሣሪያ አፈሙዙን የሚያዞርብን (እንደ ጴጥሮስ) ነቅቶ መጸለይ ሲሳነን ነው።

ሁለተኛ፥ ኢየሱስ «በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው» (ቁ. 15)። ይህንንም ያደረገው የሰይጣንን ማታለልና አስከፊነት ገሃድ በማውጣት ነው። ክርስቶስ በሞቱ፥ በትንሣኤውና በዕርገቱ የእግዚአብሔርን ትክክለኛነትና የዲያብሎስን ከንቱነት አረጋግጦአል።

ሦስተኛ፥ ድሉ «ማሸነፍ» በሚለው ቃል ውስጥ ይገኛል አንድ የሮም ጄኔራል በውጭ አገር ላይ ታላቅ ድል በማግኘት ብዙ ምርኮኞችንና ሀብቶችን ሲወስድና ለሮም አዲስ ግዛት ሲጨምር፥ «የሮም ድል» ተብሎ የሚጠራ አፈሴላዊ በዓል ተዘጋጅቶ አክብሮት ይሰጠው ነበር። ጳውሎስ በ2ኛው የቆሮንቶስ መልእክቱ ይህንን ሁኔታ ጠቅሶአል (2ኛ ቆሮ. 2፡14 ይመልከቱ)። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ድል ተቀዳጅቶ በድል አድራጊነት

ወደ ክብሩ ተመልሶአል (ኤፌ. 4፡8-11)። በዚህም ሰይጣንን ሐፍረትና ሽንፈት አከናንቦታል።

እኔና እርስዎ ክርስቶስ በዲያብሎስ ላይ ያገኘው ድል ተካፋዮች ነን። ዓለማትን በመቆጣጠር ወይም በሰዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ለሚፈልጉት ኃይሎች መጨነቅ የለብንም! የሰይጣናዊ ኃይላትና የሥልጣናት ሠራዊት ፈጽመው ተሸንፈዋል፤ ተዋርደዋልም። የክርስቶስን ድል በምናውጅበት ጊዜ የሰጠንን መሣሪያዎች መጠቀምና (ኤፌ. 6፡10-20) በእርሱም መታመን አለብን። እኛ ከዲያብሎስ ተጽዕኖ ነጻ ወጥተናል።

በክርስቶስ ያለን ስፍራና መብት ምን ያህል አስደናቂ ነው! ይህን አስመልክቶ በእምነት እየኖርን ነውን?

- 7 -

አማኝ ሆይ፥ ተጠንቀቅ!

ቆላስይስ 2፡16-23

በዋና ዋና መኪና መንገዶች ላይ ከሚደረጉ ቀይ መብራቶች ጀምሮ እስከ የሕክምና ባለሙያዎች ከሚያዝዙት መድኃኒቶች ድረስ፥ የሚሰጡት ልዩ ልዩ ማስጠንቀቂያዎች ከዕለታዊ ሕይወታችን ጋር የተያያዙ ናቸው። ሕፃናት ማስጠንቀቂያዎችን እንዲቀበሉ ማስተማር ያሻል፤ አዋቂዎችም ማስጠንቀቂያዎችን ችላ ሊሉ አይገባም። ማስጠንቀቂያዎቹ የሕይወት የወይም ሞት ጉዳዮች ናቸው።

መንፈሳዊ ሕይወትም የራሱ የሆኑ አደጋዎችና ማስጠንቀቂያዎች አሉት። እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ገብተው ከሰፈሩ በኋላ እግዚአብሔርን እንዳይረሱ ሙሴ አስጠንቅቆአቸዋል (ዘዳ. 6፡12)። ጌታችን ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ተጠንቀቁ የሚለውን ቃል ይጠቀም ነበር (ማቴ. 7፡15፤ ማር. 12፡38፤ ሉቃስ 12፡15)።

ጳውሎስም ቀደም ብሎ ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አስጠንቅቆአል (ቆላ. 2፡8)። በዚህኛው መልእክቱ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ባገኘነው ሙላት ለመደሰት ከፈለግን ልብ ማለት የሚገቡንን ሦስት ማስጠንቀቂያዎች ይሰጠናል።

«ማንም አይፍረድባችሁ» (ቆላ. 2፡16-17)

ይህ ማስጠንቀቂያ በቆላስይስ የነበረውን የኖስቲክ መምህራን ሕጋዊነት ስለሚያስከትለው ችግር ይገልጣል። ትምህርቶቻቸው የምሥራቃውያን ሰመመን፥ የአይሁድ ሕግ-አጥባቂነት፥ የፍልስፍናና የክርስትና ትምህርት ድብልቅ ነበር። የአይሁድ ሕግ-አጥባቂነት ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ ግልጽ ነው። የሰው ባሕርይ «በሃይማኖታዊ ተግባር» ለመፈጸም ትጉ ስለሆነ ይህ የሚያስገርም አይሆንም። ሥጋ መንፈሳዊ ነገሮችን ለማከናወን ደካማ ሲሆን (ማቴ. 26፡41)፥ ሃይማኖታዊ ሕጎችንና ደንቦችን ለማከናወን ግን ብርቱ ነው። ይህ ሃይማኖታዊ ሥርዓት መጠበቁ ደግሞ ሰውን በራሱ ጽድቅ እንዲመካ ያደርገዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ጳውሎስ ሦስት ጠቃሚ እውነቶችን አስቀምጦአል፡-

የነፃታችን መሠረት (2፡16)፥ ይህ «እንግዲህ» በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ቃሉም ይህንን አሳብ ካለፉት ቁጥሮች ጋር ያያይዘዋል። የነጻነታችን መሠረቱ የክርስቶስ ኢየሱስ አካልና ሥራ ነው። የእግዚአብሔር የመለኮት ሙላት ሁሉ በእርሱ ውስጥ ይገኛል (2፡9)። በመስቀል ላይ የኃጢአትን ዕዳና የሕግን ኃይል ገርስሶአል (2፡14)። አማኞች እንደመሆናችን መጠን፥ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለንም (ሮሜ 6፡14-23)።

በቆላስይስ የነበሩና ከአሕዛብ ወገን የመጡ አማኞች በፍጹም ከሙሴ ሕግ በታች አልነበሩም። ምክንያቱም ያ ሕግ የተሰጠው ለእስራኤላውያን ብቻ ነበርና (ሮሜ. 9፡4)። ክርስቲያኖች ስለሆኑ ራሳቸውን ለአይሁድ ሕግ ማስገዛት የመፈለጋቸው ጉዳይ እንግዳ ነገር ይመስላል። ጳውሎስ በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በነበሩ አሕዛብም ተመሳሳይ ችግር ደርሶበት ነበርና ለገላትያ ምዕመናን በጻፈው መልእክት የአይሁድን ሕግ ኮንኖአል (ገላ. 3፡1-5)። (በጥልቀት የገላትያን መጽሐፍ ለማጥናት «አርነት መውጣት» በሚል ርእስ ከዚሁ መጽሐፍ አዘጋጅ የቀረበውን መጽሐፍ [ቪክቶር- 1975] ይመልከቱ)።

በአይሁድ ሕግ መሠረት አልተመላለሰም ብሎ በአንድ አማኝ ላይ የሚፈርድ ሰው በእርግጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እየፈረደ ነው። ክርስቶስ የደኅንነትን ሥራ በመስቀል ላይ እንዳልፈጸመና በዚያም ላይ አንድ ነገር ማከል እንዳለብን እየተናገረ ነው ማለት ነው። እንዲሁም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያን ለሚያስፈልጉ መንፈሳዊ ፍላጎቶች ሁሉ ብቁ አይደለም ማለቱ ነው። በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ሕጉን ለሚፈጽሙ ሁሉ «የጠለቀ መንፈሳዊ ሕይወት» እንደሚሰጡ ይናገሩ ነበር። ከውጭ ሆነው ሲመለከቱ ልምምዶቻቸው ጥሩ መንፈሳዊነት ያላቸው ይመስላሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ልምምዶቻቸው ምንም መንፈሳዊ ተግባር ለማከናወን አልጠቀሙም።

የሕግ እስራት (2፡16)፥ ለሕይወታችሁ ቀንበር ስለሆነ ማንም ከዚህ የተለየ ነገር ቢነግራችሁ አትቀበሉት! ይህንንም ጴጥሮስ «በጫንቃ ላይ የተጫነ ቀንበር» (የሐዋ. 15፡10) ብሎታል። ጳውሎስም የገላትያን ሰዎች ሲያስጠነቅቅ በዚሁ ቃል ተጠቅሞአል፡- «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ» (ገላ. 5፡1)።

እነዚህ የሕግ ደንቦች ከመብላትና ከመጠጣት (ከአድርግና አታድርግ) ጋር የተያያዙ ነበሩ። በብሉይ ኪዳን ሥርዓት የተወሰኑ ምግቦች «ንጹሕ» ወይም «ንጹሕ ያልሆኑ» (ዘሌ. 11 ይመልከቱ) ተብለው ተመድበው ነበር። ዳሩ ግን ምግብ በራሱ የሚያስከትለው ችግር እንደሌለ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ አስተምሮአል። አንድን ሰው መንፈሳዊ የሚያደርገው ወይም የማያደርገው ከልብ የሚወጣው ነገር ነበር (ማቴ. 15፡1-20)። ጴጥሮስ በኢዮጴ በሰገነቱ ላይ በነበረ ጊዜ (የሐዋ. 10፡9-18)፥ እንዲሁም በአንጾኪያ በጳውሎስ በተገሰጸ ጊዜ (ገላ. 2፡11-21) ይህ ትምህርት በድጋሚ ቀርቦለት ነበር። «መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም፤ ባንበላም ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም» (1ኛ ቆሮ. 8፡8)።

በሙሴ አማካኝነት ስለ ምግብ የተሰጡት የእግዚአብሔር ትእዛዛት ከመንፈሳዊ ምክንያቶች በተጨማሪ ሥጋዊ ጉዳዮችም ከበስተጓላቸው ሳይኖርባቸው አይቀርም። ይህ ጳውሎስ የሚያነሣው ጉዳይ ግን የተለየ ነው። አንድ ሰው ለጤንነቱ ከማይበጅ ምግብ በመራቅ እፎይታ የሚያገኝ ከሆነ፥ ይህንኑ በማድረግ ለሰውነቱ መጠንቀቅ አለበት። ዳሩ ግን እርሱ ሊበላ ፈቃደኛ ያልሆነውን ምግብ በሚበሉት ላይ መፍረድና ተግባሩም የመንፈሳዊ ሕይወት መለኪያ እንደሆነ አድርጎ መገመት የለበትም። ሮሜ 14-15 ስለዚህ ጉዳይ መሠረታዊ አሳቦችን ይዞአል።

ዳሩ ግን የሕግ ሥርዓት ምግብን ብቻ ሳይሆን ቀናትንም ይጨምር ነበር። ይህም ደግሞ ለሙሴ ከተሰጡት ሕግጋት በተውሶ የተወሰደ ነበር። የብሉይ ኪዳን አይሁዳዊ የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን የሆነውን ሳምንታዊ ሰንበት እንዲጠብቅ ታዞአል (ዘጸ. 20፡9-11)። እሑድን «የክርስቲያን ሰንበት» ብሎ መጥራት ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በዚህ መልኩ አልቀረበም። ይልቁንም እሑድ «የጌታ ቀን» (ራእይ 1፡10)፥ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን (1ኛ ቆሮ. 16፡2፤ የሐዋ. 20፡7)፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል ነሥቶ መነሣት የሚታሰብበት ዕለት ነው (ዮሐ. 20፡1፥ 19፥ 26)።

እንዲሁም አይሁዶች የሚያከብሯቸው የበዓል ቀናትና (ዘሌ. 25) የተለዩ «የመባቻ» በዓላት ነበሯቸው (ኢሳ. 1፡13 ይመልከቱ)። ሃይማኖታቸው ከቀን አቆጣጠር ጋር የተያያዘ ነበር። በአሮጌው ሥርዓት ይህ ሁሉ የራሱ የሆነ ተገቢ ጠቀሜታ ነበረው፤ ዳሩ ግን በአዲሱ ሥርዓት

ውስጥ ዘላቂ የእምነት ክፍል ይሆናል ማለት አልነበረም (ዮሐ. 1፡17 ይመልከቱ)። ሕጉ እስራኤላውያንን ገና ከመጀመሪያው ለማሠልጠንና ሥርዓት ለማስያዝ ያገለገለ የሕፃናት አስተማሪ ነበር፤ ይኸውም ሕዝቡን ለመሢሑ የመጀመሪያ ምጽአት ለማዘጋጀት ነበር። አሁን ግን ኢየሱስ ስለመጣ፥ የሕፃናት መምህሩ ያንኑ ተግባር ማከናወን አያስፈልገውም (ገላ. 3፡24-4፡11)።

የብሉይ ኪዳን ሕግ ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የሚሰጠው አገልግሎት የለውም ማለት ነውን? በፍጹም አይደለም! ሕጉ አሁንም የእግዚአብሔርን ቅድስና ስለሚገልጥ በሕጉ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊታይበት ይችላል (ሉቃስ 24፡27)። «ሰው እንደሚገባ ቢሠራበት ሕግ መልካም እንደሆነ እናውቃለን» (1ኛ ጢሞ. 1፡8)። ሕጉ ኃጢአትን በመግለጥና የኃጢአትን ውጤቶች በማሳየት ያስጠነቅቃል፤ ዳሩ ግን ኃጢአትን ለመከላከል ወይም ኃጢአተኛውን ለማዳን የሚያበቃ ኃይል የለውም። ይህንን ማድረግ የሚችለው ጸጋ ብቻ ነው።

የጸጋ በረከት (2፡17)፥ ሕጉ ጥላ ሲሆን፥ እውነተኛ አካል ያለው ግን በክርስቶስ ነው። «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና» (ዕብ. 10፡1)። በኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው አካል እያለልን ለምን ወደ ጥላው እንመለሳለን? ይህ እውነተኛው አካል ፊት ለፊታችን እያለ ጥላውን ለመያዝ እንደመድከም የሚቆጠር ነው!

በሃይማኖት ሰበብ ምግቦችንና ቀናትን የሚከታተሉ ሰዎች ውጫዊ የመንፈሳዊነት ገጽታ ሊያሳዩ ቢችሉም፥ እነዚህ ልምምዶች ልባቸውን ለመለወጥ አይችሉም። መንፈሳዊ ሕይወታችንን «ልንለካበትና» እንዲያውም ልንመካበት ስለምንችል ሕግን መከተል ሰውን ደስ ያሰኘዋል። ይህ ግን ከክርስቶስ መለኪያ ሚዛን የተለየ ነው (ኤፌ. 4፡13)።

«ስለ ሽልማታችሁ ማንም እንዳያስቀራችሁ ተጠንቀቁ» (ቆላ. 2፡18-19)

በቀድሞ ትርጉም «ማንም አይፍረድባችሁ» ሲል በአዲሱ ትርጉም ደግሞ «ማንም ሰው ያለዋጋ እንዳያስቀራችሁ» የሚለው አባባል ሽልማት እንዳይቀበሉ ማወጅ ነው። ይህ የሩጫ ተወዳዳሪዎችን የሚያመለክት

ቋንቋ ነው። ዳኛው የውድድሩን ሕግጋት ስላላከበረ ተወዳዳሪውን ከሜዳ ያስወጣዋል። ተወዳዳሪው የአገሪቱ ዜጋ የመሆን መብት አይነፈገውም፤ ዳሩ ግን ሽልማት የማግኘት ክብሩን ያጣል። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመፈጸም ያልቻለ ክርስቲያን ደኅንነቱን አያጣም፤ ዳሩ ግን የጌታን ተቀባይነት ማረጋገጫና ለሚታመኑለት ሁሉ ተስፋ የሰጣቸውን ሽልማት አያገኝም (1ኛ ቆሮ. 3፡8)።

ለሚያገለግሉት ሽልማት እንደሚሰጥ ተስፋ መስጠቱ የእግዚአብሔር ባለ ጸግነትና ልግስና ተግባሩ ነው። እርሱ የኛ ባለ ዕዳ አይደለም። ከፍርድ ስላዳነን ልናመሰግነውና ሽልማት ብናገኝም ባናገኝም ልናገለግለው ይገባል። ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ከፍቅርና ከመሰጠት የተነሣ ስለሚያገለግሉት ስለ ሽልማቶቹ አስበው አያውቁም ይሆናል። በሲኦል ውስጥ የፍርድ ተዋረድ እንዳለ ሁሉ (ማቴ. 23፡14) እንዲሁም አማኞች ሁሉ በከበረው አካላቸው ክርስቶስን ቢመስሉም በመንግሥተ ሰማይም የክብር ተዋረድ ይኖራል። ከቀደሙት የእንግሊዝ ክርስቲያኖች (ፒዩሪትን) አንዱ የነበሩት ቶማስ ዋትሰን እንዲህ በማለት በትክክል ገልጸውታል፡- «ምንም እንኳ እያንዳንዱ ዕቃ ሙሉ ቢሆንም (በመንግሥተ ሰማይ) አንዱ ዕቃ ከሌላው ዕቃ የበለጠ ሊይዝ ይችላል»።

እንግዲህ፥ የዛሬው ሕይወታችን ነገ ልንቀበለው ያለንን ሽልማት ሊያሳጣን እንደሚችል ልብ ማለት ይገባል። በተለይ በዚህ ስፍራ፥ በጳውሎስ አእምሮ የነበረው አደገኛ ሁኔታ «ሚስቲሲዝም» የተባለው ሰመመን ነው። ይህም አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ቃል ወይም ከመንፈስ ቅዱስ በፍጹም ተለይቶ ከመንፈሳዊ ዓለም ጋር ቅጽበታዊ ልምምድ ማድረግ እንደሚችል የሚያስረዳ እምነት ነው። በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ራእዮችን ያዩና ከመላእክት ጋር ግንኙነት ያደርጉ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃልና መንፈስ ገለል በማድረግ ለአጋንንታዊ እንቅስቃሴዎች በሙሉ፥ ራሳቸውን ያጋልጡ ነበር፤ ምክንያቱም ሰይጣን እንዴት አድርጎ የተጭበረበሩ አስመሳይ ልምምዶችን ለሰዎች እንደሚሰጥ ያውቃልና (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15)።

ጣልቃ-መግባት የሚለው ቃል በጊዜው የነበሩ የተመስጦ ሃይማኖት ተከታዮች ይጠቀሙበት የነበረ የረቀቀ ትርጉም ያለው ቃል ነበር። የቃሉም ትርጉም «በአምልኮው ውስጠኛ ክፍል እግርን ማሳረፍ፥ ወደ ሃይማኖቱ ምሥጢራት ሙሉ ለሙሉ ዘልቆ መግባት» እንደማለት ነው።

ማንኛውም ክርስቲያን እግዚአብሔር ወዳለበት ስፍራ ለመድረስ በዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ውስጥ ማለፍ አያስፈልገውም። «ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም» የመግባት ድፍረት አለን (ዕብ. 10፡19)። ስለሆነም «ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ» (ዕብ. 4፡16)። የመላእክትን አምልኮ የወሰድን እንደሆነ መላክእት እኛን የሚያገለግሉን አገልጋዮች ናቸው! መላእክት «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» (ዕብ. 1፡14)።

በእርግጥ ይህ ሁሉ ምሥጢራዊ ሥርዓት በውሸት ትሕትና የተጋረደ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ትሕትና መስሎ የቀረበው ራሱን ሸፋፍኖ የቀረበ ትዕቢት ነበር። የኖስቲክ ተከታይ፡- «በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ብቁ ስላልሆንሁ ከመላክእት በአንዱ እጀምራለሁ» ማለቱ የማይቀር ነው።

ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጭ በማንም ወይም በምንም በኩል ወደ እግዚአብሔር አብ ለመቅረብ የሚደረገው ሙከራ ሁሉ ጣዖትን ማምለክ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ብቸኛው አማላጅ (መካከለኛ) ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡5፤ ዮሐ. 14፡6)። በመላእክት ወይም አሁን በሰማይ ባሉ ቅዱሳን በኩል አምልኮውን የሚያካሂድ ሰው ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ስለማይገዛ ትሕትናውን ሊያረጋግጥ አይችልም። የዚህ ዓይነቱ ሰው በትዕቢት ተነሣሥቶ የእግዚአብሔርን ቃል በሰው-ሠራሽ ልማዶች እየተካ ነው። «ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊ አእምሮው በከንቱ ይታበያል» (ቆላ. 2፡18)።

እውነተኛ አምልኮ ሁሉጊዜም ሰውን ትሑት ያደርጋል። አእምሮ በእግዚአብሔር ታላቅነት ሲያዝ፥ ልብም በእግዚአብሔር ፍቅር ይሞላል፤ ፈቃድም እግዚአብሔር ለሕይወት ላለው ዓላማ ይገዛል። ኖስቲኮች ግን በመጀመሪያ «በጥልቅ መንፈሳዊ እውቀት» ላይ በማተኮር የእግዚአብሔርን እውነት ችላ ብለዋል። «ውስጣዊ ምሥጢሮቻቸው» ትልቅ ጭንቅላት እንጂ የሚቃጠል ልብ ወይም የሚገዛ ፈቃድ አላደሏቸውም። «እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል» (1ኛ ቆሮ. 8፡1)።

ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው እውነተኛ መንፈሳዊ ልምምድ ወደ መገዛትና አገልግሎት እንደሚመራ መረዳት አስፈላጊ ነው። ኢዮብ ጌታን በተገናኘ ጊዜ፡- «መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን

ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በዐፈርና በዐምድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ» (ኢዮብ 42፡5-6) ብሎአል። ጴጥሮስም ከጌታው ፊት ወድቆ፡- «ጌታ ሆይ፥ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ ከእኔ ተለይ» (ሉቃስ 5፡8) ብሎአል። ኢሳይያስ ጌታን አይቶ ምንኛ ኃጢአተኛ ሰው እንደሆነ ተገንዝቦአል (ኢሳ. 6)። እንዲሁም ዮሐንስ የተነሣውን ክርስቶስን በተመለከተ ጊዜ እንደሞተ ሰው ከእግሩ ሥር ወድቆአል (ራእይ 1፡17)።

አንዳንድ ሰዎች በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ፥ አለዚያም በውይይታቸው ወይም በምስክርነታቸው ስለ እርሱ በፈዝ የሚናገሩ ይመስላሉ፤ ይህ ግን በእርሱ ፊት ርካሽ ከመሆኑም በላይ እንደ ስድብ ይቆጠራል። የበርካታ ምሁራዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች ጸሐፊ የነበሩት የታላቋ ብሪታንያ ጳጳስ ዌስትኮት አንድ ጊዜ፡- «ዓመት አልፎ ዓመት በተተካ ቁጥር ሰዎች በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ የሚያሰሙት የድፍረት ቃል እንድፈራና እንድንቀጠቀጥ ያደርገኛል» በማለት ጽፈዋል።

የሚያሳዝነው ይህ «በሥጋዊ አእምሮ በከንቱ እየታበዩ» የሚያራምዱት ሃይማኖት የአካሉ ማለትም የቤተ ክርስቲያኑ ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ለሚመጣው እውነተኛ መንፈሳዊ መና ምትክ ሆኖ መቅረቡ ነው። ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ አካል አድርገው ከሚያቀርቡ በርካታ መግለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው። (ሮሜ 12፡4-21፤ 1ኛ ቆሮ. 12-14፤ ኤፌ. 4፡4-16፤ ቆላ. 1፡18፥ 24 ተመልከት።) ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ አማኞች ሁላችንም የመንፈሳዊ አካል ማለትም የቤተ ክርስቲያን ብልቶች ነን (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)። ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን መጠን፥ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እርስ በእርሳቸው እንደሚረዳዱ ሁሉ አንዳችን ሌላውን እናገለግላለን (1ኛ ቆሮ. 12፡14-27)።

ዳሩ ግን አንድ አማኝ ከክርስቶስና ከሌሎች ክርስቲያኖች ወደሚገኘው መንፈሳዊ መና ካልተጠጋ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ደካማ ይሆናል። የሐሰት አስተማሪዎች ራስ ወደሆነው ስላልተጠጉ በመንፈሳዊ ጉስቁልና ውስጥ ነበሩ፤ ዳሩ ግን ራሳቸውን መንፈሳዊ ሊቃውንት አድርገው ይቆጥሩ ነበር። ድንክዬ ሆነህ ሳለ ራስህን ግዙፍ አድርገህ ማሰብ ምን ማለት እንደሆነ እስቲ ለአንድ አፍታ ልብ አድርግ!

የሐሰት አስተማሪዎች አማኞችን ወደ ራሳቸው ለመሳብ ይጣደፋሉ። ዳሩ ግን መንፈሳዊ አካል በመመገብ እንጂ በመጨመር አያድግም።

«ጅማትንና ማሰሪያን» ጨምሮ እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል ክፍል ለአካሉ ጤንነትና ዕድገት አስፈላጊ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎ ምንም ያህል አነስተኛ መስሎ ቢታይዎትም ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ነዎት። እንዲያውም በሕዝብ ፊት በግልጽ የሚታይ አገልግሎት የሌላቸው ሰዎችም በጓዳ አገልግሎታቸው ከሌሎቹ እኩል አስፈላጊዎች ናቸው።

በክርስቶስ መንፈሳዊ ብልጽግና መጠቀም የምንችለው በአምልኮ፥ በጸሎትና በቃሉ ነው። ሁላችንም መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን መለማመድ የምንችልበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት መሆን አለብን (ኤፌ. 4፡11-17)። ለእያንዳንዱ መንፈስ ቅዱስ የመገለጥ ስጦታ የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡7 አዲሱ ትርጉም)። አዲስ ኪዳን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ «ተለይተው ስላሉ ቅዱሳን» የሚለው የለውም።

ይሁን እንጂ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብንሆንም ራስ ወደሆነው ተጠግተን ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚሆነን ምግብ ከእርሱ ላናገኝ እንችላለን። በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት አስተማሪዎች ትምህርቶቻቸውን ወደ አጥቢያ ጉባኤ ለማስገባት ይጥሩ ነበር። ጥረታቸው ቢሳካ ኖሮ መንፈሳዊ ዕድገቱን በማፋጠን ፈንታ ያቆረቁዙት ነበር። የአጥቢያ ጉባኤ አባላት በክርስቶስ ውስጥ ካልኖሩ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ካልተሰጡና ለቃሉም ካልታዘዙ፥ ራስ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ለመለማመድ አይችሉም።

«በሃይማኖታዊ ሰመመን» ውስጥ ሰዎችን የሚስብ ማራኪ ነገር አለ። ምሥጢራትን ማወቅ፥ ወደ ጠለቁ ምሥጢራት ጠልቆ መግባትና ከመንፈሳዊ ዓለም ጋር መገናኘት ሁሉ የሚያስደስት ይመስላል።

ዳሩ ግን እነዚህ ልምምዶች በእግዚአብሔር ዘንድ የተወገዙ ናቸው። እውነተኛ ክርስቲያን የሚከብረው በክርስቶስ እንጂ በገዛ ራሱ ልምምድ አይደለም። ቃሉን ይከተላል፤ በመንፈስ ቅዱስም ይመራል። በክርስቶስ ውስጥ በመኖርም በረከትንና ፍሬያማነትን ይለማመዳል። ራስ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚያስጠጋው በቀር ሌላ ተጨማሪ ልምምድ አይሻም።

«ማንም በባርነት አይግዛችሁ!» (ቆላ. 2፡20-23)

ጳውሎስ ሕግንና የሰመመን ልምምድ ኮንኖአል፤ ቀጥሎም ራስን የማጎሳቆሉን ጥበብ ተቃውሞአል። ራስን በማጎሳቆል የሚያምን ሰው የጠበቀ ራስን የመካድና ራስን የማዋረድ ተግባራትን ይለማመዳል። ይህም ይበልጥ መንፈሳዊ ሰው ሆኖ ለመቅረብ የሚደረግ ድካም ነው። በመካከለኛው ዘመን (1500 ዓ.ም. ያህል) ይህ ራስን የማጎሳቆል ልምምድ በሰፊው ይሠራበት ነበር። ልምምዱም፡- ከጸጉር የተሠራ የሚኮሰኩስ ልብስ መልበስ፥ በማይመች መኝታ ላይ መተኛት፥ ራስን መግረፍ፥ ለቀናት (ለዓመታትም) ሳይናገሩ መኖር፥ ሳይበሉ መቆየት ወዘተ. የመሳሰሉትን የሚጨምር ነው።

በሕግ-አጥባቂነትና ራስን በማጎሳቆል ልምምድ መካከል ግልጽ የሆኑ ግንኙነቶች አሉ። ይህም የሆነው ብዙውን ጊዜ ራስን የማጎሳቆሉ ብሂል «አትያዝ፥ አትቅመስ» (2፡21) ለሚሉ ሕግጋትና ደንቦች ራሱን ስለሚያስገዛ ነው። የተወሰኑ ምግቦች ወይም ልምምዶች ቅድስና የሌላቸው ስለሆኑ መወገድ አለባቸው ባይ ነው። ሌሎች ልምምዶች ደግሞ የተቀደሱ ስለሆኑ መዘውተር አለባቸው ይላል። ራስን በማጎሳቆል የሚያምን ሰው ሕይወቱ በሥርዓት የተሸበበ ነው።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ሥርዓት ያለው ሕይወት አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። አንዳንዶቻችን አብዝተን ስለምንመገብ ወፋፍራሞች ነን። አንዳንዶቻችን ቡና ወይም እንደ ኮካ ያሉ ለስላሳ መጠጦችን አብዝተን ስለምንወስድ የተስተካከለ ጤንነት አይሰማንም። ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ ብናምንም (1ኛ ቆሮ. 6፡19-20) አንዳንድ ጊዜ ለሰውነታችን የሚገባውን ያህል ጥንቃቄ አናደርግም። «ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማል»ይላል (1ኛ ጢሞ. 4፡8)። ጳውሎስ የራሱን ሰውነት በመግራት ከቁጥጥሩ ሥር አውሎታል (1ኛ ቆሮ. 9-27)። ስለሆነም በክርስትና ሕይወታችን ለሰውነታችን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

ራስን በማጎሳቆል የሚያምን ሰው ሰውነቱን በመቆጣጠር ነፍሱን ለመቀደስ ይሞክራል። ጳውሎስ የሚቃወመው ይህንኑ የሐሰት ትምህርት ነው። ቀናትና ምግቦች ሰውን የመቀደስ ብቃት እንደሌላቸው ሁሉ ሰውነትን በመቆጣጠርም ለቅድስና የሚገኝ ትርፍ የለም። በዚህ ክፍል

ውስጥ ክርስቲያን በሃይማኖታዊ ራስን የማጎሳቆል ልምምድ እንደማይጠመድ ጳውሎስ በርካታ ምክንያቶችን ያቀርባል።

የክርስቲያኑ መንፈሳዊ ስፍራ (2፡20)፥ ራስን ማጎሳቆል ከመጀመሪያ ዓለማዊ ሥርዓቶች ጋር የተያያዘ እንጂ ከእግዚአብሔር መንግሥት ባለጸግነት ጋር የሚገናኝ አይደለም። ከዚህ ቀደም የመጀመሪያ ዓለማዊ ሥርዓቶች የሚለውን ቃል በመውሰድ «የአንድ ነገር መሠረቶች ወይም ሀሁ ዎች» የሚል ትርጉም እንደሚሰጥ ተመልክተናል (ቆላ. 2፡8)። በዚህ ስፍራ «የመጀመሪያው የዓለማዊ ሥርዓት» የሚለው ስለ ምግብ የተሰጡትን ሕግጋትና ደንቦች ያመለክታል። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን፥ በሞቱ፥ በመቀበሩና በትንሣኤው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ካለን ጎብረት የተነሣ፥ ለዚህ ሁሉ ልምምድ ሞተናል (ቆላ. 2፡12-15፤ ሮሜ 6 ይመልከቱ)። ምንም እንኳ በሥጋችን በዓለም ውስጥ ብንኖርም በመንፈሳዊ ደረጃ ግን የዓለም አይደለንም (ዮሐ. 17፡15-16)። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለተሻገርን (ቆላ. 1፡13) ሕይወታችንን የምንመራው በእግዚአብሔር ሕግጋት እንጂ በሰዎች ሥርዓት አይደለም።

ይህ ማለት ክርስቲያን ሥርዓተ-አልበኛ ነው ማለት አይደለም። አንድ ጊዜ በአንድ ክርስቲያን ትምህርት ቤት የሚማር ተማሪ ሕግጋትን መጠበቅ «መንፈሳዊ አለመሆን» እንደሆነ አጫወተኝ። እኔም ክርስቲያን ሁልጊዜም ከእርሱ በላይ ያሉትን ባለሥልጣናት ትእዛዝ ማክበር እንዳለበት (1ኛ ጴጥ. 2፡11-17) ገለጽሁለት። እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት ከመምጣቱ በፊት የትምህርት ቤቱን ሕግጋት ማወቅ እንዳለበትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ካልሆነ ግን እቤቱ መቀመጥ እንደነበረበት አስረዳሁት። ጳውሎስ ይህን ያለው ለዓመፅ ሊቀሰቅሰን ሳይሆን አንዳንድ ሕግጋትና ደንቦች ስላከበርን መንፈሳውያን እንደሆንን እንዳናስብ ሊያስጠነቅቀን ነበር።

ራስን የማጎሳቆል ሕግጋት ከንቱነት (2፡21-22)፥ በመሠረቱ እነዚህ ሕግጋት በሰዎች የተፈጠሩ እንጂ፥ ከእግዚአብሔር የተሰጡ አልነበሩም። እግዚአብሔር «ደስ እንዲለን ሁሉን ነገር አትርፎ ይሰጠናል» (1ኛ ጢሞ. 6፡17)። ምግብ «ከምስጋና ጋር ይቀበሉት ዘንድ ተፈጥሮአል» (1ኛ ጢሞ. 4፡3)። ዳሩ ግን የሐሰት አስተማሪዎቹ «ትእዛዛትና ትምህርቶች» በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተላለፈውን የእግዚአብሔር ቃል ይጻረራሉ (ማር. 7፡6-9 ተመልከት)። ትምህርቶቹ የሐሰት አስተማሪዎች

የሚያምኑባቸው ሲሆኑ፥ ትእዛዛቱ ደግሞ ትምህርታቸውን ከዕለታዊ ሕይወት ጋር ለመተግበር የሚሰጧቸው መመሪያዎች ነበሩ።

እግዚአብሔር ምግብን የሰጠን እንድንጠቀምበት ስለሆነ «ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ ሊጠፉ የተወሰኑ ናቸው» (ቆላ. 2፡22)። ኢየሱስ ምግብ ወደ ሆድ እንጂ ወደ ልብ እንደማይሄድ ገልጾአል (ማር. 7፡18-23)። እንዳያረክሱት በመስጋት የተወሰኑ ምግቦችን የሚያገልል ሰው ጌታችን ኢየሱስና ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተማሩትን አልተረዳም ማለት ነው። «በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ፤ ተረድቼአለሁም» (ሮሜ 14፡14)።

ብዙዎቻችን ጥንታውያን መነኩሳትን፥ ምሥራቃዊ የፍልስፍና ምሥጢራትንና የሂንዱ ወይም የእስልምና ትምህርትን ለመተቸት ፈጣኖች ነን። ዳሩ ግን ይህንኑ ተመሳሳይ ስሕተት ከቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ማየት ይሳነናል። በሥጋዊ ልምምድና በጤንነት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ሲኖር፥በሥጋዊ ልምምድና በቅድስና መካከል ምንም ግንኙነት የለም። አንድን ደካማ ክርስቲያን ላለማስቀየም ሆን ብለን ከአንድ ዓይነት ምግብ ወይም መጠጥ ተቆጥበን ከሆነ አንድ ነገር ነው (ሮሜ 14፡13-23)፤ ዳሩ ግን ከዚያ ምግብ መራቃችን ያንን ምግብ እየተመገበና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ከሚኖር ከሌላው ክርስቲያን ወንድማችን በላይ መንፈሳውያን ያደርገናል ብለን ማሰብ የለብንም (ሮሜ 14፡6)።

ራስን የማጎሳቆል ልምምድ አሳሳችነት (2፡23)፥ ይህንን የሚለማመዱ ሰዎች መንፈሳውያን እንደሆኑ ይነገርላቸዋል፤ ዳሩ ግን ፍሬያቸው ይህንን አያመለክትም። በአሜሪካ ውስጥ የሚገኙ የተማሩ ሰዎች ትምህርታቸው የሰውን ልብ መለወጥ ወደማይችለው ወደ ሂንዱና ወደ ሌሎችም ምሥራቃውያን መንፈሳዊ መሪዎች ሲጎርፉ ሳይ ይገርመኛል። ይህ «በራስ-ግፊት የሚመራ አምልኮ» እንጂ «በመንፈስና በእውነት» የሚደረግ እውነተኛ የእግዚአብሔር አምልኮ አይደለም (ዮሐ. 4፡24)። ትሕትናቸው የውሸት ስለሆነ ጠንካራ ሥርዓታቸው ለውስጣዊው ሰው ምንም ሊጠቅመው አይችልም።

ለሥጋዊ ፍላጎቶች ከመገዛት ይልቅ ራስን መግዛት የተሻለ መሆኑ ባያጠራጥርም፥ እንደዚህ ዓይነቱ ራስን የመግዛት ብቃት ሁልጊዜም በመንፈሳዊ መሻት እንደተነሣሣ አድርገን ማሰብ የለብንም። ራስን በማጎሳቆል የሚያምኑ በርካታ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች አስደናቂ የሆነ

ራስን የመግዛት ተግባር ያከናውናሉ። ራሳቸውን የሚያንሳቁሉ ሰዎች ይኸው ፍልስፍናቸው በጳውሎስ ዘመን በጣም የታወቀ ነበር። የናስቲክ አስተማሪዎች የሚያቀርቡትን ማንኛውንም ሥልጠና ተከታዮቻቸው ያስፋፉላቸው ነበር።

የክርስቶስ ኃይል በአማኙ ሕይወት ውስጥ ሥጋዊ ፍላጎትን ከመግታት የላቁ ነገሮችን ያደርጋል። ይኸውም በውስጡ አዳዲስ መሻቶችን ያስቀምጣል። ባሕርይ ፍላጎትን ይመሰናል። ክርስቲያን በውስጡ የእግዚአብሔር ባሕርይ አለው (2ኛ ጴጥ. 1፡4)፤ በመሆኑም ከእግዚአብሔር የሆኑ መሻቶችና ፍላጎቶች አሉት። ከውስጡ ሕይወት ስላለው መሻቶቹን ይቆጣጠር ዘንድ ውጫዊ ሕግ ማበጀት አያስፈልገውም! የእነዚህ ሰዎች ጠንካራ ሕግጋት «ሥጋዊ ስሜትን በመከላከሉ ረገድ ዋጋ ቢስ ናቸው» (ቆላ. 2፡23)። ማንኛውንም ነገር ቢሆን ከሁሉም የተሻለ በማድረግ ፈንታ ከሁሉም የከፋ አድርገው ያከናውኑታል። በዚህ ደብዳቤ፥ በመደምደሚያ ሁሉት ምዕራፎች ላይ፥ ጳውሎስ በአማኝ ውስጥ ንጽሕናንና ድልን ለመስጠት አዲሱ ሕይወት እንዴት እንደሚሠራ ገልጿል።

ይህ ክፍል ሁለተኛውን ምዕራፍ አጠናቆ የያዘ ሲሆን ዋና ትኩረቱም በአደጋ ላይ የተመረኮዘ ነው። ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን የበላይነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ገለጻ ከማድረጉም በላይ የሕግ አጥባቂነት፥ የሰመመንና ራስን የማንሳቆል ልምምድ ይቃወም ነበር። አሁን ከእኛ ይህንን መንፈሳዊ መመሪያ ማመንና በሥራ መተግበር ይጠበቅብናል።

በአምልኮ፥ በቃሉና በጸሎት ከክርስቶስ ጋር በምናደርገው ጎብረት ይህንን ሁሉ በየዕለተ ሕይወታችን እንለማመዳለን። በውስጣችን ለሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ስንሰጥ ለዕለታዊ ሕይወታችን የሚያስፈልገውን ኃይል እናገኛለን። ለአካሉ ማለትም ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ነገሮችን የምናካፍለውና ለሌሎች የአካሉ ክፍሎች ለእኛ የሚያካፍሉን ከሌሎች አማኞች ጋር ባለን ጎብረት አማካኝነት ነው። ይህ ምንኛ የሚያስደንቅ የአኗኗር መንገድ ነው!

ከሕግ አጥባቂነት የምንከላከልበት ነገር ቢኖር በኢየሱስ ክርስቶስ ያለን መንፈሳዊ እውነት ነው።የሰመመን መከላከያነት የሚጠቅመው የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ እንድንሆን ነው።

ራስን ለማነሳቆል ያለው መከላከያ በክርስቶስ በኩል ባለው በሞቱ በቀብሩና በትንሣኤው ሕይወቱ ስለምንኖር ነው።

ክርስቶስ በእርስዎ ሕይወት ውስጥ ከሁሉም በላይ ነውን? በክርስቶስ መንፈሳዊ ኃይል እየተመላለሳችሁ ነው ወይስ በአንዳንድ ሰው ሠራሽ «የሃይማኖት» ሥርዓቶች ይደገፋሉ?

- 8 -

ገነት በምድር ላይ

ቆላስይስ 3፡1-11

በቆላስይስ መልእክት ሁለት የማጠቃለያ ምዕራፎች ላይ፥ ጳውሎስ እርሱ ያስተምራቸው ወደነበሩት መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ተግባራዊ ተዛምዶዎች ያመራል። ክርስቲያኖች እውነትን እያወጁና ለእውነት እየተከላከሉ ዳሩ ግን በሕይወታቸው ውስጥ ይህንኑ ለማንጸባረቅ ካልቻሉ፥ እጅግም ፋይዳ የለውም። እውነትን አጥብቀው የሚከላከሉና በግል ሕይወታቸው እንከተላለን የሚሉትን ትምህርት የሚክዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ። «እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ስለሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል» (ቲቶ. 1፡16)።

በጳውሎስ ዘመን የነበረው የጣዖት አምልኮ ስለ ግል ምግባር የሚያስተምረው ብዙ ወይም ምንም ነገር እንደሌለ ማየት ይቻላል። አምላኪው በጣዖቱ ፊት ይሰግድና በመሠውያው ላይ መሥዋዕቱን ያኖራል። ከዚያም ወደ የቀድሞው የኃጢአት ሕይወት ይመለሳል። ሰውየው ከሚያምነው ነገር ጋር አካሄዱ ቀጥተኛ ግንኙነት አልነበረውም። ስለ መጥፎ አካሄዱም የሚኮንነው ሰው አልነበረም።

ዳሩ ግን የክርስትና እምነት ሙሉ ለሙሉ የተለየ አሳብ ወደ ጣዖት አምላኪው ጎብረተሰብ አመጣ። የክርስትና እምነት የምናምነው ነገር ከአካሄዳችን ጋር በጣም ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው የሚያመለክት ነው። በክርስቶስ ማመን ማለት ደግሞ ከክርስቶስ ጋር መተባበር ማለት ነው። እንዲሁም ሕይወቱን ከተካፈልን ምሳሌነቱንም መከተል አለብን። መንፈሱ በውስጣችን ሲኖር በኃጢአት ውስጥ አንድንመላለስ አይፈቅድልንም። በዚህ ክፍል ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ ሦስት መመሪያዎችን በመስጠት ትምህርቱን ከተግባር ጋር አዛምዶታል።

ሰማያዊውን ፈልጉ (ቆላ. 3፡1-4)

አጽንዖቱ አማኙ ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ነው።

ከክርስቶስ ጋር ሞተናል (3፡3)። የዚህ አስደናቂ እውነት ሙሉ ገለጻ በሮሜ 6-8 ውስጥ ይገኛል። ክርስቶስ ለእኛ ምትክ ሆኖ መሞቱ ብቻ ሳይሆን እኛም ከእርሱ ጋር ሞተናል (በሞቱ ተባብረናል)። ክርስቶስ የኃጢአትን ቅጣት ለመክፈል ብቻ ሳይሆን የኃጢአትን ኃይል ለመስበር ሞምር ነበር የሞተው። በመንፈስ ቅዱስ ሥራ «በክርስቶስ» ስለሆንን (1ኛ ቆሮ. 12፡13) ከክርስቶስ ጋር ሞተናል። ይህም ማለት ሊቆጣጠረን በሚፈልገው በአሮጌው የኃጢአት ተፈጥሮው ላይ ድልን ልንቀዳጅ እንችላለን ማለት ነው። «ለኃጢአት የሞትን እኛ ለወደፊት እንዴት አድርገን በእርሱ [በኃጢአት] እንኖራለን?» (ሮሜ 6፡2)።

በክርስቶስ በሕይወት እንኖራለን (3፡4)። ክርስቶስ ሕይወታችን ነው። የዘላለማዊ ሕይወት ማለት እኛ ኃጢአተኞች በአዳኛችን ስንታመን እግዚአብሔር የሚሰጠን ሰማያዊ ስጦታ አይደለም። ነገር ግን የዘላለማዊ ሕይወት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ «ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ ልጁ የሌለው ሕይወት የለውም» (1ኛ ዮሐ. 5፡12)። እኛ በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ሙታንና ሕያዋን ነን፤ ለኃጢአት የሞትንና በክርስቶስ ሕያዋን የሆንን ነን።

አንድ ሰው፥ «ሕይወት አንተ የምትኖርለት ነገር ነው» ብሎአል። ስለ እግር ኳስ ጨዋታ ወይም ስለ ሌላ ጣፋጭ ነገር ሲወራ ልጆች ደስተኞች ይሆናሉ። ስለ መኪናዎች ወይም ስለ ልጃገረዶች ሲወራ ደግሞ ወጣቶች ስሜታቸው ይማረካል። ጳውሎስ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው» ብሎአል (ፊልጵ. 1፡21)። ክርስቶስ የጳውሎስ ሕይወት ስለሆነ ከክርስቶስ ጋር ለሚያዛምደው ማንኛውም ነገር ደስተኛ ነበር። ይህም በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ሊሠራ ይገባል።

ከብዙ ዓመታት በፊት በባህላዊ ውዝዋዜዎች ወይም በዘመናዊ የዳንስ ምሽት ክበብ ላይ መገኘት ስለሚወዱ ሁለት እኅትማማቾች ሰምቼ ነበር። ከዚያም ተለወጡና በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን አገኙ። ከዚህ በኋላ ወደ ዳንስ ምሽት ክበብ ሲጠሩ የሚከተለውን ምላሽ ላኩ፡- «በቅርቡ ስለምትን በዳንስ ምሽት ክበብ ላይ መገኘት አንችልም፤ ስለዚህ ይቅርታ እንጠይቃለን» አሉ።

ከክርስቶስ ጋር ተነሥተናል (3፡1)። በሕይወት እየተመላለሱ በመቃብር ውስጥ መኖር ይቻላል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በርካታ አይሁዳውያን ስደተኞች በመቃብር ውስጥ ይሸሸጉ ነበርና

ከመቃብሮቹ በአንደኛው ውስጥ ሕፃን ልጅ እንኳ ተወልዶአል። ዳሩ ግን ኢየሱስ ሕይወቱን በሰጠን ጊዜ ከመቃብር ውስጥ አውጥቶ በሰማይ በዙፋን ላይ አስቀምጦናል። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ስለ ተቀመጠ እኛም «በክርስቶስ» አማካኝነት በዚያ ተቀምጠናል።

«ከተነሣችሁ» የሚለው ቃል የጳውሎስ አንባቢዎች ምናልባት «አልተነሡም ይሆናል» የሚለውን የሚያጠናክር አሳብ አይደለም። ምክንያቱም አማኞች እንደመሆናችን መጠን ሁላችንም በሞት፥ በቀብር፥ በትንሣኤና በዕርገት ከክርስቶስ ጋር ተባብረናል። «እንግዲህ» የሚለው ቃል የቃሉን እውነተኛ ትርጉም ይሰጣል። በክርስቶስ ያገኘነው ከፍ ያለ ስፍራ መላምት ወይም ገና ልንደርስበት የሚገባን ግብ ሳይሆን የተፈጸመ እውነት ነው።

በክርስቶስ ውስጥ ተሰውረናል (3፡3)። እኛ የክርስቶስ እንጂ የዓለም አይደለንም። በመሆኑም የምንኖርበት የሕይወት ምንጭ የሚፈልቀው ከእርሱ ዘንድ ብቻ ነው። «ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና» የሚለው መተማመኛና እርካታን ያመለክታል። የግሪክ ምሁር የሆኑት ዶክተር ኤ.ቲ. ሮበርትሰን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለውን አስተያየት ሰንዝረዋል፡- «በእግዚአብሔር ውስጥ ባለው በክርስቶስ ውስጥ ስለምንኖር፥ ማንም ሌባ ወይም ራሱ ሰይጣን እንኳ ቢሆን በክርስቶስ ካለን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም» (ሮሜ 8፡31-39)።

ዓለምን በተመለከተ የክርስትና ሕይወት «የተሰወረ ሕይወት» ነው፤ ምክንያቱም ዓለም ክርስቶስን አታውቀውም (1ኛ ዮሐ. 4፡1-6 ይመልከቱ)። የሕይወት ግባችን ይህ ዓለም ሳይሆን ሰማይ ነው። የሚማርኩንና የሚያስደስቱንም በሰማይ የሚገኙ ነገሮች እንጂ በምድር የምናያቸው ነገሮች አይደሉም። ይህ ማለት በምድር ላይ ኃላፊነቶቻችንን መወጣት የለብንም ማለት አይደለም። ይልቁንም ዋናው ዓላማችንና ጥንካሬያችን የሚመጣው ከምድር ሳይሆን ከሰማይ ነው ማለት ነው።

በክርስቶስ ከብረናል (3፡4)። ክርስቶስ አሁን በአብ ቀኝ ተቀምጦአል። ዳሩ ግን አንድ ቀን ሕዝቡን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ይመለሳል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። ይህንንም ሲያደርግ ከክርስቶስ ጋር ወደ ዘለዓለሙ ክብር እንገባለን። በክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ እኛም በክብር እንገለጣለን። እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ አገላለጽ አሁንም ቢሆን ከብረናል! (ሮሜ 8፡30)። ይሁን እንጂ ክብሩ ገና አልተገለጸም።

ክርስቶስ አስቀድሞ ክብሩን ሰጥቶናል (ዮሐ. 17፡22)። ሆኖም የክብሩ ሙሉ ለሙሉ መገለጽ የአዳኙን መመለስ ይጠባበቃል (ሮሜ 8፡17-25)።

አሁን ከክርስቶስ ጋር ካደረግነው አስደናቂ ትብብር የተነሣ ታላቅ ኃላፊነት ስላለን፡- «በላይ ያሉትን ነገሮች መሻት» አለብን (ቆላ. 3፡1)። በክርስቶስ ሞት፥ ቀብር፥ ትንሣኤና ዕርገት፥ ከዚህ ዓለም አሮጌ ሕይወት ተለይተን በአዲስ ሕይወት እንመላለሳለን።

ዳሩ ግን «በላይ ያሉትን ነገሮች» የምንሻው እንዴት ነው? ምሥጢሩ በቁጥር 2 ላይ ይገኛል፡- «ባለማቋረጥ አእምሮአችሁን፥ አትኩሮታችሁን በምድር ላይ ባሉት ሳይሆን፥ በሰማይ ባሉት ነገሮች ላይ አስቀምጡ» (ቀጥተኛ ትርጉም)። በዚህ ዓለም ስለምንኖር የዓለምን ነገር ማሰባችን አይቀርም። በሌላ በኩል ደግሞ ተስፋችን በሰማይ ስለሆነ የአእምሮአችን ትኩረት ወደ ሰማይ ሊሆን ይገባል። የእግዚአብሔር ሰው የሆኑት ዲ.ኤል.ሙዲ እንደተናገሩት «ሰማያዊ ነገር ብቻ በማሰብ በምድር ላይ ማገልገል የለብንም ማለት አይደለም»። ይህ (ዲ.ኤል ሙዲ እንደሚሉት) «ሰማያዊ የሆነ አሳብ ስለሚኖራቸው ከምድራዊ ጉዳዮች ጋር ዝምድና የለንም» ማለት አይደለም። ይልቁንም ለተግባራዊ የዕለታዊ ሕይወት ጉዳዮቻችን በሰማይ ካለው ከክርስቶስ መመሪያ እንቀበላለን ማለት ነው። በተጨማሪም ምድራዊ ኑሮአችን በሰማይ አተያይ እናያለን ማለት ነው።

በዋሽንግተን ስብሰባ ላይ ሳለሁ የመንግሥት ምክር ቤት ኮሚቴ ውይይት በቴሌቭዥን ሲተላለፍ ተመልክቼ ነበር። እንደምገምተው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አዲስ አምባሳደር ስለሚሆነው ሰው እየተወያዩ ነበር። የቀድሞው የምክር ቤቱ አባል ሕዩበርት ሐምፍሪይ አስተያየት በንግግራቸው መሀል፡- «በፖለቲካ ውስጥ የአቋቋማችሁ ሁኔታ የሚወሰነው የምትቀመጡበት ስፍራ መሆኑን ማስታወስ አለባችሁ» ሲሉ ሰማኋቸው። በእርግጥ ይህ ንግግራቸው በጊዜው የሚያመለክተው የፖለቲካ ፓርቲን አቀማመጥ ነበር። ዳሩ ግን ወዲያውኑ እኔ በክርስቶስ ካለኝ ስፍራ ጋር አዛመድሁት። አቋቋሜና አካሄዴ የሚወሰነው በተቀመጥኩበት ስፍራ ነው። እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ተቀምጫለሁ!

የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋዪቱ አገር በተቃረቡ ጊዜ ለመግባት አልፈለጉም ነበር። ካለማመናቸውና ከልባቸው ጥንካሬ የተነሣ ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ ውስጥ መንከራተት ነበረባቸው (ዘኁ. 13-14

ይመልከቱ)። እግዚአብሔርን ካመኑት ከሁለት ሰላዮች (ኢያሱና ካሌብ) በቀር የ20 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ወጣቶች ጀምሮ ያ ትውልድ በሙሉ በምድረ በዳ አለቀ። በእነዚያ 40 አስቸጋሪ ዓመታት ውስጥ ኢያሱና ካሌብ በምድረ በዳ «ድልን ለመቀዳጀት» የቻሉት እንዴት ነበር? አእምሮአቸውና ልባቸው በከነዓን ውስጥ ነበር! ርስት እንዳላቸው በመረዳት በዚያ ርስት ብርሃን ይመላለሱ ነበር።

የእንግሊዝ ንግሥት ሥልጣንና መብት ሊኖራት የቻለው በዙፋን ላይ በመቀመጥዋ ነው። የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝዳንት በዋይት ሐውስ የእንቁላል ቅርጽ ባለው ቢሮአቸው ውስጥ ስለሚቀመጡ ልዩ ልዩ መብቶችና የሥልጣን ኃይል አሏቸው። አማኝ ከክርስቶስ ጋር ከዙፋን ላይ ተቀምጦአል። በቃሉ፥ በጸሎት፥ እንዲሁም በአምልኮና በአገልግሎት ያለማቋረጥ ፍቅራችንንና አትኩሮታችንን በሰማያዊ ነገሮች ላይ ማጽናት አለብን። ልባችንንና አእምሮአችንን በሰማያዊ ነገሮች ላይ ካደረግን «እንደ ሰማይ ዘመን በምድር ላይ» ሐሴት ልናደርግ እንችላለን (ዘዳ. 11፡21)።

ምድራዊውን ግደሉ (ቆላ. 3፡5-9)

አሁን ከአዎንታዊው ወደ አሉታዊ እንመለሳለን። አሉታዊውን ነገር የማይወዱ አንዳንድ ሰዎች አሉ። «አዎንታዊ ትምህርቶችን ስጡን! አሉታዊ ማስጠንቀቂያዎችንና ተግሣጾችን ግን ተዉን!» ይላሉ። ዳሩ ግን አሉታዊ ማስጠንቀቂያዎችና ትእዛዛት ከክርስትና ትምህርት አዎንታዊ እውነታዎች የሚመነጩ ናቸው። ስለዚህ ነው ጳውሎስ «እንግዲህ ... ግደሉ» የሚለው።

ስለ ጤንነት ምንም ያህል አዎንታዊ ወሬ ቢወራ የተጎዳ የትርፍ-አንጀት አይፈወስም። ዶክተሩ «አሉታዊ» የቀዶ-ጥገና ተግባር በመፈጸም ትርፍ አንጀቱን ቆርጦ ማውጣት አለበት። በውበት ላይ ምንም ያህል ትምህርት ቢሰጥ አንድ የአትክልት ስፍራ ሊያስገኝ አይችልም። አትክልተኛው አረሞችን መንቀል አለበት! አዎንታዊና አሉታዊ ተግባራት ጎን ለጎን የሚሄዱ ሲሆን አንዱ ያለ ሌላው ሚዛናዊነት ይጎድለዋል።

«ግደሉ» የሚለው ቃል ማስወገድ ማለት ነው። ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር ስለሞትን (ቁ. 3) ሊቆጣጠረን የሚፈልገውን ምድራዊና ሥጋዊ መሻት ሁሉ ለመግደል የሚያስችል መንፈሳዊ ኃይል አለን። ጳውሎስ ራሳችንን ለኃጢአት የሞትን ዳሩ ግን በክርስቶስ ሕያዋን እንደሆንን አድርገን «እንድንቆጥር» ይናገራል (ሮሜ 6፡11)። ጌታችንም

«ቀኝ ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ጣላት» (ማቴ. 5፡29-30) በማለት ይህንኑ ተመሳሳይ አሳብ ገልጾአል።

በግልጽ እንደምንረዳው ጳውሎስም ሆነ ጌታችን ኢየሱስ ስለ ሥጋዊ ቀዶ-ጥገና እየተናገሩ አልነበሩም። ኃጢአት ከዓይን፥ ከእጅ፥ ወይም ከእግር አይመጣም። ዳሩ ግን ክፉ መሻቶች ሁሉ ካሉበት ከልብ ይመነጫል። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በእንግሊዝ አገር አንድ ሌባ ከተያዘ ቀኝ እጁ ይቆረጥ ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ ከተያዘም ግራ እጁም ይቆረጥ ነበር። አንድ ሌባ ሁለቱንም እጆቹን ቢያጣም እንኳ በጥርሱ እየተጠቀመ ሌብነቱን ቀጥሎአል። ሥጋዊ ቀዶ-ጥገና በፍጹም ልብን ሊለውጥ አይችልም።

ጳውሎስ በዚህ አንቀጽ አሉታዊ ነገር መናገር ብቻ ሳይሆን የኃጢአት ዝርዝሮችንም አቅርቦአል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ይህንን አይወዱም። እነዚህ ኃጢአቶች ከአዲሱ ሕይወት ጋር ምንም ዝምድና የላቸውም። በተጨማሪም እነዚህን ነገሮች በሚለማመዱ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይወርዳል። እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ሕይወት የሚመላለሱትን ሰዎች አያከብርም። ከእነዚህ ኃጢአቶች የተነሣ የእግዚአብሔር ቁጣ በአሕዛብ ዓለም ላይ ወርዶአል (ሮሜ 1፡18-32)። እንደገናም ቁጣው ይገለጣል። ጳውሎስ «በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣል» (ቆላ. 3፡6) በማለት ያስጠነቅቃል።

«ዝሙት» የሚለው በአጠቃላይ ሕገ-ወጥ የወሲብ አጠቃቀምን ያመለክታል። ርኩሰት «ከሞትና ፈር ከለቀቁ አኗኗር ጋር የተያያዘ ምኞት የሞላው ብልግና» ማለት ነው። ፍትወት ወደ ወሲብ ርኩሰት የሚደረገውን የአእምሮ እሽቅድድም ያመለክታል። የዚህ ዓይነቱን ፍላጎት የሚያጎለብት ሰው ሁልጊዜም ይህንኑ ፍላጎት የሚያረካበትን አጋጣሚ ሊያገኝ ይችላል። ክፉ መሻት ማለት «ወራዳ፥ ክፉ ፍላጎት» ማለት ነው። ፍላጎቶች ወደ ተግባራዊ ክንዋኔዎች እንደሚመሩ ግልጽ ነው። ሥራዎቻችን ንጹሐን እንዲሆኑ ከተፈለገ፥ በመጀመሪያ አእምሮአችንንና ልባችንን ማንጻት አለብን።

ብዙውን ጊዜ ፍላጎታችን የምናደርገውን ነገር ይወስናል። በልጅቼ ሕይወት ውስጥ ጣፋጭ ምግቦችን የመብላት ፍላጎት ካላደርሁ ያንን ፍላጎት ማርካት አለብኝ። ከዚህም የተነሣ ወፋፍራሞች ከሆኑና ጤንነታቸውም ከተቃወሰ፥ ፍላጎታቸውን መቀየርና ጣፋጭ ያልሆኑትን

ምግቦች እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው ማስተማር ይጠበቅብኛል። እነዚህ ክፉ ፍላጎቶች የሚመነጩት ከልብ ስለሆነ (ማር. 7፡21-23)፥ ጸሎታችን «አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ [መዝ. (51)፡10] የሚል መሆን አለበት።

ጳውሎስ እነዚህን የስሜት ኃጢአቶች ከዘረዘረ በኋላ ምኞት ወይም «ጣዖትን ማምለክ» (3፡5) የሚለውን ይጨምራል። ምኞት ሁልጊዜም ተጨማሪ ነገሮችን መፈለግ ነው። ይህም ቁሳቁሶችን ወይም አመቺ ሁኔታዎችን ሊያጠቃልል ይችላል። የሚመኝ ሰው ባለው ነገር በጭራሽ የማይረካ ስለሆነ ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሰዎች ባላቸው ነገር ላይ ይቀናል። ይህም መመኘት ነገሮችን በእግዚአብሔር ስፍራ ስለሚያስቀምጥ ጣዖትን ማምለክ ነው። ከዐሥርቱ ትእዛዛት የመጨረሻው «አትመኝ» የሚለው ነው (ዘጸ. 20፡17)። ይሁንና ይህ ኃጢአት የቀሩትን ዘጠኝ ትእዛዛት በሙሉ እንድንጥስ ሊያደርገን ይችላል። የሚመኝ ሰው የኃጢአት ፍላጎቱን ለማርካት፥ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ሊጠራ፥ ሊዋሽ፥ ሊሰርቅ፥ የእግዚአብሔርን ስም ሊያሰድብ እንዲሁም ሌሎችንም ኃጢአቶች ሁሉ ሊፈጽም ይችላል።

በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ አማኞች እንደዚህ ዓይነት ኃጢአቶች ይፈጽማሉን? እንዳለመታደል ሆኖ አንዳንዱ ይፈጽማሉ። ወደ ተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች እነዚህን ኃጢአቶች በመጥቀስ ያስጠነቅቃሉ። የቅዱሳንን ኃጢአቶች በመቃወም ተከታታይ ስብከቶችን ያቀረቡት መጋቢ ትዝ ይሉኛል። አንድ ቀን የጉባኤው አባላት እኚሁ መጋቢ እነዚህን መልእክቶች ላልዳኑት ሰዎች ቢሰብኩ እንደሚሻል ነገሯቸው። አንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል፥ «እንዲያውም በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚገኘው ኃጢአት በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ከሚገኘው ኃጢአት የተለየ ነው» አሉ።

መጋቢው መልሰው፡- «ልክ ነህ፥ የክርስቲያኑ ኃጢአት ከሌሎች የከፋ ነው!» አሉ።

ጳውሎስ ከስሜት ኃጢአቶች እንድንጠበቅ ካስጠነቀቀን በኋላ የማኅበራዊ ኃጢአቶችን አደገኛነት ያመለክታል (ቆላ. 3፡8-9)። ዶክተር ጂ ካምብል ሞርጋን እነዚህ፡- «ቀላል ኃጢአቶች ናቸው» በማለት ጠርተዋቸዋል። ከቁጣ፥ ከግትር አመለካከቶች፥ ከመዋሸት፥ በአማኞች መካከል የሚያሰናክል ጸያፍ ቧልት ከማቅረብ ጋር በጣም ስለተለማመድን

ስለነዚህ ኃጢአቶች ብዙም አይሰማንም። አንድ የቤተ ክርስቲያን ምእመን ዝሙት ሲፈጽም እንደነግጣለን፤ ነገር ግን በስብሰባ ላይ ትዕግሥቱ አልቆበት ሲናደድ እያየን፥ «የጽድቅ ቁጣ» ነው ብለን እናልፋለን።

በዚህ ስፍራ የምንመለከተው ሥዕል አንድ ሰው አልባሳቱን ሲቀይር ያሳየናል፡- «ገፍፋችሁታል ... ለብሳችሁታል» (ቁ. 9-10)። ይህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ይዛመዳል (ቁጥር 1)፤ ምክንያቱም ከሙታን ሲነሣ መገነጥውን እዚያ ጥሎት ተነሥቶአል (ዮሐ. 20፡1-10)። ወደ ከበረው የትንሣኤ ሕይወት ስለተሸጋገረ መገነጥዎች አያስፈልጉትም ነበር። እንደዚሁም አልዓዛር ከሞት በተነሣ ጊዜ ኢየሱስ፡- «ፍቱትና ተዉት-ይሂድ» በማለት ሕዝቡን አዝዞአቸዋል (ዮሐ. 11፡44)።

መገነጥ ከኃጢአት ተግባራት ጋር የተወሳሰበውን አሮጌ ሕይወት ያመለክታል። አሁን በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ስላለን አሮጌ ተግባራችንንና ፍላጎቶቻችንን በማስወገድ «በአዲስ ሕይወት» መመላለስ አለብን (ሮሜ 6፡4)። ይህንንም የምናደርገው በክርስቶስ ያለንን ሰፍራ በመረዳት፥ ለአሮጌው ሕይወት እንደሞትንና ለአዲሱ ሕይወት እንደምንኖር በመቁጠር ነው።

ጳውሎስ እንደቁጣ፥ ንዴትና ክፋት በመሳሰሉ በሌሎች ሰዎች ላይ ክፉ አመለካከት በሚያንጸባርቁ ኃጢአቶች ይጀምራል። ቁጣና ንዴት ተመሳሳይ ቃላት ናቸው (ቆላ. 3፡8)። በ(3፡8) የተጠቀሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያመለክታል። ንዴት በድንገት የሚፈነዳውን ቁጣ የሚያመለክት ሲሆን ቁጣ ግን የተለመዱ አመለካከቶችን ይገልጻል። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ በኃጢአት ላይ የመቆጣትና የመቅጣት መብት አለው። እንዲያውም የቅዱሳን ባሕርይ መሆን የሚገባው በኃጢአት ላይ በሚገለጽ የጽድቅ ቁጣ አለ (ኤፌ. 4፡26)። ዳሩ ግን ማንኛችንም «እግዚአብሔርን የመተካት»ና በራሳችን አመለካከት በሌሎች ላይ የመጨረሻ ፍርድ የመስጠት መብት የለንም። ክፉ ምኞት ማለት ሰዎችን የመጥላት ሁኔታ ማየት ነው። አንድን ሰው በጥላቻ የምንመለከት ከሆነ ሲሳካለት እንከፋለን፤ መከራ ሲደርስበት ደግሞ እንደሰታለን። ይህም ኃጢአት ነው።

ስድብ ሌሎችን የሚያስቀይምና ምስክርነታቸውን የሚያበላሽ ንግግር ነው። ብዙውን ጊዜ በክርስቲያኖች መካከል የዚህ ዓይነቱ ክፉ ሐሜት እንደ መንፈሳዊና እንደ ጸሎት ርእስ ይቀርባል። ለምሳሌ እንዲህ

በማለት፡- «ልትጸልይላት እንደምትፈልግ ስለማውቅ ነው እንጂ ስለ እርስዋ የማውቀውን ምሥጢር አልነግርህም ነበር።» ክፉ ንግግር ከተንኮል የሚመነጭ ነው (1ኛ ጴጥ. 2፡1)። በአንድ ሰው ላይ የጠለቀ ጥላቻ ካለህ ስለ እርሱ ክፉ ነገር ለመናገር ያገኘኸውን ዕድል ሁሉ ትጠቀማለህ።

የሚያሳፍር ንግግር ማለት የሚያስጸይፍ፥ የማይባርክ፥ ሥነ-ምግባር የጎደለው የቋንቋ አጠቃቀም ነው። በአንዳንድ ምክንያቶች ሳቢያ አንዳንድ ክርስቲያኖች የዚህ ዓይነቱን ንግግር መጠቀም ዘመናዊነት እንደሆነ ያስባሉ። አንዳንድ ጊዜ አላስፈላጊ የሆነ ቀልድ በውይይቶች ውስጥ ዘው ብለው ይገባሉ። አንድ ሰው የማይታመን ነገር ቢናገር ቆላስይስ 4፡6ን ሊያስታውሱት ይችላሉ። እንዲህ ይላል፡- «ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን።» ጨው የንጽሕና ምልክት ነው። እንዲሁም ጸጋና ንጽሕና ጎን ለጎን ይሄዳሉ።

ጳውሎስ የጠቀሰው የመጨረሻ ኃጢአት ውሸት ነበር (ቁ. 9)። ይህንኑ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ በኤፌሶን ለነበሩ አማኞችም ጽፎአል (ኤፌ. 4፡25)። መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ሲሆን (ዮሐ. 14፡17፤ 15፡26) ሰይጣን ግን የውሸት አባት ነው (ዮሐ. 8፡44)። ክርስቲያን ውሸት ሲናገር ከሰይጣን ጋር ይተባበራል፤ እውነትን በፍቅር ሲናገር ግን (ኤፌ. 4፡15) ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የትባበራል።

ቃሉ ትክክል ቢሆን እንኳ፥ ውሸት ማለት በማንኛውም መንገድ እውነትን አምታትቶ ማቅረብ ነው። የድምፅ ቃና፥ የፊት ዕይታ፥ ወይም የእጅ እንቅስቃሴ የዐረፍተ ነገሩን ትርጉም ሊያዛባ ይችላል። የልብ ስሜትም እንዲሁ ሊያደርግ ይችላል። ሰዓቴ ቢሳሳትና ለጓደኛዬ የተሳሳተ የጊዜ ስሕተት ብናገር ይህ ውሸት አይደለም። መዋሸት ለግል ጥቅም ዓላማ የማታለልና ፍላጎት ይጨምራል። አንድ የቆየ ምሳሌያዊ አነጋገር፡- «ግማሽ እውነት፥ ሙሉ ውሸት ነው» ይላል።

ጳጳስ ዋሪን ኤ.ካንድለር ስለ ሐናንያና ሰጲራ ውሸት ይሰብኩ ነበርና (የሐዋ. 5)፡- «አሁን እግዚአብሔር ልክ እንደዚያ ጊዜ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው የሚገድል ቢሆን ኖሮ እኔ የት እደርስ ነበር?» በማለት ጉባኤውን በጥያቄ አፋጠጡት። ጉባኤው ግን ለሆሳስ የላቅ ድምፅ ያሰማ ጀመር። ዳሩ ግን ጳጳሱ በታላቅ ድምፅ፡- «በዚህ ሰፍራ ቆሜ ለባዶ ቤተ ክርስቲያን እሰብክ ነበር!» በማለት ሲመልሱ፥ የሕዝቡ ፈገግታ እንደምሽት ጀምበር ጠለቀ።

የክርስቶስ የሆነውን አጠናክሩ (ቆላ. 3፡10-11)

በክርስቶስ ሕያዋን ስለሆንን በላይ ያሉትን ነገሮች መሻት አለብን። እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር ስለሞትን ያለፈው ኃጢአት ምድራዊ የሕይወት አካላት የሆኑትን ነገሮች ማስወገድ አለብን። የዚህም ውጤት ክርስቶስን መምሰል ነው። እግዚአብሔር ሊያድሰንና በልጁ መልክ ሊቀርጸን ይፈልጋል።

ገፍፋችሁታል እና ለብሳችሁታል (ቁ. 9-10) ተብለው የተተረጎሙ የግሪክ ግሦች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገውን ተግባር ያመለክታሉ። በክርስቶስ ስናምን አሮጌውን ሕይወት አውልቀን አዲሱን እንለብሳለን። አሮጌው ሰው ስለተቀበረ አዲሱ ሰው አሁን የተቆጣጣሪነቱን ሚና ይጫወታል። ዳሩ ግን የሚታደሰውን ተብሎ የተተረጎመው ቃል ተከታታይ ድርጊትን ያመለክታል፡- «ባለማቋረጥ የሚታደስ።» የደኅንነት መፈጸም ወደ ቅድስና ሂደት ይመራል። ይህም በይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰሉ መሄድን ያመለክታል።

አዲስ ለሚለው ቃል ግሪኮች ሁለት የተለያዩ ቃላት ነበሯቸው። «ኒዎስ» የሚለው «የጊዜን አዲስነት» ያሳያል። ይህም ቃል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስጥ ለ«ኒዎኦርቶዶክሲ» እና ለመሳሰሉት ቃላት ባዕድ-መነሻ በመሆን ያገለግላል። «ካይኖስ» የሚለው ደግሞ «በጥራቱ አዲስ የሆነ፥ ትኩስ» ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ሁለቱ ቃላት ተቀያይረው አገልግለዋል፤ ይሁን እንጂ መሠረታዊ ልዩነት አላቸው።

አማኝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ «አዲሱን ሰው» (ኒዎስ) ለብሶታል፤ ከዚህም የተነሣ እየታደሰ (ካይኖስ) ይኖራል። ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰለ ስለሚመጣ የጥረት ለውጥ ይስተዋላል። «አዲሱ ሰው» የኋለኛው አዳም (1ኛ ቆሮ. 15፡45) እና የአዲስ ፍጥረት ራስ የሆነው (2ኛ ቆሮ. 5፡17) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ይህ መታደስ እንዴት ሊመጣ ይችላል? በእውቀት አማካኝነት ይመጣል። እውቀት በኖስቲኮች ቋንቋ መዝገበ-ቃላት ውስጥ ከቁልፍ ቃላት መካከል ይመደብ ነበር። ዳሩ ግን እነርሱ መንፈሳዊ እውቀት ብለው ይጠሩት የነበሩት ነገር የአንድን ሰው ሕይወት ክርስቶስ ኢየሱስን ይመስል

ዘንድ ለመለወጥ አይችልም ነበር። ሰው ክርስቶስን በበለጠ ሲያውቅ የበለጠ እርሱን እየመሰለ ይመጣል (ፊልጵ. 3፡10)።

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነበር (ዘፍ. 1፡26-27)። ይህም የሰውን ሰብእናና (እውቀት፥ ስሜት፥ ፈቃድ) የሰውን መንፈሳዊነት (ከሰውነት የሆነውን ነገር) የሚያጠቃልል ነበር። ሰው ኃጢአት በሠራ ጊዜ ይህ የእግዚአብሔር አምሳል ተበላሸ። የአዳም ልጆች በአባታቸው አምሳል የተወለዱ ነበሩ (ዘፍ. 5፡1፥ 3)። ኃጢአት ካመጣው አደገኛ ሁኔታ በተቃራኒ፥ ሰው አሁንም የእግዚአብሔር አምሳል አለው (ዘፍ. 9፡6፤ ያዕ. 3፡9)።

በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረን ስናበቃ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር አምሳልነት ተለይተን ነበር። ዳሩ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ወደዚያ ወደ እግዚአብሔር አምሳል ልንመለስ እንችላለን! በአእምሮአችን መንፈስ መታደስ አለብን (ኤፌ. 4፡23)። በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እያደግን ስንሄድ፥ የከበረው የእግዚአብሔር አምሳል ተካፋይ ለመሆን በእግዚአብሔር መንፈስ እንለወጣለን (2ኛ ቆሮ. 3፡18)። እግዚአብሔር በአእምሮአችን መታደስ ይለውጠናል (ሮሜ 12፡2)። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ይጨምራል። ከአሮጌው ሕይወት ነጻ የሚያወጣን ደግሞ እውነት ነው (ዮሐ. 8፡31-32)።

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዓላማ «የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ» ነው (ሮሜ 8፡29)። ይህም ባሕርይን፥ የውስጡን ሰው መንፈሳዊ ጥራትን ያመለክታል። ኢየሱስ ክርስቶስን ስናይ እርሱን እንመስላለን፤ የከበረ አካልም ይኖረናል (1ኛ ዮሐ. 3፡1-3)። ዳሩ ግን ምጽአቱን ስንጠባበቅ ሳለ እርሱን ልንመስልና ቅዱስ አምሳሉን ልንካፈል እንችላለን። ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል ሲጠቀም የሚያካሂደው የማያቋርጥ የመታደስ ሂደት ነው።

ሰብአዊ ደረጃዎችና ልዩነቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚሆነው የተቀደሰ አኗኗር ግርዶሽ ሊፈጥሩ አይገባም። በኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልዩነቶች ሁሉ ይወገዳሉ (ቆላ. 3፡11)። በክርስቶስ የብሔረሰቦች ልዩነት አይኖርም («የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የለም»)። የቀድሞ የሃይማኖት ልዩነቶችም አይቆጠሩም («የተገረዘም ያልተገረዘም የለም»)። ናስቲኮች መገረዝ ለመንፈሳዊ ሕይወት አስፈላጊ እንደሆነ ያስተምሩ ነበር (ቆላ.

2፡11-15)። ዳሩ ግን ይህ ባህላዊ ሥጋን የመግረዝ ተግባር ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጠው ፋይዳ እንደሌለ ጳውሎስ በግልጽ አስቀምጧል።

እንዲሁም በክርስቶስ ምንም ዓይነት የባህል ልዩነት («አረማዊም እስኩቴስም») የለም። ግሪኮች ያልሆኑትን ሁሉ ያልሠለጠኑ ሕዝቦች አድርገው ይቆጥሩ ነበር፤ እስኩቴስ የተባሉትም ከሁሉም ዝቅተኛ የነበሩ ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ በክርስቶስ የአንድ ሰው ባህላዊ ደረጃ መሠልጠን ወይም አለመሠልጠን የሚጠቅም ወይም የሚጎዳ አይደለም። የኢኮኖሚ ወይም የፖለቲካ ደረጃውም ቢሆን ፋይዳ የለውም («ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን ልዩነት አያመጣም»)። ባሪያ ነጻነቱን ለማግኘት መትጋት እንዳለበት ጳውሎስ በግልጽ ተናግሮአል (1ኛ ቆሮ. 7፡20-23)፤ ዳሩ ግን ከማኅበራዊ ደረጃው የተነሣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደተጎዳ አድርጎ ማሰብ የለበትም።

እነዚህ ሁሉ ሰብአዊ ልዩነቶች የ«አሮጌው ሰው» እንጂ የ«አዲሱ ሰው» ባሕርያት አይደሉም። ለገላትያ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ፥ ጳውሎስ «ወንድም ሴትም የለም» ስለሚል የዖታ ልዩነትም እንኳ ተፍቆአል። የጳውሎስ መደምደሚያ «ክርስቶስ ሁሉ በሁሉም ነው» የሚል ነበር። «ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3፡28)።

የቤተ ክርስቲያንን ጎብረት ከኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከአካሉና ከሥራው ውጭ በሚገኝ በማንኛውም ነገር ላይ መመሥረት ስሕተት ነው። እንደዘር፥ ቀለም፥ ወይም ማኅበራዊ ይዞታ በመሳሰሉ ሰብአዊ ልዩነቶች ላይ የሚመሠረቱ አገልግሎቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም። መንፈሳዊነት አንዱ ክርስቶስን በትክክል የሚያውቁትንና እርሱን ለማስከበር የሚሹትን ሰዎች በፍቅር ተቀብሎ ማስተናገድ ነው። «የላቁ ቅዱሳን» የኖስቲክ የቆላስይስ አማኞችን ከተቀሩት የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ለመገንጠል ይጣጣሩ ነበር። ይህም ትክክል አልነበረም። ወደ ክርስቶስ በምንመጣበት ጊዜ በሥጋ ብሔራዊ ውርሳችንን ባናጣም እንኳ ያንኑ ውርስ መንፈሳዊው ነገር የትኛው እንደሆነ ለመፈተን አንጠቀምም።

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ «ክርስቶስ ሁሉ በሁሉም ነው» የሚለው ትኩረት የተደረገበት ነጥብ ነው። «በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ» (ቆላ. 1፡18)። በክርስቶስ ምሉዓን ስለ ሆንን ሰዎችን ከሚለያዩ ምድራዊ ልዩነቶች በስቲያ አቅንተን ልንመለከትና በጌታ መንፈሳዊ አንድነት ልንደሰት እንችላለን። እንደ ዛሬዎች የሐሰት አስተማሪዎች፥ የኖስቲክ

የሐሰት አስተማሪዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ በክርስቶስ ያገኘውን የአንድነት ባለጸግነት ለመቀማት ይሞክሩ ነበር። ተጠንቀቁ!

እኛ በክርስቶስ ሕያዋን ስለሆንን ሰማያዊውን ነገር መሻት አለብን። ከክርስቶስ ጋር ስለሞትን ምድራዊውን ነገር መግደል አለብን። ክርስቶስን ወደ መምሰል ልናድግ እንችላለን፤ ስለሆነም የክርስቶስ የሆነውን ነገር ልናጠናክርና መንፈስ ቅዱስ አእምሮአችንን በማደስ በይበልጥ ወደ እግዚአብሔር አምሳል እንዲያመጣን መፍቀድ አለብን።

ወደ አንድ ስፍራ ለመሄድ የታጠቁ ሰዎች

ቆላስይስ 3፡12-17

ይህ ክፍል ጳውሎስ ክርስቲያኖች የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርገውን ግፊት ያጠቃልላል። ክፍሉ የአልባሳትን ምሳሌ በማቅረብ ይቀጥላል፡- «ገፋችሁታል ... ለብሳችሁታል» (ቁ. 8-10)። አንባቢዎቹ የኃጢአትን መገነዣዎችና አሮጌውን ሕይወት እንዲያወልቁና የቅድስናንና በክርስቶስ የሚገኘውን አዲስ ሕይወት «የጸጋ አልባሳት» እንዲለብሱ ያበረታታቸዋል።

በዚህ ክፍል ትኩረት የተደረገው በአነሣሽ ምክንያቶች ላይ ነው። አሮጌ ተግባራት አውልቀን የአዲስ ሕይወት መልካም ብቃቶችን መልበስ ያለብን ለምንድን ነው? ጳውሎስ በአዲስ ሕይወት እንመላለስ ዘንድ የሚያበረታቱንን አራት አነሣሽ ምክንያቶች ይዘረዝራል (ሮሜ 6፡4)።

የክርስቶስ ጸጋ (ቆላ. 3፡12-14)

ጸጋ ለማይገባቸው ኃጢአተኞች እግዚአብሔር የሚሰጠው ችሮታ ነው። ጳውሎስ የቆላስይስን ሰዎች የእግዚአብሔር ጸጋ ምን እንዳደረገላቸው ያስታውሳቸዋል።

እግዚአብሔር መረጣቸው (3፡12)። ምርጦች የሚለው ቃል «የእግዚአብሔርም ምርጦች» ማለት ነው። እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረው ቃል በጸጋ የመዳንን ትርጉም እንድንረዳ ይረዳናል፡- «እግዚአብሔር የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር ስለበዛችሁ አይደለም፤ እናንተ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር ጥቂቶች ነበራችሁና፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ ... በጽኑ እጅ [ከግብጽ] አወጣችሁ» (ዘዳ. 7፡7-8)።

ይህ የመለኮታዊ ምርጫ ተአምር እኛ ባለን ወይም ባደረግነው በማንኛውም ነገር ላይ አልተደገፈም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን በክርስቶስ የመረጠን «ዓለም ሳይፈጠር» በፊት ነበር (ኤፌ. 1፡4)። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሰው ባደረገው በጎ ነገር ወይም ሥራ መሠረት ቢያድን ኖሮ ማንም ሰው ባልዳነም ነበር። ሁሉም የተፈጸመው

በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ይህም ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር እንዲሆን ነው።

በመሠረቱ፥ ምርጫ ለእግዚአብሔር ልጆች የሚሆን «የተቀደስ ምሥጢር» ነው፤ እኛ አማኞች ላልዳኑት ሰዎች የምንገልጽላቸው ትምህርት አይደለም። «ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል» (2ኛ ጢሞ. 2፡19)፤ ስለሆነም ዘለዓለማዊ ዓላማዎቹን እንዲፈጽም ለእርሱ መተው አለብን። የኛ ድርሻ የወንጌሉን የምሥራች ለጠፋው ዓለም ማካፈል ነው።

እግዚአብሔር ለያቸው (3፡12)። ይህ ቅዱስ ለሚለው ቃል ፍችው ነው። በክርስቶስ ስላመንን ከዓለም ተለይተን ወደ ጌታ መጥተናል። እኛ የራሳችን አይደለንም። ይልቁንም ሙሉ ለሙሉ የእርሱ ንብረቶች ነን (1ኛ ቆሮ. 6፡19-20)። ወንዱንና ሴቷን አንድ ላይ በማጣመር ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ይኸውም ለጋብቻ ሥርዓት እንደሚለያቸው ሁሉ ደኅንነትም አማኙን ለኢየሱስ ክርስቶስ ይለየዋል። በሠርጉ ፍጻሜ ላይ ሙሽራዪቱ ከክብር ሚዜዋ ጋር ጠፍታ ብትገኝ አስደንጋጭ ክንውን አይሆንምን? እንደዚሁም ክርስቲያን ለዓለምና ለሥጋ እንደሚኖር አድርጎ መቁጠር የከፋ ነገር ነው።

እግዚአብሔር ይወዳቸዋል (3፡12)። የማያምን ሰው ኃጢአት በሚሠራበት ወቅት የቅዱሱን ፈጣሪና ዳኛ ሕግጋት የሚያፈርስ ፍጡር መሆኑ ነው። ዳሩ ግን ክርስቲያን ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ የአባቱን አፍቃሪ ልብ የሚያሳዝን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት ነው። በዓለም ውስጥ ካሉ አነሣሽ ኃይሎች ሁሉ እጅግ የላቀው ፍቅር ነው። አማኝ ለእግዚአብሔር ባለው ፍቅር እያደገ ሲሄድ እርሱን የመታዘዝ ፍላጎቱ ይጨምርና ከክርስቶስ በተቀበለው አዲስ ሕይወት መመላለስ ይጀምራል።

እግዚአብሔር ይቅር ብሎአቸዋል (3፡13)። «በደላችሁንም ይቅር አላችሁ» (ቆላ. 2፡13)። የእግዚአብሔር ይቅርታ ሙሉና ፍጻሜ ያለው እንጂ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ወይም ከፊል አይደለም። ቅዱሱ አምላክ ኃጢአተኞች የሆንን እኛን ይቅር ሊለን የሚችለው እንዴት ነው? ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ካቀረበው መሥዋዕት የተነሣ ነው። እግዚአብሔር ይቅር ያለን ለእኛ ሳይሆን «ለክርስቶስ ብሎ» ነው (ኤፌ. 4፡32)።

በእግዚአብሔር ተመርጠን፥ በእግዚአብሔር ተለይተን፥ በእግዚአብሔር ተወደንና በእግዚአብሔር ይቅር ተብለን እንኖራለን።

እነዚህ ሁሉ የጸጋ ውጤቶች ናቸው። ከእነዚህ የጸጋ በረከቶች የተነሣ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት አንዳንድ ጥብቅ ኃላፊነቶች አሉት። የክርስትናን ሕይወት ውብ አልባሳት መጎናጸፍ አለበት። ጳውሎስ ስምንት ጸጋዎችን ይዘረዝራል።

ምሕረትን፥ ርኅራኄን ... ልበሱ (3፡12)። የግሪኩ ቃል ይህንን የአንጀት ርኅራኄ ይለዋል። ምክንያቱም እኛ በልባችን እንደሚሰማን የምናምነው ይህ ጥልቅ ስሜት የግሪክ ሰዎች በአንጀት አካባቢ እንደሚሰማ አድርገው ይወስዱት ነበር። አማኞች እንደ መሆናችን መጠን እርስ በርሳችን ምሕረትና ርኅራኄ ሊኖረን ይገባል (ፊል. 2፡1-11 ይመልከቱ)። ይህም እንደ ቴሌቭዥን የምንዘጋውና የምንከፍተው ነገር ሳይሆን ከሌሎች ጋር በቀላሉ ለመኖር የሚያስችለን የማያቋርጥ የልብ ዝንባሌ ነው።

ቸርነትን ... ልበሱ (3፡12)። እኛ የዳንነው እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ቸርነቱን ስላበዛልን ነው (ኤፌ. 2፡7፤ ቲቶ 3፡4)። እኛም በተራችን ለሌሎች ቸርነትን ማሳየት አለብን። የእግዚአብሔር ትእዛዝ «እርስ በእርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኖች ሆኑ» (ኤፌ. 4፡32) የሚል ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምንመለከታቸው እጅግ አስደናቂ የቸርነት ሥዕሎች አንዱ ንጉሥ ዳዊት ሽባውን ልዑል ሜምፊቦስቴን ያስተናገደበት ሁኔታ ነው (2ኛ ሳሙ. 9 ይመልከቱ)። የዳዊት ፍላጎት ለንጉሥ ሳኦል ቤተሰብ «የእግዚአብሔርን ቸርነት» ማሳየት ነበር። ይህም ለሳኦል ልጅ ለዮናታን ከነበረው ፍቅር የተነሣ ነው፤ የተገኘውም ሰው የዮናታን ልጅ ሜምፊቦስቴ ሲሆን እርሱም ድህነት የተጫጫነው ሽባ ሰው ነበር። ዳዊት ነገሩን ከሕግ አንጻር ቢመለከት ኖሮ ሜምፊቦስቴን በኮነነው ነበር። ምክንያቱም ይህ ሰው የበደለኛ ሰው አባል ነበር። ዳሩ ግን በፍቅርና በጸጋ ላይ ተነሣሥቶ የቸርነትን ተግባር አደረገለት።

ዳዊት ሜምፊቦስቴን ፈለገና እንዳይፈራ ዋስትና ሰጠው። ሜምፊቦስቴን እንደ ቤተሰቡ አባል በቤተ መንግሥት ውስጥ እንዲኖርና ከንጉሡ የተትረፈረፈ ገበታ እንዲመገብ ጋበዘው። ይህ የእግዚአብሔር ቸርነት ነው! እኔና እርስዎ ከዚህ የበለጠ ቸርነት ተደርጕልናል፤ ምክንያቱም ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን፥ ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም በሰማይ እንኖራለን።

ትሕትናን ... ልበሱ (3፡12)። በጳውሎስ ዘመን የነበረው የአረማውያን ዓለም ለትሕትና ስፍራ አይሰጥም ነበር። ይልቁንም ኩራትንና የበላይነትን ከፍ አድርገው ይመለከቱ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደር የማይገኝለት የትሑት ልቦና ምሳሌ ነው (ፊል. 2፡1-11)። ትሕትና ራስን ዝቅ አድርጎ መመልከት አይደለም። ይልቁንም በእግዚአብሔር ፊቃድ ውስጥ ስለ ራስ ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት ማለት ነው (ሮሜ 12፡3)። የልብ ትሕትና ያለው ሰው በመጀመሪያ ስለ ሌሎች እንጂ ስለ ራሱ አያስብም።

የዋህነትን ... ልበሱ (3፡12)። የዋህነት ኃይልን ከቁጥጥር ሥር የማድረግ ብቃት እንጂ ደካማነት አይደለም። ይህ ቃል በዝግታ የሚነፍሰውን ነፋስ፥ ለበሽተኛ የሚታዘዘውን መድኃኒት፥ የተገራውን ፈረስ ለማመልከት ይጠቅም ነበር። በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ ኃይል አለ። ነፋስ ማዕበል ሊፈጥር ይችላል፤ ከመጠን ያለፈም መድኃኒት ሰውን ሊገድል ይችላል፤ ፈረሱ የታሰረበትን ገመድ በጥሶ ሊጋልብ ይችላል፤ ዳሩ ግን ይህ ኃይል ከቁጥጥር ሥር ያለ ነው። የዋህ ሰው ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥር ሥር ስለሆነ አብዝቶ አይናደድም።

ትዕግሥትን ... ልበሱ (3፡12)። የዚህ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም ለረጅም ጊዜ ሳይቆጡ መቆየት ማለት ነው። ትዕግሥት የሌለው ሰው የሚናገረውንና የሚሠራውን አጥብቆ ሳያስብበት ሲሆን ራሱንም የመቆጣጠር ብቃት ያንሰዋል። አንድ ሰው ታጋሽ በሚሆንበት ጊዜ ነገር ከሚቆሰቁሱ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ጋር ብቀላን ሳይሻ በሰላም ሊሠራ ይችላል። መቆጣት የተቀደሰ ባሕርይ ምልክት ስለሆነ በቦታው ቢደረግ መልካም ነው። ይሁን እንጂ ትክክል ባልሆኑ ነገሮችና ምክንያቶች ፈጥኖ መቆጣት ተገቢ አይደለም።

«እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ» (ቆላ. 3፡13)። የዚህ ቀጥተኛ ትርጉም፡- ከመቆጣት ይልቅ ለማረም ትክክለኛ ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ራስን በራስ መቆጣጠር ነው። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይታገሣል። ወዲያውኑ በችኮላ አይፈርድም (ሮሜ 2፡4፤ 3፡25) ትሕትና፥ ትዕግሥትና መቻቻል አንድ ላይ ይሄዳሉ።

ይቅር ተባባሉ (3፡13)። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ይቅር ስለመባባል የጻፈው ወደ ትክክለኛ ውጤት መርቶናል። አዛኝና ጠብ ቀስቃሽ ሁኔታዎችን እየታገሠ ክርስቲያን ከብቀላ ርቆ መኖር ብቻ ሳይሆን፥ ችግር

ፈጣሪውንም ሰው ይቅር ማለት አለበት። ይህንን ካላደረገ በልቡ ውስጥ የጥላቻ ስሜት ሊያድርና ወደ ታላላቅ ኃጢአቶች ሊመራው ይችላል።

ይቅር ማለት የክርስቶስን ዱካ መከተል ነው (ኤፌ. 4፡32)። እንዲሁም ይቅርታ ልብን ወደ እግዚአብሔር የፍቅር ሙላት ይመራል። በሌላው ሰው ላይ የምንሰቅፈው ነገር ሲኖር ወዲያውኑ በልባችን ይቅር ማለት አለብን። [«የቤተሰብ ይቅርታ» ሌላው ጉዳይ ነው። ወደተቀየመን ሰው ዘንድ ልንሄድና በፍቅር ልናነጋግረው ይገባል (ማቴ. 18፡15-35)።]

ፍቅርን ልበሱት (3፡14)። ይህ ከሁሉም የክርስትና ምግባራት የላቀ ሲሆን ሌሎችን ምግባራት በሙሉ እንደሚያስተሣሥር «መቀነት» ነው። 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 እንደሚገልጸው፥ ጳውሎስ የዘረዘራቸው መንፈሳዊ መመዘኛዎች ሁሉ የእውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር ክፍሎች ናቸው። ፍቅር የመጀመሪያ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሲሆን፥ እንደ ደስታ (ቁ. 16)፥ ሰላም (ቁ. 15)፥ ትዕግሥት፥ የውሃት፥ ቸርነትና ትሕትና (ቁ. 12) የመሳሰሉ ሌሎች ይህንኑ ተከትለው ይመጣሉ።

ፍቅር በሕይወታችን ውስጥ ሲገዛ እነዚህን ሁሉ መንፈሳዊ ሥነ ምግባራት ስለሚያስተሳስር በውስጡ አንድነት ይታያል፤ ይህም መንፈሳዊ ብስለትን ያመለክታል። ይህ አንድነትና ብስለት ሕይወትን ሚዛናዊና የሚያድግ እንዲሆን ይረዳል። የኖስቲክ ዘይቤ ይህንን የማድረግ ብቃት አልነበረውም።

የክርስቶስ ሰላም (ቆላ. 3፡15)

በዚህ ቁጥር ጳውሎስ ከባሕርይ ወደ ጸባይ ይመለሳል። ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያከናወነ እንዳለ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? አንዱ መልስ፥ በልቡ የሚሰማው የክርስቶስ ሰላም አለ። ክርስቲያን ውስጣዊ ሰላም ሲያጣ፥ እግዚአብሔርን በሆነ መንገድ እንዳልታዘዘ ያውቃል።

ይግዛ ተብሎ የተተረጎመው ቃል የስፖርተኞች ቋንቋ ነው። ትርጉሙ «በስፖርተኞች ላይ ባለሥልጣን በመሆን፥ ሽልማቶችን መስጠት» ማለት ነው። ጳውሎስ የዚህን ቃል ሌላ ገጽታም ተጠቅሟል፡- «ማንም ሽልማት እንደማይነባችሁ አድርጎ አይናገር» (የቆላ. 2፡18 ቀጥተኛ ትርጉም)። በግሪክ ጨዋታዎች ብቁ ያልሆኑትና የውድድሩን ሕግ የሚጥሱትን ተወዳዳሪዎች የሚያገልሉ ዳኞች ነበሩ።

የእግዚአብሔር ሰላም በሚያምን ልባችን ውስጥ «ዳኛ» ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንታዘዝ ሰላሙ በውስጣችን ይገኛል፤ ዳሩ ግን ከፈቃዱ ወጣ ስንል (ሳናስተውልም እንኳ) ሰላሙን እናጣለን።

ዳሩ ግን እውነተኛ ያልሆነ የልብ ሰላም ስላለ መጠንቀቅ አለብን። ዮናስ ሆነ ብሎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቢተላለፍም በማዕበሉ በምትራወጠው መርከብ ውስጥ የሰላም እንቅልፍ ተኝቶ ነበር! «ስለዚያ ሳስብ ሰላም ይሰማኛል!» የሚለው ብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመኖራችን በቂ ማስረጃ አይሆንም። መጸለይ፥ ለፈቃዱ ራሳችንን መስጠትና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ፈቃዱን መሻት አለብን። የልብ ሰላም ብቻ ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ሰላም አይደለም።

በዚህ ውስጥ የተጨመረ ሌላም ነገር አለ፡- ይኸውም በልባችን ውስጥ ሰላም ካለን፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሰላም ይኖረናል። ለአንድ አካል ስለተጠራን በዚያ አካል ውስጥ የሚኖረን ግንኙነት የአንድነትና የሰላም መሆን አለበት። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ከሆንን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየትና መከፋፈልን እንደምናመጣ የተረጋገጠ ነው። ዮናስ ኃጢአቱ ማዕበሉን እየፈጠረ ሳለ በሰላም ያንቀላፋ መስሎት ነበር!

አንድ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሰላም ሲያጣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆኑ አቅጣጫዎች መሄድ ይጀምራል። የውስጥ ሰላሙን ለማካካስ የዓለምና የሥጋ ነገሮችን መከታተል ይጀምራል። ለመሸሽ ይፈልጋል፤ ዳሩ ግን ከራሱ ለመሸሽ አይችልም! የእግዚአብሔርን ሰላም በውስጡ ሊለማመድ የሚችለው ኃጢአቱን ሲናዘዝ፥ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሲቀበልና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲያደርግ ብቻ ነው።

በልብ ውስጥ ሰላም ሲኖር ከናፍርትም ምስጋናን ያንጠባጥባሉ፡- «የምታመሰግኑም ሁኑ» (ቆላ. 3፡15)። ከእግዚአብሔር ፈቃድ የወጣ ክርስቲያን በምንም ዓይነት ለእግዚአብሔር እውነተኛ ምስጋና ሊያቀርብ አይችልም። ዳዊት ኃጢአቱን በሸሸገ ጊዜ ሰላሙንና ምስጋናውን አጥቷል [መዝ. (32) እና (51)]። ዳሩ ግን ኃጢአቶቹን በተናዘዘ ጊዜ ዝማሬው ተመለሰለት።

የክርስቶስ ቃል (ቆላ. 3፡16)

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ማለት ነው። የሐሰት አስተማሪዎች ሰው-ሠራሽ ልምዶች፥ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ሰብዓዊ ፍልስፍናዎችን አንግበው ወደ ቆላስይስ ዘለቁ። የእግዚአብሔርን ቃል ከትምህርቶቻቸው ጋር ለማስማማት ጣሩ፤ ዳሩ ግን አልሆነላቸውም። ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ አድርጎ ያሳያል።

ለቆላስይስ ሰዎች ደኅንነትን ያጎናጸፈው የወንጌሉ የእውነት ቃል እንጂ የሐሰት አስተማሪዎች ቃል አልነበረም (ቆላ. 1፡5)። ይኸው ተመሳሳይ ቃል ሕይወትን ይሰጠናል፤ እንዲሁም ያቆመናል፤ ያበረታናልም (1ኛ ጴጥ. 1፡22-2፡3)።

በውስጣችን በሙላት «እንዲያድር» ከፈቀድንለት ቃሉ ሕይወታችንን ይለውጣል። ማደር ማለት «በቤት ውስጥ መሆን» ማለት ነው። የክርስቶስን ጸጋና ሰላም ከተለማመድን፥ ቃሉ በልባችን ውስጥ ያድራል። የእግዚአብሔር ቃል ትርጉም ያለው ኑሮ እንድንኖር ምን ያህል በመንፈሳዊ ነገር የበለጸገ እንደሆነ እንረዳለን።

ይሁን እንጂ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ነገር የጻፈው ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ብቻ ነው ብለን ማሰብ የለብንም። ምክንያቱም እንዲጸፍ ያደረገው ለጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን አካል ነው። የክርስቶስ ቃል በእናንተ መካከል ይኑርባችሁ የሚለው ሊሆን የሚችል ትርጉም ነው። በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ከኖረ፥ በቤተ ክርስቲያን ጎብረትም እንዲሁ ይኖራል።

ዛሬ ልክ በጳውሎስ ዘመን እንደነበረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ አደገኛ ሁኔታ ይታያል። ይኸውም የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለእግዚአብሔር ቃል የሚሰጡት ጊዜ አናሳ መሆኑ ነው። በሰንበት ክፍሎችና በሰበካ መድረኮች ቀለል ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች እጥረት ያለ ይመስላል። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ለፊልሞች፥ ለሙዚቃ ዝግጅቶችና ለሌሎች አዝናኝ ፕሮግራሞች የበለጠ ፍላጎት አለው። በርካታ የዳኑ ሰዎች ለማንበብ፥ ለማጥናትና በቃል ለመያዝ ጊዜ ስለማይወስዱ የእግዚአብሔር ቃል በልባቸው ውስጥ በሙላት እንደሚኖር በታማኝነት ሊያረጋግጡ አይችሉም።

ጳውሎስ እንዳስቀመጠው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታችንና አምልኮን በዝማሬ በምንገልጽበት ሁኔታ መካከል ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለ። ራሳችንንና ሌሎች ሰዎችን የምናጽናናበትና የምናስተምርበት አንዱ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በዝማሬ በማገልገል ነው። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስን የማናውቅና የማናስተውል ከሆነ በታማኝነት ከልባችን ልንዘምር አንችልም።

ምናልባትም በአብያተ ክርስቲያናታችን ውስጥ የሚታየው ይህ «የቅዱሳት መጻሕፍት ድህነት» ዛሬ ለምናያቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ መዝሙራት መበራከት መንስኤ ሳይሆን አይቀርም። አንድ ሰባኪ እንደሚያሰማው የውሸት ስብከት እንዲሁ ዘማሪ የውሸት ዝማሬ ሊያቀርብ አይገባም። አብዛኞቹ፥ ታላላቅ የእምነት መዝሙሮች፥ የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት በሚያውቁ አማኞች ተዘጋጅተዋል። ዛሬ የሚደመጡ በርካታ «መንፈሳዊ መዝሙር» ተብየዎች ስለ እግዚአብሔር ቃል ጥቂት ወይም ምንም እውቀት በሌላቸው ሰዎች ተጽፈዋል። በዝማሬ የማመስገኑን ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቃል መገንጠሉ አደገኛ ነገር ነው።

በመሠረቱ መዝሙረ ዳዊት ከብሉይ ኪዳን የተወሰደ መዝሙር ነው። ለብዙ መቶ ዓመታት በእንግሊዝኛ ተናጋሪው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ አብያተ ክርስቲያናት ከመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የተወሰነውን ብቻ ይጠቀሙ ነበር። ዛሬ ሰዎች የቅዱሳት መጻሕፍት በተለይም የመዝሙረ ዳዊትን መዝሙራት ወደ መጠቀም ሲመለሱ ሳይ በጣም ደስ ይለኛል። የቅኔ መዝሙሮች ከመዝሙረ ዳዊት በቀጥታ የተወሰዱ ሳይሆኑ በአማኞች የተጻፉ የምስጋና ዝማሬዎች ነበሩ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የበለጸገ የመዝሙር ውርስ አላት። ዳሩ ግን ብዙዎቹ ወደ ጎን እንዳይተዉ እሰጋለሁ። መንፈሳዊ መዝሙሮች፥ ከመዝሙረ ዳዊት ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መገለጫዎች ነበሩ። መዝሙር ውዳሴን በምንዘምርበት ጊዜ ለጌታ እንቀኛለን። መንፈሳዊ መዝሙር በምንዘምርበት ጊዜ እርስ በእርሳችን እንጽናናለን።

ጳውሎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት ምን መምሰል እንዳለበት ገልጾአል (ቆላ.3፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡26)። አማኙ ለራሱ፥ ለሌሎች አማኞችና እንዲሁም ለጌታ እንደሚዘምር ያስተውሉ። ዝማሬአችን ከልብ የመነጨ እንጂ የከንፈር እንቅስቃሴ ብቻ መሆን የለበትም። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቃል በልባችን ውስጥ ከሌለ ከልባችን

ልንዘምር አንችልም። የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። ምክንያቱም ይህ ለእግዚአብሔር የምናቀርበውን የግልና የጋራ አምልኮን ያበለጽጋል።

ዝማሬያችን በጸጋ መሆን አለበት። ይህም ስንዘምር ልክ የመዝሙር ስጦታ ወይም ችሎታ እንዳላቸው ሰዎች ሳይሆን በልባችን ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ልንዘምር ይገባናል ማለት ነው። በሕመም ስንሆን ወይም ሁኔታዎች ያልተመቻቸ ሲመስለን ጌታን በዝማሬ ለማምለክ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገናል። ጳውሎስና ሲላስ በዚያ የፊልጵስዩስ ወኅኒ ቤት ውስጥ የዘመሩት ጸጋ ስለበዛላቸው ነው (የሐዋ. 16፡22-25)። ዝማሬያችን በልባችን ያለውን የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንገልጽበት እንጂ ሥጋዊ ችሎታችንን የምናንጸባርቅበት ሊሆን አይገባም።

አንድ ሰው ስኬታማ የክርስትና ሕይወት ለሦስት መጻሕፍት ትኩረት እንደሚሰጥ ተናግረዋል፤ እነዚህም፡- የእግዚአብሔር መጽሐፍ ለሆነው መጽሐፍ ቅዱስ፥ ለባንክ ደብተር እና ለመዝሙር መጽሐፍ ናቸው። እኔ በዚህ አሳብ እስማማለሁ። ብዙውን ጊዜ ለእግዚአብሔር የማቀርበውን ምስጋና ለመግለጽ ይረዳኝ ዘንድ በጸሎት ጊዜዬ መዝሙር ውዳሴን እጠቀማለሁ። አንድ አማኝ በቃሉ እውቀት ሲያድግ ምስጋናውን ለእግዚአብሔር በሚገልጽበትም መንገድ እያደገ ይሄዳል። ታላላቅ የአብያተ ክርስቲያናት መዝሙሮች፥ የወንጌል መዝሙሮችና እውነትን የሚያስተምሩ መንፈሳዊ መዝሙሮች የተለየ ትርጉም ስለሚሰጡት ሊያደንቃቸው ይጀምራል። ትርጉም የማይሰጡ መዝሙሮችን ብቻ መዘመር ራስን ከመንፈሳዊ ሙላት መግታት ነው።

ይህንን ክፍል ከማጠቃለላችን በፊት በኤፌ. 5፡18-6፡9 ያለውን ተመሳሳይ ክፍል መመልከት አለብን። ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክት፥ በመንፈስ ስለመሞላት አጽንዖት ሰጥቶ ሲናገር፥ ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክት በቃሉ ስለመሞላት አትኩሮ ተናግሮአል። ዳሩ ግን የዚህ መንፈሳዊ ሙላት መረጃዎች አንድ ዓይነት ናቸው። አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ እንዴት እናውቃለን? በመንፈስ የተሞላ ክርስቲያን ደስተኛ፥ አመስጋኝና በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛ ነው (ኤፌ. 5፡19-21)። እነዚህ ሁሉ በቤትም ሆነ በመሥሪያ ቤት ውስጥ በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ውስጥ ይንጸባረቃሉ (ኤፌ. 5፡22-6፡9)። አንድ አማኝ በእግዚአብሔር ቃል እንደተሞላ እንዴት እናውቃለን?

በእግዚአብሔር ቃል የተሞላ ክርስቲያን ደስተኛ፥ አመስጋኝና በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛ ነው (ቆላ. 3፡16-4፡1)።

የክርስቶስ ስም (ቆላ. 3፡17)

በዘመናዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ለስሞች የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው። ዳሩ ግን የጥንቱ ዓለም ለሰው ስም የሚሰጠው ግምት እጅግ ከፍተኛ ነበር። ብዙውን ጊዜ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከአንድ አስፈላጊ ገጠመኝ ወይም አዲስ ዕድገት በኋላ እግዚአብሔር የሰውን ስም ይለውጥ ነበር።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን የክርስቶስን ስም ተሸክመናል። ክርስቲያን የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሙሉ ሦስት ጊዜ ብቻ ተጽፎ ይገኛል (የሐዋ. 11፡26፤ 26፡28 እና 1ኛ ጴጥ. 4፡16)። በመጀመሪያ ይህ ስም የተሰጠው በንቀት ሲሆን ቀስ በቀስ የክብር ስም ሆነ። ስለሆነም የክርስቶስ ስም ከእርሱ ጋር መተባበራችንን ያመለክታል። እኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ነን።

እንዲሁም የእርሱ ስም ሥልጣን ማለት ነው። በቼክ ላይ የተፈረመ የሰው ስም ገንዘብን ከባንክ ለማውጣት ሥልጣን አለው። በገንዘብ ደረሰኝ ላይ የተፈረመ የሊቀ መንበር ስም ደረሰኙን ሕጋዊ ያደርገዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የመጸለይ ሥልጣን የተሰጠንም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው (ዮሐ. 14፡13-14፤ 16፡23-26)። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነና ለእኛ ብሎ ስለሞተ፥ በስሙ፥ ሥልጣን አለን።

የምንለውና የምናደርገው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መፈጸም አለበት። በቃላችንና በተግባራችን ስሙን ማስከበር አለብን። የኢየሱስን ስም የማያስከብር ማንኛውም ነገር ወደ ሕይወታችን እንዲገባ ከፈቀድን ኃጢአት እያደረግን ነው። ሁሉንም ነገር በስሙ ሥልጣን ለስሙ ክብር ማድረግ አለብን።

በኢየሱስ ስም መጠራት ትልቅ ዕድል ነው። ይሁን እንጂ፥ ሚን ያለ ኃላፊነትም አለበት። ስሙን ስለተሸከምን ስደትና መከራን እንቀበላለን (ዮሐ. 15፡20-21)። ከተለያዩ ውይይቶች ውስጥ እንዳስተዋልሁ፥ ለሰዎች ባፕቲስት (መጥምቃዊ)፥ ፕረስቢቴሪያን፥ ሉተራን፥ ቃለ ሕይወት፥ መካነ ኢየሱስ፥ ሙሉ ወንጌል፥ እንዲያውም ከሀዲ (ኤቲየስት) እንደሆኑ ቢናገሩም ምንም ምላሽ ላያገኙ ይችላሉ። ዳሩ ግን ክርስቲያን

እንደሆኑ በመናገር፥ የክርስቶስን ስም ወደ ውይይቱ ቢያስገቡ ወዲያውኑ ምላሽ ያገኛሉ። ምላሹም ብዙውን ጊዜ አሉታዊ ነው።

እያንዳንዱ ወላጅ ልጁን የቤተሰቡን ስም እንዲያከብር ለማስተማር ይሞክራል። ዳሩ ግን ሰውዬው ቅድመ-ዝርያዎቹ ለዓመታት ተንከባክበው ያቆዩትን ስም በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሊያበላሽ ይችላል። ለምሳሌ ያህል ይሁዳ የሚለው የዕብራይስጥ ስም የተከበረ ነበር። ትርጉሙም «ምስጋና» የሚል ነው። በአዲስ ኪዳን ግን የዚሁ ስም በአስቆሮቱ ይሁዳ ምክንያት የሰዎች አስተሳሰብ ስሙ ያበላሸባቸው ስለሆነ ዛሬ ልጁን ይሁዳ ብሎ የሚጠራው ማነው?

በዚህ የቆላስይስ መልእክቱ ጳውሎስ እንደገና ምስጋና ማቅረብን እንደጠቀሰ ልብ ይበሉ። በክርስቶስ ስም የምናደርገው ማንኛውም ነገር ምስጋና ከማቅረብ ጋር መግጠም አለበት። ምስጋና ለማቅረብ የማንችል ከሆነ ባናደርገው ወይም ባንናገረው ይሻላል። በቆላስይስ ውስጥ ምስጋና ስለማቅረብ ከተጠቀሱት ስድስቱ ውስጥ ይህ አምስተኛው ነው (1፡3፥ 12፤ 2፡7፤ 3፡15፥ 17፤ 4፡2)። ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ በሚጽፍበት ወቅት የሮም እስረኛ እንደነበር ብናስታውስ በምስጋና ላይ የቀረው ትኩረት የበለጠ አስደናቂ ትርጉም ይሰጠናል።

እነዚህ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ባለው አኗኗር የሚረዱ አራት መንፈሳዊ ማነቃቂያዎችን ሰንመለከት፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ማዕከላዊነት ልባችን ይነካል። ክርስቶስ ይቅር ስላለን እኛም ሌሎችን ይቅር እንላለን (ቁ. 13)። በልባችን ውስጥ መግዛት ያለበት የክርስቶስ ሰላም ነው (ቁ. 15)። የክርስቶስ ቃል በሙላት ሊኖረን ይገባል (ቁ. 16)። የክርስቶስ ስም መለያችንና ሥልጣናችን መሆን አለበት። «ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው» (3፡11)።

በልባችን ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከክርስቶስ ጋር ስለተባበረን፥ ለተቀደሰ አኗኗር የምንፈልጋቸው ሀብቶች ሁሉ አሉን። የክርስቶስን ጸጋ ስለተቀበልን፥ ለእርሱ ለመኖር እንሻለን። በክርስቶስ ሰላም ደስ ስለተሰኘን፥ እርሱን ለመታዘዝ እንሻለን። በክርስቶስ ቃል በኩል ስለ በለጸግን፥ በክርስቶስም ስም ከፍ ከፍ ስላልን፥ እኛም እርሱን ለማክበር እንሻለን።

ከዚህ የበለጠ ማነቃቂያ ልንሻ እንችል ይሆን?

- 10 -

የቤተሰብ ጉዳይ

ቆላስይስ 3፡18-4፡1

በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦችንም ይለውጣል። በዚህ ክፍል ጳውሎስ ወደ ቤተሰብ አባላት ያነጣጥራል፤ እነርሱም፡- ባሎችና ሚስቶች፥ ልጆች፥ እንዲሁም የቤት ውስጥ ሠራተኞች ናቸው። ሐዋርያው ሁላቸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስደሰት ይኖሩ ዘንድ ስለሚለምን እነዚህ ሰዎች አማኞች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

ዛሬ የቤተሰቦች አኗኗር ሙሉ ለሙሉ የተበላሸ ነው። አንድ የተመለከትሁት ዘገባ እንደሚያመለክተው፥ በአሜሪካ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በአሁኑ ወቅት በርካታ የፈራረሱ ቤቶች ይገኛሉ። ከእያንዳንዳቸው ሁለት ጋብቻዎች ውስጥ አንድ ፍች ይኖራል። አንድ ወላጅ ብቻ ያላቸው ልጆች እየተበራከቱ ናቸው። ከጠቅላላው የእናትነት ጸጋ ከተቸራቸው ሴቶች መካከል ግማሾቹ ከቤት ውጭ የሚሠሩ ሲሆን፥ ብዙዎቹ ጨቅላ ሕፃናት ያሏቸው ናቸው። ዕድሚያቸው ከ6-16 ዓመት የሆኑ የአሜሪካ ሕፃናት በየሳምንቱ ከ20-24 ሰዓታት ቴሌቭዥን በማየት ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። የሚያዩትም ነገር ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል። አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን አግባብ ባልሆነ መንገድ በመደብደብ በአካላቸው ላይ ጉዳት በአእምሮአቸውም የሥነ-ልቦና ችግር የደረሰባቸው ልጆች ቁጥር እየበዛ ሄዶአል። በየዓመቱ ከ2 እስከ 4 ሚሊዮን የሚደርሱ የዚህ ዓይነት ጉዳዮች ወይም አቤቱታ ለፖሊስ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ቀርቦአል። ሆኖም ከዚህ የሚበልጡት የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ችግሮች በፍጹም እንዳልተመዘገቡ ይታወቃል።

እግዚአብሔር በምድር ላይ የመሠረተው የመጀመሪያው ተቋም ቤተሰብ ነበር (ዘፍ. 2፡18-25፤ ማቴ. 19፡1-6)። የቤተሰብ የአቋም ሁኔታ የኅብረተሰብንና የአገርን ሁኔታ ይወስናል። የቤተሰብ የሥነ- ምግባር መበላሸት የመጨረሻው ዘመን ምልክት ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡1-5)። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ኮንፊዩሽስ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «የአገር ጥንካሬ የመነጨው በውስጡ ከነበሩት ቤተሰቦች አንድነት ነው።» እንደ ግለሰቦች

ማድረግ ከምንችላቸው ታላላቅ ነገሮች አንዱ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያላቸውን ክርስቲያን ቤተሰቦች ማነጽ ነው። ጳውሎስ የቤተሰቡን የተለያዩ አባላት በመዘርዘር ለጠንካራና ፈሪሃ-እግዚአብሔር ላለበት ቤተሰብ የሚያስፈልጉትን ነገሮች አመልክቶአል።

ባሎችና ሚስቶች፡- ፍቅርና መገዛት (ቆላ. 3፡18-19)

ጳውሎስ ሚስቶችን በመጀመርያ የጠቀሰው እጅግ ደካሞች ስለነበሩ አይደለም። ሴቶች በሮማ ግዛት የነበራቸውን ስፍራ ሙሉ ለሙሉ ወንጌል ለውጦአል። አዲስ ነጻነትና ሥልጣንም ሰጥቶአቸዋል። አንዳንዶቹ ግን ይህን ነጻነትና ሥልጣን በሚገባ ሊይዙት አልቻሉም ነበር። በዚህም ምክንያት ጳውሎስ ገሥጾአቸዋል። (ተመሳሳይ ተግሣጾች በኤፌ. 5፡21-33 እና 1ኛ ጴጥ. 3፡1-11 ይገኛሉ።)

መገዛት ሲባል እንደ «ባርነት» ወይም «የበላይነት» አድርገን ማሰብ የለብንም። ቃሉ ወታደራዊ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም «በደረጃ ተዋረድ ማስቀመጥ» ማለት ነው። አንዱ ተራ ወታደር ሌላው ደግሞ ኮሎኔል የመሆኑ እውነታ የግድ አንዱ ሰው ከሌላው ይሻላል ማለት አይደለም። የተለያየ ደረጃ እንዳላቸው ብቻ ያሳያል።

እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር «በአግባብና በሥርዓት» አድርጓል (1ኛ ቆሮ. 14፡40)። በጎበረተሰቡ ውስጥ የሥልጣን ተዋረድ ባይኖር ኖሮ ሥርዓት-አልበኝነት ይሰፍን ነበር። ሴት ለባልዋ መገዛት አለባት ማለት ወንዱ ከእርሷ የተሻለ ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም በቤት ውስጥ ወንዱ ራስ የመሆንና የመምራት ኃላፊነት አለው ማለት ነው።

ራስ መሆን ማለት በፍቅር መምራት እንጂ አምባገነን ወይም ጌታ መሆን አይደለም። እንዲያውም ባልና ሚስት ሁለቱም ለጌታና አንዳቸው ለሌላው መገዛት አለባቸው (ኤፌ. 5፡21)። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ሥር የሚሆን አንዱ ለሌላው የሚሰጠው የጋራ አክብሮት ነው።

እውነተኛ መንፈሳዊ መገዛት የዕድገትና የሙላት ምሥጢር ነው። ክርስቲያን ሴት ለጌታና ለባልዋ በምትገዛበት ጊዜ በሌላ በማንኛውም መንገድ የማታገኘውን ነፃነትና ሙላት ትለማመዳለች። ይህ የጋራ ፍቅርና መገዛት ባልና ሚስቱ እግዚአብሔር እንዲሆኑለት ወደሚፈልገው ደረጃ የሚደርሱበትን የዕድገት ሁኔታ በቤት ውስጥ ያመቻቻል።

ክርስቲያን ሚስት «በጌታ» መሆኗ፥ ለሥጋዊ ግለኝነት ማመካኛ ሊሆን አይችልም። እውነቱ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። ምክንያቱም እርሷ ስለዳነች ቃሉን እንድትታዘዝና ለባልዋ እንድትገዛ አስፈላጊ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ «ወንድ ወይም ሴት የለም» (ገላ. 3፡28) የሚለው እውነት ሲሆን፥ በደስታ መገዛቷም ሚስት የጌታ ለመሆኗ መረጃ ይሆናል።

ይሁን እንጂ ባል ሚስቱን የማፍቀር ኃላፊነት አለበት። እንዲሁም በዚህ ስፍራ ለ«ፍቅር» የተጠቀሰው ቃል ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጠው የመሥዋዕትነትና የአገልግሎት ፍቅር አጋፔ ነው። ጋብቻ በሰብአዊና እርግጠኛነት ስሜት ባልዳበረበት ፍቅር ሊጀምር ቢችልም፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ወደሚመጣው መንፈሳዊ የአጋፔ ፍቅር ጠልቆ ማደግ አለበት። በተመሳሳይ የምንባብ ክፍል (ኤፌ. 5፡21-33) «ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት» ባል ሚስቱን መውደድ እንዳለበት ጳውሎስ በግልጽ ተናግሯል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለንተናውን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። በፈቃዱ ለኛ ሞቷል! አንድ ሰው ለሚስቱ ያለው ፍቅር በስጦታዎችና በቃላት ብቻ ሳይሆን ለደኅንነቷና ለደስተኛነቷ በሚያቀርበው መሥዋዕትነትና አሳቢነት ጭምር ይገለጻል።

ጳውሎስ ለባሎች ልዩ የማስጠንቀቂያ ቃል ይጨምራል፡-«መራራም አትሆኑባቸው» (ቆላ. 3፡19) ይላል። ሚስቶች ማድረግ ሲገባቸው ባለማድረጋቸው ወይም ማድረግ የማይገባቸውን በማድረጋቸው ባሎች በሚስቶቻቸው ላይ የጥላቻ ስሜት እንዳያድርባቸው መጠንቀቅ አለባቸው። በቤት ውስጥ «መራራ ሥር» የጋብቻን ሕይወት ሊመርዝና ለሰይጣን ዕድል-ፈንታ ሊሰጠው ይችላል (ዕብ. 12፡15፤ ኤፌ. 4፡31)። ክርስቲያን ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ግልጽና ታማኝ በመሆን ስሜቶቻቸውን አለመደበቅና አለመዋሸት ይጠበቅባቸዋል። የቤተሰብ ልዩነቶችን ለማስወገድ «እውነትን በቅንነት መናገር» (ኤፌ. 4፡15) መልካም ነው። ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖር ከተፈለገ «በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ» የሚለውን ልንከተለው የሚገባን የጥበብ ቃል ነው (ኤፌ. 4፡26)።

ሚስቱን ከልቡ የሚወድ ባል በቤት ውስጥ ሸካራ ባሕርይ ሊያሳይ ወይም ሥልጣኑን በመጠቀም የጭካኔን ተግባር ሊፈጽም አይችልም። «ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም

አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል» (1ኛ ቆሮ. 13፡4-5)።

እንደ እውነቱ ከሆነ አንዲት ሴት ለሚወዳት ባሏ ለመገዛት ብዙም የሚቸግራት አይሆንም። ለእርስዋ ከሁሉም የሚሻለውን እንደሚፈልግ እንጂ ሊጎዳት በመፈለግ አንዳችም ተግባር እንደማይፈጽም በሚገባ ታውቃለች። ባል ለሚስቱ የሚያሳየው ፍቅር የሚለካው ለእርስዋ በሚከፍለው መሥዋዕትነት ሲሆን፥ ሚስት ለባልዋ ያላት ፍቅር የሚለካው ደግሞ ለእርሱ ባላት ሙሉ መገዛት ነው። በፍቅር ድባብ ውስጥ መሥዋዕትነትና መገዛት ካለ ደስተኛ ቤተሰብ መመሥረት ይቻላል።

ደስተኛ ጋብቻ ከመቅጽበት ዱብ የሚል ሳይሆን ሁልጊዜም ተግቶ በመሥራት የሚመጣ ነው። ለእርሱ በመገዛት ከክርስቶስ ጋር በምንመላለስበት ጊዜ አንዳችን ለሌላው ለመገዛትና አንዳችን ሌላውን ለማገልገል ምንም ችግር አይኖርብንም። ዳሩ ግን ራስ-ወዳድነት በነገሠበት ስፍራ ግጭትና መከፋፈል ይኖራል። በልብ ውስጥ መራርነት ካለ በመጨረሻ በቤት ውስጥ አምባጓሮ ይነሣል።

ለማፍቀርና ለመገዛት የሚያስችለንን ኃይል ከወዴት እናገኛለን? ከጌታ ዘንድ እናገኛለን። ቀደም ብለው የተገለጹትን «የጸጋ አልባሳት» ከለበስን (ቆላ. 3፡5-14)፥ ልባችን በክርስቶስ ሰላምና በክርስቶስ ቃል ከተሞላ፥ ለቤተሰቡ ደስታና አንድነት የሚሆን አስተዋጽኦ እናበረክታለን። በመጀመሪያ ክርስቶስን፥ ቀጥሎ ሌሎችንና በመጨረሻም ራሳችንን ለማስደሰት ዐቅደን ከኖርን ጠንካራ ጋብቻና መንፈሳዊ ቤት ለማነጽ እንችላለን።

ወላጆችና ልጆች፡- ማበረታቻና ታዛዥነት (ቆላ. 3፡20-21)

በእነዚህ የክርስቲያን ቤተሰቦች ውስጥ ልጆችም ነበሩና ጳውሎስ ከደብዳቤው የተወሰነውን ክፍል ለእነርሱ ይሰጣል። የተለመደው የጋብቻ ውጤት ልጆችን መውለድ ነው፤ ባህላችን እንደሚል፡- «የጋብቻ ትርጉሙ ልጅ ወልዶ መሳሙ ነው»። እንዲሁም ዕድለኞች ልጆች ፍቅርና መገዛት ባሉባቸው የክርስቲያን ቤቶች ውስጥ የሚወለዱት ናቸው። ለመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን የተሰጠው የእግዚአብሔር ትእዛዝ «ብዙ ተባዙ» የሚል ነበር (ዘፍ. 1፡28)። ይህም ትእዛዝ የተሰጠው ሰው

በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ነበር። የጋብቻ ግንኙነትና ልጆችን መውለድ ኃጢአት አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ካዘጋጃቸው ተግባራት የሚመደቡ ናቸው። ልጅ በመውለዱ ሂደት ውስጥ ባልና ሚስት በእግዚአብሔር የፍጥረት ሥራ ውስጥ ተካፋዮች ይሆናሉ።

በዚህ ስፍራ በርካታ ነገር የተነገረው ስለ ልጆች መብት ነው። በመሠረቱ ልጆች መብት አላቸው። ከእነዚህም መካከል አንደኛው የመወለድ መብት ነው። ሌላው «በጌታ ምክርና በተግሣጽ» (ኤፌ. 6፡4) ሊያድጉ በሚችሉበት የተለወጠ ክርስቲያን ቤት ውስጥ የመወለድ መብት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር፥ በፍቅር የሚያሠለጥኑ፥ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያደሩባቸውን ወላጆች የማግኘት መብት አላቸው።

ጆን ኤች. እስታርኪ በጭካኔው የታወቀ እንግሊዛዊ የብርትሽ ወንጀለኛ ነበር። ይህ ሰው የገዛ ሚስቱን ገድሎአል። ከዚያም ወንጀሉን አመነና ተገደለ። ባለሥልጣኖቹም ስልቨሽን አርሚ የተባለ መንፈሳዊ ድርጅት መሥራች የሆኑትን ጄኔራል ዊሊያም ቡዝ የእስታርኪን የቀብር ሥነ-ሥርዓት እንዲያስፈጽሙ ጠየቋቸው። ጄኔራል ቡዝ ስለ እስታርኪ አስከፊ ሁኔታ በመጋፈጥ በብዙ ሕዝብ ፊት ቆሙ። እርሳቸውም በዚህ ብዙ ሕዝብ መካከል ሲቆሙ እንደዚህ ያለ የተቆጣና አስፈሪ ፊት በዘመናቸው አይተው አያውቁም ነበር። ነገር ግን የመጀመሪያ ቃሎቻቸው ሕዝቡን አስደንቋቸዋል፡- ይህም ቃል «ጆን ኤች እስታርኪ የምትጸልይለት እናት አልነበረችውም!» የሚል ነበር።

ልጆች መብት ብቻ ሳይሆን ኃልፊነትም አለባቸው። ቀዳሚ ኃላፊነታቸውም መታዘዝ ነው። ራሳቸውን በሚያስደስቱ ነገሮች ብቻ ሳይሆን «በሁሉ» መታዘዝ አለባቸው። ወላጆቻቸው የተሳሳተ ነገር እንዲያደርጉ ይጠይቁዋቸው ይሆን? ወላጆች ለጌታና አንዳቸው ለሌላቸው የሚገዙ ከሆነ፥ እርስ በእርሳቸውም የሚዋደዱና ልጆቻቸውንም የሚወዱ ከሆን እንዲህ ያለ ነገር ሊጠይቋቸው አይችሉም።

ወላጆቹን መታዘዝ ያልተማረ ልጅ ማንኛውንም ዓይነት ባለ ሥልጣን በመታዘዝ ያድጋል ማለት ዘበት ነው። አስተማሪዎቹን፥ ፖሊስን፥ የሥራ አለቆቹንና ከእርሱ በልጦ የሚገኘውን ባለሥልጣን ሁሉ አይታዘዝም። በማኅበረሰባችን ውስጥ የሚታየው ለባለሥልጣን ያለመታዘዝ በቤት ውስጥ ያለውን ያለመታዘዝ ያንጸባርቃል።

ባመዛኙ ልጆች ይፋ ያወጡታል እንጂ ችግሩን የሚፈጥሩት እነርሱ አይደሉም። ራሳቸውን በሥርዓት መምራት የማይችሉ ወላጆች ልጆቻቸውን ፈር ማስያዝ አይችሉም። አባትና እናት ራሳቸው ለባለሥልጣን የማይገዙ ከሆኑ በሌሎች ላይ ባለሥልጣናት ሊሆኑ አይችሉም። ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ትክክለኛ ሚዛናዊነት የሚታይበት መንፈሳዊና ሥጋዊ ሥልጣን ሊለማመዱ የሚችሉት ለእርስ በርሳቸውና ለጌታ ሲገዙ ብቻ ነው።

የልጅ የታዛዥነት መለኪያው «በሁሉም» ነገር ሲሆን ዓላማውም ጌታን ለማስደሰት ነው። ወላጆች ለጌታ የተሰጡ ካልሆኑ ወላጆችን አስደስቶ ጌታን ያለማስደሰት ይቻላል። በፍቅርና በእውነት ድባብ የሚኖር የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነብና አብሮ የሚጸልይ ቤተሰብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና እርሱንም ደስ ለማሰኘት ብዙም አይቸገርም።

በቁጥር 21 «አባቶች» የሚለው ቃል በዕብ. 11፡23 እንዳለው «ወላጆች» ተብሎ ሊተረጎም ይችል ነበር። ወላጆች ለልጆቻቸው መታዘዝ ይችሉ ዘንድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው ጳውሎስ በግልጽ ያስቀምጣል። «ልጆቻችሁን አታበሳጩዋቸው» (ቆላ. 3፡21) የሚለው ለወላጆች የተሰጠ ትእዛዝ ሲሆን ብዙ ጊዜ ሲጣስ እንመለከታለን። ብዙውን ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸው አንድን ነገር ሲጠይቁ ወዲያውኑ አይሆንም! በማለት ያስደነግጧቸዋል። ዳሩ ግን ወላጆች ልጆቻቸው የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች ሁሉ በጥንቃቄ ሊሰሙና ሊገመግሙ ይገባቸው ነበር። ብዙውን ጊዜ ወላጆች አሳባቸው እጅግ በተለያየ መጠን በመቀያየር ለልጆቻቸው ችግሮች ይፈጥራሉ። አንዳዴም ቅጥ ካጣ ልቅነት ወደ ከረረ ሕግ-አጥባቂነት በመቀየር ልጆቻቸውን ያውካሉ።

አባቶችና እናቶች ልጆቻቸውን ማበረታታት እንጂ ተስፋ ማስቆረጥ የለባቸውም። ወላጆች ሊያደርጓቸው ከሚችሏቸው እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ከልጆቻቸው ጋር ጊዜ ማሳለፍ ነው። በአንድ ከተማ የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው አባቶች ከትናንሽ ልጆቻቸው ጋር በቀን 37 ሰከንዶች ብቻ አብረው ያሳልፉ ነበር። ወላጆቻቸው ይህን ያህል ሥራ እየበዛባቸው፥ ከእነርሱ ጋር አብረው ለመሆን ጊዜ እንደሚመድቡ ማወቅ ለልጆች ታላቅ መጽናኛ ነው።

እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸው በሚናገሩበት ወቅት በትዕግሥት ማዳመጥ አለባቸው። ሁልጊዜም የሚሰማ ጆሮና የሚያፈቅር ልብ በአንድነት ይጓዛሉ። አንዲት ሕፃን ልጅ ለአባቷ፡- «እኔን ለመውለድ ጊዜ ወስደሃል፤ እኔን ለማዳመጥ ግን ጊዜ የለህም!» ብላለች። እንዴት ያለ ወቀሳ ነው!

ለልጆች፥ በተለይም ለክርስቲያን ልጆች ሕይወት ቀላል አይደለም። ችግሮቻቸው ለእኛ ቀላል ቢመስሉንም ለእነርሱ ከባዶች ናቸው። ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸውን በጥንቃቄ ማዳመጥ፥ ስሜቶቻቸውንና ሞንቀቶቻቸውን መካፈል፥ ከእነርሱ ጋር አብሮ መጸለይና ማበረታታት አለባቸው። ቤት በዓለም ሁሉ ከሚገኙ ስፍራዎች የላቀ ደስታ የሚታይበትና ከሁሉም የተሻለ ስፍራ መሆን አለበት!

ተስፋ የቆረጡ ልጆች ለሰይጣንና ለዓለም ተስማሚ ቀለቦች ናቸው። አንድ ልጅ ከቤት ውስጥ የራስ መተማመን ብርታት ሲያጣ ከሌላ ስፍራ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል። አንዳንድ ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸው ስብእናቸውን፥ ስጦታቸውንና የሙያ እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ያለመርዳታቸው ሁኔታ የሚያሳዝን ነው። እንዲሁም ክርስቲያን ወላጆች አንዱን ልጅ ከሌላው በማወዳደር በቤት ውስጥ አላስፈላጊ ፉክክር ሲፈጥሩ መመልከት የበለጠ የከፋ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ወላጆች እርስ በእርሳቸው ለመዋጋት ልጆችን እንደመሣሪያ ይጠቀማሉ። አባት አንደኛውን ልጅ አንድን ነገር እንዳያደርግ ይከለክሉታል። እናት ደግሞ የአባትን ትእዛዝ በመጣስ መሥራቱን እንዲቀጥል ድጋፍዋን ትሰጣለች። ግራ የተጋባው ልጅ በወላጆቹ መካከል ይዋከባል። ወዲያውም ሁለቱንም እንዴት እንደሚያስተናግዳቸው ይማራል። ውጤቱ ግን ምግባራዊና መንፈሳዊ ውድቀት ነው።

አንድ ቤተሰብ በእርግጥ እውነተኛ ክርስቲያን ከሆነ፥ የመጽናኛ ስፍራ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ቤት ውስጥ ልጅ ከጦርነት የሚጠለልበትን ስፍራ ያገኛል። ደግሞም ሌሎች ጦርነቶችን ለመዋጋትና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ የሚያስችሉትን ሽክሞች ለመያዝ ጥንካሬ ያገኛል። የሚያፈቅር ልብ፥ የሚያይ ዓይን፥ የሚሰማ ጆሮና የሚረዳ እጅ ያገኛል። መሻቶቹ ሁሉ ከቤት ስለሚሟሉለት ሌላ ስፍራ ለመሄድ አይከጅልም። በእንዲህ

ዓይነቱ ቤት ውስጥ ልጁ ክርስቶስን ለማመንና ለእርሱም ለመኖር መፈለጉ የማይቀር ነው።

ጒቶችና ባሪያዎች፡- ቅንነትና ታዛዥነት (ቆላ. 3፡22-4፡1)

በጳውሎስ ዘመን የባርነት ሥርዓት የተጠናከረ ተቋም ነበር። ቢያንስ ግማሽ የሚሆኑ ሰዎች ባሪያዎች ሲሆኑ ብዙዎቹ በሀብታሞች ቤት ውስጥ ታላላቅ ኃላፊነቶችን የሚወጡ በጣም የተማሩ ሰዎች ነበሩ። በብዙ ቤተሰቦች ውስጥ የባሪያዎችን ልጆችን ለማስተማርና ለማሠልጠን ይረዱ ነበር።

የዚያን ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን ባርነትን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ለማጥፋት ያልፈለገችው ለምን ነበር? በመጀመሪያ ደረጃ፥ ቤተ ክርስቲያን በማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ የተመሠረተውን ተቋም ለመለወጥ የሚያስችል የፖለቲካ ኃይል የሌላት የጥቂት ሰዎች ቡድን ነበረች። ጳውሎስ፥ ክርስቲያን ባሪያዎች ከቻሉ ነፃነታቸውን መጎናጸፍ እንደሚችሉ በጥንቃቄ አሞአል (1ኛ ቆሮ. 7፡21)። ዳሩ ግን ዓመፅ አልቀሰቀሰም ወይም የነበረውን ሥርዓት እንዲቀለብሱ አላስተማረም።

አንድ ነገር ግልጽ ሊሆን ይገባል፤ ይኸውም፡- የቀድሞዱቱ ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ወንጌሉን በማሰራጨት ነፍሳትን መማረክ እንጂ በማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት አልነበረም። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ፀረ-መንግሥት አቋም ወስደው ቢለዩ ኖሮ ነፍሳትን በመማረኩና ቤተ ክርስቲያን በማስፋፋቱ ረገድ መሰናክል ይገጥማቸው ነበር። ክርስቲያኖች በመንግሥትና በማኅበረሰቡ ውስጥ ታማኝነትና መልካም ሥነ-ምግባር ለማስፈን ተካፋይ መሆናቸው መልካም ቢሆንም፤ ይህ ግን ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ወንጌልን ለፍጥረታት ሁሉ የመስበኩን ሥራ በፍጹም መተካት የለበትም (ማር. 16፡15)።

የቆላስይስ መጽሐፍ ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው ሦስት መልእክቶች አንዱ እንደነበር አይዘነጋም። ሌሎቹ ሁለቱ መልእክቶች ኤፌሶንና ፊሊሞና ናቸው። ጳውሎስ ለፊሊሞና የጻፈውን አጭር መልእክት በማንበብ በባርነት ላይ ያለውን አመለካከት መረዳት ይችላሉ። ጳውሎስ ፊሊሞናን ክብላይ ባሪያውን በጭካኔ እንዲያስተዳድረው አልመከረውም። አሁንም ባሪያ ቢሆንም እንኳ እንደ ወንድም እንዲቀበለው ይጠይቃል። በመሠረቱ አናሲሞስ ይህን መልእክት ወደ ቆላስይስ ከወሰዱት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር! (ቆላ. 4፡9)።

ክርስቲያን ባሪያ (አገልጋይ) ለጌታው ሙሉ ታዛዥነት ማሳየት አለበት። ይህም ጌታን እንደማገልገል ነው። ክርስቲያን አገልጋይ አማኝ ጌታ ቢኖረው ሁለቱም በጌታ ወንድማማች በመሆናቸው፥ ያ አገልጋይ ለጌታው ማድረግ ከሚገባው መታቀብ አይገባውም ነበር። ምንም ነገር ቢሆን አገልጋዩ ክርስቲያን ስለሆነ የተሻለ ሥራ ለማከናወን መትጋት አለበት። በዚህ የልብን አንድነት በማሳየት ለጌታው ሙሉ መሰጠትን ያቀርባል። ሥራውን የሚያከናውነው ለጌታ እንደሚሠራ ሁሉ ከልብ እንጂ በታካችነት አልነበረም። «የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና» (ቆላ. 3:24)።

እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ጌቶቻቸውን በመታዘዝ ለማገልገል ያልተከፋፈሉ እና ታማኝ ልቦች ለክርስቲያን አገልጋዮች አስፈላጊዎች ነበሩ። እነዚህም ትእዛዛት የመታዘዝን አዎንታዊ ገጽታ የሚያመለክቱ ነበሩ። አገልጋዮች ከቅጣት ነጻ ለመሆን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማስደሰት መታዘዝ ነበረባቸው። ምድራዊ ጌታቸው (አሳዳሪያቸው) ምሥጋና ባይሰጣቸውም እንኳ ሽልማታቸውን ከጌታ ያገኙ ነበር። እንደዚሁም ባይታዘዙና ምድራዊ ጌታቸውም (አሳዳሪያቸውም) ባይቀጣቸው እንኳ ጌታ ያለመታዘዝን ጽዋ ያጠጣቸው ነበር። እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላምና (የሐዋ. 10:34፤ ሮሜ 2:11፤ ኤፌ. 6:9፤ ያዕ. 2:1፥ 9)።

ዛሬ በማኅበረሰባችን ውስጥ ባሪያዎች የሉንም። ዳሩ ግን እነዚህን መመሪያዎች ለማንኛውም በታማኝነት ለማከናወን ሥራ ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ክርስቲያን ሠራተኛ በሥራው ከሁሉም የላቀ ሰው ሆኖ መገኘት አለበት። ሕግጋቱንና ደንቦቹን ማክበር እንጂ መጨቃጨቅ የለበትም። አለቃውን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስንም ማገልገል አለበት። ተቆጣጣሪ ቢኖርም ባይኖርም መሥራት አለበት። አንድ ክርስቲያን እነዚህን መመሪያዎች ተከትሎ ከሠራ ምንም እንኳ አለቃው ለይቶ ላያውቀውና ላይሸልመው ቢችልም፥ ከክርስቶስ እጅ ሽልማቱን ይቀበላል።

ከበርካታ ዓመታት በፊት እጅግ ተግቶ በመሥራቱ ምክንያት ከሥራው የተፈናቀለ ጓደኛ ነበረኝ። ወደ ኮሌጅ ለመግባት ገንዘብ ያጠራቅም ነበርና ለአሠሪው በየዕለቱ መልካም ዕለታዊ ሥራ ለማከናወን ይፈልግ ነበር። ችግሩ ግን የእርሱ ታታሪነት የአንዳንድ ሰነፍ ሠራተኞችን

ስንፍና ያጋልጥ ነበርና፥ ይዋጉት ጀመር። በመጨረሻም ከእነርሱ መካከል አንዱ በሐሰት ከሰሰውና ከሥራው እንዲባረር አደረገ። ሥራውን ቢያጣም፥ በጎ ሕሊና እግዚአብሔር ሸለመው።

ውስብስብ ገጽታ በሚንጸባረቅበት በዛሬው የውድድር ዓለም፥ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን እየታዘዙ በሥራ ላይ መቆየት ወይም ዕድገት ማግኘት ለክርስቲያን አስቸጋሪ ነው። ዳሩ ግን እግዚአብሔርን እንደቀድሞው ሊታዘዝና ለሚፈልገውም ነገር እርሱን ሊተማመን ይገባል። ያልዳኑ ሠራተኞች የክርስቲያኑን ዕድገት ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል፤ ዳሩ ግን ምናልባት ይህ ለክርስቲያኑ ለመመስከርና በሕይወቱም ምስክርነቱን በመረጃ ለማስደገፍ የሚረዳው አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። ጥቂት ተጨማሪ ብሮች ከማግኘት ይልቅ የጠፉት ነፍስ መመለስ እጅግ የከበረ ዋጋ ያለው ተግባር ነው።

ባሎችና ሚስቶች እንዲሁም ወላጆችና ልጆች የጋራ የሆኑና አንዱ ለሌላው የሚደረጉ ኃላፊነቶች እንዳሏቸው ሁሉ፡- ጌቶችና አገልጋዮችም እንዲሁ ናቸው። ክርስቲያን ጌቶች አገልጋዮቻቸውን በአግባብና በአክብሮት ያስተናግዷቸው ዘንድ ጳውሎስ ይገሥጻቸዋል። ይህም ለሮማ ጌቶች አዲስ አሳብ ነበር። ምክንያቱም አገልጋዮቻቸውን እንደ «ዕቃዎች» እንጂ እንደ ሰዎች አይቆጥሯቸውም ነበር። ጌቶች በአገልጋዮቻቸው ላይ ሙሉ ተቆጣጣሪነት ስለነበራቸው ደስ ያላቸውን ሁሉ ሊያደርጉባቸው ይችሉ ነበር። ደኅንነት ያላገኙ የሮም ጌቶች አገልጋዮቻቸውን በትክክል ስለማስተናገድ አስበው አያውቁም ነበር። ለአገልጋዮች ምንም መልካም ግድረግ አይገባም ብለው ያስቡ ነበር።

ወንጌል ባርነትን ከመቅጽበት አላስወገደም፤ ዳሩ ግን በአገልጋዩና በጌታው መካከል ያለው ልዩነት ቀስ በቀስ ተለውጦአል። ማኅበራዊ መመዘኛዎችና ግፊቶች ከክርስትና አሳቦች ጋር ባይስማሙም፥ ክርስቲያን የሆነ ጌታ እነዚህን አሳቦች ልክ በቃሉ ውስጥ እንደተጻፈው መለማመድ ነበረበት። አገልጋዩን ልክ እንደሰውና በክርስቶስ ወንድም እንደሆነ አድርጎ መቀበል ነበረበት (ገላ. 3፡28)። አገልጋዩን በአግባብና በትክክል ማስተናገድ እንጂ ማስጨነቅ አልነበረበትም። እንዲሁም ክርስቲያን አገልጋይ በጌታ ነጻ ሰው ሲሆን፥ ጌታው ለክርስቶስ ባሪያ ነው (1ኛ ቆሮ. 7፡22)። በተመሳሳይ ሁኔታ ማኅበራዊና ሥጋዊ ግንኙነቶቻችን ሁልጊዜም በመንፈሳዊ ግንኙነቶቻችን መገዛት አለባቸው።

ይህንን በጣም ተግባራዊ የሆነ የቆላስይስ ክፍል ስንከልስ ሳለ፥ አማኞች እንደመሆናችን በሕይወታችን ውስጥ የሚታየውን የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይነትን እንመለከታለን። ክርስቶስ የቤታችን ራስ መሆን አለበት። ይህ በቅደም ተከተል የተሰጠው የተግሣጾች ዝርዝር የቆላ. 3፡17 ተግባራዊ ተዛምዶ ነው፡- «በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።» በዕለታዊ ግንኙነቶቻችን መመላለስ የሚገባን በእርሱ ኃይልና ሥልጣን ነው። እርሱ በሕይወታችን ውስጥ የበላይ (ቀዳሚ) ከሆነ እርስ በርሳችን እንዋደዳለን፤ እንገዛለን፤ እንታዘዛለን፤ በጌታ እርስ በርሳችን በትክክል እንቀባበላለን።

ኤፌሶን 5፡18-6፡9ን በመከለስ፥ ስናጠናው ከነበረው ክፍል ጋር ያለውን ተመሳሳይነት ብንመለከት መልካም ነው። ይህ የኤፌሶን መልእክት ክፍል በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ላይ ሲያተኩር፥ የቆላስይስ መልእክት ግን በቃሉ በመሞላት ላይ ያተኩራል። ይሁን እንጂ የሙላቱ መረጃዎች አንድ ዓይነት ናቸው። እነርሱም ደስታ፥ ምስጋና እና በመገዛት መኖር ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በቃሉ ቁጥጥር ሥር መሆን ማለት ነው።

የመንፈሱና የቃሉ ሙላት በቤት ውስጥ አስፈላጊ ነው። የቤተሰቡ አባላት በእግዚአብሔር መንፈስና በእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር ሥር ከሆኑ ደስተኞች፥ አመስጋኞችና ተገዢዎች ይሆናሉ፤ እርስ በርሳቸውም አብረው ለመኖር ብዙ ችግር አይኖርባቸውም። በመንፈሱና በቃሉ ከተሞሉ፥ ክርስቲያን አሠሪዎችና ሠራተኞች በአግባቡ እየተስተናገዱ ሥራቸውን ያከናውናሉ።

የችግሮች ሁሉ ምንጭ የልብ ሁኔታ ሲሆን፥ ልብንም ሊለውጥና ሊቆጣጠር የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

አብረዎት የሚኖሩ ሰዎች በመንፈሱና በቃሉ እንደተሞሉ ሊያረጋግጡልዎት ይችላሉን?

- 11-

ንግግር ቀላል አይደለም!

ቆላስይስ 4፡2-9

የንግግርን ኃይል ከቶ አያሳንሱ።

አንድ ዳኛ የሚያስተላልፋቸው የፍርድ ቃላት ጥቂቶች ቢሆኑም፥ የሰውየው ሕይወት መዳን ወይም መኮነን የሚወስነው በነዚሁ ጥቂት ቃላት ነው። አንድ ዶክተር የምርመራ ውጤትን የሚያስተላልፈው በጥቂት ቃላት ቢሆንም፥ ከእነዚህ ቃላት የተንሣ በሽተኛው አንድም በደስታ ይፈነድቃል፤ አለበለዚያም ተስፋ በመቁረጥ ነገር-ዓለሙን ይተወዋል። ንግግሩ የሚካሄደው በቃል ቢሆን ወይም በጽሑፍ፥ በቃላት ውስጥ ያለው ኃይል ግን ከፍተኛ ነው። «ማይን ካምፕፍ» በተባለው የአዶልፍ ሒትለር መጽሐፍ ውስጥ በተመዘገቡት ቃላት መሠረት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት 125 ሰዎች ሕይወታቸው እንዳለፈ ሰምቻለሁ።

የንግግር ኃይል ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ሲሆን፥ እግዚአብሔር በሚያዘው መንገድ ልንገለገልበት ይገባል። በያዕቆብ መልእክት ውስጥ ምላስ (አንደበት) ከልጓምና ከመቅዘፊያ፥ ከእሳትና ከመርዘኛ እንስሳ፥ ከፍሬያማ ዛፍና ከውኃ ምንጭ ጋር ተወዳድሮአል (ያዕቆብ 3)። እነዚህ ሦስት ጥንድ ጥንድ መግለጫዎች ምላስ ለመምራት፥ ለማጥፋትና ለማስደሰት የሚያስችል ኃይል እንዳለው ያስተምሩናል። ምላስ በሰውነታችን ውስጥ ትንሽ አካል ስትሆን ዳሩ ግን ለልማት ወይም ለጥፋት የሚሆኑ ታላላቅ ነገሮችን ለመፈጸም ትችላለች።

በዚህ አጭር ክፍል ውስጥ ጳውሎስ አራት አስፈላጊ የንግግር አገልግሎቶችን ዘርዝሮአል።

መጸለይ (ቆላ. 4፡2-3)

ምናልባት ጸሎትና አምልኮ የንግግርን ስጦታ በከፍተኛ ደረጃ የምንጠቀምባቸው መስኮች ናቸው። ጳውሎስ ወዳጆቹ እንዲጸልዩለት ሲጠይቅ ኃፍረት አልተሰማውም ነበር። ሐዋርያ ቢሆንም እንኳ ለራሱና ለአገልግሎቱ የጸሎት ድጋፍ ያስፈልገው ነበር። ጳውሎስን የመሰለ ታላቅ ክርስቲያን የጸሎት አስፈላጊነት ከተሰማው እንደኔና እርስዎ ላሉ ደካማ ሰዎችማ እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ እገዛ ምን ያህል ያስፈልገን ይሆን!

በእነዚህ ጥቂት ቃላት ጳውሎስ አጥጋቢና መንፈሳዊ የጸሎት ሕይወት ምን ዓይነት ባሕርያት እንዳሉት ገልጾአል።

በመጀመሪያ፥ ጸሎታችን በእምነት መሆን አለበት። «በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ» (4፡2)። ይህም ማለት «በጸሎት ሕይወታችሁ ጽኑ፤ ለጸሎት የተሰጣችሁ ሁኑ፤ አታቋርጡም» ማለት ነው። ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የጸለየችው በዚህ መንገድ ነበር (የሐዋ. 1፡14፤ 2፡46)። ብዙዎቻችን የምንጸልየው መስሎ ሲታየን ብቻ ነው። ሲሰማን ወይም ችግር ሲኖርብን ብቻ እንጸልያለን። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ግን «ሳታቋርጡ ጸልዩ» የሚል ነው (1ኛ ተሰ. 5፡17)። ይህ ማለት ቀኑን ሙሉ ጸሎቱን ስናነበንብ መዋል አለብን ማለት አይደለም። ይልቁንም ባለማቋረጥ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት ማድረግ አለብን ማለት ነው። በዚህም ጊዜ ጸሎት ልክ እንደምንተነፍሰው አየር የተለመደ ይሆናል።

ይህ ማለት እግዚአብሔር ጸሎትን ለመመለስ ፈቃደኛ ስላልሆነ በማያቋርጥ ጸሎት እርሱን «ማሰልቸት» አለብን ማለት አይደለም። እውነቱ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ለመመለስ ይደሰታል። ዳሩ ግን አንዳንድ ጊዜ እምነታችንን እና መስጠታችንን ለማሳደግ፥ እንዲሁም በትክክለኛው ጊዜ ዓላማዎቹን ለመፈጸም የጸሎት መልሶችን ያዘገያል። የእግዚአብሔር መዘግየት ሁልጊዜም እግዚአብሔር መልሱን ነፍጎናል ማለት አይደለም። ሳናቋርጥ በምንጸልይበት ጊዜ ልባችን እግዚአብሔር ለሚሰጠን መልስ ይዘጋጃል። ምላሹ ከመምጣቱ በፊት እንኳ በጸጋ እያደግን እንሄዳለን።

እንዲሁም ጸሎታችን በትጋት መሆን አለበት። በምንጸልይበት ጊዜ መትጋትና መበርታት አለብን። «ንቁና ጸልዩ» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዛት ይገኛል። ነህምያ ስለ ጸሎት ሲናገር፡- «ወደ አምላካችንም ጸለይን፤ ከእነርሱም (ከጠላቶቹ) የተነሣ በእንጻራቸው ተጠባባቂዎች በሌሊትና በቀን አደረግን» አለ (ነህ. 4፡9)። ኢየሱስም «ንቁና ጸልዩ» የሚለውን ሐረግ ተጠቅሞአል (ማር. 13፡33፤ 14፡38)፤ ጳውሎስም እንደዚሁ (ኤፌ. 6፡18)።

በመሰልቸትና በድካም የተደረገ ጸሎት ኃይል የለውም። በመሠውያው ላይ እሳት ከሌለ፥ የዕጣኑ ሽታ ወደ እግዚአብሔር መድረስ አይችልም! [መዝ. (141)፡2]። እውነተኛ ጸሎት መንፈሳዊ ብርታትና

ንቃት ይፈልጋል። ይህም የሚገኘው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። በመሰልቸት የተደረገ ጸሎት መልስ የለውም።

በተጨማሪም ጸሎታችን ከምስጋና ጋር መቅረብ አለበት (ቆላ. 4:2)። ምስጋና ለተሳካ ጸሎት ወሳኝ ነው (ፊል. 4:6)። ነገራችን ሁሉ «ስጠን-ስጠን» ማለት ከሆነና ለስጦታዎቹ እግዚአብሔርን የማናመሰግን ከሆነ ራስ-ወዳዶች ነን ማለት ነው። ለእግዚአብሔር እውነተኛ ምስጋና ማቅረብ ለጸሎታችን መነቃቂያ ከሚሆኑ መንገዶች አንዱ ነው።

ሁልጊዜም እግዚአብሔርን የምናመሰግንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። ይህንን ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክት፥ ስለ ምስጋና በሚናገርበት ክፍል ውስጥ በስፋት ተመልክተናል (1:3፥ 12፤ 2:7፤ 3:15፥ 17፤ 4:2)። ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በሚጽፍበት ወቅት እስረኛ እንደነበረ ስናስታውስ፥ ይህንን አጽንዖት የበለጠ እናደንቃለን።

በመጨረሻም፥ ጸሎታችን ዓላማ ሊኖረው ይገባል!! «ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ» (4:3)። ብዙውን ጊዜ ጸሎቶቻችን ግልጽ ያልሆኑና አጠቃላይ ናቸው። «ጌታ ሆይ፥ ወንጌላውያንን ባርክ!» እንላለን። በግልጽ ለተለዩ ጉዳዮች ብንጸልይ ምንኛ ጸሎታችን በሰመረ ነበር። ይህንንም በማድረግ እግዚአብሔር ጸሎቱን መቼ እንደመለሰው በማወቅ ልናመሰግነው በቻልን ነበር። ምናልባት በግልጽ ለይቶ ከመጸለይ ይልቅ ጠቅለል እያደረግን እንድንጸልይ የሚያደርገን እምነት ማጣታችን ሳይሆን አይቀርም።

የጸሎት ዓላማ የሰው ፈቃድ በሰማይ እንዲሆን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ላይ እንዲሆን እንደሆነ በሚገባ ተነግሮአል። ጸሎት እግዚአብሔር አንድን ነገር እንዲያደርግ ወይም እንዲሰጥ መናገር አይደለም። ጸሎት እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ የሚፈልገውን እንዲያደርግና እንዲሰጥ ማሳሰብ ነው (1ኛ ዮሐ. 5:14-15)። ቃሉን በማንበብና ከአባታችን ጋር ጎብረት በማድረግ ፈቃዱን ስለምናውቅ ያኔ ያቀደውን ነገር ከፍጻሜ እንዲያደርስ በድፍረት እንጠይቀዋለን። የደብልን ሊቀ ጳጳስ ሪቻርድ ትሬንች (1807-1886) በትክክል እንዲህ ብለዋል:- «ጸሎት የእግዚአብሔርን እምቢተኝነት ማሸነፍ ሳይሆን፥ ፈቅደኛነቱን አጥብቆ መያዝ ነው።»

በእርግጥ፥ በአንደበታችን ምንም ሳናሰማ በልባችን ብቻ መጸለይ ይቻላል (1ኛ ሳሙ. 1:13)። ይሁን እንጂ በዝምታ ብንጸልይ እንኳ

አውጥተን ባናሰማቸውም፥ ቃላትን እየተጠቀምን ነው። ቃላቶቹ ቢነገሩም ባይነገሩም እውነተኛ ጸሎት በመጀመሪያ ከልብ የሚፈልቅ መሆን አለበት።

እውነተኛ ጸሎትን ለመለማመድ፥ የጳውሎስን የእስር ቤት ጸሎቶች በምሳሌነት ያጥኑ (ፊልጵ. 1፡9-11፤ ኤፌ. 1፡15-23፥ 3፡14-21፤ ቆላ. 1፡9-12)።

ቃሉን ማወጅ (ቆላ. 4፡3-4)

ጳውሎስ የአገልግሎት በሮች እንዲከፈቱ እንጂ የወኅኒው በሮች እንዲከፈቱ አልጸለየም (1ኛ ቆሮ. 16፡9፤ የሐዋ. 14፡27)። ለጳውሎስ ነፃ ሰው ከመሆኑ ይልቅ ታማኝ አገልጋይ መሆኑ የበለጠ አስፈላጊ ነበር። ጳውሎስ በወኅኒ ቤት ሆኖ በጻፋቸው ጸሎቶች ሁሉ፥ የእርሱ ሽክም የግል ደኅንነት ወይም ቁሳቁሳዊ እርዳታ ለማግኘት ሳይሆን መንፈሳዊ ባሕርይና በረከት ለማግኘት መሆኑን ልብ ማለቱ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ጳውሎስ የታሰረው «ከክርስቶስ ምሥጢር» የተነሣ ሲሆን ይህም ከአሕዛብ ጋር የተያያዘ ነበር (ኤፌ. 3፡1-13 ይመልከቱ)። ምሥጢሩም እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ለአሕዛብ ያለውን ዓላማ የሚያካትት ነበር፤ ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይሁዶችና አሕዛብ አንድ ስለሆኑ ነው (ኤፌ. 2፡11-22)። ጳውሎስ በአይሁድ መቅደስ መታሰሩን የሚገልጸውን ታሪክ ያንብቡ (የሐዋ. 21፡18-22፡30)። አሕዛብ የሚለውን ቃል እስከተናገረበት ጊዜ ድረስ አይሁዶች ጳውሎስን በትዕግሥት ሲያዳምጡት እንደነበር ልብ ይበሉ (22፡21-22)። ጳውሎስን ለወኅኒ ያበቃው ለአሕዛብ የነበረው ሽክምና አገልግሎት ነበር።

በአማኝ አይሁዶች መካከልም እንኳ አሕዛብን ዝቅ ለማድረግ ሚዛናዊነት የጎደለው ተግባር ይከናወን ነበር (የሐዋ. 15፡1-5)። ይህ የሕግ-አክራሪ ቡድን አሕዛብ ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት የአይሁድን ሥርዓት እንዲከተሉ በሥርዓት አይሁድ እንዲሆኑ ይፈልግ ነበር! ጳውሎስና በርናባስ ለጸጋው ወንጌል ይህንን ዛቻ ፊት ለፊት የተጋፈጡ ሲሆን ጉባኤው ለእነርሱ ወስኖአል። ዳሩ ግን ሕግ-አጥባቂው ቡድን ጳውሎስንና አገልግሎቱን መቃወም ቀጠለ። መልካም የምሥራች የሆነው የክርስቶስ ምሥጢር ወደ አሕዛብ እንዲደርስ አልፈለጉም ነበር። የአይሁድን የበላይነት ለማስጠበቅ ይፈልጉ ነበር።

ጳውሎስ ለእስራት የዳረገውን ነገር ለማድረግ እግዚአብሔር እንዲረዳው መጠየቁ ምንኛ እንግዳ ነገር ነው! አገልግሎቱን የማቆም ወይም መልእክቱን የመለወጥ ፍላጎት አልነበረውም። ጆን ባንያን ሕግ ጥሰህ ሰብከሃል ተብሎ ወደ ወኅኒ በወረደ ጊዜ ሁለተኛ ላለመሰበክ ቃል ከገባ እንደሚለቀቅ ሲነገረው፡- «ዛሬ ከእስር ቤት ብወጣ፥ በእግዚአብሔር እርዳታ ነገ ወንጌሉን ስሰብክ እውላለሁ» በማለት ነበር የመለሰው።

ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ ሳለ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት ሊያካፍል ይችላል? የጳውሎስ ጉዳይ ለብዙ ሰዎች ለውይይት ይቀርብ ነበር። በተጨማሪም ላሰሩት ወታደሮችም ይሰብክ ነበር (ፊል. 1፡12-18)። በሰንሰለት ታስሮ መኖር ለጳውሎስ ምን ማለት እንደሆነ እስቲ በዓይነ-ሕሊናዎ ያስቡት! በዚህ ምስክርነት ጳውሎስ ነጻ ሰው ቢሆን ኖሮ በሮም ውስጥ ወደሚገኙ ወንጌል ሊደርስ ወደማይችልባቸው አንዳንድ ስፍራዎች ሊደርስ አይችልም ነበር። «ከቄሣር ቤተሰብ የሆኑ ቅዱሳን» እንኳ ነበሩ! (ፊል. 4፡22)።

በጸሎት የወንጌል ስርጭት ይበልጥ ኃይል ይኖረዋል። ወደ ጸጋው ዙፋን ስንቀርብና የእግዚአብሔርን በረከት ስንሻ የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ይናገረናል። የእግዚአብሔርን ቃልና ጸሎት እግዚአብሔር እራሱ ስላጣመራቸው መለየት የለብንም (የሐዋ. 6፡4)።

በለንደን የሚገኘውን የታላቁ ሰባኪ የስፐርጂንን መሰብሰቢያ አዳራሽ በመጎብኘት ለነበረ አንድ ሰው የሕንፃውን ዙሪያ ራሳቸው መጋቢ ስፐርጀን እያስጎበኙት ነበር።

በጉብኝቱም ወቅት፡- «የዚህን አገልግሎት የኃይል ምንጭ ለማየት ትፈልጋለህን?» ብለው ጠየቁት። ከዚያም «ኃይላችንን የምናገኘው ከዚህ ነው፤ እኔ በፎቁ ውስጥ ስሰብክ፥ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች በዚህ ስፍራ ይጸልያሉ» በማለት መለሱለት። ታዲያ፥ ጌታ የእስፐርጀንን ስብከት መባረኩ የሚያስደንቅ ነውን?

እርስዎም የቤተ ክርስቲያን አባል እንደመሆንዎ መጠን፥ ለቤተ ክርስቲያንዎ መጋቢ በመጸለይ በሰብክት አገልግሎቱ ሊረዱት ይችላሉ። ለመጋቢዎ፡- «ማድረግ የምችለው ትንሽ ነገር ቢኖር ለአንተ መጸለይ ነው» ሊሉት አይገባም፤ ምክንያቱም ከሁሉም የላቀውና ታላቁ ነገር በጸሎት መርዳትዎ ነውና! መጋቢዎ ቃሉን ሲያዘጋጅ፥ ሲያጠናና

ሲያሰላስል መንፈስ ቅዱስ ወደ ጠለቀ የቃሉ መገለጽ እንዲመራው ይጸልዩለት። መጋቢዎ በሚሰብከው ቃል እንዲኖርና በግል ሕይወቱም ቃሉ በእውነት እንዲሠራ ይጸልዩለት። ቃሉን በሚሰብክበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የመገለጽ ነጻነት እንዲሰጠውና ቃሉም ወደ ሰዎች ልብና አእምሮ ዘልቆ እንዲገባ ይጸልዩለት። ለሌሎች የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችም ደግሞ መጸለይ ጠቃሚ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል መናገር ትልቅ ዕድልና ከፍተኛም ኃላፊነት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለማካፈል የግድ ለዚህ አገልግሎት የተመደበ ሰባኪ ወይም ወንጌላዊ መሆን አያስፈልግም። በዕለታዊ ውይይቶች ውስጥ እንኳ የቃሉን ዘር በሰዎች ልብ መዝራትና እግዚአብሔር ያንን ዘር በማጠጣት ፍሬ እንዲያፈራ እንዲያደርገው መጸለይ ይቻላል።

ለጠፉት መመስከር (ቆላ. 4፡5-6)

«በውጭ ባሉቱ» የሚለው ቃል ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውጭ ያሉትን ያመለክታል። ኢየሱስ ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱና በውጭ ባሉት መካከል ልዩነት አድርጓል (ማር. 4፡11)፤ ጳውሎስም ይህንኑ አድርጓል (1ኛ ቆሮ. 5፡12-13)። ዳግመኛ የተወለድን ሁላችን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስለሆንንና የእርሱን ሕይወት ስለምንካፈል በመንፈሳዊ ሁኔታ «የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች» ነን።

ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን መንፈሳዊ የበላይነት ሊሰማን አይገባም። በአካባቢያችን ለጠፉት የመመስከርና ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የመመለስ ኃላፊነት አለብን። ይህንን ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ በጥበብ የመመላለስ ኃላፊነት አለብን (ቆላ. 4፡5)። መመላለስ የሚያመለክተው በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የምናንጸባርቀውን ባሕርይ ነው። ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውጭ የሆኑ ግለትም ያልዳኑ ሰዎች እኛን ይመለከቱናል፤ በእኛ ላይም ከፍተኛ አትኩሮት ያደርጋሉ። በመሆኑም፥ በሕይወታችን ውስጥ ምስክርነታችንን የሚያጎድፍ አንዳች ነገር ሊኖር አይገባም።

ስለ ዶክተር ዊል ኤች. ሑተን ብዙ ጊዜ የሚነገር አንድ ታሪክ አለ፤ አርሳቸው በኒው ዮርክ ከተማ የካልቪሪ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሲሆኑ፥ በኋላም እስከ 1946 ዓ.ም. በሞት እስከተለዩበት ድረስ የሺካጎ ሙዲ የ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ፕሬዝዴንት በመሆን ያገለገሉ ሰው ነበሩ። እናም ዶክተር ሑተን በአትላንታ ውስጥ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን

መጋቢ በሆኑበት ወቅት፥ በዚያች ከተማ የሚኖር አንድ ሰው ዶክተር ሉተንን እየተከታተለ በባሕርያቸው ላይ ዘገባ የሚያቀርብ ሰው በምሥጢር ቀጠረ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላም ሲከታተላቸው የቆየው ሰው ወደ ቀጣሪው ተመልሶ የዶክተር ሉተንን ሕይወት ከስብከታቸው ጋር እንደሚስማማ ገለጸ። የዶክተር ሉተን ሕይወት ከስብከታቸው ጋር የተጣጣመ ነበር። ከዚህም የተነሣ ያ ሰው ክርስቲያን ሆነ።

«በጥበብ መመላለስ» ማለት ምን ማለት ነው? አንደኛው፥ ወንጌሉን ለማካፈል አስቸጋሪ የሚሆን ነገር ላለማድረግ ወይም ላለመናገር እንጠነቀቃለን ማለት ነው። እንዲሁም ደግሞ ለምስክርነት እግዚአብሔር በሚሰጠን ዕድል ለመጠቀም ንቁዎች መሆን አለብን ማለት ነው። «ዘመኑን እየዋጃችሁ» ማለት በጊዜው ያለውን ዕድል መጠቀም ማለት ነው (ኤፌ. 5፡16)። ቃሉ የንግድ ቋንቋ ሲሆን አንድን ሰው በሚመለከትበት ጊዜ እንደታማኝ ሠራተኛ አጋጣሚውን የሚጠቀምበትን ክርስቲያን ያመለክታል። ነጋዴ አንድ የንግድ ስምምነት ባገኘ ቁጥር ስምምነቱን እንደሚፈጽም ሁሉ፥ ክርስቲያንም ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ በተገኘው አጋጣሚ ይጠቀማል።

በጥበብ መመላለስ በተጨማሪም ሥራችንን ማከናወንን፥ ዕዳችንን መክፈልንና ቃላችንን መጠበቅን ያጠቃልላል። «በውጭ ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ» ይሁን (1ኛ ተሰ. 4፡12)። አንድ ጓደኛዬ ለቤተ ክርስቲያኑ ዕቃዎችን ለመግዛት ወደ መደብር ይሄዳል። ዕቃ ሻጩም «እገሌ የቤተ ክርሲትያናችሁ አባል ነውን?» በማለት ጠየቀው። ጓደኛዬም የቤተ ክርስቲያናቸው አባል እንደሆነ ገለጹለት። ሻጩም ያ የቤተ ክርስቲያን አባል ምን ያህል ገንዘብ ከመደብሩ እንደተበደረና የተበደረውን ገንዘብ መልሶ ለመቀበል ምን ያህል ችግር እንደገጠመው ይነግረው ጀመር። ጓደኛዬ ለዚያ ሰው ለመመስከር ቢፈልግ ኖሮ፥ ምናልባት ውጤቱ ከንቱ ሳይሆን አይቀርም ነበር።

በአጠቃላይ ክርስቲያኖችና በተለይ ደግሞ ክርስቲያን መሪዎች «በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባዋል» (1ኛ ጢሞ. 3፡7)። የቤተ ክርስቲያን አባላት አዲስ መጋቢ በሚመርጡበት ወቅት፥ ከጎረቤቶቹና ከሚያውቁት ነጋዴዎች ማንነቱን ማጣራት አለባቸው። ምንም እንኳ ያልዳኑ ሰዎች በመንፈሳዊ ዕውርነት ውስጥ ቢሆኑም (2ኛ ቆሮ. 4፡3-4)፥ የዚህን ዓለም ነገሮች በተመለከተ ከፍተኛ

የመመርመር ችሎታ አላቸው (ሉቃስ 16፡8)። ዕዳውን ያልከፈለና ላልዳኑ ሰዎች መጥፎ ምስክርነት ያለውን ሰው ለመጋቢነት አገልግሎት መጋበዝ እንዳለመታደል የሚቆጠር አሳዛኝ ነገር ነው።

በማያምኑ ሰዎች ፊት በጥበብና በጥንቃቄ መመላለስ ብቻ በቂ አይደለም። በተጨማሪም ከእነርሱ ጋር መነጋገርና የወንጌሉን መልእክት ለእነርሱ ማስተላለፍ አለብን፤ ዳሩ ግን ወደ ክርስቶስ እንዲያመለክትና ጌታን እንዲያስከብር ንግግራችንም በጸጋ ቁጥጥር ሥር መዋሉን ማረጋገጥ አለብን። ይህም ማለት በንግግር የሚገለጠው በልብ የሞላው ስለሆነ፥ ጸጋ ከልባችን መኖር አለበት ማለት ነው (ቆላ. 3፡16)። ጸጋ በልባችንና በአንደበታችን ካለ፥ ታማኝ ምስክሮች እንጂ ፈራጆች ወይም አጉል ተከራካሪዎች አንሆንም!

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በንግግሩ ሁሉ ጸጋ ነበረው። «ከአፉም ከሚወጣው ከጸጋው ቃል የተነሣ እየተደነቁ፡- ...» (ሉቃስ 4፡22)። በመዝሙር 45 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠቀሱት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ፡- «ሞገስ (ጸጋ) በከንፈሮችህ ፈሰሰ» (ቁ. 2) የሚል ይገኝበታል። ጌታችን ከኃጢአት ጋር በሚጋፈጥበትም ጊዜ ሳይቀር ጸጋን የተሞሉ ቃላት ይናገር ነበር።

ንግግራችን «ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ» (ኤፌ. 4፡29) ይገባል። ዳሩ ግን በልባችንና በአንደበታችን ጸጋ ከሌለን፥ ያንን ለማድረግ አይቻልም። እግዚአብሔር «እውነትን በፍቅር» እንድንናገር ነው የሚፈልገው (ኤፌ. 4፡15)።

ጳውሎስ «በጨው እንደተቀመመ» (ቆላ. 4፡6) የሚለውን አባባል ለምን ተጠቀመ? በዚያን ጊዜ ጨው ምግብን ለረዥም ጊዜ ለማቆየትና እንዲሁም ለቅመምነት ያገለግል ነበር። ንጹሕና በትክክል የተቀመመ መሆኑን ለማረጋገጥ በንግግራችን ውስጥ ጨው መጨመር አለብን። «ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ» (ኤፌ. 4፡29) እንዳለ ሁሉ ንግግራችን ንጹሕ መሆን አለበት።

እንዲሁም ጨው መሥዋዕቶች ውስጥ ይጨመር ነበር (ዘሌ. 2፡13)። ምናልባት ጳውሎስ የሚለው የምስጋና ቃሎቻችን መንፈሳዊ መሥዋዕቶች ስለሆኑ፥ ቃሎቻችን ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ መሥዋዕቶች አድርገን መቁጠር አለብን ነው (ዕብ. 13፡15)። ቃሎቻችን ለእግዚአብሔር እንደሚቀርቡ መሥዋዕቶች የሚታዩ መሆናቸውን ብናስተውል ትክክለኛ

ነገሮችን በትክክለኛ ሁኔታ ለመናገር እገዛ እንደሚያደርግልን ጥርጥር የለውም።

ክርስቲያንን በተለይም በማያምኑ ሰዎች ፊት አሳፋሪ ነገር ሲናገር እጅግ የሚያሳዝን ነው። «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን» (1ኛ ጴጥ. 3፡15)። የዋህነት የመሰሪነት ተቃራኒ ሲሆን፥ ፍርሃት የአጉል ድፍረትና ጋጠ-ወጥነት ተቃራኒ ነው። በክርስቲያን ንግግር ውስጥ ሁሉንም አውቃለሁ ለሚል አመለካከት ስፍራ የለም። ማወላወል የሌለበት ጠንካራ እምነት ሊኖረን ቢገባም፥ በጸጋ የተሞላ የፍቅር መንፈስ ማዳበር እንዳለብን መዘንጋት የለብንም።

የክርስቲያኖች ንግግርና ኑሮ የሚስማማ መሆን አለበት። ከግድ የለሽነት ሕይወት በበለጠ ምስክርነትን የሚያግድ ነገር የለም። ባሕርይ፥ ጸባይና ንግግር በሙሉ በጋራ ተስማምተው ሲሠሩ ኃይል ላለው ምስክርነት በሮችን ይከፍታሉ።

ሽክምን መካፈል (ቆላ. 4፡7-9)

ጳውሎስ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ስለራሱ ሁኔታ አልተናገረም፤ ነገር ግን ስላለበት ሁኔታ ለቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን እንዲያካፍሉ ቲኪቆስና አናሲሞስ ለተባሉ ሁለት መንፈሳዊ ወንድሞች ተወላቸው። ይህም ሌላው የንግግር አገልግሎት ነው። መሻቶቻችንና ሽክሞቻችንን ከሌሎች ጋር ልንካፈል እንችላለን፤ እነርሱም በማጽናናት ይረዱናል።

ጳውሎስ ከኤፌሶን ሲወጣ፥ ሌሎች ሰባት አማኞች ሸኝተውት ነበር፤ ከነዚህም መካከል አንዱ ቲኪቆስ ነበር (የሐዋ. 20፡4)። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ ከአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት፥ በይሁዳ ለሚገኙ የአይሁድ ቅዱሳን ችግረኞች ቅዱሳን የፍቅር ስጦታ እንዲያደርጉ ይረዱ ነበር (1ኛ ቆሮ. 16፡1፤ 2ኛ ቆሮ. 8-9)። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው 2ኛ መልእክት የሚያመለክተው ሁለት ወንድሞች ቲኪቆስና ጥሮፊሞስን ሳይሆን አይቀርም (2ኛ ቆሮ. 8፡19-24 ይመልከቱ)።

ቲኪቆስ የጳውሎስን የሮም እስራት የተካፈለ ሲሆን፥ ጳውሎስን በብዙ መንገዶች እንደረዳ የማያጠራጥር ነው። ጳውሎስ፥ ቲኪቆስና አናሲሞስ ለኤፌሶን (ኤፌ. 6፡21) እና ለቆላስይስ (ቆላ. 4፡7-9) መልእክቶችን እንዲያደርሱ መረጣቸው። በተጨማሪም ለፊሊሞና

የተጻፈውን የግል ደብዳቤ አድርሰዋል። ጳውሎስ ቲኪቆስን በሮም የነበረበትን ሁኔታ ለቆላስይስ ሰዎች እንዲናገር አዘዘው።

ጳውሎስ ስለ ቲኪቆስ የሰጠው ገለጻ በእውነት ምን ያህል ግሩም ክርስቲያን እንደነበረ ያስረዳል። ምንም እንኳ ሁኔታው አስቸጋሪ ቢሆንም ከጳውሎስ ጋር ለመሰንበት ፈቃደኛ የሆነና የተወደደ ወንድም ነበር። ሁኔታዎች ሁሉ በአንተ ላይ የተነሡ በሚመስልበት ወቅት ከጎን የሚቆም ክርስቲያን ወንድም ማግኘት ምንኛ የሚያጽናና ነገር ነው!

እንደዚሁም ቲኪቆስ ታማኝ አገልጋይ ነበር። ፍቅሩ በተግባር ተገልጾአል። ጳውሎስን አገልግሎአል፤ ጳውሎስንም በመወከል አገልግሎአል። አንድ ሰው እንዳስቀመጠው በዓለም ውስጥ ከሁሉም የሚልቀው ነገር ለሌሎች ድጋፍ የመሆን ችሎታ ነው። ይህም እውነት ነው። ጳውሎስ ለሥራው መጠናቀቅ በቲኪቆስ ላይ ለመደገፍ ችሎ ነበር።

በተጨማሪም ቲኪቆስ ከጳውሎስ ጋር አብሮ የሚሠራ አገልጋይ ነበር። ምንም እንኳ እርሱ ራሱ ሐዋርያ ባይሆንም ጳውሎስን በሐዋርያዊ አገልግሎቱ ይረዳው ነበር። ጳውሎስና ቲኪቆስ በጌታ አገልግሎት አብረው ሠርተዋል። በኋላም ጳውሎስ ቲኪቆስን ወደ ቀርጤስ (ቲቶ 3፡12) ከዚያም ወደ ኤፌሶን (2ኛ ጢሞ. 4፡12) ልኮታል።

ከእስረኛው ጳውሎስ ጋር መተባበር ለቲኪቆስ ቀላል አልነበረም፤ ምክንያቱም ጳውሎስ በርካታ ጠላቶች ነበሩት። እንዲሁም ደግሞ ጳውሎስን በተለያዩ አገልግሎቶች በመርዳት ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወሩም ቀላል ነገር አልነበረም። በመሆኑም ቲኪቆስ የመረጠው ቀላሉን መንገድ ሳይሆን፥ መሆን የሚገባውንና ትክክለኛውን መንገድ ነበር። ዛሬም ለአብያተ ክርስቲያናት እንደ ቲኪቆስ ያሉ ብዙ ምእመናን ያስፈልጉናል!

ጳውሎስ ከቆላስይስ የመጣውን አናሲሞስንም «ከእናንተ አንዱ» በማለት ጠቅሶታል። እርሱም ከጌታው ከፊሊሞና ኮብልሎ የሄደ ሲሆን፥ ጳውሎስ በሮም ከሰጠው አገልግሎት የተነሣ ወደ ክርስቶስ የተመለሰ ሰው ነበር። ጳውሎስም ፊሊሞና ይቅር ብሎ እንዲቀበለው ከሚጠይቅ ደብዳቤ ጋር አናሲሞስን መልሶ ወደ ጌታው ይልከዋል። እዚህ ላይ፥ ጳውሎስ አናሲሞስን ታማኝ እና የተወደደ ብሎ መጥራቱ አስገራሚ ነው። አናሲሞስ አዲስ አማኝ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ እውነተኛነቱን ለጳውሎስ አረጋግጦ ነበር ማለት ነው።

እነዚህ ሁለት ሰዎች የሚፈጽሟቸው ጣምራ ተግባራት ነበሩ፤ ይህም፡- የቆላስይስ ክርስቲያኖችን ማጽናናትና የጳውሎስን ሁኔታ መግለጽ ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዚህ ዓይነት መንገድ መረጃ መለዋወጣቸው ስሕተት ይሆን? በእርግጥ አይደለም! ጳውሎስ ገንዘብ እየለመነ አልነበረም፤ ወይም ደግሞ እንዲያዝኑለት የሚጠብቅ አልነበረም። የፈለገው ነገር ቢኖር የቆላስይስ ቅዱሳን የነበረበትን ሁኔታ ተረድተው እንዲጸልዩለት ብቻ ነበር። አንዳንድ ክርስቲያን አገልጋዮች እርዳታ ለማግኘት ሲሉ አግባብነት በጎደለው መንገድ በሁኔታዎች «እንደሚጠቀሙ» ቢታወቅም ጳውሎስ ግን እዚህ ዓይነት ሰው አልነበረም። እርሱ የፈለገው ነገር ቢኖር በቆላስይስ የነበሩ ወዳጆቹ እውነተኛውን ነገር ተረድተው በጸሎት እንዲደግፉት ብቻ ነበር።

በቤታችን ውስጥ ከተለያዩ ወንጌላውያን የጸሎት ጥያቄ ያለባቸውን ደብዳቤዎች እንቀበላለን። ደብዳቤዎቹን በማንበብ ስለ ችግራቸውና ስለ ሸክማቸው ብዙ የምንረዳው ነገር አለ። በራሴ የግል የጸሎት ጊዜ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ዝርዝር ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ የሚያስታውሱኝን ብዙ የጸሎት ማስታወሻዎች እጠቀማለሁ። ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለሌሎች ለመጸለይ እንዲያስችሉኝ እውነቶችን ለማወቅ እሻለሁ። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ጸሎቶችን እንዴት እንደመለሰ ስረዳ ደስ ይለኛል፤ ይህም እምነቴን ያጠናክረዋል።

አራቱ አስደናቂ የንግግር አገልግሎቶች፡- መጸለይ፥ ቃሉን ማወጅ፥ መመስከርና የሌሎችን ሸክም መካፈል ናቸው። ምላሳችንን ለሐሜት፥ ለክፉ ትችት እና ለሌሎችም የኃጢአት ዓላማዎች ከማዋል ይልቅ በእነዚህ አገልግሎቶች መሳተፍ ምንኛ ደስ ይላል!

እስኪ ከዘማሪው ዳዊት ጋር፡- «አቤቱ፥ ለአፌ ጠባቂ አኑር፥ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ» [መዝ. (141)፡3] እያልን እንጸልይ።

- 12 -

ወዳጆች፥ ሮማውያን፥ የአገሬው ሰዎች

ቆላ. 4፡10-18

ጳውሎስ ነፍሳትን ወደ ጌታ የሚያመጣ ብቻ ሳይሆን ወዳጅ ማፍራትንም የሚያውቅ ሰው ነበር። በአቆጣጠር ላይ ካልተሳሳትሁ በሰቱቀር፥ በሐዋርያት ሥራና በመልእክቶቹ ውስጥ ከእርሱ ጋር ጎብረት ያደርጉ የነበሩ (በስም የተጠቀሱና ያልተጠቀሱ) ከ100 የሚበልጡ የተለያዩ ክርስቲያኖች አሉ። በሮሜ 16 ውስጥ ብቻ 26 የተለያዩ ወዳጆችን ዘርዝሮአል።

በጳውሎስ ዘመን፥ እያንዳንዱን ደብዳቤ በግል ሰላምታ መደምደም የተለመደ ነበር። ወዳጆች እስከዚህም እርስ በእርሳቸው አይጠያየቁም ነበር፤ የደብዳቤ አገልግሎትም በጣም ዝግምተኛና ውስን ነበር። በእርግጥ የጳውሎስ ደብዳቤዎች ከማኅበራዊ ጉዳይ የላቁ ነበሩ። ደብዳቤዎቹም ለወዳጆቹ የነበረውን እውነተኛ መንፈሳዊ ሸክም ይገልጹ ነበር። በዚህ የማጠቃለያ ክፍል ጳውሎስ በአገልግሎት ከሚተባበሩት ስድስት ሰዎች የግል ሰላምታዎችን የነበሩ ለቆላስይስ ሰዎች ይልካል፤ ይኸውም፡- ከአርስጥሮኮስ፥ ከማርቆስ ዮሐንስ፥ ከኢዮስጦስ ኢያሱ (ሁላቸውም አይሁዶች የሆኑ)፥ ከኤጳፍራ፥ ከሉቃስና ከዴማስ (አሕዛብ የሆኑ) ነበር። ከዚያም በላይ ጳውሎስ ለሁለት የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ልዩ ሰላምታ ይጨምራል። ለአንደኛውም መጋቢ ልዩ ቃል ይልክለታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የእነዚህን የስም ዝርዝሮች ስናነብ ብዙም ላይሰማን ይችላል። ዳሩ ግን ከመድረኩ በስቲያ መለስ ብለን ከጳውሎስ ጋር በሚያገለግሉበት ጊዜ፥ የእነዚህ ሰዎች ሕይወት ምን እንደሚመስል ስንመለከት፥ የስም ዝርዝሩ በጣም አስደናቂ ትርጉም ይሰጠናል። እነዚህን ሰዎች በሦስት ምድቦች ከፍለን ልንመለከታቸው እንችላለን።

ከጳውሎስ ጋር የነበሩ ሰዎች (ቆላ. 4፡10-11፥ 14)

ይህ ሦስት አይሁዳውያን (አርስጥሮኮስ፥ ማርቆስ ዮሐንስ፥ ኢዮስጦስ ኢያሱ) እና አንድ አሕዛብ (ሉቃስ) የሚገኙበት ቡድን ነበር። ሁላቸውም ሐዋርያው ጳውሎስ በተቸገረበት ወሳኝ ወቅት በመድረስ ታማኝነታቸውን ያስመሰከሩ ነበሩ። እነዚህ ከእርሱ ጋር አብረው የቆዩ ሰዎች ናቸው።

አርስጥሮኮስ (ቆላ. 4፡10) ከጳውሎስ ጋር አብሮ እንደታሰረና አብሮ እንዳገለገለ ተገልጸአል (ቁ. 11)። አርስጥሮኮስ ከመቄዶንያ የመጣ ሲሆን ከጳውሎስ የጉዞ ተባባሪዎች አንዱ ነበር (የሐዋ. 19፡29)። በመጀመሪያ ከተሰሎንቄ የመጣ ሲሆን (የሐዋ. 20፡4)፥ በኤፌሶን በተነሣው ውካታ ሕይወቱን በፈቃዱ ለአደጋ አጋልጦ ነበር (የሐዋ. 19፡28-41)። እንዲሁም ከጳውሎስ ጋር ወደ ሮም ተጉዞአል (የሐዋ. 27፡2)። ይህም ማለት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 27 ውስጥ እጅግ ሥዕላዊ በሆነ ገለጻ የጻፈውን ማዕበልና የመርከብ መሰበር ምክንያት የደረሰውንም ችግር አብሮ ተካፍሎአል ማለት ነው።

ሁኔታው ምንም ዓይነት ቢሆን አርስጥሮኮስ ከጳውሎስ ጋር አብሮ ነበር፤ በኤፌሶን በውካታ ውስጥ፥ በባሕር ላይ ጉዞ፥ በማዕበልና በእስራትም ቢሆን አልተለየውም ነበር። አርስጥሮኮስ የሮም የሕግ እስረኛ የነበረ አይመስልም። «ከእኔ ጋር የታሰረ» የሚለው አርስጥሮኮስ ሐዋርያውን ለመርዳትና ለማጽናናት እስራቱን እንደተጋራ የሚያመለክት ይሆናል። አርስጥሮኮስ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለወንጌሉ በፈቃዱ የታሰረ ሰው ነበር።

ምናልባት የጓደኞቹ እርዳታ ባይታከልበት ኖሮ ጳውሎስ የፈጸማቸውን ተግባራት ሁሉ መፈጸም ባልቻለም ነበር። አርስጥሮኮስ ከጳውሎስ ታላላቅ አጋሮች አንዱ በመሆን ሠርቶአል። ቀለል ያለ አማራጭ አልፈለገም። ሁኔታው ጫን እያለ ሲመጣም «እግሬ-አውጪኝ» አላለም። ከጳውሎስ ጋር ተሰቃይቶ አገልግሎአል።

ማርቆስ ዮሐንስ (ቆላ. 4፡10) ሁለተኛውን ወንጌል የጻፈ ሲሆን፥በቀድሞው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቶአል። እርሱም የኢየሩሳሌም ተወላጅ የሆነ አይሁዳዊ ነበር። እናቱ ማርያም ቤቷን ለአማኞች መሰብሰቢያ እንዲሆን ሰጥታ ነበር (የሐዋ. 12፡12)። ማርቆስ ዮሐንስ በመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጉዞው ከጳውሎስ ጋር የመጣው (የሐዋ. 13፡1-3) የበርናባስ ወንድም ልጅ ነበር። ማርቆስ በክርስቶስ ለማመን የበቃው በጴጥሮስ አገልግሎት ሳይሆን አይቀርም (1ኛ ጴጥ. 5፡13)።

ጳውሎስና በርናባስ ለሐዋርያዊ አገልግሎት ሲወጡ ማርቆስን ረዳታቸው አድርገው ወስደውት ነበር። ምናልባት ለጉዞ ስለሚያስፈልጉ ነገሮች በማዘጋጀትና በማሟላት ወዘተ. ሳያግዛቸው አልቀረም። ዳሩ ግን

ሁኔታው አስቸጋሪ ሲሆን ሰባኪዎቹን ተሰናብቶ ወደ ቤቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (የሐዋ. 13፡5-13)።

ማርቆስ ዮሐንስ ለምን ጉዞውን እንዳቋረጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም። ምናልባት ወደ አደገኛ ስፍራ ሊሄዱ ስለተዘጋጁ ፍርሃት ተሰምቶት ይሆናል። ምናልባት ጳውሎስ የሐዋርያዊ ተልእኮውን በመሪነት መያዙና ዘመዱ የሆነውን በርናባስን መተካቱ ቅር አሰኝቶትም ይሆናል። ወይም ጳውሎስ ለአሕዛቦች የሚያበረክተውን አገልግሎት አልወደደውም ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

በኋላ ጳውሎስና በርናባስ ሁለተኛውን ሐዋርያዊ ጉዞ ለማድረግ በተዘጋጁበት ወቅት ጳውሎስ፥ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ከእነርሱ ጋር እንዳይሄድ ከለከለው (የሐዋ. 15፡36-41)። ጳውሎስ በዚህ ወጣት ላይ ባደረገው ግምገማ ተሳስቶ ይሆን? ምናልባት ሊሆን ይችላል፤ ዳሩ ግን ማርቆስ ዮሐንስ በቀደመው አገልግሎት ከመንገድ ተመልሶ ስለ ነበር ጳውሎስ ለወሰደው ጥንቃቄ ልንወቅሰው አንችልም። ጳውሎስ የጠፉትን ነፍሳት ለክርስቶስ ለመማረክ እየጣረ ነበር እንጂ አስደላች የሽርሽር ጉዞ እያደረገ አልነበረም። ማንኛውም ዓይነት አደጋ ወይም ችግር ጳውሎስን ለጠፉ ኃጢአተኞች ወንጌሉን ከማድረስ ሊገታው አይችልም ነበር። ማርቆስ ዮሐንስ በጳውሎስና በርናባስ መካከል ክፍፍል መፍጠሩ እጅግ የከፋ ነገር ነበር። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ማርቆስን ይቅር እንዳለውና፡- «ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛል ይዘኸው ከአንተ ጋር አምጣው» (2ኛ ጢሞ. 4፡11) በማለት እንደጻፈ ማስታወስ አለብን።

ማርቆስ፥ ቲቶ እና ጢሞቴዎስ ለሐዋርያው ጳውሎስ ልዩ ተወካዮች ሆነው ያገለገሉ ወጣቶች ነበሩ። ችግሮች ወደ ነበሩባቸው አብያተ ክርስቲያናት ይልካቸውና ችግሮቹን ለማቃለል አስተዋጽኦ እንዳላቸውም ይተማመንባቸው ነበር። ማርቆስ ዮሐንስ በእግዚአብሔር ጸጋ የመጀመሪያ ውድቀቱን በማሸነፍ ጠቃሚ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመሆን በቅቶአል። እንዲያውም የማርቆስን ወንጌል ለመጻፍ የተመረጠ ሰው ነበር!

እግዚአብሔርን ለማገልገል የተነሣበት የመጀመሪያው እርምጃ ላልተሳካለት ሰው ሁሉ ማርቆስ ትልቅ መጽናኛ ነው። ቁጭ ብሎ ሲተክዝ አልኖረም። ዳግም ወደ አገልግሎቱ በመሰማራት ለጌታና ለሐዋርያው ጳውሎስ ታማኝነቱን አሳይቷል። ማርቆስ ከጳውሎስ ጋር ከቆዩት ሰዎች አንዱ ነበር።

እዚህ ላይ እንደበርናባስ ወጣቱን ክርስቲያን ሁሉ በጌታ ማበረታታት መልካም እንደሆነ ልጨምር እሻለሁ። ማርቆስ፥ ምናልባት በርናባስ ባይረዳው ኖሮ ብቻውን አሁን የደረሰበት ስፍራ ሊደርስ ይችል ይሆናል፤ እኔ ግን እጠራጠራለሁ። እግዚአብሔር ማርቆስን እንዲያጽናና፥ ወደ አገልግሎትም ዳግም እንዲመልሰው በርናባስን ተጠቀመ። በርናባስ ሰሙና ምግባሩ የተጣጣመለት ሰው ነበር። በርናባስ ማለት «የመጽናናት ልጅ» ማለት ነው (የሐዋ. 4፡36)።

ኢዩስጦስ የተባለ ኢያሱ (ቆላ. 4፡11) ከጳውሎስ ጋር ያገለገለ አይሁዳዊ አማኝ ሲሆን፥ ስለ እርሱ የምናውቀው ነገር የለም። ኢያሱ (ኢየሱስ) የሚለው የተለመደ የአይሁድ ስም ሲሆን፥ በተጨማሪም እንደ ኢዮስጦስ በሚል የሮማውያን ስም መጠራት ለአይሁዶች አዲስ አልነበረም። ኢየሱስ ኢዮስጦስ የተባለ እግዚአብሔርን በታማኝነት ማገልገሉ ሥራቸው ለዓለም ሁሉ ያልታወቀላቸውን አማኞች ይወክላል። የምናውቀው ነገር ቢኖር ከጳውሎስ ጋር አብሮ የሚያገለግልና ለጳውሎስ መጽናኛ የሆነ ሰው እንደነበር ነው። ይሁን እንጂ ጌታ የዚህን ሰው የታማኝነት ሕይወትና አገልግሎት መዝግቦ አስቀምጦአል። በዚሁ መሠረት ሽልማቱን ያጎናጽፈዋል።

ሉቃስ (ቆላ. 4፡14) በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ሰው ነበር። ከአሕዛብ ወገን ቢሆንም፥ የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራን እንዲጽፍ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነበር። ምናልባት የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ ለመጻፍ ብቸኛ አሕዛብ ሳይሆን አይቀርም። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በሙሉ ከአይሁድ ወገን ነበሩ። በተጨማሪም ሉቃስ ሐኪም ሲሆን በጳውሎስ እጅግ የተወደደ ሰው ነበር። የሕክምና ሙያ በግሪኮች ይወደድ ስለነበር ሐኪሞች ከፍተኛ ማኅበራዊ ተፈላጊነት ነበራቸው። ምንም እንኳ ጳውሎስ ሰዎችን የመፈወስ ኃይል ቢኖረውም ከሐኪም ጋር ተጉዞአል!

ሉቃስ ከጳውሎስና ከቡድኑ ጋር የተቀላቀለው በጢሮአዳ ነበር። (በሐዋ. 16፡10 በነጠላ ስም ሳይሆን፥ በብዙ ቁጥር እንደተጻፈ ልብ በል።) ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘ ሲሆን (የሐዋ. 20፡5-19) ወደ ሮምም ሲጓዝ አብሮት ነበር (የሐዋ. 27፡1-28፡16)። በዚያ ቀውጢ ወቅት የሉቃስ መገኘትና ሙያው ለጳውሎስ ከፍተኛ መጽናኛ እንደነበር አያጠራጥርም። እግዚአብሔር በተአምራታዊ መንገድ

ብርታትና ፈውስ ሊያመጣ ቢችልም እንደ ሕክምና ባሉ በተፈጥሮ የተሰጡትንም ነገሮች ይጠቀማል። እኔና ባለቤቴ በአፍሪካ ለሚሠሩ ወንጌላውያን ባገለገልንበት ወቅት፥ የሕክምና ዶክተር የሆነው ወዳጃችንና ባለቤቱ አብረውን ተጉዘው ነበር። እነዚህ ሰዎች ላደረጉልን እርዳታ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቅርበንላቸዋል።

ሉቃስ እስከመጨረሻው ድረስ ከጳውሎስ ጋር ቆይቶአል (2ኛ ጢሞ. 4፡11 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ሉቃስን የሐዋርያትን ሥራ እንዲጽፍና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈው የቀድሞዱቱን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም የጳውሎስን አገልግሎት እንዲያስተላልፍልን መርጦታል። ሉቃስ ሙያውን በእግዚአብሔር አገልግሎት ለሚጠቀምና ጌታ ወደሚልከው ሰፍራ ሁሉ ለመሄድ ራሱን ለሰጠ ሰው ጉልህ ምሳሌ ነው። ሉቃስ የተወደደ ክርስቲያን፥ የሰለጠነ ሐኪም፥ ጥሩ ጓደኛና ጥንቁቅ የታሪክ ጸሐፊና እነዚህን ሁሉም በግሩም ሁኔታ አንድ ላይ አጠቃልሎ የያዘ ሰው ነበር።

የጸለየው ወንድም (ቆላ. 4፡12-13)

ይህን መጽሐፍ ማጥናት ስንጀምር ኤጳፍራን ተመልክተናል። ምክንያቱም የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው እርሱ ነበር (ቆላ. 1፡7-8)። በኤፌሶን ከነበረው ከጳውሎስ አገልግሎት የተነሣ ወደ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ የደኅንነትን የምሥራች ለወገኖቹ ለማካፈል ወደ አገሩ ተመለሰ። በተጨማሪም ኤጳፍራ በሎዶቅያና ኢያራ አብያተ ክርስቲያናትን ሳይቆረቁር አልቀረም (ቆላ. 4፡13)። በዛሬው ዘመን አገላለጽ ኤጳፍራ «የቤት ለቤት አገልጋይ» ነበር።

ኤጳፍራ ወንጌሉን ለማዳረስ ያነቃቃው ምን ነበር? እርሱ «የክርስቶስ ባሪያ» ነበር (ቁ. 12)። ጳውሎስ «ከተወደደ ከእኛም ጋር አብሮ ባሪያ የሆነው ...» በማለት ይጠራዋል (1፡7)። ኤጳፍራ ኢየሱስ ክርስቶስን ከመውደዱም በላይ እርሱን ለማገልገልና የማዳኑን መልእክት ለማዳረስ ፈለገ፤ ዳሩ ግን ይህን ያደረገው ለብቻው አልነበረም። ኤጳፍራ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ከሌሎች ቅዱሳን ጋር አብሮት በመሥራት የሚያምን ሰው ነበር። እርሱም «ባሪያ» ብቻ ሳይሆን «አብሮ የሚሠራ ባሪያ» ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ከመስክ ሥራው ለመፈናቀል ስለተገደደው የጋራ ወዳጃችን ከአንድ በውጭ አገር የሚኖር የወንጌላውያን መሪ ጋር ስንነጋገር

ነበር። እርሱም «የኃጢአት ወይም ሌላ ዓይነት ችግር አልነበረበትም። ዋናው ችግሩ ብቸኛ መሆኑ ነው። ከሌሎች ሰዎች ጋር ተስማምቶ ለመሥራት አልቻለም። በወንጌል ሥራ አንድም ተባብሮ መሥራት፥ አሊያም ምንም ነገር አለመሥራት ብቻ ነው የሚፈለገው» በማለት ገለጸልኝ።

ከኤጳፍራ የአገልግሎት ምሥጢሮች አንዱ የጸሎት ሕይወቱ ነበር። ኤጳፍራና ጳውሎስ በአንድ ክፍል ውስጥ ስለነበሩ ኤጳፍራ ሲጸልይ ጳውሎስ ተመልክቶአል። የጸሎት ሕይወቱን ያወቀው በዚህ ነበር። የዚህ ሰው የጸሎት ሕይወት ምን ይመስል ነበር?

ያለማቋረጥ ይጸልይ ነበር (ቁ. 12- «ሁልጊዜ»)። ይህ ሰው «በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ» (ቆላ. 4፡2) ለሚለው የጳውሎስ ምክር መልካም ምሳሌ ነበር። ኤጳፍራ ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች እንደሚያደርጉት ደስ ሲለው ብቻ የሚጸልይ አልነበረም። ጸልይ የሚል ትእዛዝ ሲደርሰው ወይም ሌሎች አማኞች ሲጸልዩ ሲያይ የሚጸልይ ሰው አልነበረም። የእግዚአብሔርን በረከት በመሻት ያለማቋረጥ ይጸልይ ነበር።

በትጋት ይጸልይ ነበር (ቁ. 12 - «ይጋደላል»)። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ቃል «በኃዘን መዋጥ» የሚል ትርጉም ሲኖረው ጌታችን በአትክልት ስፍራ ስላሳለፈው የጸሎት ጊዜ ከተሰጠው ገለጻ ጋር አንድ ዓይነት ነው (ሉቃስ 22፡44)። ለኤጳፍራ ጸሎት ከባድ ሥራ እንደነበር እንረዳለን! ይህ የግሪክ ቃል ሯጮች ራሳቸውን ለውድድሩ ሙሉ ለሙሉ የሚሰጡበትን ሁኔታ ለመግለጽ ያገለግል ነበር። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስፖርተኞች ለውድድራቸው የሚጠቀሙበትን ጥረት ያህል ወይም ፍላጎት በጸሎታቸው ላይ ቢያውሉ ኖሮ፥ መንፈሳዊ መነቃቃት ይኖረን ነበር!

ለሰዎች በግል ይጸልይ ነበር (ቁ. 12 - «ስለ እናንተ»)። የኤጳፍራ ጸሎት በዓለም ዙሪያ ለሁሉም በአጠቃላይ የሚደረግና ለግለሰቦች መጸለይን የማይጨምር አልነበረም። የምልጃ ጸሎቱን የመሠረተው በቆላስይስ፥ በሎዶቅያና በሂራፖሊስ በነበሩት ቅዱሳን ላይ ነበር። አንዳንድ ሰዎችን በስም እየጠራ ይጸልይ እንደነበር አያጠራጥርም። ለኤጳፍራ ጸሎት ሰዎችን የማያካትት ሃይማኖታዊ ልምምድ አልነበረም፤ ምክንያቱም እነዚህን ሰዎች በልቡ ተሸክሞ በግል ይጸልይላቸው ነበርና።

ስለምን እንደሚጸልይ ያውቅ ነበር። ኤጳፍራን «ስለምን ትጸልያለህ?» ብሎ የመጠየቅ አጋጣሚ አግኝተው ቢሆን ኖሮ መልስ አያጣም ነበር። ታላቅ መሻቱም በእነዚያ ሦስት ማጎበረ-ምእመናን ውስጥ የሚገኙ አማኞች በክርስትና እምነታቸው ወደ ብስለት ይደርሱ ዘንድ ነበር። ጳውሎስ የኤጳፍራን ጸሎት ለማጠቃለል ግሩም ቃላት ተጠቅሞአል፤ እነዚህም ቃላት የቆላስይስን መጽሐፍ መልእክት ጭምር የሚያጠቃልሉ ናቸው፡- «በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ ...»።

ኤጳፍራ እነዚህ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁና እንዲያደርጉ አጥብቆ ይፈልግ ነበር። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ እንጂ በከፊሉ ላይ ብቻ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ አልፈለገም። (በቆላስይስ መጽሐፍ ውስጥ «ሁሉ» የሚለው ቁልፍ ቃል ሲሆን ከ30 ጊዜ በላይ አገልግሎአል)። እንዲሁም በእግዚአብሔር ፈቃድ ተረድተውና ፍጹማን ሆነው እንዲቆሙ ይፈልግ ነበር። የኖስቲክ አስተማሪዎች እነዚህን የክርስቲያኖች «ፍጹምነትና ብስለት» እንደሚሰጡ ይናገሩ ነበር፤ ዳሩ ግን ይህንን ለማድረግ አልቻሉም። እነዚህን በረከቶች ልናገኝ የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ሙላት የሚገኘው በክርስቶስ ብቻ ስለሆነ «በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል» (ቆላ. 2፡9-10)።

ይህ ጥያቄ በሳል የመሆንንና በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ዋስትና የማግኘትን አሳብ ይይዛል። እንዲሁም ከጳውሎስ የጸሎት ሸክም ጋር ይስማማል (ቆላ. 2፡2)። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሙሉ ዋስትና ማግኘት ግሩም በረከት ነው! ለክርስቲያን በሕይወቱ መዋለል አስፈላጊ አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናውቅና ልንደሰትበት እንችላለን። ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲማርና ሲኖርበት በእምነቱ እየበሰለ ይሄዳል፤ የእግዚአብሔርንም ሙላት ይለማመዳል።

በመሥዋዕትነት ይጸልይ ነበር (ቁ. 13 - «እጅግ እንዲቀና» ወይም «አብዝቶ እንደሚጨነቅ»)። እውነተኛ ጸሎት ከባድ ነው። ኢየሱስ ጌቴሴማኒ ስፍራ ሲጸልይ እንደ ደም ነጠብጣብ ያለ ላብ ከአካሉ ይመነጭ ነበር። ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በጸሎት «ይጋደል» ነበር (ቆላ. 2፡1)፤ ኤጳፍራም እንዲሁ ይጨነቅ ነበር። ይህም ማለት እግዚአብሔር ይመልስልን ዘንድ ከእርሱ ጋር መታገል አለብን ማለት አይደለም። ዳሩ

ግን በቅንዓትና ከልብ በመነጨ አሳብ ራሳችንን ለጸሎት መስጠት አለብን ማለት ነው። ሽክም ከሌለ፥ በረከት ሊኖር አይችልም። እዚህ ላይ ጆን ኤች. ጁወት ስለ ጸሎት የተናገሩትን ብንጠቅስ ተገቢ ይመስለናል፡- «ምንም ዋጋ ያልተከፈለለት ጸሎት፥ ምንም ነገር ሊፈጽም አይችልም» ብለዋል።

ከጳውሎስ ጋር የነበሩት ሰዎች ሁሉ በተለያየ ሁኔታ ሲገለጹ፥ በጸሎት አገልግሎቱ የተጠቀሰ ኤጳፍራ ብቻ ነው። ይህም ሌሎች ሰዎች አይጸልዩም ነበር ማለት ሳይሆን፥ ጸሎት ለእርሱ ዐቢይ መሻቱና አገልግሎቱ ነበር ማለት ነው። ኤጳፍራ ከጳውሎስ ጋር አብሮ የታሰረ ቢሆንም (ፊሊ.. ቁ. 23)፥ እስራቱ እንኳ ወደ ሰማይ አደባባዮች ከመግባትና በአብያተ ክርስቲያናት ለሚገኙ እኅቶቹና ወንድሞቹ ከመጸለይ አላገደውም ነበር።

ኢ. ኤም. ባውንድስ የዱሮ ትውልድ የጸሎት ተጋዳይ ነበሩ። ብዙውን ጊዜ ጠዋት ማልደው በመነሣት፥ የዕለቱን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ለበርካታ ሰዓታት ይጸልዩ ነበር። በጸሎት ርእሰ-ጉዳይ ላይ የጻፏቸው በርካታ መጻሕፍት፥ ባውንድስም እንደ ኤጳፍራ፥ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት በጸሎት መጋደል እንደሚገባ የተረዱ ሰው መሆናቸውን ይመሰክራሉ።

ኤጳፍራ በሦስት የተለያዩ ከተሞች ለሚኖሩ አማኞች መጸለዩ እጅግ ያስደንቀኛል። ዛሬ ምእመናን በሌሎች ስፍራዎች ለሚገኙ አማኞች ይቅርና ለራሳቸው መጋቢና ለቤተ ክርስቲያን ቢጸልዩ እንኳ ታድለናል! ምናልባት መንፈሳዊ መነቃቃት የሚዘገይበት አንዱ ምክንያት አንዳችን ለሌላው በትጋት ስለማንጸልይ ይሆናል።

የኮበለለው ሰው (ቆላ. 4፡14)

ዴማስ በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን እነዚህም ማጣቀሻዎች አሳዛኝ ታሪክ ያስረዳሉ። በመጀመሪያ «አብሮኝ የሚሠራ ... ዴማስ» ተብሎ ከሦስት መልካም ሰዎች ከማርቆስ፥ ከአርስጥሮኮስና ከሉቃስ ጋር ተጠቅሶአል (ፊሊሞና ቁ. 24)። በቆላስይስ 4፡14 ላይ ደግሞ እንዲሁ ዴማስ ተብሎ ተጠቅሶአል። በዚህ ስፍራ የተለየ ገላጭ ቃል አልታከለበትም። ዳሩ ግን የመጨረሻው ማጣቀሻ ዴማስ የደረሰበትን አሳዛኝ ሁኔታ ይገልጻል፡- «ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና» (2ኛ ጢሞ. 4፡10)።

በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞው በአንድኛው ክፍል፥ ማርቆስ ዮሐንስ ጳውሎስን ትቶ ነበር፤ ዳሩ ግን እንደገና ተመለሰ። ዴማስ ግን ዳግም ያልተመለሰ ይመስላል። ኃጢአቱም የአሁኑን ዓለም መውደዱ ነበር። ዓለም የሚለው ቃል ይህችን ዓለም የሚያሸከረክረውን ሁለተናዊ የነገሮች ቅንጅት ወይም «እግዚአብሔር የሌለበትን ማኅበረሰብ» ያመለክታል። ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ዓለም አማኞችን «የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት» እንደምትስባቸው ገልጾአል (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)። ከእነዚህ ከሦስቱ ዴማስ በየትኛው ወጥመድ እንደተያዘ አናውቅም። ምናልባት በሦስቱም ወጥመዶች ሊሆን ይችላል።

ዳሩ ግን ልክ ዴማስ እንዳደረገው ክርስቲያኖች ዛሬም ወደ ዓለም ሊሳቡ እንደሚችሉ እናውቃለን። ሁልጊዜም ለዚህ ዓለም ነገሮች እየኖሩ በአስመሳይ ሃይማኖታዊ ሥርዓት መመላለስ ምንኛ ቀላል ነገር ነው! ዴማስ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚችል መስሎት ነበር፤ በመጨረሻም ከሁለቱ በአንዱ ለመጠቃለል መወሰን ነበረበት። የሚያሳዝነው ግን በሕይወቱ ላይ የተሳሳተ ውሳኔ ወሰነ።

የዴማስ ወደ ዓለም መሄድ ጳውሎስን በከፍተኛ ደረጃ ሳይጎዳው አልቀረም። የመከሩ ሠራተኞች ቁጥር በጣም አነስተኛ ስለነበር የዴማስ እርምጃ የጌታንም ሥራ ጎድቶታል። ይሁንና ውሳኔው ከሁሉም በላይ የጎዳው ራሱ ዴማስን ነው። ዘላለማዊነት ለሌለው ነገር ሕይወቱን አባክኖአል። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል» (1ኛ ዮሐ. 2፡17)።

ጳውሎስ ከወዳጆቹና አብረውት ከሚያገለግሉ ሰዎች ሰላምታ ካስተላለፈ በኋላ፥ ራሱም በሎዶቅያና በሂራፖሊስ ለሚገኙ እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርባል። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስን በሥጋ አይተው ባያውቁም (ቆላ. 2፡1)፥ ይወዳቸውና ስለ መንፈሳዊ ደኅንነታቸው ሸክም ይሰማው ነበር።

ስለ ንምፉን በቤቱ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ እንደሚካሄድ ብቻ እንጂ ሌላ የምናውቀው ነገር የለም። (በ1980 የአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም መሠረት ንምፉ ብለው ይጠሩታል፤ ከዐረፍተ ነገሩም አገባብ የሴት ስም እንደሆነ ታውቆአል።) በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ክፍለ-ዘመናት አካባቢ፥ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት

ስብሰባዎች በግለሰብ ቤቶች ውስጥ ይደረጉ ነበር። ዛሬም ቢሆን በርካታ አዳዲስ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሚጀምሩት በዚህ ዓይነት ነው። የክርስትና እምነት ከስደት ተነሥቶ ይፋ የመንግሥት ድጋፍ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ፥ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች አልተመሠረቱም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ የጎብረቱ ማዕከል እስከሆነ፥ ድረስ ጉባኤው የትም ቢሰበሰብ ችግር የለውም። (ስለ «ቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን» ተጨማሪ ምሳሌዎች ለማግኘት ሮሜ 16፡5 እና 1ኛ ቆሮ. 16፡19ን ተመልከት።)

የጳውሎስ ትልቁ ዓላማ የእግዚአብሔር ቃል በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዲነበብና እንዲጠና ነበር። ማንበብ ማለት ድምፅን «ከፍ አድርጎ ማነብነብ» እንደ ማለት ነው። የእነዚህ መልእክቶች ቅጂዎች ለእያንዳንዱ አባል ሊደርሱ አይችሉም ነበር። በአብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት፥ የእግዚአብሔርን ቃል በሕዝብ ፊት ወደ ማንበቡ ልምምድ እንድንመለስ አጥብቄ ለማሳሰብ እወዳለሁ። «ለማንበብ ... ተጠንቀቅ» (1ኛ ጢሞ. 4፡13) ሲል የእግዚአብሔርን ቃል በሕዝብ ፊት ማንበብን ያመለክታል።

ከጳውሎስ ዘንድ ይላኩ የነበሩት እነዚህ የተለያዩ መልእክቶች ለእነዚህ ሁሉ ጉባኤዎች ተስማሚ መሆናቸውን ልብ ማለት ያሻል። በራሴ አገልግሎት፥ የእግዚአብሔርን ቃል በበርካታ የተለያዩ ሥፍራዎችና ሁኔታዎች ውስጥ አካፍያለሁ። ቃሉም ወደ ሰዎች ልብ ከመድረስና መሻታቸውን ከማሟላት ተቆጥቦ አያውቅም። በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንኳ የእግዚአብሔር ቃል ለልብ የሚደርስ መልእክት አለው። የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜም ተስማሚ ስለሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ችግሮች ለመቅረፍ መታረም ወይም መለወጥ አያሻውም።

ከሎዶቅያ የምናገኘው መልእክት ምን ነበር? በእርግጠኝነት ለመናገር አንደፍርም። አንዳንድ ምሁራን የጠፋው ለኤፌሶን የተጻፈው መልእክት እንደሆነ ያስባሉ፤ ይሁን እንጂ ይህ አሳብ መላምት እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። ይህ ክፍል መጥፋቱ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከተጻፈው ቃል ውስጥ የተወሰነውን ክፍል አጥተናል ወደሚለው ድምዳሜ አይወስደንም። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከላካቸው መልእክቶች ውስጥም የተወሰነው ክፍል ጠፍቷል፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ

ምሪት ቃሉን መስጠት ብቻ ሳይሆን በቃሉ ውስጥ ሊሆን የሚገባውን ክፍል እንዳይጠፋ ከፍተኛ ጥበቃ አድርጎአል። በመሆኑም ስለሌለን ነገር ከመደነቅ ይልቅ ያለንን መጠቀም ይኖርብናል።

ቆላስይስ 4፡17ን ከፊልሞና 2 ጋር ስናወዳድር፥ አከሪጳ ከፊልሞና ቤተሰብ ውስጥ አንዱ እንደሆነ እንመለከታለን። የፊልሞና ልጅና በፊልሞና ቤት ውስጥ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሳይሆን አይቀርም። በእርግጥ ይህንን ለማረጋገጥ ባንችልም ትክክለኛ ድምዳሜ ይመስላል። ይህም አፍብያ የፊሊሞና ሚስት እንደነበረች ያመለክታል።

ጳውሎስ ከሰላምታ በኋላ የጠቀሳቸው የመጨረሻ ቃላት አከሪጳ አገልግሎቱን በታማኝነት ይቀጥል ዘንድ በተሰጡት ማበረታቻዎች ላይ ያነጣጥራል። አከሪጳ ተስፋ ቆርጦ ነበርን? የናስቲክ የሐሰት አስተማሪዎች ቤተ ክርስቲያኑን በማጥለቅለቅ ችግሮችን ፈጥረውበት ይሆን? አናውቅም፤ ዳሩ ግን የአብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች ከበርካታ ችግሮች ጋር እንደሚፋጠጡ፥ በርካታ ሸክሞች እንዳሉባቸውና ሁልጊዜም የማበረታቻ ቃል እንደሚሹ እናውቃለን።

ጳውሎስ አከሪጳን አገልግሎቱ ከእግዚአብሔር እንደተሰጠውና አንድ ቀን የሥራውን ዘገባ የሚያቀርብ የእግዚአብሔር ሠራተኛ እንደሆነ ያስታውሰዋል። አገልግሎቱን የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ በተገቢው መንገድ ይወጣ ዘንድ ሊረዳው ይችል ነበር። አገልግሎት እኛ ለእግዚአብሔር የምናደርገው ሳይሆን እግዚአብሔር በእኛ በኩልና በእኛ ውስጥ የሚሠራው ተግባር ነው።

እንድትፈጽመው የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ ይፈጽሙት ዘንድ ያዘጋጃቸው ግልጽ ዓላማዎች እንዳሉት ያመለክታል። እርሱ አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ እንፈጽም ዘንድ በውስጣችንና በእኛ በኩል ሥራውን ያከናውናል (ኤፌ. 2፡10 ተመልከት)። በመሠረቱ፥ መፈጸም የሚለው ከቆላስይስ መልእክት ዋና አሳብ ጋርም አብሮ ይሄዳል። የኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ለእያንዳንዱ አማኝ ተሰጥቶታል። አስቀድመን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለ «ተሞላን» አገልግሎቶቻችንን ለማሟላት እንችላለን።

የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በተግባር የማንተረጉም ከሆነ ጥናታችን ከንቱ ነው። ይህንን መልእክት ካነበብንና ካጠናን በኋላ ለመቼውም ቢሆን የምንፈልገው ነገር ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለን ከመረዳት በቀር

የምናደርገው ነገር የለም። የእግዚአብሔር ሙላት በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ በእርሱ ተሞልተናል። ይህ ለአከሪጳ ምንኛ የሚያበረታታ እውነት ሊሆን ይገባል! ዛሬስ ለእኛ ደግሞ ምን ያህል የሚያጽናናን ሊሆን ይገባል!

ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ መልእክቱን ለጸሐፊው ይናገርና እርሱም ይጽፍለት ነበር (ሮሜ 16:22 ተመልከት)፤ በመጨረሻም ላይ ስሙን ጽፎ ይፈርምበታል። ሁልጊዜም በመልእክቱ ፍጻሜ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ይጽፍ ነበር፤ ይህም የመልእክቱ «ምልክት» ነበር (2ኛ ተሰ. 3:17-18 ተመልከት)። የፊርማውና የ«ጸጋው» ቃል አንድ ላይ መጠቀሱ መልእክቱ እውነተኛ የጳውሎስ መልእክት እንደሆነ ያረጋግጣል።

አዲስ ኪዳን ስለ ጳውሎስ እስራቶች በርካታ ማጣቀሻዎችን ይዘአል። (የሐዋ. 20:23፤ 23:18፥ 29፤ 26:29፤ ፊልጵ. 1:7፥ 13-14፥ 16፤ 2ኛ ጢሞ. 1:8፤ 2:9፤ ፊሊሞ. ቁ. 10፥ 13፤ ኤፌ. 3:1፤ 4:1 ተመልከት።) ጳውሎስ እስራቱን እንዲያስቡ ለምን ይፈልጋል? በመጀመሪያ ደረጃ እስራቶቹ ለጠፉት ነፍሳት በተለይም ለአሕዛብ ያለውን ፍቅር የሚያስገነዝቡ ነበሩ። «ስለዚህም አሕዛብ ስለሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር» ነኝ ይላል (ኤፌ. 3:1)። የጳውሎስ እስራቶች ለጌታ ላለው ታዛዥነትና አሕዛብ ወንጌልን ይሰሙ ዘንድ ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ለመሆኑ መረጃ ናቸው።

ዛሬም እንኳ ለጌታ ታማኞች በመሆናቸው ምክንያት በእስራት የሚማቅቁ ለጌታ የተሰጡ ክርስቲያኖች አሉ። እነዚህን ወገኖች ልናስባቸውና ልንጸልይላቸውም ይገባል። «ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ» (ዕብ. 13:3)።

ወደዚህ አስደናቂ ጥናት ፍጻሜ ስንመጣ በክርስቶስ ኢየሱስ ምሉዓን እንደሆንን ልብ ልንል ያሻል። በመሆኑም በክርስቶስ ካገኘነው ትምህርት የበለጠ ከሌላ የምናገኝ ቢመስለን ልንጠነቀቅ ይገባል። የእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ የሚገኘው በእርሱ ስለሆነ፥ እግዚአብሔር የሚፈልግብንን ዓይነት ሕይወት እንድንኖር ሙሉ ለሙሉ አስታጥቆናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ አዳዲስ ልምምዶችን በመለማመድ አናድግም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በቃሉ በኩል አስቀድሞ የገለጠልንን ነገር ከሕይወታችን ጋር በማዛመድ ልናድግ እንችላለን።

በክርስቶስ ምሉዓን እንደሆኑት ሰዎች እንኖር ዘንድ ጌታ ይርዳን።

«... ሁን» በሚል ርእስ ታትመው በስርጭት ላይ የሚገኙ መጻሕፍት

1.	ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)	14.10
2.	ርኅሩኅ ሁን (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1–13)	6.10
3.	የበረታህ ሁን (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14–24)	6.50
4.	በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1–12)	5.35
5.	ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13–28)	4.60
6.	ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)	8.90
7.	አርነት መውጣት (ገላትያ)	9.40
8.	ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)	8.25
9.	ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)	9.60
10.	ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ)	9.25
11.	ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶና ፊልሞና)	8.85
12.	ንቃ (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)	11.85
13.	በብስለት ማደግ (የያዕቆብ መልእክት)	11.20
14.	ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)	8.45

በዝግጅት ላይ ያሉ

1. እውነተኛ ሁን (1ኛ የዮሐንስ መልእክት)
2. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
3. ፍለጋ የሌለው ባለጠግነት (ኤፌሶን)